በድጋሚ የታተመ



# ዋበብ


## ፩

አጁባሠለ

(ኃይለጊዮርጊስ ማሞ)

# ጥበብ

# ፩



*«እኔም ብርሃን ከጨለማ
እንደሚበልጥ እንዲሁ
ጥበብ ከስንፍና እንዲበልጥ አየሁ»
መክ. 2:13*

# ከጲላጦስ

**(ኃ/ጊ.ማ)**

የቴሌግራም

ቻናላችንን ለማግኘት

*@amharicbooks24*

ወይም

ይሄን ይጫኑ

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው
All rights reserved
1997 E.C.

አሣታሚ:-
ሻላ ፕሮሞሽን ሰርቪስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር
☎ 634736 ✉ 110377
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

Scanned by CamScanner

## መታሰቢያነቱ

ለሲስተር አሰገደች ጥጋቡ
ለአዚብ ፋንታሁን
በተለይ ለሳሊም ኃይለጊዮርጊስ
ይሁንልኝ::

## መፅሐፉ ተበረከተ

ፅሁፎቼን መፅሐፍ ለማድረግ የነበረኝን ሕልም ለፈታልኝ
ውድ ወንድሜ አባይ ወርቅዬ፣ አስቀድማ ሕልሙን
በውስጤ ለጫረችው ውድ እህቴ ስንዱ አበበ፣
በተፈታው ሕልም ላይ የበኩሉን ላበረከተው
በዕውቀቱ ስዩም፣ እንዲሁም የተፈታውን ሕልም
ላሰማመረችው አሰገደች ጥላሁን ምስጋና ያንስባችኋል::

Scanned by CamScanner

# መግቢያ

ይኽ መፅሐፍ እንደ«ሰው» ማሰብ ለሚፈልጉ ሁሉ ተፅፏልና መግቢያም ሆነ አጥር አልተበጀለትም።

ጲላጦስ

Scanned by CamScanner

# ማሰብ ባትችል፤ ማሰብ እንደምትችል እወቅ

ሰውን እንዲያስብ ልታደርገው ባትችልም፤ ማሰብ እንደሚችል ልትነግረው ግን ትችላለህ የሚለው የጥንታውያን ፈላስፎች አባባል የዚህ ፀሐፊ እምነትና መሠረት ነው፡፡ እነሆም የፍልስፍናውን ዓለም ገቶ አሃዱ ብለን ለመጀመር ማሰብ እንጀምራለን፡፡ ማሰብ ለመጀመር ስንነሣ ደግሞ «ማሰብ አስጀምሮ ያላስጨረሰንን » ሰው ሕይወት ማየት የግድ ይሆናል፡፡

ስለ መልኩ አስቀያሚነት በዘመኑ የነበሩ ሰዎች እንደፃፉት ከሆነ እሱን አይቶ የማይስቅ አልነበረም፤ ትልቅ መላጣ ጭንቅላት፣ በላዩ ላይ ትንሽ ፊት፣ ረዥምና ቅጥ ያጣ ፂም... ወዘተ የእሱ «ውበት» መገላጫዎች ነበሩ፡፡ የጓደኞቹ የቀልድ ምንጭ የእሱ ፊት ቢሆንም እሱም ስለራሱ ፊት ተጨማሪ ቀልድ እየፈጠረ አብሮ ይስቅ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን፡፡

አባቱ ድንጋይ ጠራቢ፣ እናቱ ደግሞ የልምድ አዋላጅ ነበሩ፡፡ ይኸ ሰው ከድህነቱም በላይ ሥራ ፈት ነበር፡፡ የሚስቱንና የሦስት ልጆቹን ሕይወት ለማኖር ይበቃል የሚለውን ያህል ከሰራ በኋላ ቀሪ ጊዜውን የሚያሳልፈው «በማውራት» ነበር፡፡ ሁለተኛ ሚስቱ የነበረችው የዛንታፔ አስቸጋሪ ባህርይ ሰውየው አብዛኛውን ጊዜ ከቤቱ ርቆ እንዲውልና እንዲያመሽም የራሱን ድርሻ አበርክቷል፡፡ ሰውየው በሚስቱ ላይ የነበረው



Scanned by CamScanner

ትዕግስት የሚገርማቸው ጓደኞቹ «ምነው ትዕግስትህ በዛ?» በማለት ሲጠይቁት «ትዕግስት ጥሩ ነው! እሳትን መታገስ የቻለ በብርድ ውስጥ መኖር ይችላል» ይላቸው ነበር::

ከእንቅልፉ በማለዳ ተነስቶ ቁርሱን በፍጥነት ይበላና ወጥቶ ይሄዳል... የሚሄደው በየአደባባዩ ከሚሰበሰቡት ሰዎች ጋር ለማውራት አሊያም ከመሰሎቹ ጋር ለመከራከር ነበር:: የሰውዬው ክርክር አስቀድሞ ሲሉት ጠቢባን ስላላነሱት ብሎም ፈፅሞ ስላላሰቡት ነገር ነበር::... ስለሰጡ::

አንድ ወቅት የአቴና ጠባቂና ገገር ከፍተኛ «ሹመት» ሰጠ ... ይኸ ሹመት የአቴናን ሰዎች በሙሉ ያስገረመና ያስደነገጠም ነበር:: «ከአቴና ሁሉ ካሉ ጠቢብ» የሚል ሹመት የተሰጠው ሰው በዚያች ከተማ የሚታወቀው በሥራ ፈትነቱና በክርክር ወዳድነቱ ነበር:: «በሹመቱ» የተገረመው የአቴና ሕዝብ ገገርው እንዴት ይህን ከፍተኛ ሹመት ሊሰጠው እንደቻለ ሲጠይቁት... «እኔን ከአቴና ሰዎች ሁሉ ጠቢብ የሚል ሹመት ያሰጠኝ ጠቢብነቴ ሳይሆን የገዢውን አላዋቂነት ያወቅኩ ብቸኛው ሰው በመሆኔ ነው» በማለት መልሷል:: ይህ የአቴና ብቻ ሳይሆን የምድራችን ጠቢብ ሰው ሶቅራጥስ ነው::

ዕውቀትን ሰባኪ የነበረው ጠቢቡ ሶቅራጥስ የናዝሬቱ እየሱስ ከአራት መቶ ዓመት በኋላ መጥቶ በየመንደሩና በየአደባባዩ እየዞረ ፍቅርን እንደሰበከ ሁሉ እሱም በየዞረበት ስለሎጂክ ሰበከ:: ሶቅራጥስ በሚያስተምርበት አደባባይ ተገኝቶ የሰማ ማሰብ ባይችል ማሰብ እንደሚችል አውቆ ይሄድ ነበር ይላሉ የታሪክ ፀሐፊዎች::

አንድ ወቅት ሶቅራጥስ በአቴና ከተማ ሲዘዋወር በአንዱ አደባባይ ጠቢብ ሰው ቆሞ ስለ ፅናት (courage) ሲያስተምር ቁጥሩም የበዛ ሕዝብ ሲሰማው አስተዋለ:: ከሕዝቡም ጋር ተቀላቅሎ የጠቢቡን ሰው ንግግር ማዳመጥ ጀመረ:: ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ ድምፁን ከፍ አድርጐ በመጮህ ጠቢቡን በጥያቄ አቋረጠው::

«ንግግርህን በማቋረጤ ይቅርታ ይደረግልኝና ፅናት ስትል ምን

ማለት እንደሆነ ብትነግረኝ» አለው::

«ዕናትማ ጠላት እየቀረበህ ቢመጣም አንተ ግን ከቦታህ ሳትነቃነቅ መጠበቅ ነው...» በማለት ጠቢቡ መለሰ::

«ነገር ግን እቅድህ ከሽፎ መሸሽ ቢኖርብህስ?» አለ ሶቅራጥስ::

«በእርግጥ በዚያን ጊዜ ዕናት ሌላ ይሆናል:: ቦታህን ይዘህ አትቆይምና» ጠቢቡ መለሰ::

«ስለዚህ ዕናት ከቦታህ አለመነቃነቅ ወይንም ከቦታህ መሸሽ ማለት ካልሆነ ታዲያ ዕናት ምንድን ነው?» ሶቅራጥስ ጠየቀ::

ያ ጠቢብ ሰው በሕዝቡ ፊት እግሩ መንቀጥቀጥ ጀመረ... «ሶቅራጥስ ሆይ ፈተንከኝ፤ አሁን ሳስበው በትክክል ዕናትን የማውቀው አልመሰለኝም» አለ::

«እኔም አላውቀውም» አለ ሶቅራጥስ:: «ነገር ግን ዕናት አዕምሮህን ከመጠቀም የተለየ ነገር አይመስለኝም፤ የተለየ ቢሆን ደግሞ ይደንቀኛል:: ይህም ማለት በማንኛውም አደጋ ውስጥ ብትሆን ትክክለኛውን ነገር ብቻ ማድረግ ከቻልክ ያ ዕናት ነው» በማለት በንግግሩ ላይ አከለበት::

«እንዲያውም የዕናት ትክክለኛ ትርጉሙ እሱ ነው» በማለት በአደባባዩ ከተሰበሰቡት አንዱ ጮኸ:: ሶቅራጥስ ወደዚያ ሰው ዞሮ ተራመደና እንዲህ አለ...

«እንግዲያውስ ዕናት ማሰብ እንደሚገባህ ማሰብ ነው በሚለው ትርጉም ለጊዜውም ቢሆን ብንስማማስ... የዕናት ተቃራኒው ደግሞ አዕምሮን በስሜት እያስገደዱ መንዳት ነው ብንልስ?» በማለት ጠየቀ::

ወደ ሶቅራጥስ ፊቱንም ልቡንም አዙሮ ይሰማ የነበረው ሕዝብ መስማማቱን ገለፀ:: ሶቅራጥስ ጠቢቡም ተስማምቶ እንደሆነ ለማወቅ ቆሞበት ወደነበረው ከፍታ ፊቱን አዞረ... ጠቢቡ ግን አልነበረም::

ከሶቅራጥስ በፊት የነበረው የፍልስፍና ዓለም አትኩሮትና እምነት በተፈጥሮ ላይ የተመሠረተ ነበር:: በቴለስ መሪነት በጥንታዊቷ የግሪክ



Scanned by CamScanner

ከተማ ማልተስ ላይ ያቆጠቆጠው ፍልስፍና «የማንኛውም አውነታ ምንጩ ውኃ ነው» ብሎ ተነሣ:: ሌላው ነገር ሁሉ ከውኃ መጣ ነው ነገሩ:: በመቀጠል የቴለስ ተማሪ የነበረው አኔክስማንደር ደግሞ «የእውነታ ሁሉ ምንጭ አፔሮን ነው» አለን:: አፔሮን ምንድነው ሲባል «እኔም አላውቀው» ሆነ መልሱ:: የእሱ ተማሪ አኔክስማነስ ደግሞ «እኔም የመጣው ከአየር ነው፤ አየር ባይኖር አሁን ለዓይናችን እውነት ሆነው የምናያቸው (ዛፍ፣ ድንጋይ፣ ሰው...) ባልኖሩ ነበር» አለ:: እንዲህ እያለ ብዙዎችም እያመኑበት የሄራክሊተስ ዘመን ላይ ደረሱና እሱም «የእውነታ ሁሉ ምንጭ እሣት ነው» አለን:: እነዚህና መሰል እምነቶች ለዘመናት ሲታመኑባቸው ኖሩና ሶቅራጥስ ላይ ደረሰ:: እንግዲህ ለዘመናት የሰው ልጅ ስለ እውነታ የነበረውን እሳቤና እምነት የገለበጠ ይህ ሰው ነው:: ለሶቅራጥስ እውነታ «የሰው ልጅ አዕምሮ» ሆነ::

«የእኔ ጉዳይ ሰው እንጂ ድንጋይ፣ አየር፣ አፈር፣ ዛፍ፣ ወይም ውኃ አይደለም» የሚለው ሶቅራጥስ እሱን የሚያስጨንቁ ጥያቄዎች «ሰው ምንድነው?» «መልካምና መጥፎ ሰውስ ማነው?» «ሰው በራሱስ ምን መሆን ይችላል? ... ወዘተ» የሚሉት ነበሩ::

«የመልካምነት መሠረቱ ዕውቀት፣ የክፋት መሠረቱ ደግሞ አለማወቅ ናቸው» የሚለን ሶቅራጥስ «የእውቀት መጀመሪያ አለማወቅን ማወቅ ነው... ማወቅ ደግሞ ከማሰብ ይጀምራል» ብሏል:: ለዚህም ነው የግሪክ ጠቢባንንና አዋቂዎችን በጥያቄው ሲፈታተናቸው መልስም እያሳጣ ሲያሳፍራቸው የኖረው:: ሶቅራጥስ ሲናገር «ከብዙ ጠቢባን ጋር ስነጋገር የሚገርመኝና የሚያሳዝነኝ እናውቃለን በሚል ሃሣብ የመከፈሳቸው ሳይሆን አላዋቂነታቸውን አለማወቃቸው ነው... እኔ አለማወቄን የማውቅ ሰው በመሆኔ በእነሱ መካከል እንደ ታላቅ ጠቢብ ተከበርኩ» ብሏል:: እንደነዚህ ዓይነቶቹን ሰዎች ዕለት ዕለት በጥያቄው ሲፈታተናቸው ይውል ነበር:: ስለዚህ ሰው ስብህናና እውቀት ተቀንጭቦ ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት ታትመው ከወጡ ሪደርስ ዳይጀስት መጽሔቶች ላይ

የቃረምኩትን ልበትን::

አንድ ቀን አንድ መምህር ወደ እሱ ሊተዋወቀው መጣ:: ሶቅራጥስም ሰውየው መምህር መሆኑን ሲረዳ:- «ለመሆኑ ለተማሪዎችህ እንዳች እውቀትህን ከማካፈልህ በፊት የራስህን አላዋቂነት ተገንዝበሃል?» በማለት ጠየቀው:: ከፍ ያለ ከበሬታ ለሶቅራጥስ የነበረው መምህርም:- «በእርግጥ ምንም እንደማላውቅ አውቃለሁ» በማለት መለሰ::

«እንግዲያስ ለተማሪዎችህ ሂድና ይህንኑ ንገር» አለው::

«አለማወቄን ስነግራቸው ጥለውኝ ቢሄዱስ?» በማለት ጠየቀው::

«ያን ጊዜ ነፃ ስለምትሆን እዚህ መጥተህ ትማራለህ» በማለት መለሰለት::

በሌላ ጊዜ ደግሞ በዘመኑ ከሚከበሩትና ከሚፈሩት የግሪክ ባለስልጣናት ከአንዱ ጋር በመንገድ ተገናኝተው «ባለስልጣን ሆኜ ሳለ ባለስልጣን የመሆን ትርጉሙ ግን እስከአሁን አልገባኝም» በማለት ሶቅራጥስን ለጠየቀው ጥያቄ እንዲህ በማለት መለሰለት:- «ባለስልጣን ማለት የራሱን ፍላጐት መቆጣጠር የማይችል ነገር ግን የሕዝቡን ፍላጐት መቆጣጠር የሚፈልግ ሰው ማለት ነው»::

ለሶቅራጥስ «የዚህ ዓለም ችግር ሁሉ ምንጭ አላዋቂነት (ignorance) ነው:: ስለዚህም ብቸኛው መፍትሄ ደግሞ እውቀት ነው» ይለናል::

«ችግሩ ግን እውቀት እንዴት ይገኛል? የተገኘው እውቀት ትክክለኛ እውቀት መሆኑንስ እንዴት እናውቃለን? ለመሆኑ እውቀት ሰጪውስ ማነው?» በማለት ይጠይቃል:: «አንድ ቀን በመንገድ ላይ እየተዘዋወርኩ ጠቢብ ሰው መፈለግ ጀመርኩ፤ እግሬ እስኪነቃ በአቴና ጎዳና ሙሉ ቀን ዞሬ ያገኘኋቸውን ሰዎች ብጠይቃቸው «ሁሉን እናውቃለን» ነበር:: አለማወቁን የሚያውቅ አንድ ሰው ሳላገኝ ወደ ቤቴ ተመለስኩ» በማለት ሶቅራጥስ ሃዘኑን ይገልፃል::

«የግሪክ ሰዎች እኔን እጅግ ጠቢብ ቢያደርጉም እኔ ደግሞ የማውቀው አለማወቄን ነው፤ አለማወቄን ማወቅ ብቻም ሳይሆን አውቃለሁ ብዬም

እስቤ አላውቅም» በማለት ስለ እራሱ ይናገራል።

የብዙዎችን ጠቢባን ምንም አለማወቅ ለማሳወቅ የሞከረው ይህ ሰው ከወዳጆቹ በላይ ያተረፋቸው ጠላቶች እጅግ የበዙ ነበሩ። ለመሆኑ ጠላቶቹ ለምን በዙ? እንዴትስ አጠፉት? ሃሣብ አስጀምሮ ላላስጨረሰን ሶቅራጥስ ምስጋና ይግባውና የዚህን ጠቢብና ፈላስፋ ቀሪ ታሪክ በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለስበታለን።

# «ሳያስቡ ከመኖር እያሰቡ መሞት ይሻላል»

*አንድ ቀን ሶቅራጥስ ዘወትር ወደሚያስተምርበት አደባባይ በማለዳ ወጥቶ ቆመ::* የአቴና ሕዝብ እንደልማዱ የሶቅራጥስን ትምህርት ለመስማት በዙሪያው ከበበው:: እሱ ግን ዓይኑን አንድ ቦታ መሬት ላይ ተክሎ በሐሣብ ሄዷል:: ሕዝቡ መጠበቅ ጀመረ:: አንድ ሰዓት... ሁለት ሰዓት... ስድስት ሰዓት... ግማሹ ለምሳው መበተን ጀመረ:: የሶቅራጥስ ዓይኖች ግን ከተተከሉበት፣ አካሉም ከቆመበት አልተነቃነቀም::

መጨረሻው ምን ይሆን? ብሎ በዙሪያው ተሰብስቦ የሚጠብቀው ሕዝብ በጉጉት ማማጥ ጀመረ፤ ለምሳው የሄደውም ተመልሶ በዙሪያው ክምችቱ በዛና መጨረሻውን የሚጠብቀው ቁጥር ጨመረ:: መምሽት ሲጀምርና ግማሹ ወደ ማደሪያው መበተን ሲይዝ መጨረሻውን ሳላይ አልሄድም ያለው ደግሞ በአዳሩ ቆርጦ መጠበቁን ያዘ:: ታሪኩን ለማሳጠር ሶቅራጥስ በዚያ ሁኔታ ሃያ አራት ሰዓት ሞላው:: በዙሪያው የተሰበሰበው ሕዝብ አብዛኛው ቆሞ በዋለበት ቦታ እየተቀመጠ እንቅልፍ ይዞት ሄዷል::

መጨረሻውን ለማየት እጅግ ጓጉተው ያደሩት ጥቂቶች ደግሞ በንቃት አፍጥጠው ሲከታተሉ ሶቅራጥስ ከጭንቅላቱ ነቅነቅ አለና አንድ ነገር እንዳገኘና እንደተረዳ ፈገግ ብሎ መራመድ ጀመረ:: በሁኔታው

ከተገረሙት አንዱ ተከተለውና «አንድ ቀንና አንድ ሌሊት ሙሉ የምንጠብቀው አንተን ነበር:: ለመሆኑ ምን ስታደርግ እንደነበር ልትነግረኝ ትችላለህ?» በማለት ጠየቀው:: የሶቅራጥስ መልስ አጭር ነበር:: «እያሰብኩ!»::

ለዚህም ይመስላል አብርሃም ኮፕላን "The New World of Philosophy" በሚለው መጽሐፉ «ሶቅራጥስ ፍልስፍናን ከተሰቀለችበት ደመና አውርዶ ገበያ መሀል ጣላት፣ ገበያተኛው ግን አሁንም የሚፈልጋት ከደመናው ውስጥ ነው» ብሏል::

«ሰው ከእንስሳ የሚለየው በማሰቡ ነው» የሚለው ሕግ ለሶቅራጥስ ቦታ የለውም፤ ምነው ቢሉ «ማሰብ የለየው ሰውን ከእንስሳ ሳይሆን ሰውን ከሰው ነው» ይለናል:: «ለግሪክ አማልክት ሕዝቡ የሚሰግደው ስለሚያምንባቸው ሳይሆን ማሰብ ስለማይችል ነው» ይል ነበር:: በተለይም ከፕሌቶ ጀምሮ ተከታዮቹ የነበሩትን በሙሉ በዚህ እውቀት ሊያጠምቃቸው ተነሣ::

«ሰው በውስጡ ያለውን ብቃት ቢረዳ አሁን ያለበት ቦታ ባላፈረው ነበር... ማሰብ የሚችለው ፍጡር ማሰብ ለማይችሉት አማልክት እንዴት ይሰግዳል?» በማለት ጠይቆ ለመሰዋት ያበቃውን ሎጂክ በተከታዮቹ ልብ ውስጥ ዘራ::

ይህ ትምህርቱና አስተሳሰቡ በአቴና ወጣቶች ዘንድ መወደድና መከበርን ቢያተርፍለትም በአቴና ሽማግሌዎች ግን ከመጠላት ብሎም ከመጥፋት አላተረፈውም:: «አማልክቶቻችንን ተሳደበ፣ አዋረደን፣ የወጣቶቹን ልብ በከንቱ ትምህርቱ በከለ... ወዘተ» የሶቅራጥስ ወንጀሎች ሆኑ:: በተለይም ደግሞ በሶፊስቶች ዘንድ (ስለ ሶፊስቶች የፍልስፍ እምነት ወደፊት እናያለን) ከፍተኛ ጥላቻን አተረፈ:: ለሶፊስቶች መልካ ወይም መጥፎ፤ ሐሰት ወይም እውነት የለም:: በምድር ላይ ከተሳካል አንተ እውነተኛና መልካም ሰው ነህ:: ስኬትህ በማንኛውም ወንጀል ላ የተመሠረተም ቢሆን ለሶፊስቶች ቁም ነገሩ «መጨረሻ ላይ ተሳክቶልሃ



Scanned by CamScanner

ወይ?» ነው፡፡ ይልቁንም ሶፊስቶች አስተማሪነታቸው ለሀብታሞች ብቻ ስለነበር የአቴና ሀብታሞችና አዛውንቶች በሶቅራጥስ ላይ ውንጀላ ሲጀምሩ ከፍተኛ እገዛ ማድረጋቸው ይታወቃል፡፡

ለምሳሌ የአቴና አማልክት ስለ ቅድስና የነበራቸውን አሳቤ አስመልክቶ ከጊዜው ጠቢባን ጋር ሶቅራጥስ ያደረገውን ምልልስ የእሱ ደቀመዝሙር ፕሌቶ ከፃፈው በኋላ Lane Cooper; Plato: The Collected Dialogues (ፕሌቶ ሄራሊተስ በማለት ይጠራቸው ነበር፡፡) በማለት ያሰፈረውን እንመልከት፡፡

ሄራሊተስ፡- «እግዚአብሔር ቅድስናን ይወዳል፤ ተቃራኒውን ደግሞ ይጠላል፡፡»

ሶቅራጥስ፡- «ይህን አባባላችሁን ራሱን እንፈትነው፡፡ አንድ «አምላክ» ወይም ሰው ይሄን ብያለሁ ስላለ እንቀበለዋለን? ወይስ እንፈትነዋለን?»

ሄራሊተስ፡- «ብንፈትነውም ይህ ቃል ዘላለማዊና ትክክል ነው»

ሶቅራጥስ፡- «አንድ ነገር ቅዱስ ነው የምንለው አማልክት ፈትነውት ቅዱስ ስለሆነ ነው? ወይስ ቅዱስ ነው ስላሉ?»

ሄራሊተስ፡- «አባባልህን አብራራው፡፡»

ሶቅራጥስ፡- «ቅድስናውና እሱን የሚሸከመው የተቀደሰው ሁለት አካል ናቸው፤ የሚታየውና የሚያየው አካል አሁንም ሁለት ነገሮች ናቸው፤ እንዲሁም የሚመራውና የሚመራ ሁለት ናቸው፤ በነዚህ ሁሉ ሁለቱ ነገሮች እንዴት እንደሚለያዩና፤ ልዩነታቸውም ይገባችኋል?»

ሄራሊተስ፡- «አዎን ይገባናል፡፡»

ሶቅራጥስ፡- «በዚሁ መንገድ ማፍቀር አንድ ነገር ሲሆን መፈቀርም እንዲሁ ሌላ ነው፡፡»

ሄራሊተስ፡- «ትክክል፡፡»

ሶቅራጥስ፡- «አንድ ነገር የሚታየው በሌላ አካል ለመታየት ስለሚችል ሳይሆን ነገር ግን ሌላ አካል ስላየው ነገሩ ሊታይ ቻለ፡፡ ወይም አንድ ነገር ተመሪ የሆነው ነገሩ በራሱ ተመሪ ስለሆነ አይደለም፤



Scanned by CamScanner

ግዝፈ ነገር ግን መሪ ስላለው ነገሩ ተመሪ ሆነ። ወይም እንደ አካል ሸክም የሆነው በራሱ ሸክም ስለሆነ አይደለም፤ ነገር ግን ተሸካሚ ስላለው ነገሩ ሸክም ሆነ። ይህ ማለት አንድ ውጤት በራሱ ላይ የመጣበት አካል ውጤቱ የራሱ ሳይሆን ምክንያት ስላለው ነው። ውጤት የሆነ ነገር በራሱ ውጤት አያመጣምና...»

ሄራሊተስ፡- «ትክክል።»

ሶቅራጥስ፡- «በዚህ ከተስማማን አንድ ነገር ሲፈቀር የተፈቀረው አካል ወደ ሌላ ነገር ይለወጣል?»

ሄራሊተስ፡- «አይለወጥም።»

ሶቅራጥስ፡- «እንግዲህ አንድን ነገር የሚያፈቅሩት ሰዎች ያፈቀሩት በራሱ የሚፈቀር ስለሆነ አይደለም፤ ነገር ግን ተፈቃሪ ያደረገው በሌሎች መፈቀሩ ነው?»

ሄራሊተስ፡- «የግድ ነው።»

ሶቅራጥስ፡- «ስለ ቅድስናስ ምን ትላላችሁ? እንደ እናንተ ክርክር ቅድስና በአማልክት ሁሉ ዘንድ የተፈቀረ ነው።»

ሄራሊተስ፡- «ትክክል።»

ሶቅራጥስ፡- «በራሱ ቅዱስ ስለሆነ ወይስ በአማልክት ስለተፈቀረ?»

ሄራሊተስ፡- «በራሱ ቅዱስ ስለሆነ።»

ሶቅራጥስ፡- «እንግዲያውስ ቅዱስ ስለሆነ እንጂ የተፈቀረው፤ ስለተፈቀረ አይደለም ቅዱስ የሆነው?»

ሄራሊተስ፡- «ይመስላል።»

ሶቅራጥስ፡- «ወይስ ቅድስና በአማልክት ዘንድ ተወዳጅና አስደሳች ስለሆነ ተፈቀረ ማለት ነው?»

ሄራሊተስ፡- «እሱም ጥርጥር የለውም።»

ሶቅራጥስ፡- «ስለዚህ ቅዱስ ነገር ቅዱስ የሚሆነው አማልክት ስለሚወዱት እንጂ በራሱ ቅዱስ ስለሆነ አይደለም፤ አልያም በአማልክት የተፈቀረው ቅዱስ አካል እና ቅድስና ሁለት የተለያዩ አካል ናቸው



Scanned by CamScanner

ማለት ነው?»

ሄራሊተስ:- «ይኸማ እንዴት ሊሆን ይችላል?»

ሶቅራጥስ:- «መጀመሪያ በተስማማነው መሠረት ቅዱስ የሆነው ነገር የተፈቀረው በራሱ ቅዱስ ስለሆነ እንጂ ስለተፈቀረ ቅዱስ አልሆነማ?»

ሄራሊተስ:- «ትክክል::»

ሶቅራጥስ:- «ነገር ግን አሁን የማየው አማልክት በቅድስና ደስ የሚላቸው ስለአፈቀሩት ነው፤ ወይስ ቅድስና በራሱ ተፈቃሪ ስለሆነ?»

ሄራሊተስ:- «ሁለተኛው ትክክል ይመስላል::»

ሶቅራጥስ:- «እንዲህ ከሆነ ቅድስና በራሱ ምክንያትም ውጤትም ነው ማለት ነዋ?»

ሄራሊተስ:- «ትክክል::»

ሶቅራጥስ:- «ታዲያ የሚታይ የሚኖረው የሚያይ ስላለ ከሆነ፣ ተመሪ የኖረው መሪ ስላለ ነው ካልን፤ ሸክም ያለው ተሸካሚ ስለኖረ ከሆነ በዚህም ሕግ ከተስማማን በራሱ ምክንያትና ውጤት የሆነውን፤ የሚታይም የሚያይም የሌለውን ቅድስናን አማልክት እንዴት አዩት?»

ሄራሊተስ:- «ይሄ ከባድ ፈተና ነው::»

ሶቅራጥስ:- «ከመሠረቱ አንድ ነገር በራሱ ምክንያትም ውጤትም ሊሆን እንዴት ይችላል? አንድ ነገር የሚፈቀረው የሚያፈቅረው ሲኖረው ከሆነ ነገሩ በራሱ ተፈቃሪ ሳይሆን የተፈቀረ ነገር ነው ማለት ነዋ...?»

የሶቅራጥስ እነዚህና መሰል ፈተናዎቹ የግሪክ አማልክትን አራክሷል፤ የወጣቶቹንም ልብ አበላሽቷል በሚል ክስ ተመሰረተበት::

ሶቅራጥስ በአቋሙ ኢ-አማኒ አልነበረም:: የብዙ አማልክትን መኖር ግን የሚነቅፍ በአንድ አምላክም መኖር የሚያምን ነበር:: አንድ ማለዳ ከቤቱ ወጥቶ ወደ አደባባይ ሲያመራ በእሱ ጉዳይ የፍትሕ ወንበር ተዘርግቶ «ምን እንፍረድበት?» ሲባባሉ ተመለከተ:: ብዙም አልተደነቀም:: «ከእነዚህ ሰዎች ከእዚህ በላይ አልጠብቅም» በማለት ወደሚያስተምርበት አደባባይ አቀና::



Scanned by CamScanner

በማግስቱ 500 አባላት ያሉት የዳኞች ችሎት ተቋቋመና ሶቅራጥስ ጉዳዩን እንዲያስረዳ ተጠየቀ፡፡

«የወጣቶቹን ልብ አልበከልኩም፤ የእኔ ሥራ እውነትን መፈለግ ብቻ ነበር፡፡ በፍለጋውም እንዲያግዙኝ አስተማርኳቸው... እኔን የምትከሱት ጥፋተኛ ሆኜ ሳይሆን የእናንተን አላዋቂነት በመግለጤ ነው፡፡ የእናንተን አላዋቂነት የገለጥኩት ደግሞ ስለምጠላችሁ ሳይሆን ከፍ ሳደርጋችሁ ስላሰብኩ ነበር፡፡ አንድ እውነት ግን አለ፡፡ ሰው ሳያስብ ከማኖር እያሰበ ቢሞት ይሻለዋል፡፡ እንደእናንተ ከመኖር እንደእኔ መሞትም እጅግ የተሻለ ይመስለኛል፡፡ ይሁንና ሰው ለመልካምና ለክፋ ሊፈረድበት ይችላል እንጂ እንዲሞትና እንዲኖር ሊፈረድበት አይገባም፡፡ እኔን ብትገድሉኝ በራሳችሁ ላይ ትልቅ ስህተት ሰራችሁ፡፡ ምክንያቱም እኔ ብሞት አንዳች ስህተት አልፈፀምኩም፤ እናንተ ግን እኔን በመግደል ወንጀለኞች ትሆናላችሁ» በማለት ተናገረ፡፡

ችሎቱ በድምፅ ብልጫ ሞት ፈረደበት፤ ይኸው ፍርድም ተነገረው፡፡ ሶቅራጥስም፡- «ለእኔ ሞት ከሁለት ነገሮች አንዱ ነው፡፡ የመጀመሪያው ወደ ዘላለማዊ ዝምታ ውስጥ መግባት፤ ወይም ሁለተኛው ወደ ሌላ ዓለም መሸጋገር ነው፡፡ ለእኔ ሁለቱም አስደሳች ነው፡፡ ወደ ዘላለማዊ ዝምታ ብገባም እንደእናንተ የሚረብሸኝ አይኖርም፤ ወደ ሁለተኛው ዓለምም መሸጋገር ከሆነ እርግጠኛ ነኝ በዚያ ጥላቻ፣ ቅናት፣ ስድብ ብሎም አሁን እናንተ እንደምታደርጉት የሞት ፍርድ የለም» አለ፡፡ አስገዳዮቹም ወስደው አሰሩት፡፡

ከመገደሉ አንድ ቀን በፊት የእሱ ደቀመዝሙር የነበረው ክሪቶ ገንዘብ ሰብስቦ ለጠባቂዎች ጉቦ ለመስጠትና እሱን ለማስመለጥ እየሞከረ እንደሆነ ነገረው፡፡ ሶቅራጥስም፡- «በዘመኔ ሁሉ ለሕግ እንደኖርኩ አሁንም ለእሷ ለመሞት እንደተዘጋጀሁ ታውቃለህ፤ ሕግን ገድዬ እኔ ነፃ ከምሆን እኔ ሞቼ ሕግ ነፃ ትሁን» በማለት የፕሌቶን ሃሳብ ሳይቀበለው ቀረ፡፡ ለዚህም ነው የሶቅራጥስ ተከታዮችና አድናቂዎች፡- «ማሰብ ሳይችሉ



Scanned by CamScanner

እንደ ካሊባን ዙፋን ላይ ከመቀመጥ በወህኒ ቤት እንደ ሶቅራጥስ እያሰቡ መኖር ይሻላል» የሚሉት፡፡

በማግስቱ መርዝ የያዘው አስገዳይ ወደ ሶቅራጥስ ቀረበ፡- «መርዙን ትጠጣና በእግርህ መንቀሳቀስ ትጀምራለህ፤ ከትንሽ ሰዓታት በኋላ እግርህ መያያዝ ይጀምራል፣ ያን ጊዜ እግርህን በያዘህ ቦታ በጀርባህ ተኛና ፊትህን በልብስህ ሸፍን፤ በቅፅበትም ትሞታለህ» አለው፡፡

ሶቅራጥስም መርዙን ተቀበለ፡፡ ከመጠጣቱ በፊት ለአስገዳዩ የመጨረሻውን ቃል ተናገረ፡- «እኔ ወደ ሞት አንተ ደግሞ ወደ ሕይወት እየሄድን ነው፤ የትኛው ይሻላል፤ እግዚአብሔር ያውቃል!» ... መርዙን ጠጣ፡፡



Scanned by CamScanner

# እምነትህ አዕምሮህን ካልገዛ፤ አዕምሮህ እምነትህን ይገዛል

የዜን ቡድሂስት እምነት አራማጅ ከወንዝ ዳር ተቀምጦ በተመስጦ ውስጥ ባለበት ሰዓት አንድ ወጣት ዋናተኛ በጩኸቱ አቋረጠው፡፡ «መምህር ሆይ! የአንተ ደቀ መዝሙር መሆን እፈልጋለሁ»፡፡

«ለምን?» በማለት መምህሩ ጠየቀው፡፡

«ምክንያቱም እግዚአብሔርን ማግኘት ስለምፈልግ» ሆነ የወጣቱ መልስ፡፡

መምህሩ ወደ ወንዙ በቅፅበት ዘሎ ገባና የወጣቱን ጭንቅላት በወንዙ ውስጥ ለጥቂት ደቂቃ ደፍቆ ይታገል ጀመር፡፡ ወጣቱ እንደምንም ተንፈራግጦ እየቃተተ ከወንዙ መውጣት ሲጀምር መምህሩ፡- «እንደ እውነት እስኪ ንገረኝ፤ አሁን ከውኃ በታች ሆነህ በሕይወት እጅግ የፈለከው ነገር ምንድን ነበር?» በማለት ጠየቀው፡፡

«አየር!» በማለት ወጣቱ ጮኸ፡፡

«ጥሩ ነው» አለ መምህሩ፡፡ «ወደ ቤትህ ሂድ፤ አሁን አየር የፈለከውን ያህል እግዚአብሔርን መፈለግ ስትጀምር ያን ጊዜ ወደ እኔ ተመልሰህ ና» አለው፡፡

* * *

«ማንም በምድር ላይ የኖረ ሰው ቢያንስ ለአንድ ቀን ከንቱና



Scanned by CamScanner

የማይረባ ነገር ሳይናገር አልቀረም...» ይለናል ታላቁ ጠቢብ ሞንቴኝ፡- «ይህንን ድርጊት ለአንድም ቀን አድርጎት አያውቅም የምለው ሰው ቢኖር ግን ዜን ነው» በማለት ይናገራል፡፡

ዴይስ ሱዙኪ ስለ ዜን እምነትና ፍልስፍና በሰፊው ያሳወቀን ራሱም የዜን እምነትና ፍልስፍና መምህር የነበረ ሰው ነው፡፡ ሱዙኪ እንዲያውም ዜን የሚለውን ቃል የእንግሊዝኛ ቃል ያደረገ ብቸኛው ሰው በመባልም ይታወቃል፡፡ «ማንም የዜን ተከታይ ነኝ ሲል ቡድሂስት ነኝ ከማለቱ በተጨማሪ ራሱን ከጃፓን የባህል እምነት ጋር ለማቆራኘቱ የሚያጠራጥር አይሆንም» ይለናል፡፡ የኖህ ድራማ፣ የሻይ ስነ ስርዓት፣ የአትክልት ቦታ አያያዝ፣ የሰይፍ ውድድር... እነዚህ ባህሎች ሁሉ የዜን እምነት ውጤቶች ናቸው፡፡ የዜን ፍልስፍና ከምዕራባውያኑ የሚለየው ዋናው ነገርም ይኸው ነው -- «ህያው ፍልስፍና» (Living Philosophy) መሆኑ፡፡

ዜን ሃይማኖት አይደለም፤ ቅዱሳት መፃህፍት ወይም ሌላ ሃይማኖታዊ ምልክት የለውም፤ የተለየ ባህልም ሆነ አምልኮ አይደረግለትም፡፡ የቡድሂዝም አንድ ቅርንጫፍ የሆነ እምነት ቢሆንም ከእሱ የሚለየው ዋናው ነገር በስነ መለኮት ትምህርት ላይ አለመመስረቱ ነው፡፡ ዴይስ ሱዙኪ እንደሚለን፡- «የፈጣሪን ስራ ከማየት አልፈህ የእሱን ስራ ጠያቂ ያደረገህ ማነው?» ይለናል፡፡ የዜን ተከታይ ስትሆን ስለ እግዚአብሔር አያገባህም፡፡ እሱም ስራውን ይሰራል፤ አንተም ስራህን ስራ... እንዲያውም «በምድር ላይ ስትኖር ራስህን እንደሞተ ሰው ቁጠረው» ይላል፡፡ «ምክንያቱም ራስህን እንደሞተ ሰው ከቆጠርህ ለመኖር የሚያንጓጓህ፤ ለመሞትም የምትፈራው አንዳች ነገር አይኖርም፡፡ መፍራት ስታቆም ደግሞ ማሸነፍ ትጀምራለህ... ለምሳሌ የምዕራባውያን እምነትና ፍልስፍና 'ዛሬን ስትኖር በምድር ላይ የምትኖርባት የመጨረሻዋ ቀን አድርገህ አሳልፋት' ነው፡፡ በዜን ግን 'ዛሬን ራሷን እንደ ትናንት አድርገህ ውሰዳት'» ይሉናል፡፡



Scanned by CamScanner

ስለ ዜን ፍልስፍናና እምነት ከመናገሬ በፊት ራሱ ዜን ምንድነው የሚለውን ለአንባቢዎቼ ትንሽ ላካፍል:: ዜን የዜን ቡድሂዝም እምነት መጠሪያ ነው:: ዜን ቡድሂዝም መልክ እየያዘ የመጣ የፍልስፍና የእምነት ዘይቤ የሆነው በ7ኛው ክ.ዘ. ሲሆን ይህ እምነት የህንድ፣ የቻይናና የጥንቱን የቡድሂዝም ሃሳብ በተለይም የማሃያናን ባህል በመያዝ የተመሰረተ ነው:: እንቅስቃሴውን በዋናነት የመሩት እምነቱን የተቀበሉት ጃፓናውያን እንደሆኑ ሲታወቅ ወደ ምዕራቡ ዓለም የገባ ፍልስፍና ከሆነም ቆይቷል::

ዜን የሚለው ቃል የመጣው ከጃፓን ሲሆን ትርጉሙም «በተመስጦ ማሰላሰል» (Meditation) ማለት ነው:: ማሰላሰል የሚለው የዜን ትርጉም በሁለት መንገድ የሚከናወን ሲሆን የመጀመሪያው «ዮጋ» የሚሉትና ጥልቅ የሆኑ ፍልስፍናዎችንና አባባሎችን በተመስጦ በማሰላሰል የሚካሄድ ሲሆን ይህ በዜን ዘንድ አእምሮን የማሰራት ጥበብ እንደሆነ ታምናበታል:: ሁለተኛው ከላይ እንደ ምሳሌ የጠቀስናቸው የሻይ ስነ ስርዓት፣ የሰይፍ ውድድር... የመሳሰሉት ናቸው::

የዜን እምነት አራማጅ ሆኖ በሚገባ ተምሯል የሚባለው «ሳቶሪ» በሚባለው ደረጃ ላይ የደረሰ ሰው ብቻ ነው:: «ዜን ሆኖ ሳቶሪ ያልሆነ ሰው ማለት ፀሐይ ሆኖ ሙቀትና ብርሃን የሌለው እንደማለት ነው» ይላሉ የዜን እምነት ተከታዮች:: ዶይስ ሱዙኪም «የአንድን ነገር ተፈጥሮ በጥልቀት የመረዳት ጥበብ ወይም ችሎታ ሳቶሪ ነው» ይለናል::

ዜን ስትሆን ፍፁም ነፃነት ትፈልጋለህ፤ ይህ ነፃነትህን እግዚአብሔር እንኳ እንዲሻማህ አትፈልግም:: ዶይስ ሱዙኪ:- «ለነገሩ ራሱ እግዚአብሔር በአንተ ምን አገባውና፤ እንዲያውም እግዚአብሔር ሲኖርህ የምትቀበለው የእግዚአብሔር የሆነን ነገር ብቻ ይሆናል፤ ይህ ደግሞ እንዳታስብ ራስህን በጣም መግታት ነው» ይለናል::

ከታሪክ እንደምንረዳው ዜን ቡድሂዝም የመጣው ከሳዳሀርታ ጉተማ ትምህርት ነው:: ሳዳሀርታ ጉተማ ከክርስቶስ ልደት 500 ዓመት በፊት



Scanned by CamScanner

የአሁኗ ሕንድ ልዑል ነበር:: በዙሪያው በሚያየው የሰው ልጅ መከራ ብሎም አላዋቂነት የታወከው የ29 ዓመቱ ልዑል የምቾት ኑሮውን በእውቀት ፍለጋ ሊለውጠው ተነሳ:: ከ6 ዓመት አድካሚ ጥረት በኋላ ከፍተኛውን የዕውቀት ደረጃ ተካነ:: እንግዲህ ከዚህ በኋላ ነው «በዕውቀት የነቃው» (One who is awake) ተባለ:: በሕንድም ለዚህ ሰው ቡድሃ የሚል ስም ተሰጠው:: በጥቅሉ ስናየው ይህ በእውቀት የነቃው ሰው በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ ለለውጥ የተጋለጡ መሆናቸውንና ሳይለወጥ የሚቀር አንዳች ነገር አለመኖሩን የተረዳ ነው:: «በራሱ ቋሚ ካልሆነ ነገር ጋር ራስን ማቆራኘት ትርፉ መከራ ነው:: ስለዚህም አንድ ሰው ቋሚ ካልሆነው ምድራዊ ነገር ራሱን ቢያላቅቅ (ከራሱም ጨምሮ) ያን ጊዜ ከመከራ ነፃ ይሆናል» ይላል::

ይህ የቡድሃ ትምህርት ሲወርድ ሲዋረድ ለዘመናት በተከታዮቹ ሲታመንበትና እነሱም ሲያስተላልፉት ቆዩ:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በ475 ዓ.ዓ. ቦድሂዳርማ ከሕንድ ወደ ቻይና ተጉዞ ይህንኑ ትምህርት በቻይና ምድር አስፋፋው:: እንግዲህ በቻይና ምድር የገባው ቡድሂዝም አስቀድሞ በሃገሩ ከነበረው የታዎኢዝም እምነትና ፍልስፍና ጋር ተቀላቀለና የቻን የቡድሂዝም ትምህርት ቤትን አስገኘ:: ከክርስቶስ ልደት በፊት በ1200 ዓ.ዓ. የቻን ቡድሂዝም ትምህርት ከቻይና ወደ ጃፓን ተሻገረና በዚያ የዜን ቡድሂዝም (ዜን) ተባለ:: የዜን ቡድሂዝም አመጣጥ በአጭሩ ይህን ሲመስል ለመሆኑ እምነትና ፍልስፍናው እንዴት ያለ ነው::

የዜንን እምነትና ፍልስፍና በሰፊው ካራመዱት አንዱ ዴይስ ሱዙኪ መሆኑን ከላይ ገልፀናል:: አንድ ወቅት አንድ የዜን መምህር ተማሪው ስለዘላለማዊ ሕይወት በተለይም ስለ ገነት ምን ማሰብ እንዳለበት ሲጠይቀው:- «እሱን ለቡድሃ ተውለት፤ እሱ የእኛ ስራ አይደለም» አለው:: በሌላ ጊዜ ይኸው መምህር ለመሞት በሚያጣጥርበት የመጨረሻ ሰዓት ተማሪው ወደ አልጋው ቀርቦ:- «እግዚአብሔር ይቅር የሚልህ



Scanned by CamScanner

ይመስልሃል?» በማለት ሲጠይቀው... «እስንማ አትጠራጠር፤ ሌላ ምን ስራ አለው?» በማለት መልሶለታል፡፡

የዜን እምነትና ፍልስፍና መገለጫው ዝምታ ነው፡፡ ታዲያ መገለጫው ዝምታ የሆነ እምነትና ፍልስፍናን እንዴት ነው የምትማሩት፣ ተብለው ሲጠየቁ ተከታዮቹ፡- «እኛ ወደ ዜን መጣን እንጂ እሱ አልመጣብንም፤ ወደ እሱ ስንመጣም የጠበቅነው መማርን ነበር፤ ነገር ግን የተማርነው መጠበቅን ራሱን ማስወገድ ነው» ይላሉ፡፡ አንድ ቀን አንድ መነኩሴ ወደ ዜን መምህር መጣና ስለ ዜን ቡድሂዝም እንዲያስተምረው ጠየቀው፡፡ መምህሩም፡- «ሰው በማይኖርበት ሌላ ቀን ተመልሰህ ና፤ ያን ጊዜ አስተምርሃለሁ» አለው፡፡ መነኩሴውም ከብዙ ቀን እልህ አስጨራሽ ጉጉትና መመላለስ በኋላ መምህሩን አገኘው፡፡ «ዛሬ ማንም የለም፤ የዜን ሚስጥርን አስተምርሃለሁ ብለህ ቃል ገብተህልኛል» አለው፡፡ መምህሩ፡- «ጠጋ በልና በጆሮህ ልንገርህ» አለው፡፡ መነኩሴውም ይኸንኑ አደረገ፡፡ «ዜን በቃል ሊገለፅ የማይችል ነገር ነው» በማለት መምህሩ ስለ ዜን አስተማረው፡፡ እንግዲህ የዜን ተከታዮች የዝምታ እምነት እስከዚህ ድረስ ነው፡፡ ይሁንና አንዳንድ ፈላስፎች፡- «ዜን በቃል ሊገለፅ የማይችል ነገር ነው ማለት በራሱ ዜንን መግለፅ ነው» በማለትም ይተቻሉ፡፡

በሌላ ቀን ደግሞ አንድ ተማሪ ወደ ዜን መምህር መጣና «በቃላት ንግግር ሳልጠቀም ነገሮችን መማርና መረዳት የምችልበትን መንገድ አሳየኝ» አለው፡፡ መምህሩ «በል ቃላት ሳትጠቀም ጥያቄህን ጀምር» አለው፡፡ ነገሩ እዚያ ላይ አበቃ፡፡ ዴይስ ሱዙኪ እንደሚነግረን፡- «የዜን መምህር ማለት የዛፍ ቅርንጫፍ በጥርሱ ነክሶ የተንጠለጠለ ሰው ማለት ነው፡፡ ለአንተ ጥያቄ መልስ አይሰጥም፤ ምክንያቱም መልስ ለመስጠት አፉን ሲከፍት ይወድቃልና፡፡ ስለዚህ የዜን ቋንቋ ተግባር እንጂ ቃላት አይደለም» ይለናል፡፡

የዜን ተከታይ መሠረቱ የቱንም ያህል ዝምታ ነው ቢባልም መምህሩ



Scanned by CamScanner

ተማሪውን የሚያስተምርበት ዘይቤ በጃፓንኛ ሞንዶ ይባላል። ይህም በቃለ ምልልስ መምህሩ ተማሪውን ወደ ሳቶሪ ደረጃ የሚያደርስበት ነው። ስለ ዜን እምነትና ፍልስፍና ይበልጥ ያሳያሉ ያልኳቸውን ወጎች ትንሽ ልጨምር።

አንድ ቀን አንድ የዜን መነኩሴ የሆነ ወጣት ቶኪዮ ከተማ የሚገኝ ዩኒቨርስቲን ጎብኝቶ ወደ መምህሩ ሲመለስ የክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ አንብቦ ያውቅ እንደሆነ መምህሩን ጠየቀው። አንብቦ እንደማያውቅ ሲገልፅለት ተማሪው እንዳነበበና አንድ ይዞ እንደመጣም ነገረው። መምህሩም «እስኪ ጥቂት አንብብልኝ» አለው። ተማሪውም ከማቴዎስ ወንጌል ውስጥ በመለወጥ ተራራ (Mountain of Transfiguration) የተፈፀመውን አነበበለትና እየሱስ ስለ ምድር አበቦች የተናገረውን ማንበብ ሲጀምር መምህሩ አቋርጦት ተነሳና «አየህ! ይኸን ቃል የተናገረው ሰው ማንም ቢሆን በጣም አዋቂ ነው፤ እኔም እስከዛሬ ያስተማርኩህ ይኸንኑ ነበር» በማለት ጥሎት ሄደ።

በሌላ ጊዜ ደግሞ አንድ የዜን እምነትና ፍልስፍና ተከታይ መነኩሴ በበረሃ ውስጥ ጠፋ። በረሃብና በውኃ ጥም እጅግ ተንገላቶ በነበረበት ሰዓት ከአንድ እንደ እሱ በበረሃ ጠፍቶ ከሚንገላታ መንገደኛ ጋር ተገናኙና ጉዞ ጀመሩ። በጣር ጉዞ ላይ እንዳሉ ወደ አንድ ትልቅ ቅጥር ደረሱ። ቅጥሩ ቁመቱ ትልቅ በመሆኑ በውስጡ ያለውን ለማየት ባይቻላቸውም የውኃ ፏፏቴና የወፎች ጫጫታ በግልፅ ይሰማቸው ነበር። በአጥሩ ላይም አሻግሮ ፍሬያቸውን ያንዠረገጉ ዛፎች ይታያሉ። መንገደኛው በቅፅበት በአጥሩ ላይ ዘሎ በመውጣት የበረሃ ጓደኛውን እንኳን ለመሰናበት ትዕግስት አጥቶ ወደ ቅጥሩ ውስጥ ለመዝለል ተዘጋጀ። ዜኑ ግን ወደ በረሃ ተመልሶ ጉዞውን ጀመረ። ይሄን ጊዜ ቅጥሩ ላይ ቆሞ የዜኑን ድርጊት ሲመለከት የነበረው ሰው «ወዴት ነው የምትሄደው?» በማለት ጮኸ። «በበረሃ ላይ እንደኔው የጠፉ ጓደኞቼን ይዤ ልመጣ ነው...» አለው። «እርግጠኛ ነኝ በዚያ ትሞታለህ!» በማለት

በድጋሚ ጮኸ፡፡ ዜኑም «ብቻዬን ገነት ከምገባ ከሰው ጋር ገሃነም ውስጥ ልኑር» በማለት ጉዞውን ቀጠለ፡፡

ዲይስ ሱዙኪ አንዱና ዋነኛው የሰው ልጅ ችግር «ቃላትን ከእውነታው ጋር ማምታታት ነው» ይለናል፡፡ ይሄንኑ የዜን ሃሳብ በምሳሌ ሲገልፅልን፡- «ዓሣ የምንይዝበት ቅርጫት ዓሣ እስኪያዝልን ድረስ ጥሩ ነው፡፡ ነገር ግን ዓሣውን ለመመገብ ጠረጴዛችን ላይ ካደረሰልን በኋላ ስለ ቅርጫቱ መጨነቅ ምን ይሉታል?» በማለት ጠይቆ «የቃላትም ሥራ ይኸው ነው፡፡» ብሏል፡፡ የዜን የፍልስፍና ወግ ሰፊ ነውና አሁንም ልቀጥል፡፡

አንድ ቀን የዜን መምህር ከተማሪው ጋር ሲሄድ የቡድሃ ምስል ያለበት ቦታ ይደርሳሉ፡፡ ተማሪው በቅፅበት ለቡድሃ ምስል ተደፍቶ መስገድ ሲጀምር መምህሩ ተጠጋና በጥፊ አጮለው፡፡ ተማሪው «መምህር ሆይ፤ ለቡድሃ መስገድ የሚያኮራ አይደለምን?» በማለት ሲጠይቀው «እሱማ ነው፤ ነገር ግን የሚያኮራንም ነገር ለመተው መቻል እጅግ የሚያኮራ ነው» አለው፡፡

በሌላ ቀን አንድ መነኩሴ ወደ ዜን መምህር መጣና... «ክረምት ይወጣል፤ በተራው ደግሞ በጋ ይመጣል፤ ከነዚህ ማምለጥ የሚቻለው እንዴት ነው?» በማለት ጠየቀው፡፡ መምህሩ «ለምን ክረምት ሲሆን በሙቀት ወደምትቃጠልበት በበጋ ደግሞ በቅዝቃዜ ወደምትንቀጠቀጥበት ቦታ አትሄድም» አለው፡፡ መነኩሴው «በእርግጥ እሱ የተሻለ ነው፤ መምህር ሆይ እንደሱ ዓይነት ቦታ የትነው የማገኘው?» በማለት ጠየቀ፡፡ የመምህሩ መልስ አጭር ነበር፡- «ገሃነም»፡፡

«ዜን ምንድነው?» በማለት ተማሪው ላነሳው ጥያቄ ከመምህሩ ያገኘው መልስ «ዜንማ አሁን የተናገርከው ነው» ነበር፡፡ ዜን በየቀኑ ከምትናገረው፣ ከምትበላው፣ ከምትጠጣው ሌላው ይቅርና ከእንቅልፍህም ጋር በአልጋህ ላይ የተገናኘ ነው ይላል፡፡

አንድ ማለዳ ሁለት የዜን ቡድሂስቶች ወደ አንድ መንደር ጉዞ



Scanned by CamScanner

ጀምረው ሳለ በመንገዳቸው ላይ ያለው ወንዝ ዳር እንደደረሱ የሴት ልጅ ጩኸት ሰምተው ወደዚያው ይሮጣሉ፡፡ በዚያም አንዲት ወጣት ሴት የወንዙ ውኃ እየገፈተረ ወደ መኻል ሲወስዳት አስተዋሉ፡፡ በቅፅበት አንዱ ዜን ወደ ወንዙ ዘሎ በመወርወር እየዋኘ ደርሶ ተሸክሞ በማውጣት ከሞት አዳናት፡፡ ሁለቱ ዜኖች ጉዞአቸውን ቀጥለው ትንሽ እንደሄዱ ከወንዙ ዳር ቆሞ ይመለከት የነበረው ዜን ማጉረምረም ጀመረ፡፡ ወዳያውም «እኛ የዜን ቡድሃ ተከታዮች መቀደስ እንዳለብን ሴትን በእጃችን እንኳን መንካት እንደሌለብን ታውቃለህ፡፡ እንዴት ሴት ልጅ በዛ ላይ ራቁቷን ትሸከማታለህ?» በማለት ጠየቀው፡፡ «ወንድሜ እኔ የተሸከምኳትን ሴት ወንዙ ዳር ነው ትቻት የመጣሁ፤ አንተ ግን አሁንም ተሸክመሃታል» በማለት መለሰለት፡፡

የምዕራባውያን የእምነት ፍልስፍና «አንድ ሰው የእውቀት ዛፍ የምታበቅለውን ፍሬ በላ፤ ክፉንና ደጉንም ለየ (አወቀ)» ነው፡፡ በዜን ቡድሃ እምነት ደግሞ የሰው ታሪኩ የሚጀምረው ካላዋቂነት ነው፡፡ ከእውቀት ዛፍ እንጂ የእውቀትን ፍሬ አልበላም ይላሉ፡፡ ዴይስ ሱዙኪ እንደሚለን ደግሞ «ወደ ዜን እምነት ስትመጣ አላዋቂነትህ እጅግ ጎልቶ ይሰማሃል» ይላል፡፡

<u>በዜን እምነትና ፍልስፍና እምነትህ አዕምሮህን ካልገዛ፤ አዕምሮህ እምነትህን መግዛት ይጀምራል</u>፡፡ የዜን መምህር አንድ ቀን ለተማሪዎቹ «ቡድሃ ማለት የእናንተ አዕምሮ ነው» በማለት አስተማራቸው፡፡ ይህን የሰማ ተማሪ በነጋታው የተማረውን ሊያሰላስል ሰው ወደማይደርስበት ዱር ሄደ፡፡ በዚያ ዱር ውስጥም ይህንኑ ሲያሰላስል ሃያ ዓመት አሳለፈ፡፡ አንድ ቀን የዜን መምህሩ ሌላ ተማሪ በዚያ ጫካ ሲያልፍ አገኘውና «እባክህን የዜን መምህሩ ዋና ትምህርት አሁን ምንድነው?» ብሎ ጠየቀው፡፡ አዲሱ ተማሪም «ቡድሃ ማለት የእናንተ አዕምሮ አይደለም የሚል ነው፤ እኔም ይሄን ላሰላስል እየሄድኩ ነው» አለው፡፡

የዜን እምነት መሠረቱ ራስህን እንደሞተ መቁጠር ነው ብለናል፡፡



Scanned by CamScanner

ዴይስ ሱዙኪም ይህንኑ ሲያጠናክርልን «ሰው በእውነት ነፃ የሚሆነው ራሱን እንደሞተ ሲቆጥረው ነው» ብሏል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የዜን መምህር ለተማሪዎቹ ሲያስተምር ያካፈላቸው ነው ተብሎ በሚታመንበት ወግ የዜን ፍልስፍና ጉዞአችንን እናጠቃል።

አንድ ገበሬ ዕድሜው ገፍቶ እርሻ ለመዋል ጉልበቶቹ ደከሙ። በዚህ ምክንያት ጊዜውን ከደጅ ተቀምጦ ማሳለፍ ጀመረ። ይህን የተመለከተ የገበሬው ልጅ በአባቱ ተቀምጦ መዋል ደስተኛ አልሆነም። «እንግዲህ አርጅቷል፤ ስለዚህ እኔ እንዳበላው ነው የሚጠብቅ፤ ነገር ግን በራሱ ከእንግዲህ ምንም ጥቅም የለውም» በማለት አሰበና ከእርሻው ሲመለስ የሬሳ ሳጥን ገዝቶ መጣ። በማግስቱም አባቱን ከእንቅልፉ ቀስቅሶ «በል ሳጥኑ ውስጥ ግባ» አለው። ሽማግሌው አባትም የታዘዘውን አደረገ። ልጅም አባቱን የከተተበትን የሬሳ ሳጥን ተሸክሞ ወደ ተራራ ጫፍ ላይ ወጣ። ከዚያ ሳጥኑን ቁልቁል ለመወርወር ወጣቱ ሲዘጋጅ የሽማግሌው አባቱን «አንዴ ክፈትልኝ!» የጥሪ ድምፅ ሰማ። ልጅም ሳጥኑን ከፍቶ አባቱን ምን እንደሚፈልግ ጠየቀው። አባትም «ልጄ ሆይ፤ ይህን የመሰለ የሬሳ ሳጥን ወደ ገደሉ ጥለህ ከምታበላሸው እኔን አውጣና ወርውረኝ፤ ሳጥኑን ልጆችህ ለአንተ ይጠቀሙበታል» አለው።



Scanned by CamScanner

# ለአንዱ የገነት መግቢያ፣ ለሌላው የገሃነም ደጅ ነው

«ጄምስ ቻፌንስ በአሜሪካ ሰሜን ካሮሊና ግዛት የሚኖር ሀብታም ገበሬ ነበር:: ከመሞቱ ጥቂት ዓመታት በፊት እ.ኤ.አ በ1905 በምስክሮች ፊት ኑዛዜውን አስነብቦ ፈረመ:: ከኑዛዜው ቃል መረዳት እንደሚቻለው ቻፌን ከነበሩት አራት ልጆች መካከል ለሦስተኛ ልጁ ለማርሻል የነበረውን ሀብት በሙሉ እንዲወርስ የሚፈቅድ ነበር:: በ1921 እ.ኤ.አ ቻፌን ሞተና በኑዛዜው መሠረት ማርሻል የአባቱ ሀብት ሙሉ ወራሽ ሆነ:: ይሁንና ከአራት ዓመት በኋላ ማለትም በ1925 እ.ኤ.አ የቻፌን ሁለተኛ ልጁ የሆነው ጄምስ (በአባቱ ስም ነው የሚጠራው) በህልሙ አባቱ መጥቶ እንዳነጋገረው ገልፆ በንግግራቸውም ወደ እናታቸው ቤት ሄዶ አዘውትሮ ይለብሳት የነበረውን ኮት እንዲፈትሽ እንዳዘዘው ተናገረ:: በአባቱ ትዕዛዝም መሠረት ወደ እናታቸው ቤት ሄዶ ኮቱን መፈለግ ሲጀምር በአባታቸው ቃለ ኑዛዜ መሠረት ኮቱም ለማርሻል እንደተሰጠ እናቱ ነገረችው:: ጄምስ ምስክሮች ይዞ ወደ ማርሻል ቤት በመሄድ ኮቱን መፈለግ ጀመረ:: ከጥቂት ፍለጋ በኋላ የአባቱ ኮት ተገኘና ኪሱ ሲበረበር በአንዱ ውስጥ የተጠቀለለ ወረቀት ተገኘ:: በወረቀቱ ላይ ሁሉም እንደመሰከሩት የአባቱ ፅሁፍ ሰፍሮ ነበር:: እንዲህም ይነበባል:- «የአባቴ የነበረውን መፅሐፍ ቅዱስ ፈልጋችሁ ከዘፍጥረት መጽሐፍ



Scanned by CamScanner

ላይ 27ኛውን ምዕራፍ አንብቡት» ይላል:: በዚህም መሠረት ሀብቱ ለአራቱም ልጆች ሊካፈል ይገባል የሚል ክርክር ተጀመረ:: ይሁንና ውርስን ሙሉ በሙሉ ተቀብሎ የነበረው ማርሻል በጊዜው ሞቶ ስለነበር ሚስቱን መጠየቅ የግድ ሆነ:: የማርሻል ሚስትም በመስማማቷ ሀብቱ ለቀሪዎቹ ልጆች እንደ አዲስ ተካፈለ::»

እንግዲህ ጥያቄው ከሞት በኋላ ሕይወት ባይኖር የእነማርሻል አባት ቻፊን እንዴት ለጀምስ ነገሩን ሁሉ ሊገልጥለት ቻለ? የሚል ይሆናል::

ከዘመናችን የፍልስፍና ምሁራን አንዱ አንቶኒ ፍሊው በጉዳዩ ላይ በሰነዘረው አስተያየት:- «...ጀምስ አባቱ ከመሞቱ በፊት አስቀድሞ ነግሮት የነበረውን ለጥቂት ዓመታት ዘንግቶት ከዕለታት በአንድ ቀን ግን ነገሩን በተኛበት አስታወሰው፤ በህልሙ አባቱ ሲያናግረውም የተመለከተው ከዓመታት በፊት በእውን ሲነግረው የነበረውን ነው::... ለነገሩ የቻፊን ነፍስ በእውነትም ካለች ቦታዋ ገነት ካልሆነም ገሃነም ይሆናል እንጂ ምድር ላይ ምን ትሰራለች?... በጉዳዩ ላይ ለመፍረድ በዳኝነቱ ወንበር ላይ የተቀመጥኩት እኔ ብሆን ኖሮ ቻፊን ራሱ ቀርቦ ነገሩን ካላስረዳ የቀድሞ ኑዛዜው ፀንቷል ብዬ መፍረዴ አይቀርም ነበር» ብሏል::

መቼም ከፍልስፍናው ጎራ ተሰልፎ ለምን እሞታለሁ? ከሞትኩ በኋላስ የምሄድበት አለኝ? ብሎ ያልጠየቀ ፈላስፋ ማግኘት አይቻልም:: ብዙዎቹ ፈላስፎች «የምትሞተው የሰውነትህ ሴል ሕዋስ በዕድሜ ብዛት አልያም በበሽታ ስለሚሞት ነው፤ ሌላ ነገር የለም» ይሉናል:: ሌሎቹ ደግሞ «የምንሞተው ለሕይወት ሲባል እንደሆነስ?» በማለት ይጠይቁና «ሕይወት ሁልጊዜ ወጣትና አዲስ ሆና ለመገኘት ያረጀውን የመለወጫ ጥበብዋ ሞት ብቻ ነው» ይላሉ::

እንግዲህ ሞት አሮጌውን ማስወገጃና አዲሱን የመቀበያ ጥበብ ነው በማለት እንጀምርና ሞትና ከሞት በኋላ አለ የሚባለውን ነገር በመጠኑ እንመርምር::



Scanned by CamScanner

ሞትን ከዚያም በኋላ ሊኖር የሚችለውን ሕይወት በኒኮላይ ፌዶሮቭ እምነትና ፍልስፍና ማየት ብንጀምርስ፡፡ ታላቁ የራሽያ ፈላስፋ ኒኮላይ ፌዶሮቪች ፌዶሮቭ (1829 - 1903 እ.ኤ.አ) የዘላለማዊነት ወይም የፀረ ሞት ፍልስፍናን (Immortalist/Anti-death Philosophy) የመሠረተ ምሁር ነበር፡፡ ይህ ራሽያ በዘመናት ካፈራቻቸው ፈላስፎች ታላቁን ቦታ የሚሰጠው ፌዶሮቭ በምዕራቡ ዓለም እምብዛም ግምት የሚሰጠው አይሁን እንጂ ከእሱ በላይ በዓለም ታላላቅ ስም ያላቸው እንደ ዶስቶቪስኪ፣ ሌዎ ቶልስቶይ እና አፋንሲ ፌት ዓይነቶቹ ለፌዶሮቭ የነበራቸው ከበሬታና ግምት እጅግ ከፍተኛ እንደነበር በታሪክ ይጠቀሳል፡፡ ወደ ፌዶሮቭ እምነትና ፍልስፍና እንመለስ፡-

«በምድር ላይ ስኖር አንድ የተረዳሁት ነገር ቢኖር በሀብታምና በደሀ መካከል ካለው ልዩነት ይልቅ በተማረውና ባልተማረው መካከል ያለው እጅግ የሰፋ መሆኑን ነው» የሚለን ፌዶሮቭ፡- «የተማረው ከሥራ ይልቅ በማሰብ ላይ ይበረታል፤ ያልተማረው ብርታት ደግሞ ከማሰብ ይልቅ ሥራ ላይ ነው፡፡ ታዲያ የተማረውን ስለ ገነት ወይም ስለ ዘላለማዊ ሕይወት ብትነግረው 'መጀመሪያ ላስብበት' ይልሀል፡፡ አስቦበት ሲመለስ ደግሞ መልሱ 'ገነት የሚባል ነገር የለም፤ ይልቅ ገነትን እዚሁ ምድር ላይ እንስራው' ነው፡፡ ያልተማረው ለማሰብ ጊዜ ስለሌለው ገነት አለ የሚለው የአንተ ንግግር ለእሱ በቂው ነው፤ በዚያው እምነት ይኖራል፤ በዚያው እምነትም ይሞታል...» ፌዶሮቭ ይሄን ጠይቆ ከሞት በኋላ ስለሚኖረን ሕይወት እንዲህ ይላል፡-

«እኔ ለምሳሌ አንድ ሰው ነኝ፤ ማመን የምችለውም አንድ ነገር ነው፤ መሆንም የምችለው አንድ ነገር ነው፤ ገነት የሚገቡት ደግሞ የተመረጡት ናቸው፤ ካልተመረጥኩ የዘላለም እሳት ይጠብቀኛል፡፡ ትልቁ ጥያቄ ደግሞ ለመመረጥ የሚያበቃው መመዘኛ (Criteria) እንደ ሃይማኖቱ የተለያየ ከመሆኑ ላይ ነው፡፡ የአንዱ የገነት መግቢያ ለሌላው የገሃነም ደጅ ነው፡፡ ለአንዱ እግዚአብሔርን መምሰያ ለሌላው የሰይጣን ወንድምነት



Scanned by CamScanner

ይሆናል…

«እንደ እኔ እምነት ዘላለማዊ መሆንና እግዚአብሔርን መምሰል ከፈለግን የጋራ ገነት መፍጠሩ የተሻለ ይመስለኛል። የእሱ ፈጣሪዎች ደግሞ እኛ የተማርነው ነን» ይለናል።

«እንግዲያውስ ስለዘላለማዊነት ንገረን?» በማለት ፌዶሮቭ ተጠየቀ።

«እሱን እንድነግራችሁ መጀመሪያ አስቀድሞ የሞቱት ሲነሱ ማየት አለብኝ» ብሎናል።

«እግዚአብሔርን ስለመምሰልስ…?» ተባለ።

«ሁላችንም 'የምንመስለው ሳይሆን የምንሆነው' እንደ እግዚአብሔር ነው። ጨካኝም ብትሆን ደግ፤ ቁጡም ብትሆን ታጋሽ፤ የምትገድልም ብትሆን የማትገድል… እሱን ነው የምትሆነው… ምክንያቱም እግዚአብሔር ሁሉንም ነውና» ብሏል።

ፌዶሮቭ እግዚአብሔርን ስለመምሰል ባሰፈረው ሀተታ ደግሞ «እግዚአብሔር ስጋና ደም የለውም ትላላችሁ። እንግዲህ አስቀድሞ ሲፈጥራችሁ እሱን አስመስሎ ካልሰራችሁ እሱን መምሰል ለምን ፈለጋችሁ?» በማለት ይጠይቃል።

ስለ ፌዶሮቭ ፍልስፍና በሌላ ምዕራፍ ስለምንመለስበት በዚሁ እናቁምና ወደ ተነሳንበት ርዕስ ተመልሰን የሌሎቹን ፈላስፎች እምነት ደግሞ እንቃኝ። እ.ኤ.አ በ1937 ዓ.ም. በኦስትሪያ ቪዬና ላይ የተመሠረተው Vienna Circle of Logical Positivists መሪ የነበረው ሞሪትዝ ሽሊክ «ከሞት በኋላ ሌላ ሕይወት አለ» ለሚለው እምነት የራሱን ፍልስፍና እንዲህ አስቀምጦታል:-

«…በእርግጥ ለእኔ የሚፈጥርብኝ ስሜት የተለየ ነው። ምክንያቱም ከሞት በኋላ ሕይወት ካለ በቀብሬ ስነስርዓት ላይ የእኔ መገኘት አይቀሬ ይሆናልና። የሚቀፈው ነገር ታዲያ ስጋዬ መሬት ውስጥ ሲገባ ቆሜ ማየቴ ነው። ለማንኛውም ይሄንን ነገር በትዕግስት ጠብቄ ማየቴ አይቀርም» ብሏል።



Scanned by CamScanner

ከእሱ ቀጥሎ ይሄንን ተመሳሳይ ጉዳይ ያነሳው ጆን ዊዝደም ነበር:: እሱም ሲናገር:- «የራሴ ቀብር ላይ መገኘት ምን ሊመስል እንደሚችል መገመት እችላለሁ:: ወዳጆቼ በጥቁር ሱፍና ከረባት አጊጠው፣ አበቦችን ደርድረው፣ በሬሳ ሳጥን ውስጥ ከአበቦች ስር የሚታይ ፊት (ምናልባት ፊቱን ሳይ እደነግጥ ይሆናል)... » ብሏል::

አንቶኒ ፍሊው የሁለቱን ፍልስፍናዎች ማጠቃለያ ሲሰጠን:- «ከሞት በኋላ ሕይወት ካለህ በራስህ ቀብር ላይ ትገኛለህ... እንግዲህ በቀብርህ ላይ ከተገኘህ ደግሞ አልሞትክም ማለት ነው... ከመሞትህ በፊት አስቀድሞ የሞተውን ጓደኛህን እንደቀበርክ ሁሉ ዛሬም ራስህን እየቀበርክ ነው፤ የሚያሳዝነው ግን በቀብርህ ላይ መገኘትህን ማንም አለማወቁ ነው» ይለናል::

ይህ የገነት መግቢያ መስፈርት (criteria) ግራ ያጋባቸው ፈላስፎች ሌላ የሚሉትም አለ:- «ሂትለር በሚሊዮን የሚቆጠሩ አይሁዶችን የፈጀ ነው:: እንደዕድል ሆኖ ከመሞቱ በፊት ለቄስ ሃጢያቱን ቢናዘዝ ኖሮ ገነት መግባቱ አይቀርም ነበር:: የሚያሳዝነው ደግሞ እሱ የገደላቸው አይሁዶች መስፈርቱን ሳያሟሉ በመሞታቸው ገሃነም ይገባሉ:: ከዚህ በኋላ ሂትለር ከእግዚአብሔር ጋር አይሁዶች ደግሞ ከሰይጣን ጋር ዘላለማዊውን ሕይወት ይገፋሉ ማለት ነው::»

የሰው ልጅ የሚፈራው ሞቱን ሳይሆን ከሞት በኋላ የሚኖረውን «ሕይወት» ነው የሚሉ ምሁራን ብዙ ናቸው:: ለምሳሌ ታላቁ ደራሲ ቪክቶር ሁጐ «የሰው ልጅ እንደራሱ ሞት የሚያስጨንቀውና የሚያስፈራው ነገር የለም:: ይህ ፍርሃት ደግሞ ሃይማኖትን ፈጥሮአል» ይላል:: የፈረንሣይ ንጉስ የነበረው ናፖሊዮን በናፖርትም በአንድ ወቅት ሲናገር:- «ሰዎች ከአሁኑ የምድራዊ ሕይወታቸው ይልቅ ለሁለተኛው ይጓጓሉ፤ እኔም ለዚህ ነው ሕዝቤ ጳጳስ ባይኖረው ኖሮ አንድ ጳጳስ እፈጥርለት ነበር የምለው» በማለት ተሳልቋል::

እዚህ ላይ ዛሬ በፍልስፍና እምነታቸው ከሚያስደነግጡን በባሰ



Scanned by CamScanner

መልኩ ድንቅ ፈላስፋዎች በኢየሱስ ዙሪያም እንደነበሩ መመስከር ስለሚቻል አንድ ሁለቱን እንመልከት፡-

*«እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደእኔም እወስዳችኋለሁ። ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ፣ መንገዱንም ታውቃላችሁ። ቶማስም፡- ጌታ ሆይ ወደምትሄድበት እናውቅም እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው።» (ዮሐ.14:4-5)* (ሰረዝ የተጨመረ)

ለሦስት ዓመት ከስድስት ወር ከኢየሱስ ጋር አብሮ መከራን የተካፈለው ሰውዬ ከምድራዊ ሕይወት ሌላ አዲስ ሕይወት እንደሚኖር አያውቅም ነበር። ለዚህም ነው፡-*«ሌሎቹ ደቀመዛሙርት፡- ጌታን አይተነዋል አሉት። እርሱ ግን፡- የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ ካላገባሁ አላምንም አላቸው።» (ዮሐ.20:25)* (ሰረዝ የተጨመረ)

ይህ ሰው ታዲያ ከሶፊስቶች በምን ይለያል? የሶፊስቶች እምነት መገለጫ፡- «አንድ ነገር እውነት የሚሆነው ለስሜት ህዋሳትህ መልስ ከሰጠህ ብቻ ነው» ይላሉ። ይኸው የፍልስፍና እምነት በቶማስ ልብ ውስጥ ነፍስ ዘርቶ ይታያል።

የሌላው ደቀመዝሙር የፊልጶስ ጥያቄ ደግሞ ኢየሱስን ብቻ ሳይሆን ፈላስፎቹንም ያስገረመ ነበር፡-

*«እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ፣ አይታችሁትማል አለው።*

*ፊልጶስ፡- ጌታ ሆይ፣ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው።» (ዮሐ.14:7-8)* (ሰረዝ የተጨመረ)

«ታዲያ እንዲህ ዓይነቱ ፈላስፋ ዛሬ የሚገኘው ገነት ይሆን?» በማለት የዘመናችን ፈላስፎች ይጠይቃሉ።

የፍልስፍናው ዓለም ምሁራን ሌላም ጥያቄ አላቸው፡- «ለመሆኑ ከሞት በኋላ ሕይወት አለ ብለን ከተቀበልን ወዳጃችን ሲሞት የምናለቅሰው



Scanned by CamScanner

ለምን ይሆን? ለጥቂት ዓመታት ተለያይተን ስለምንኖር? ወይስ ከሞት በኋላ ሕይወት ለመኖሩ እርግጠኛ ባለመሆናችን? አልያም ደግሞ የወዳጃችንን መሄጃ (ገነት ወይም ገሃነም) ስለማናውቅ፤ የእኛንም እርግጠኞች ስላልሆንን ከሆነስ?»

እዚህ ላይ የአሪስቶትልን ፍልስፍና ለዚህ ሃሳብ ሳያነሱ ማለፍ የተገባ አይሆንም። የአሪስቶትል የፍልስፍና ሃሳብ ካታርሲስ (Catharsis) ስሜትን ማጥለል ይባላል። ስለካታርሲስ ቲዎሪ በአጭሩ ላስቀምጥ፡-

«አንድ ሰው የቅርብ የሆነ ዘመዱ ወይም ወዳጁ ሲሞት የሚያለቅሰው ለሟቹ ሰው በማዘን ሳይሆን በማዘኑና በማልቀሱ ግን ራሱ የሚያገኘው እፎይታ (relief) ስለአለ ነው። በለቅሶውም የራሱ ሃጢያትና ክፋት ካሳ እንደሚያገኝለት ያምናል።» በሌላ አገላለፅ አሪስቶትል ይህንኑ ሲያስረዳን፡- «አንድ ንፁህ ሰው በሞት ሲቀጣ ብትመለከትና ብታለቅስ፤ ንፁሁ ሰው ያለጥፋቱ በመሞቱ ሳይሆን ያለቀስከው ራስህን በሰውዬው ቦታ በማስቀመጥ 'እኔ በዚህ ሰው ቦታ ብሆንስ?' በሚል ስሜት ስለምትንገላታ ነው። እንግዲህ በሰው ሞት ውስጥ የራስህን ሞት ማየት ካታርሲስ ይባላል» ይለናል።

የእሱ አስተማሪ የነበረው ፕሌቶ ደግሞ ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወት ሲናገር፡- «የእኔ ዘላለማዊነት በገነት ሳይሆን በሰዎች ልብ ውስጥ ነው። ምክንያቱም አስተማሪው በምድራዊ ሕይወቱ ከሚያፈራቸው ይልቅ ትቶት በሚያልፈው ሥራው የሚፈጥራቸው እጅግ ይበዛሉና» ብሏል።

በዚህ ዓይነት ከቀጠልን ስለዘላለማዊነት (eternity) በፈላስፎቹ የተሰነዘሩትን አስተያየቶችና ትንታኔዎች ለማየት በራሱ ዘላለም ሳያስፈልገው ይቀራል?



Scanned by CamScanner

# ገሃነም የገባኸው በእግዚአብሔር ቁጣ ሳይሆን በራስህ ምርጫ ነው

የዚህን ምዕራፍ የፍልስፍና ወግ በዚህች ቀልድ ብንጀምርስ፡-

አንድ የፍልስፍና ፕሮፌሰር ተማሪዎቹን የመጨረሻውን ዓመት ፈተና ለመፈተን ወደ ክፍሉ ገባ:: በክፍሉ ውስጥ ገብቶም መጀመሪያ ያደረገው ነገር ቢኖር ወንበሩን ጠረጴዛው ላይ መጫን ነበር:: «ለአንድ ዓመት ያስተማርኳችሁን የፍልስፍና ትምህርት መሠረት በማድረግ የዚህን ወንበር አለመኖር አረጋግጡልኝ» በማለት ፈተናውን ለተማሪዎቹ አቀረበ::

ብዙዎች መፃፍና ብሎም የፃፉትን ማጥፋት ለሰዓታት ተያያዙት:: አንዳንዶቹ ተማሪዎች የወንበሩን አለመኖር ለማሳየት የልብወለድ ድርሰት የሚያህል ፅሁፍ ፃፉ:: ከመሃከላቸው አንዱ ተማሪ ግን መልሱን ለመፃፍ የፈጀበት ጊዜ ሦስት ሴኮንድ ነበር::

በሳምንቱ ፕሮፌሰሩ የፈተናውን ውጤት ይዞ መጣ:: ከዚያ ተማሪ በስተቀር ሁሉም ወድቀዋል:: የተማሪው መልስ እንዲህ የሚል ነበር፡-

«የትኛው ወንበር?»

* * *



Scanned by CamScanner

ብዙውን ጊዜ ፍልስፍና በባዶ ነገር የተሞላ ቅዠት አድርገው የሚመለከቱት በርካታ ናቸው። በተለይም ደግሞ ፍልስፍና ግላዊ እምነትን የመንካትና ብሎም ጥርጣሬ ውስጥ የመጣል ባህርይው እስከመጠላት አድርሶታል። ለመሆኑ እምነትን መሠረት ያደረገ ፍልስፍናስ የለም? ለዚህ መንደርደሪያ ይሆነን ዘንድ ቀጥሎ የምናየው ከፍልስፍናው ጐራ ስለሚመደቡት ነገር ግን ፍልስፍናቸውን በእምነታቸው ላይ ስለመሠረቱት የሚስቲሲዝም አራማጆች ይሆናል። በምዕራባውያን ዘንድ ስለ ሚስቲሲዝም ስናነሳ በተለይ Perennial Philosophy የሚያነሳው ሃሳብ እምነቱን በሰፊው የሚያብራራና የሚያራምድ ሆኖ ተገኝቷል። የዚህ የPerennial Philosophy መስራች የሆነው Aldous Huxley *"The Cloud of Unknowing"* በሚለውና በተለይ በእንግሊዞች ዘንድ በሚታወቀው መንፈሳዊ ጽሑፉ የሚስቲሲዝምን መንፈሳዊ ሚስጥራት ሊያሳየን የሞከረ ሰው ነው። እንደ ሀክስሌይ ሐሳብ ዛሬ የምናያቸው መንፈሳዊ ልምምዶችና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዛት በእርግጥ ለእኛ ያገለግላሉን? ተብሎ ሲጠየቅ መልሱ «አትጠራጠሩ» የሚል ነው። ሀክስሌይ ሃሳብ ልገፋበት ስለማልፈልግ ስለሚስቲሲዝም አራማጆችና በተለይም በዚህ የእምነት ፍልስፍና ትልቅ ቦታ ስለሚሰጠው St. John of the Cross ማንሳት እወዳለሁ።

የዘመኑ ፈላስፎች «አለአግባብ ትርጉም ተሰጥቶት የባከነ ቃል ቢኖር ሚስቲሲዝም ነው» ቢሉም ከተራና የተለመደው ትርጉሙ እንጀምርና ይህን ሚስቲሲዝም ጠለቅ ብለን ለማየት እንሞክር።

*«በተመስጦ በሆነና በፍቅር ነፍስህ ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታና ብሎም ጥልቅ በሆነ አንድነት ውስጥ ስትገባ ይህ እምነት ሚስቲሲዝም ይባላል።»*

እንግዲህ ይህ አንድነት ነፍስህን ከፍ ወደአለ ደረጃ በማድረስ ከእግዚአብሔር ጋር በመገናኘት ብቻ አታቆምም፤ ነገር ግን ራሷም ወደ እግዚአብሔርነት ትለወጣለች፤ «በድርጊቷም እንደ እግዚአብሔር



Scanned by CamScanner

ትሆናለች» እንደ ማለት ነው ይላሉ የሚሲቲሲዝም አራማጆች:: ስለዚህም «ተፈጥሮ በራሷ እውነታ (Reality) አይደለችም፤ የተፈጥሮን እውነታ ለማየት ከፈለግህ ሚስቲሲዚም የተሻለው መንገድ ነው» ይሉናል ::

ከሚስቲሲዚም አራማጆች አንዱና ታላቅ ቦታም የሚሰጠው ቅዱስ ዮሐንስ (St. John of the Cross 1542-1591) ነው:: የዚህ ሰው ታላቅ ሥራ ተደርጎ የሚወሰድለት «The Ascent of Mount Carmel» የሚለው ፅሁፋ ነው:: Ascent የሚለው ቃል ማሳረግ እንደማለት ነው:: Mount Carmel ደግሞ የቀርሜሎስ ተራራ በሚል ስያሜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናውቀውና ነብዩ ኤልያስ የሐሰተኛ ነቢያት ጣኦታትን ለማፈራረስ እውነተኛውን እግዚአብሔርን ለመጥራት መስዋዕቱን ያሳረገበት ቦታ ነበር:: ቅዱስ ዮሐንስ በተለይ በዚህ መጽሐፋ የዚህን ቦታ ክስተት ያስቀመጠው በግጥም ሲሆን በድርጊቱ ውስጥ እንዴት ነፍስ ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ሆና በራሷ እንደ እግዚአብሔር መስራት እንደምትችል ሊያሳየን ሞክሯል::

*«ኤልያስም:- እስራኤልን የምትገለባብጥ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ትታችሁ በአሊምን የተከተላችሁ አንተና የአባትህ ቤት ናችሁ እንጂ እኔ አይደለሁም... እስከመቼ ድረስ በሁለት ሃሳብ ታንከሳላችሁ? እግዚአብሔር አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ፤ በአል ግን አምላክ ቢሆን እርሱን ተከተሉ አለ... መስዋዕተ ሰርክ በሚቀርብበት ጊዜ ነብዩ ኤልያስ ቀርቦ:- አቤቱ የአብርሃምና የይስሐቅ የእስራኤልም አምላክ ሆይ፣ አንተ በእስራኤል ላይ አምላክ እንደ ሆንህ እኔም ባሪያህ እንደ ሆንሁ <u>ይህንም ሁሉ በቃልህ እንዳደረግሁ ዛሬ ይገለጥ...</u> የእግዚአብሔርም እሳት ወደቀች፣ የሚቃጠለውን መስዋዕቱንም እንጨቱንም ድንጋዮቹንም አፈሩንም በላች፤ በጉድጓዱ ውስጥ ያለውን ውሃም ላሰች...» (1ኛ ነገሥ. 18:20-40)* (ሰረዝ የተጨመረ)

ቅዱስ ዮሐንስ በዚህ ታሪክ ሊያሳየን የሚሞክረው የኤልያስ ነፍስ በራሷ እንደ እግዚአብሔር መሆኗን ነው:: «ነፍሱ ከእግዚአብሔር ብርሃን



Scanned by CamScanner

ጋር ተዋህዳ በጨለማው ምድር ላይ የኃይል ብርሃንን ፈንጥቃለች፡፡ ይህ ማለት ግን የኤልያስ ነፍስ እግዚአብሔርን ሆናለች ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም በፈጣሪና በተፈጣሪ መካከል ያለው ልዩነት ይገባናልና፡፡ ነገር ግን ነፍስህ በፍቅርና በፍፁም ፍቃደኝነት ከመለኮታዊው ፍቃድና ፍቅር ጋር ስትዋሀድ ወይም ለመለኮታዊ ኃይልና ፍቅር ማለፊያ ስትሆን ያንጊዜ በነፍስህ የእግዚአብሔርን ስራ ትገልጣለህ፤ ወይም ነፍስህ እንደ እግዚአብሔር ትሆናለች» ይለናል ቅዱስ ዮሐንስ፡፡

ይህንኑ በምሳሌ ሲያብራራልን፡- «በቤትህ መስተዋት ትይዩ ፀሐይ ወጥታለች እንበል... የቤትህ መስተዋት ደግሞ ያደፈና የቆሸሸ ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ የፀሐይዋ ጨረር ነፀብራቅም የሚያስጠላ ወይም እስከነአካቴው የማይታይ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የፀሐይዋ ጨረር በቆሻሻው ይዋጣልና፡፡ ነገር ግን መስተዋቱ ከቆሻሻ የፀዳና ንፁህ ከሆነ የፀሐይዋን ጨረር እንደአመጣጡ ያንፀባርቀዋል፤ ያሳልፈዋልም፡፡ ከቤት ውጭ ነፀብራቁ፤ ከቤት ውስጥ ደግሞ ብርሃኑ በሚገባ ይታያል፡፡ ነፍስህም እንደዚህ መስተዋት ነች፡፡ እግዚአብሔርን የመሆን መለኮታዊ ብርሃን ዕለት ዕለት በነፍስህ መስተዋት ላይ ይወርዳል፤ ነገር ግን እንደ ነፍስህ ሁኔታ ይዋጣል ወይም ይንፀባረቃል...

«እንግዲህ ነፍስህ ፀድታ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ ፀሐይ ስትሞቅ ራሷን ወደ እግዚአብሔርነት ታሸጋግራለች፤ እንደ እግዚአብሔርም ትሆናለች፡፡ ምክንያቱም የእሱ ልዕለ ኃያል ጥበብ ይገናኛታልና፡፡ አንድ ነገር ልብ በል! መስኮቱ ተፈጥሮውን ሳይቀይር የፀሐይዋን ጨረር በማንፀባረቅ ፀሐይን እንደመሰለ እንዲሁም ነፍስህ የእግዚአብሔርን ፀሐይ በማንፀባረቅ እንደ እግዚአብሔር ትሆናለች፡፡ ይህ የሚሆነው ግን ነፍስህ ከማንኛውም ምድራዊ ነገር ተላቅቃ ብቻዋን ለእግዚአብሔር በፍቅርና በንፅህና ስትቀርብ ነው...» ይለናል፡፡

«ይህ የነፍስ ንፅህና ደግሞ ከስጋ እጅግ የላቀ ነው» የሚለን ቅዱስ ዮሐንስ፡-«የእስራኤል ሕዝብ ከባርነት ወጥቶ ወደ ተስፋይቱ ምድር



Scanned by CamScanner

ሲጓዝ በምድረ በዳ ያንጎራጉር ነበር፡፡ መናው ሰለቸን! አስጠላን! አሉ (መና የመላዕክት እንጀራ መሆኑን ልብ ይበሉ)፡፡ ለዚህ ምክንያታቸው በግብፅ ምድር ይበሉት የነበረው የሥጋና የጣፋጭ ምግብ ትዝታ ነው፡፡ እንደዚሁ ነፍስህ ታላቁን እግዚአብሔርዊነት ልትቀዳጅ የምትችለው ከምድራዊውና ከተለመደው ተራ ነገር ስትነፃ ብቻ ነው...

«በምድር ላይ የለመድከው ብርሃን ለአንተ ታላቅ ከሆነ ነፍስህ ከዚያ በላይ ብርሃን ለማሰብ ያዳግታታል፡፡ ነገር ግን ነፍስህን እጅግ የላቀ ብርሃን እንዳለ ብታሳምናትና ብታለማምዳት ያ ብርሃን በአንተ ውስጥ ማለፍ ይጀምራል... ብርሃኑ በውስጥህ ሲያልፍ ደግሞ የምታንፀባርቀው ያንኑ ብርሃን ነው፤ እንደ እግዚአብሔር ሆንኩ ማለትም ይኸው ነው፡፡» በማለት ቅዱስ ዮሐንስ የሚስቲሲዚምን ምንነት ሊያሳየን ሞክሯል፡፡

የእምነቱ አራማጅ ፈላስፎች በጥቅሉ የሚነግሩን ደግሞ «በመሆን ውቅያኖስ ውስጥ ገብተህ መዋኘት ስትችል ፍጡር መሆንህ ያበቃና የፈጣሪ አንድ አካል መሆንህን ትረዳለህ፤ በዚያውም የሃይማኖት ምንነት ይገባሃል» ይላሉ፡፡

የሚከተሉትን ድንቅ የሚስቲሲዚም አራማጆችን አባባል መመልከቱ ይበልጥ ይጠቅማል እላለሁ፡-

* አምላኬ ሆይ! በእኔው እንባ ለራሴ እያለቀስኩ ከእግዚአብሔር ወደ እግዚአብሔርነት ሄድኩ፡፡

(Byazid of Bitsum)

* እኔነቴ እግዚአብሔር ነው፡፡ ከእኔነቴም አምላክ በቀር ሌላ አላውቅም፡፡

(St. Catherine of Genoa)

* ውስጣዊ ብርሃን ከምስጋናም ከነቀፋም በላይ ነው፡፡ ይህ ዓለም ዳርቻ እንደሌለው ሁሉ ውስጣዊ ብርሃንም በሰላምና በሙላት በውስጤ አለ... ብርሃንህን የምታጣው ስታሳድደው ብቻ ነው፡፡ ልትቆጣጠረው እንደማትችል ሁሉ ልታስወግደው እንደማትችል ግን ተረዳ፡፡

(Yung-Chia-Ta-Shih)



Scanned by CamScanner

* እንደ መንፈስ ስትሆን ከጊዜያዊነት ወደ ዘላለማዊነት ትሸጋገራለህ:: እንደ ስጋ ስትሆን ደግሞ ከዘላለማዊነት ወደ ጊዜያዊነት ትለወጣለህ:: እውነትን ማግኘት ማለት በመለኮታዊ ብርሃን እግዚአብሔርን ማግኘት ነው... ይህም ብርሃንን በብርሃን እንደመፈለግ ነው::

(Meister Eckhart)

* ገሃነም የገባኸው በእግዚአብሔር ቁጣ ሳይሆን በራስህ ምርጫ ነው::

(William Law)

* ነፍስህ የተያዘችበት ምድራዊ ነገር የቱንም ያህል ጥሩ ቢሆን ነፃነትን ያመጣልኛል ብለህ አታስብ::

(St. John of the Cross)

ሚስቲሲዚም ለሌሎቹ ፈላስፎችስ ምንድነው? ታላቁ የዘመናችን ፈላስፋ ዊል ዱራንት The Pleasure of Philosophy በሚለው መጽሐፉ:- «ሚስቲሲዚም ሃይማኖት አይደለም:: ነገር ግን ሞራላዊ ሕግ ነው:: የሞራል ሕግ ደግሞ የሚሰራው ለተማረው ክፍል ብቻ ነው፤ የተማረው ደግሞ የሞራል ሕግ አይፈልግም፤ ስለዚህም ሚስቲሲዚም 'ሙቀቱ የማይሰማህ በሩቁ የተቀጣጠለ እሳት ሆኖ ቀርቷል'» በማለት አስፍሯል::

ሌላው የዘመናችን ፈላስፋ ስለሚስቲሲዚም በተናገረው እናብቃ:-

«ለእኔ ሚሲቲሲዚም 'የሕንድን ፍልስፍና ስትወድ ከሩዝ በቀር ሌላ ምግብ የለም' እንደማለት ነው:: አንድ ቀን በባቡር በመጓዝ ላይ ሳለሁ በሰማያዊው ሰማይ ላይ ደመናው በመስመር በመስመር ተዘርግቶ የተፈጥሮን ውበት አሳየኝ:: በዚያን ወቅት የተፈጥሮ ውበት ስቦኝ ራሴን በሃሳቤ በደመናው ላይ እንዳንሳፈፍኩት ትዝ ይለኛል:: እንግዲህ እኔ እግዚአብሔር ሆኛለሁ ማለት ነው?»



Scanned by CamScanner

# «የሚገርመኝ የጓደኛዬ ሞት ሳይሆን የእኔ መኖር ነው»

እጅግ ታላላቅ የዘመናችን ጠቢባን፣ ፈላስፎች፣ ሳይንቲስቶች፣ የሃገር መሪዎች... ስለዚህ ሰው የሚናገሩት አንድና ተመሳሳይ ነገር ነው... ጥቂቱን እንመልከት:-

«ምድራችን ካፈራቻቸው ጭንቅላቶች ወደር የማይገኝለት::»

«እንዲህ ዓይነቱ አዕምሮ በመቶ ዓመት አንዴ ከተገኘ ለዚህ ምድር በቂ ነው::»

«አዋቂ ሳይሆን ራሱ እውቀት ነው::»

«የሰው ልጅ ሥልጣኔን የምመዝነው በእሱ ግኝት ነው::»

«የሰው ልጅ ሕይወት በእሱ እውቀት ሥር ወድቃለች::»

ይኸ ሰው ደግሞ ስለራሱ እንዲህ አለ:- «ዝናዬ በሰፊው እየና በመጣ ቁጥር የማልረባ እየሆንኩ መጣሁ፣ በእርግጥ ይኸ በሰዎች ዘንድ የተለመደ ነው...»

ተማሪዎቹንም መከረ:- «በውዳሴ እንዳትደክሙ በሥራ አምልኩ፣ ሌላ አማራጭ የለውምና:: ወጣት ሆኜ በጣም የምደሰትበት ነገር ቢኖር ማንም ስለእኔ ጉዳይ ሳይል በአንዲት ቦታ ተቀምጬ የራሴን ሥራና ምርምር ማድረግ ነበር:: ያ ሥራና ምርምር አሁን ምን እንዳተረፈል ተመልከቱ::»



Scanned by CamScanner

ታላቁ ሳይንቲስት አልበርት አይንስታይን ማርች 14/1879 ኡልም በምትባል አንዲት አነስተኛ የጀርመን ግዛት ተወለደ:: በ1880 እ.ኤ.አ. ከወላጆቹ ጋር ወደሙኒክ ተጉዞ የልጅነት ሕይወቱን በዚያ ጀመረ:: በ1894 እ.ኤ.አ. ቤተሰቡ ወደጣልያን ሲጓዝ አይንስታይን በሙኒክ ትምህርቱን ለመቀጠል ቢቀርም በዚያው ዓመት መጨረሻ ግን ትምህርቱን በማቋረጥ ወደጣልያን ተጉዞ ከቤተሰቡ ጋር ተቀላቀለ:: በጣልያን የፖሊ ቴክኒክ ት/ቤት ገብቶ ለመማር የመግቢያ ፈተና ወስዶም በመውደቁ አራጉ ካቶሊክ ት/ቤት ገብቶ ለመማር ተገደደ::

«የእኔ ሥራ በዚህ ዓለም ምስጢራት መደነቅ ነው» የሚለው አይንስታይን ከወጣትነት ጊዜው ጀምሮ ከፍተኛ የማሰብ ችሎታ እንደነበረው ከታሪኩ እንረዳለን:: አንዳንድ ወዳጆቹ ስለሕይወት በነበረው ፍልስፍና በመደነቅ የፈላስፋነት ካባም ሊደርቡለት ከጅለው ነበር:: ለፍልስፍና ትልቅ ግምትና አክብሮት የነበረው አይንስታይን:- «ፍልስፍናን ስታያት ማር በተለወሰ የዕውቀት ብዕር የተፃፈች ትመስላለች:: ለዚህም ነው ልታነባት ወደህ ስትጀምራት ግልፅና ጣፋጭ ትመስልና ወደውስጧ ጠልቀህ ስትገባ ግን የአንተን የአላዋቂነት እሬት ታስልስሃለች...

«ፍልስፍና በመጪው ዘመን የሰው ልጅ የሚመራባት ትሆናለች ብዬ አልገምትም፤ ለጥቂቶችና የላቀ አዕምሮ ላላቸው ግን ማረፊያ ቤተ መቅደስ እንደምትሆን አምናለሁ» ብሏል::

የአይንስታይንን የእምነት ፍልስፍና ላጤነ ግን ወዳጆቹ የፈላስፋነት ካባ ሊደርቡለት መከጀላቸው እምብዛም አይደንቀውም::

እ.ኤ.አ. በ1915 በእንግሊዞች ላይ ደርሶ ስለነበረው እልቂት የሚገልፅ አንድ ደብዳቤ ከስዊዘርላንዳዊ ጓደኛው ኤድጋር ሜየር ደረሰው:: ሜየር በደብዳቤው መጨረሻ:- «እግዚአብሔር እንግሊዞችን በመቅጣቱ ደስ ሊልህ ይገባል» አለው:: አይንስታይን ለጓደኛው በፃፈው የመልስ ደብዳቤ:- «ለምን ይህን ደብዳቤ እንደፃፍክልኝ አልገባኝም:: እኔ ከእግዚአብሔርም ሆነ ከእንግሊዞች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌለኝ በሚገባ

ታውቃለህ:: የሰውን ዘር በምድር ላይ እየቀጣ ያለው እግዚአብሔር ከሆነ ኃላፊነቱን ሊወስድ ይገባ ነበር፤ እግዚአብሔር የሚባል ነገር አለመኖሩ ግን በራሱ ይቅር አስብሎታል» በማለት መልሶለታል::

«እስከዛሬ በምድር ላይ ስኖር ለአንድም ቀን እሰ ብዬ አስቤው የማላውቀው ነገር እግዚአብሔር ነው» የሚለው አይንስታይን አንድ ወቅት በተማሪዎቹ:- «ራስህን ከእግዚአብሔር በላይ ታየዋለህ?» ተብሎ ተጠይቆ ነበር:: እሱም ሲመልስ:- «አዎን! ከኢየሱስ በላይ ማድረግ ከቻልኩ እንዴት ከእግዚአብሔር ላንስ እችላለሁ:: እኔ ከማደርገው በላይ ታደርጋላችሁ አላለም እንዴ?» በማለት መልሷል::

የቅርብ ጓደኛው አይሁዳዊው ሄይል ፍሬድማን:- «የአይሁድ ዘር ሆነህ በእግዚአብሔር አለማመንህ ምናልባት መጽሐፍ ቅዱስ ያለማንበብህ ውጤት ይሆናል?» በማለት ለፃፈለት ደብዳቤ ደግሞ በላከለት መልሱ «መጽሐፍ ቅዱስ ያነበብኩት ኮፒውን ነው:: በሙሴ የተፃፈው ኦሪጅናሉ ካለህ አባክህ ላክልኝ... በእግዚአብሔር መኖር የማላምን ኃይማኖተኛ መሆኔን ግን አሁንም የረሳኸው አይመስለኝም» ብሎታል::

አይንስታይን ሲበዛ ብቸኝነቱን የሚወድ ሰው ነበር:: «የሰዎች ወዳጅነት ጊዜያዊ እንደሆነ በሚገባ ተረድቻለሁ፤ ስለዚህም በሙቀቱ ላለመቃጠል፣ በቅዝቃዜውም ላለመንቀጥቀጥ ርቄ መኖርን መርጫለሁ:: ያን ጊዜ የሙቀት መጠኑ መካከለኛ ይሆናል» ይላል:: ፍቅረኛው ከነበረችው ግሪካዊቷ ሚሌቫ ጋር በትዳር ለ17 ዓመታት አብረው ኖረዋል:: «በእነዚህ ዓመታት» አይንስታይን እንደሚነግረን «ብዙ ነገር ለመረዳት ስችል ሚሌቫ ግን ምስጢር እንደሆነችብኝ ቀርታለች» ብሏል:: ሚሌቫ የሳንባ በሽታ ፊቷ ላይ ከፍተኛ ጉዳት ካደረሰባት በኋላ መራርነቷ ከፍተኛ እየሆነ እንደመጣ የሚነግረን አይንስታይን ከዓመታት የትዳር ዘመን በኋላ ቢፋቱም ከልጆቹ ጋር የነበረውን ግንኙነት በእጅጉ እንደጉዳቸበትና ይህም ከሰው ርቆ ለመኖሩ የራሱን ድርሻ እንዳበረከተ ይናገራል::

በጀርመን ወታደሮች ባህርይና ድርጊት እጅጉን ይበሳጭ የነበረው



Scanned by CamScanner

አይንስታይን በጣልያን ኑሮውን ሲመሰርት የጀርመን ዜግነቱን ሰርዞ የስዊስ ዜግነት እንዲሰጠው ጠየቀ፤ ጥያቄውም ተቀባይነት አገኘ:: ይህንኑ አስመልክቶ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ:- «ሰው በሕግ ፊት የእኩልነት መብቱና ነፃነቱ የማይጠበቅበትና የወደደውን ማስተማር የማይችልበት ሃገር ዜጋ ለመሆን ስለማልፈልግ ብቻ ይህን ወስኛለሁ» በማለት ተናግሯል::

የአቶሚክ ኢነርጂን ቀመር በማግኘት የታላቅ ዕውቀት ባለቤትነቱን ካረጋገጠ በኋላ በዲሴምበር 11/1945 የኖቤል ሽልማት ተቀብሎ ንግግር እንዲያደርግ ተጋበዘ:: ንግግሩ አጭር ነበር:- «ጦርነቱን አሸንፈናል፤ ሰላምን ግን አላሸነፍንም (We won the war; but not the peace)»:: የአቶሚክ ኢነርጂ ቀመር በመጠቀም የአውቶሚክ ቦምብ ከተሠራ በኋላ «የኒውዮርክ ታይምስ» ጋዜጣ አዘጋጅ ወደ አይንስታይን መኖሪያ በማቅናት በእሱ ግኝት ስለተሰራው አውዳሚ መሣሪያ የተሰማውን ጠየቀው:- «እኔ የማውቀው አንድም የአውቶሚክ ቦምብ አለመስራቴን ነው፤ ሰዎች መስራታቸውን ግን ሰምቻለሁ» አለው:: ይህን ማለቱ የእሱ ግኝት ዓላማ ለሰው ልጅ ልማት እንጂ ጥፋት እንዳልነበር፤ ነገር ግን ሰዎች ግኝቱን በመጠቀም የጥፋት መሣሪያ መስራታቸውን ለመግለፅ ነው::

ለጋዜጠኛው በማከልም እንዲህ አለው:- «ልብ በል! እኔ አውቶሚክ ኢነርጂን ቀድሜ ባላገኘው ኖሮ ጀርመኖች ማግኘታቸው አይቀርም ነበር:: በዚህም ግኝታቸው የሰው ዘር ቁንጮ እኛ ነን ለሚሉት እንደማረጋገጫ ይጠቀሙበታል:: ምናልባት የእኔ ስህተት ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት የአውቶሚክ ቦንብ እንዲሰራ ሲጠይቀኝ መፈረሜ ነበር፤ ለእሱም ቢሆን ይቅርታ አይነፈገኝም:: የጊዜ ጉዳይ እንጂ ጀርመኖች እሱንም መስራታቸው አይቀርም ነበር» ብሏል:: ጋዜጠኛው በማስከተል አንድ ጥያቄ አቀረበለት:- «ታዲያ አውቶሚክ ቦንብን የሰሩት እንዴት መቆጣጠር ያቅታቸዋል?» አይንስታይን ለጥያቄው ሲመልስ «ይህ የሚያሳየው ከፊዚክስ ይልቅ ፖለቲካ ከባድ መሆኑን ነው» አለው::

ስለዓለም ሰላም ተጠይቆም በሰጠው መልስ:- «ሦስተኛው የዓለም ጦርነት በምን እንደሚካሄድ ባላውቅም አራተኛው ግን በድንጋይና በዱላ እንደሚሆን አውቃለሁ» በማለት የሰው ልጅ ስልጣኔ መጥፊያ የመቃረቡን ስጋት ገልፆ «ለዚህች ዓለም ሰላም ማምጣት ከተፈለገ ግን የጋንዲን ሃሳብ ብቻ ስራ ላይ ማዋል በቂ ነው» ብሏል::

ሳይንሳዊ ግኝቱን አስመልክቶ የፈረንሣይ የፈላስፎች ማህበር በኤፕሪል 6/1922 ባደረገለት ግብዣ ላይ ተገኝቶ:- «የእኔ ቲዎሪ ስኬታማ ከሆነ ጀርመኖች የጀርመን ዜጋ፣ ፈረንሣውያን ደግሞ የዓለም ዜጋ ይሉኛል:: የእኔ ቲዎሪ ደግሞ ሀሰተኛ ከሆነ ፈረንሣዮች ጀርመናዊ፣ ጀርመኖች ደግሞ አይሁድ ይሉኛል» በማለት ተናግሯል::

«ስለነገ ለአንድ ቀን ተጨንቄ አላውቅም፣ ምክንያቱም በፍጥነት እንደሚመጣ አውቃለሁና» የሚለን አይንስታይን የእርጅና ዘመኑን ፕሪንስተን በምትባለው የአሜሪካ ግዛት ለማሳለፍ በመወሰን በግዛቷ ኑሮውን መስርቶ ነበር:: በዚያን ወቅት አንዲት ወጣት የአይንስታይንን በሕይወት መኖር ሰምታ በመደነቅ «እስከዛሬ በሕይወት አለህ?» በማለት መገረሟን የሚገልፅ ደብዳቤ በኦገስት 25/1946 ላከችለት:: እሱም «እስከዛሬ ከህያዋን ጋር አብሬ በመቆየቴ ይቅርታ እጠይቃለሁ፣ ለነገሩ ለዚህም መፍትሄ አለው» የሚል መልስ ልኮላታል::

በዚሁ ወቅት የቅርብ ጓደኛው የነበረው ማይክል ባስ አረፈና በእሱ የቀብር ስነስርዓት ላይ ተገኝቶ ሲተክዝ የተመለከቱት ጋዜጠኞች ምን እንደተሰማው ሲጠይቁት በሰጠው መልስ:- «የሚገርመኝ የጓደኛዬ መሞት ሳይሆን የእኔ እስከዛሬ መኖር ነው» አላቸው:: ሌላው ጋዜጠኛ «ለመሆኑ ስትሞት እዚሁ ነው መቀበር የምትፈልገው?» በማለት ጠየቀው:: «የእኔ ፍላጐት ሬሳዬ እንዲቃጠል ነው:: ይህን ያህል ሕዝብ በቁሜ ካመለከኝ ይበቃኛል፣ ከሞትኩ በኋላ ደግሞ አጥንቴን እንዲያመልክ አልፈልግም» በማለት መልሶለታል::

አይንስታይን መደነቅም ሆነ መወደስ ፈጽሞ አይወድም::



Scanned by CamScanner

አዘውትሮም፡- «እኔን የሚያስቀኝ አዋቂ ነህ የሚለኝ ሰው ብቻ ነው» በማለት ይናገር እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን:: እሱ መደነቅ ባይወድም የሚያደንቃቸው ብዙ ሰዎች እንዳሉ ግን አልሸሸገም:: የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ለነበረው ሩዝቬልት ያለውን ከፍተኛ ፍቅርና አክብሮት ሲገልፅ፡- «በሩዝቬልት ፕሬዚዳንት መሆን ከእኔ በላይ ማንም ሊያዝን አይችልም:: ምክንያቱም በየዕለቱ ላገኘው ባለመቻሌ ነው» ብሏል:: በተመሳሳይ የእስራኤል ፕሬዚዳንት ስለነበረው ዌይዝማንም ሲናገር፡- «በተመረጠ ሕዝብ መሃል የተመረጠ ሰው» ብሎታል::

ከከንፈሩ ፒፓ የማይለየው አይንስታይን የ«ኒውዮርክ ታይምስ» ጋዜጣ አዘጋጅ የእርጅና ዘመኑን የሚያሳልፍባትን የፕሪንስተንን ከተማ እንዴት እንዳገኛት ላቀረበለት ጥያቄ በሰጠው መልስ «እንዳልተጨሰ አዲስ ፒፓ!» በማለት ለከተማዋ ያለውን ፍቅር ገልጿል::

«ከሁለት ጦርነት፣ ከሁለት ሚስትና ከሂትለር ተርፌአለሁ» የሚለው አይንስታይን በመጨረሻ ዘመኑ ስለጋብቻ የነበረው አመለካከት በከፍተኛ ጥላቻ  የተሞላ ነበር:: አብዛኛውን ጊዜውንም የሚያሳልፈው በቤተ መጽሐፍት ውስጥ አልያም ጀልባ ሲቀዝፍ በመዋል ነበር::

አይንስታይን በስተመጨረሻ ያገኘውን የንፅፅር ሕግ (Theory of Relativity) ብዙዎች በቀላሉ ሊረዱት ባለመቻላቸው ለማስረዳት ይቸገር ነበር:: አንድ ቀን ይህንኑ ጥያቄ ላነሳበት ተማሪው በቀላል ምሳሌ እንዲህ በማለት አስረዳው፡- «ከቆንጆ ሴት ጋር በሚያምር አትክልት ቦታ ለአንድ ሰዓት ተቀመጥ፤ አንዱ ሰዓት እንደ አንድ ደቂቃ ይሆንብሀል:: በጋለ ምድጃ ላይ ደግሞ ሱሪህን አውልቀህ ለአንድ ደቂቃ ተቀመጥ፤ አንዱ ደቂቃ እንደ አንድ ሰዓት ይሆንብሀል:: የንፅፅር ሕግም ይኸው ነው»::

አልበርት አይንስታይን ኤፕሪል 16/1955 ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: የቀብር ሥነ ሥርዓቱም የመጨረሻ ዜግነቱን በተቀበለባት አሜሪካ፣ ፕሪንስተን ግዛት ተፈፀመ::



Scanned by CamScanner

# «ተናግረህ ማሳመን ካልቻልክ ባትናገር ይሻላል»

አይሁድ «ራሱን ንጉስ ብሏል» በማለት ኢየሱስ ላይ ክስ መስርተው ሊያስገድሉት ወደ አገረ ገዢው ግቢ ሄዱ:: በዚያም እንደደረሱ «ይኸ ክፉ ሰው ነው፤ ራሱን የአይሁድ ንጉስ ብሏል» በማለት ለአገረ ገዢው ጲላጦስ አመለከቱ:: ጲላጦስም ኢየሱስ ላይ የተመሰረተውን ክስ ከሰማ በኋላ... «እውን አንተ ንጉስ ነህ?» በማለት ኢየሱስን ጠየቀው:: «አንተ አልህ» በማለት ኢየሱስ በትህትና መለሰ:: ተዕሮ ባናነበውም ጲላጦስ «ታዲያ ንጉስ ካልሆንክ እዚህ ምን ትሰራለህ?» ያለው ይመስለኛል:: «ለእውነት ልመሰክር ስለተወለድኩ...» አለ ኢየሱስ:: ጲላጦስም ለኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ለዘመናት የፈላስፎች ፈተና የሆነችውን ጥያቄ ወረወረ:- «እውነት ምንድር ነው?»

ታላቁ ፈላስፋ ኒቼ:- «መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር ዳር አነበብኩት፤ በዚያ መጽሐፍ ውስጥም ላከብረው የሚገባኝ አንድ ሰው አገኘሁ፤ እሱም ጲላጦስ ነው:: እሱ የጠየቀው ጥያቄ መልስ አግኝቶ ቢሆን ኖሮ ፍልስፍና የሚባል ነገር አይኖርም ነበር:: ምክንያቱም የጥያቄዎች መጀመሪያ ብቻ ሳይሆን መጨረሻም ይኸው ነው:: ሌላው ጥያቄው ሁሉ ትርፍ ነውና» ብሏል::

የእውነት ምንድነው ጥያቄን ለመመለስ የመጀመሪያ ሙከራ



Scanned by CamScanner

አድርገዋል የሚባሉት ሶፊስቶች ናቸው። ለዛሬ የእነሱን ፍልስፍና ለዚህ ጥያቄ ከሚሰጡት መልስ ተነስተን ለማየት እንሞክራለን። ለሶፊስቶች እውነት የስሜት ሕዋስህ ነው። አንድ ነገር በዓይን ከታየ፣ በአፍንጫ ከተሸተተ፣ በእጅ ከተዳሰሰ፣ በምላስ ከተቀመሰ ወይም በጆሮ ከተሰማ ነገሩ እውነት ነው። ስለዚህ ለጲላጦስ ጥያቄ መልሱን አግኝተነዋል፦ «እውነት የስሜት ሕዋስ (sensation) ነው» በማለት አስቀመጡ።

ፕሌቶ እዚህ ላይ ተነሳና «እናንተ እውነት የምትሉት ይህ ከሆነማ እውነት የለም ማለት ነው» አለ። «እንዴት?» በማለት ሶፊስቶች ጠየቁ። ፕሌቶ በምሳሌ ነገራቸው፦ «አንተ ጣፍጦህ የምትጠጣው ወይን ጠጅ ለእኔ ከመረረኝ ወይን ጠጁ ወይ ጣፋጭ አለበለዚያም መራር መሆን እንጂ ሁለቱንም መሆን እንዴት ይችላል? የመቅመስ የስሜት ሕዋስ ግን አንዱን ነገር ሁለት አደረገው። ስለዚህም የነገሩን እውነትነት አላሳወቀንም። በሌላ ምሳሌ ደግሞ... አንድ ሚዳቋ ዝንጀሮና ነብር ፊት ብታቆማት አንዲቷን ሚዳቋ ሁለቱም እኩል ያይዋታል። የሚያይዋት ሚዳቋ ግን እኩል ስሜት በሁለቱ እንስሳት ላይ አታሳድርም፤ ሚዳቋዋ ግን ለሁለቱም እኩል ትታያለች። ለአንዱ ስሜት አትሰጥም፤ ለሌላው ረሃቡን ትቀሰቅሳለች። ስለዚህ ሚዳቋዋ በአንድ (የማየት) የስሜት ሕዋስ ታይታ ሁለት ትርጉም ሰጠች። እንግዲህ አንዱ ነገር ሁለት ትርጉም ከሰጠ የነገሩ እውነትነት አብቅቷል» አለ።

የሶፊስቶችን የፍልስፍና እምነት ገደል የከተተው ደግሞ «እውነትም ሆነ እውቀት የሚባል ነገር የለም» የሚለውና የስኬፕቲሲዝም ፍልስፍና መስራች ፊሮ ነበር። «እንኳን የአንተ ሃሳብ ቀርቶ የአንተ ራስህ መኖርን እውነት ለመሆኑ እንዴት እርግጠኛ ትሆናለህ?» የሚለን ፈላስፋ ነው። ታዲያ የሶፊስቶቹም «የስሜት ሕዋስ የእውነት ማረጋገጫ ነው» የሚለውን እምነታቸውን እንዲህ በመጠየቅ ፈተነው፦

«ከፀሐይና ከመሬት የትኛው ይበልጣል?»

ሶፊስቶችም መለሱ፦ «ፀሐይ።»

ፊሮ ጠየቀ:- «ምነው አሁን ሳያት ሽምብራ አከለችብኝ?»

ሶፊስቶች መለሱ:- «ለምድር በርቀት ስለምትገኝ::»

ፊሮ ጠየቀ:- «እንግዲያውስ አሁን የማየው እውነት አይደለማ?»

ከዚያ በኋላ ሶፊስቶች የመለሱትን አላውቅም:: («ስለ ምንም ነገር እርግጠኛ እንዳትሆኑ» በማለት ያስተማራቸው የፊሮ ተማሪዎች ግን ሲሞት እንዳላለቀሱለት አውቃለሁ:: ስለሚጠሉት ሳይሆን መሞቱን እርግጠኛ መሆን ስላቃታቸው ነበር::)

ሶፊስቶች የሶቅራጥስ ዘመን ፈላስፎች ነበሩ:: የሶፊስቶችን ትምህርት በነፃ ለማግኘት የማይታሰብ ነበር:: ለዚህም ነበር አስተማሪነታቸው ለግሪክ ሀብታሞችና ለልጆቻቸው ብቻ ሆኖ የቀረው:: በዚህም ከፍተኛ ገንዘብ ያገኙበት እንደነበር ታሪካቸው ይነግረናል:: በትምህርታቸው አበክረው የሚናገሩት የአቴና ትምህርት ከነበረበት ልማዳዊ አካሄድ ወደተሻለና የላቀ ደረጃ መምጣት እንደሚያስፈልገው ነበር:: ለዚህም እንደዋነኛ መሠረት ያደረጉት «የመናገር ጥበብ» (The art of speaking well ) ነው:: «ቋንቋን መናገርህ በራሱ በቂ አይደለም» የሚሉት ሶፊስቶች «ተናግረህ ማሳመን ካልቻልክ ባትናገር ይሻላል፤ ምክንያቱም የአንተ ንግግር ተራና ውዳቂ ነውና» ይላሉ:: «ይህ ተናግሮ የማሳመን ጥበብ ደግሞ በትምህርት የሚገኝ ነው» በማለት በዚያ ላይ ያተኩራሉ:: በሶፊስቶች እምነት ገንዘብ ካለህ የተሳካልህና እውነተኛ ሰው ነህ:: የገንዘቡ ምንጭ ከየትም ይሁን እሱ ለሶፊስቶች ትርፍና አላስፈላጊ ነገር ነው:: ለነገሩ የሥነ ምግባር (ethics) ትምህርት ጀማሪዎችም እነሱ ናቸው ይሏቸዋል::

የመጀመሪያው ሶፊስት በመባል የሚታወቀው ፕሮታጎራስ (490-420 B.C.) ነው:: ፕሮታጎራስ አቴንስን በተደጋጋሚ በመጎብኘት የገዢዋ የፔሪክልስ ወዳጅ ለመሆን የበቃ ሰው ነበር:: ይህ ወዳጅነቱም ቱሪ ለምትባለውና በወቅቱ በአቴና ቅኝ ግዛት ስር ወድቃ ለነበረችው ሃገር የመተዳደሪያ ሕግ እንዲያወጣላት ዕድሉን አስገኘለት:: አንዳንዶች ለዚህ



Scanned by CamScanner

ስራው ሌሎች ደግሞ በግልፅ በማይታወቅ ሁኔታ በመርከብ ከአቴና ወጥቶ ሲሄድ በደረሰበት አደጋ እንደሞተ ይናገራሉ:: ፕሮታጎራስ:- «ስለ እግዚአብሔር የማውቀው ነገር የለም፤ ምክንያቱም የእኔ እውቀት እሱን ለማወቅ የሚበቃ አይደለምና» ይላል:: ስለ እውነት ያለው አስተሳሰብ ደግሞ እንዲህ ነበር:- «ሰው የሁሉ ነገር መመዘኛ ነው:: አንድ ነገር የሚኖረው ሰው ሲኖር ነው፤ ነገሩ የማይኖረው ደግሞ ሰው ሳይኖር ነው::» ይህ ማለት ተጨባጭ እውነት የሚባል ነገር የለም፤ የዓለምን እውነት እያንዳንዱ ሰው እንደራሱ መገለጥ ይመለከተዋል ነው::

ፕሮታጎራስ ለተማሪዎቹ ደጋግሞ የሚመክረውና የሚያስተምረው ደካማውን ሃሳብ ጠንካራ አድርጎ ስለመከራከር ነበር:: በዚህም ሰዎች ስለአንድ ነገር ያላቸውን አስተሳሰብ መቀየር ይቻላል ብሎ ያምናል:- «የአንተ አስተሳሰብና እምነት ከሌላው በምንም መንገድ የተሻለና የላቀ ሊሆን አይችልም፤ ነገር ግን ጠቃሚ ሊሆን ይችላል:: ሕግና ልማዶቻችንን የምንከተላቸው ከሌላው የተሻሉና የላቁ ስለሆኑ ሳይሆን የሚጠቅሙ ብቻ ስለሆኑ ነው» ይለናል::

የኤምፒዲዮክልስ ተማሪ የነበረው ጐርጂያስ (483-376B.C.) ሌላው የሶፊስቶችን እምነት ያራመደ ፈላስፋ ነበር:: ይህ ሰው ከትውልድ ሃገሩ ጣሊያን ወደ አቴና በአምባሳደርነት ተልኮ በነበረበት ወቅት በድንቅ ንግግሩና ትምህርቱ የአቴናውያንን ቀልብና ልብ እንደማረከ በታሪክ ይነገራል:- «ዋና ተግባሬ ግሩም ተናጋሪዎችን ማፍራት ነው» የሚለን ጐርጂያስ «እውነት የሚባል ነገር የለም፤ ቢኖር እንኳን ነገሩን እውነት የሚያደርገው የአንተ ተናግሮ የማሳመን ችሎታ እንጂ የነገሩ እውነትነት አይደለም» ይላል:: ይህንንም ሲያብራራልን:- «ምንም ነገር የለም፤ አንድ ነገር ቢኖር እንኳን መኖሩን ማወቅ አንችልም፤ ማወቅ ብንችል እንኳን ስለዚያ ነገር ማስረዳት አንችልም፤ ምክንያቱም አለ ብለን የምናስበው ነገር የለምና፤ ስለዚህም አለ ብለን ነገሩን ስላሰብን ብቻ



Scanned by CamScanner

እንዴት በድፍረት አለ ብለን እንፈርዳለን» ይላል::

«ለምሳሌ» ይላል ጐርጊያስ «አንድን ነገር ሁለት ሰዎች እንዴት እንደሚያዩት ብትጠይቅ በጣም የተለያየ መልስ ታገኛለህ፤ ስለነገሩ አስረዱኝ ብትላቸው ደግሞ ከሁለቱ ሰዎች የአንዱ ንግግር ስለነገሩ የበለጠ ሊያሳምንህ ይችላል:: ለዚህም ነው ነገሮች እውነት ናቸው ብለን እንድናምን የተሻለ ተናጋሪ ሰው መፍጠር አለብን የምንለው… ይህ ደግሞ በእኛ ትምህርት እንጂ በሌላ አይገኝም» ይለናል::

በዚህ መልክ እጅግ የበዙ የፍልስፍና ሥራዎቹን አበርክቷል የሚባለው ጐርጊያስ ከሥራዎቹ በአሁኑ ወቅት አሉ የሚባሉት ሦስት ብቻ ናቸው:: ከሦስቱ በአንዱና ታላቅ ሥራው ተደርጐ በሚወሰድለት "Ecomium on Helen of Troy" ውስጥ በአሰፈረው የፍልስፍና ሃሳብ፡- «የሃገር ክብር ፅናት፣ የሰውነት ክብር ውበት፣ የነፍስ ክብር ጥበብ፣ የተግባር ክብር ኃይል፣ የንግግር ክብር ደግሞ እውነት ነው» ይለናል::

ሌላው የሶፊስት ፍልስፍና አራማጅ ደግሞ አንቲፎን ነበር:: አንቲፎን ከሌሎቹ እጅግ የተሻለና የበረታ ፈላስፋ እንደነበር የሚነገርለት ሰው ነው:: ስለ አንቲፎን ሕይወት ብዙ የሚታወቅ ነገር ባይኖርም ትምህርቶቹ ግን በሶፊስቶች ፍልስፍና ሰፊውን ቦታ ይዞ ይገኛል::

«ከሕግና ልማድ ይልቅ ልንከተለውና ልናከብረው የሚገባን ተፈጥሮን ነው» የሚለን አንቲፎን «ሕግና ልማድ ስትጥስ ሌላው ሰው ምስክር ሆኖ ካልተመለከተህ በቀር እንደጣስክ አይቆጠርም፤ ተፈጥሮን ግን ማንም ሊጥስ አይችልም… ለምሳሌ ከሽምግልናና ከወጣትነት ለእኔ የበለጠው እውነት ሽምግልና ነው:: ምክንያቱም ሽማግሌው ወጣት ነበር፤ ወጣቱ ግን ሽማግሌ አልሆነም:: የሽማግሌው ወጣትነት እውነት ነው (በአንድ ወቅት ወጣት ነበርና)፤ የወጣቱ ሽማግሌ መሆን ግን እርግጠኛ አይደለሁም (ወጣቱ ሳይሽመግል ሊሞት ይችላልና):: ስለዚህ የበለጠ እርግጠኛ የሆንኩበት ሽምግልና ለእኔ እውነት ነው:: የተፈጥሮ እውነት የማይጣሰው እንዲህ ነው» ይለናል::



Scanned by CamScanner

«አንድን ነገር እውነት የሚያደርገው የአንተ የንግግር ኃይል ነው» የሚለን አንቲፋን ማቴሪያሊስት ነበር የሚሉትም አሉ:: ይህንንም በራሱ ምሳሌ ሲነግረን:- «ለምሳሌ አልጋህ የተሰራው ከእንጨት ነው፤ እንጨት ደግሞ የዛፍ ውጤት ነው:: አልጋህን መሬት ውስጥ ተክለኸው ለመብቀል እንኳን ቢችል የሚሆነው ዛፍ እንጂ አልጋ አይደለም:: ስለዚህም አልጋ ተክለህ ዛፍ አገኘህ:: ታዲያ እውነት ያለው ከነገሩ ነው ወይስ ከአንተ ንግግር?» ይላል:: ይህ የእሱ ሃሳብ አሪስቶትልንም አበክሮ እንዲያስብ ያደረገው ጉዳይ ነበር::

ስለሌላው የሶፊስቶች ፍልስፍና አራማጅ ፕሮዲከስ (5ኛው ክ.ዘ.) በመጠኑ ላንሳ:: ፕሮዲከስ በሶፊስቶች ፍልስፍና አንዱና ምናልባትም ከፍተኛውን ቦታ የሚይዘው ነው:: የፕሮዲከስን የፍልስፍና ትምህርት ገብቶ ለመስማት የሚታደሉት በጣም ጥቂቶች ነበሩ ይባላል:: ምክንያቱም የትምህርቱ ክፍያ በወቅቱ እጅግ ከፍተኛ ስለነበር ነው:: የእሱ ትምህርት ሁለት ክፍል የነበረው ሲሆን የመጀመሪያው 50 ድራህማ (በእኛ 50 ብር ሊሆን ይችላል) ሲያስከፍል በሁለተኛው ደግሞ ገብቶ ለመማር የሚያስከፍለው 1 ድራህማ ብቻ ነበር:: ታዲያ ሶቅራጥስ ስለፕሮዲከስ ሲናገር:- «50 ድራህማ አስከፍሎ የሚያስተምረው ትክክለኛ ቃላትን መርጦ ስለመናገር ነው፤ ነገር ግን የሚያስተምራቸው ቃላት በራሳቸው ትክክለኛ መሆናቸውን ምን እርግጠኛ አደረገው?» በማለት ጠይቋል:: ፕሮዲከስም እንደሌሎቹ ሶፊስቶች የሚያበክረው የንግግር ኃይልና ውበት ላይ ነበር:: በዚህም ትምህርቱ በአቴናውያን ዘንድ ከፍተኛ መደነቅን አትርፎ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን::

ሶቅራጥስም በጥሩ ተናጋሪነታቸው ከሚያደንቃቸው ሰዎች አንዱ ፕሮዲከስ እንደነበር አልሸሸገም:: በአንድ ወቅት ሶቅራጥስ ለተማሪዎቹ ሲያስተምር ስለፕሮዲከስ የተናገረው ነው ተብሎ በሚነገረው ቀልድ ልሰናበት:- «ፕሮዲከስ አንድ ቀን የ50 ድራህማ የሚያስከፍለውን ትምህርቱን ጨርሶ በሁለተኛውና 1 ድራህማ ብቻ ተከፍሎ በሚገባበት



Scanned by CamScanner

ክፍል ጠለቅ ያለ የፍልስፍና ሃሳብ ሲያስተምር ቆየና በድንገት ትምህርቱን አቋረጠ:: ታዲያ ተማሪዎቹ ለምን እንዳቋረጠባቸው ጠየቁት:: ፕሮዲከስም:-'አዳልጦኝ 50 ድራህማ ወደሚያስከፍለው ትምህርት ገ... በማለት መልሶላቸዋል» ይለናል ሶቅራጥስ::



Scanned by CamScanner

# «እነሆ! ከአዳም ጐን አንዲት አጥንት ወጣች፤ እስከዛሬም ታመዋለች»

ከምዕራባውያን ፈላስፎች ታላቅ ክብር የሚቸረው ባውሴት እግዚአብሔርን ቢያገኘው፤ እግዚአብሔርም አንድ ጥያቄ ብቻ የማቅረብ ዕድል ቢሰጠው ያ ጥያቄ ምን ሊሆን እንደሚችል በተማሪዎቹ ተጠይቆ ሲመልስ:- «ሔዋንን እንዴት እንደፈጠርካት ንገረኝ እለው ነበር» አላቸው:: ባውሴት ይህን ይበል እንጂ በሌላ አጋጣሚ ሲናገር:- «እግዚአብሔር አዳምን ፈጥሮ ከጨረሰ በኋላ አተኩሮ ተመለከተውና ከዚህ የተሻለ መስራት እችል ነበር በማለት አሰበ:: ለጥቂት ጊዜም አሰላሰለና ሰውን በመፍጠሩ ተፀፀተ» ይለናል:: እግዚአብሔር ሔዋንን ስለመፍጠሩ ባውሴት «እጠራጠራለሁ» ብሏል:: «ለዚህም ነው» ይላል «እግዚአብሔር ከአዳም በኋላ እምብዛም ሰው ለመፍጠር ያልተጨነቀው»::

«እግዚአብሔር ሔዋንን የፈጠረበት ብቸኛው ምክንያት የአዳም ጥያቄ ነው» የሚሉን ምዕራባውያን ፈላስፎች «ለነገሩ ሔዋን ሳትፈጠር አስቀድሞ ብዙ ተባዙ ስላለን ምድርን ለመሙላት የእሷ መምጣት እምብዛም አስፈላጊ አልነበረም:: የሚገርመው ግን ከጐኑ አጥንት ወጥታ ተመልሳ የአዳም የጐን ውጋት መሆንዋ ነው» ይላሉ:: ፈላስፎቹ አክለውም:- «እግዚአብሔር በመጀመሪያ ዓለምን ፈጠረ:: በቀጣዩ ቀን ሰውን ፈጠረና ከስራው ሁሉ አረፈ:: በማግስቱ ሴትን ፈጠረ:: ከዚያን

ቀን ጀምሮ እግዚአብሔርም ሆነ ሰው እረፍት አላገኙም» ይሉናል።

እግዚአብሔር አስቀድሞ የፈጠረው ሔዋንን ነው የሚሉንም አሉ። ታዲያ አንድ ቀን ሔዋን እግዚአብሔር በገነት ሲንሸራሸር አገኘችው። «እባክህ እግዚአብሔር ከእዚህ የገነት ፍሬ መብላት፣ ከአባብም ጋር መጫወት ሰልችቶኛልና ወንድ ፍጠርልኝ» አለችው። እግዚአብሔርም በአንድ ነገር ከተስማማች ወንድ እንደሚፈጥርላት ነገራት። ብቸኝነት ያንገፈገፋት ሔዋን የእግዚአብሔርን ጥያቄ ያለማንገራገር እንደምትቀበል ነገረችው።

«ወንድን እፈጥርልሻለሁ፤ ነገር ግን እሱ ከአንቺ ቀድሞ እንደተፈጠረ፣ አንቺም ከእሱ እንደወጣሽ ታሳምኚዋለሽ» አላት። ሔዋንም፡- «ጌታ ሆይ! ወንድን ፍጠርልኝ እንጂ ያልከኝን አደርጋለሁ» በማለት በደስታ ፈነደቀች። እግዚአብሔር በቅፅበት ወንድን ከሔዋን የጐን አጥንት ምዝዝ አድርጎ አጠገቧ ቁጭ አደረገው። ሔዋን ደስታዋን መቆጣጠር አቅቷት ስትፈነድቅ «በይ ስም አውጭለት» አለ እግዚአብሔር። ሔዋንም «አዳም» ብዬዋለሁ አለች። በዚህም ለእግዚአብሔር የገባችለትን ቃል ፈፀመች። አዳም ማለት የፍጥረት መጀመሪያ ማለት ነዋ!

በዚህ ታሪክ ከተስማማን ሴት ውሸትን የተማረችው ከእግዚአብሔር ሊሆን ነው። እግዚአብሔር ደግሞ አይዋሽም፤ እንዲያውም ሔዋን ድንገት አዳልጧት ለአዳም እውነቱን ትነግረው ይሆናል በማለት በእሷ ላይ ክትትሉን እስከዛሬ አላቋረጠም። የመጀመሪያ ሥራው ያደረገውም ሔዋን የምትናገረውን ሁሉ አዳም እንዳያምናት ማድረግ ነበር። በዚህ በኩል እግዚአብሔር የተሳካለት አይመስልም። እንዲያውም አዳም ከእግዚአብሔር ይልቅ የሚያምነው ሔዋንን ሆነ። እግዚአብሔር አትብላ ያለውን ፍሬ በልቶ በሕይወት ከመኖር የሔዋንን ቃል ሰምቶ መሞትን መረጠ። በዚህም እግዚአብሔር ቂም ቋጥሮ «ትሞታለህ» አለው። አዳም እንግዲህ ለፍቅር የተሰዋ የምድራችን የመጀመሪያው ጀግና መሆኑ ነው።



Scanned by CamScanner

ሔዋን የእግዚአብሔርን ቃል ትፈፅም እንጂ ራሱን እግዚአብሔርን መጠራጠሯ ደግሞ አልቀረም:: በተለይም አዳም በገነት ውስጥ ሲዞር አምሽቶ ከመጣ ቁጣዋና ግልምጫዋ አዳምን ማበሳጨት ጀምሮ ነበር:: ታዲያ አንድ ቀን አዳም ሲዞር ካመሸበት በድካም ተመልሶ አልጋው ላይ ጉትን እንዳሳረፈ እንቅልፍ ይዞት ሄዷል:: ከእንቅልፉ በድንገት የባነነው ሔዋን ደረቱን ስትቆነጥጠው ነበር፤ በድንጋጤ የነቃው አዳም ምን እያደረገች እንደሆነ ሔዋንን ጠየቃት:: የሔዋን መልስ አጭር ነበር:- «የጉድን አጥንትህን እየቆጠርኩ!» (እግዚአብሔር ሌላ ሴት ሰርቶለት ይሆናል ብላ መጠርጠሯ ነበር::)

አንድ በምዕራባውያኑ ዘንድ የተለመደ ቀልድ ላውጋችሁ:: በምድር ላይ የነበረው የሰው ዘር በሙሉ ይሞትና ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይሄዳል:: ታዲያ በዚያ እግዚአብሔር ለሁሉም አንድ ትዕዛዝ ይሰጣል:: ይኸውም ወንድን የበደሉ ሴቶች በግራ በኩል እንዲሰለፉና እንዲመዘገቡ ነበር:: ሴቶች በሙሉ ይሰለፉና ይመዘገባሉ:: ምዝገባው ሲያልቅ በሉ ወደ ገነት ሂዱ ይላቸዋል:: የወንዶች ተራ ይደርስና በሴት የተበደላችሁ ወንዶች በአንድ መስመር፤ ሴትን የበደላችሁ ደግሞ በሌላው መስመር ተሰለፉና ተመዝገቡ ይላል:: በሴት የተበደሉት ሰልፍ በወንዶች ሲሞላ ሴትን በበደሉት ሰልፍ ላይ የቆመው ግን አንድ ወንድ ብቻ ነበር:: እግዚአብሔር ሰልፉን ሲመለከት በጣም ተቆጣና:- «እናንተ በእኔ መልክና ምሳሌ ሰርቻችሁ በሴት ስትበደሉ መኖራችሁ ሊያሳፍራችሁ ይገባል:: በእሱ ደስ የሚለኝ አንዱ ልጄን ተመልከቱት፤ ከእሱም ተማሩ:: ልጄ ሆይ በአንተ ኮራሁ:: እንዴት በእዚህ ሰልፍ እንደገባህ በል ለሌሎቹ ንገራቸው» በማለት እግዚአብሔር አዘዘው::

ሰውዬው ግን ግራ በተጋባ መንፈስ:- «ጌታ ሆይ! በዚህ ሰልፍ ለብቻዬ መቆሜ ለእኔም ግራ የገባኝ ነገር ነው:: ምክንያቱም በእዚህ በኩል እንድሰለፍ ያዘዘችኝ ሚስቴ ነበረች» በማለት መለሰለት::

መቼም የፍልስፍና ተግባር ሕይወትን መዳሰስ ሲሆን የሕይወት



Scanned by CamScanner

አንዱ ክፍል ደግሞ ሴቶች ናቸውና ፍልስፍና እነሱንም በሚገባ ዳሷል:: ወንድን ጓደኛህ ልታደርገው ስትችል ከሴት ጋር ግን ከትውውቅ በላይ (Acqueintance) ልታልፍ አትችልም ያለው ማን ነበር?

ታሪክ እንደሚነግረን በጥንታዊ የአይሁዶች ሕግ አንድ ሰው ሴት ልጅ ከወለደ ሻማ አያበራም፤ ሴት ልጅ የወለደች እናትም የመንፃት ጊዜዋ ወንድ ልጅ ስትወልድ ከሚኖርባት እጥፍ ጊዜ ነበር (እንደረከሰች ትቆጠራለችና):: እንዲሁም የአይሁድ ወንድ ከእግዚአብሔር ጋር ራሱን የተቀራረበ አድርጎ ስለሚያምን በየዕለቱ ከሚፀልያቸው ፀሎቶች አንዱና ዋነኛው «አምላኬ ሆይ! አሕዛብ ወይም ሴት አድርገህ ስላልፈጠርከኝ አመሰግንሀለሁ» ነበር:: ይህ እምነት በምስራቁ ጎራ በአንድ ወቅት ተስፋፍቶ እንደነበርና እንዲያውም በአንዳንድ ሃገሮች ወንድ ልጅ ያልወለደች ሴት የተናቀች እንደነበረች ታሪክ ዘጋቢዎች አስፍረውት እናገኛለን::

እግዚአብሔር ሔዋንን ወንድ እንዳያምናት ያደረገው ጥረት ሙሉ በሙሉ ከሽፏል ማለትም አይቻልም:: ታላቁ ራሽያዊ ደራሲ ቶልስቶይ ወዳጆቹ ወጋቸውን ሲሰልቁ በመንገድ አገኛቸው:: የወዳጆቹ ወግ ስለ ሴት እንደነበር የተረዳው ቶልስቶይ:- «ወጋችሁ ውሸት ነበር ማለት ነዋ፤ እኔ ስለ ሴት እውነትን የማወራው አንድ እግሬ በመቃብር አፋፍ ላይ ተንጠልጥሎ ነው:: ያን ጊዜ እውነቱን ተናግሬ ወደ መቃብሬ እዘላለሁ» አላቸው:: ምናልባት የቶልስቶይ ፍርሀት ስለ ሴት እውነቱን ተናግሬ በምድር ላይ አያኖሩኝም ይሆን?

አርስቶትል ስለሴት ሲናገር «ተፈጥሮ በመጀመሪያ ወንድን ፈጠረች፤ ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ወንድን መስራት ስትጀምር ሥራዋ ከሸፈባትና ሴት ሆነች» አለ:: እንግዲህ ሴት የተፈጥሮ ክሽፈት ናት ማለቱ ነው:: በአርስቶትል ሃሳብ ብዙዎቹ ፈላስፎች ሲስማሙ «ይህን ጉዳይ ራሱ እግዚአብሔርም አምኖበታል፤ አድርጎታልም» በማለት ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለሙሴ በመጨረሻ በሰጠው



Scanned by CamScanner

ትዕዛዝ:- «የእስራኤል ወንድ ልጆች፣ ሴቶችን፣ እናቶችንና ከብቶችን እንዲሁም የቤታቸውን ንብረት ሰብስበው ከግብፅ እንዲወጡና እሱም እንዲመራቸው» ማዘዙን ይጠቅሱና «እንግዲህ ሴት ለወንዱ እንደ አንድ የንብረቱ ክፍል አድርጎ እግዚአብሔርም ቆጥሯታል» ይሉናል።

ብዙዎቹ ፈላስፎች ሴትን የተፈጥሮ ስህተት አድርገው ለመሳል ቢሞክሩም ፕሌቶ «ስህተቱ የተፈጥሮ ሳይሆን የወንዶቹ ሃሳብ ነው» በማለት ያጣጥለዋል። ስለዚህም ሲናገር:- «ቆንጆ ልጃገረድ በአጠገቡ ስታልፍ አንገቱን ጠምዝዞ በዓይኑ የማይከተል በልቡም የማይመኝ ወንድ ለመኖሩ እጠራጠራለሁ» ይለናል።እንደ ፊሮ ዓይነቶቹ የኋለኛ ዘመን ፈላስፎቹ ደግሞ ይህንን ሲሰማ:- «ወንዱ በዓይኑ የተከተለው በልቡም የተመኘው የራሱን ምኞት እንጂ የሴቷን ውበት አይደለም... እንዲያውም አይሁዶች ስለሴት የነበራቸውን እምነትና ንቀት እግዚአብሔር እንዳዘዘውና ሕግ ሆኖም እንዲኖር የሰሩት ሥራ ተሳክቶላቸዋል» ይለናል።

የቅርብ ዘመናት የዓለማችን ድንቅና ብርቅ ሰዎችም እምነት ከፈላስፎቹ ብዙም ያልራቀ ሆኖ እናገኘዋለን። ካውንት ኬንሰርሲንግ በጋብቻ ጉዳይ ላይ የእሱና የጓደኞቹን እውነተኛ ተሞክሮ በመጣጥፍ መልክ አንድ መድብል አዘጋጅቶ ለግምገማ ሴሚናር ይጠራል። በሴሚናሩ እንዲገኙለት ከጋበዛቸው ሰዎች አንዱ በርናርድ ሾው ነበር። ሾው የግብዣው መልዕክት ሲደርሰው የሰጠው መልስ «ሚስቱ በሕይወት እያለች ስለጋብቻ ሕይወቱ እውነትን የሚፅፍ አንድም ወንድ ስለሌለ በውሸት መድብል ላይ ለመተቸት አልገኝም» የሚል ነበር።

ምንም እንኳን ፈላስፎቹም ሆኑ ፀሐፍት ይህን ይበሉ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢዮብ «...ምነው ጠላቴ ስለ እኔ መጽሐፍ በፃፈ» በማለት የተመኘው ሁሉ የደረሰው ለሴት ሆኖ እናገኘዋለን።

በእውቀቱ ከፍተኛ ክብርና ዝና የነበረው ኦቶ ዊንግር «ወንድ እንጂ ሴት ነፍስ የላትም፣ ስትፈጠር ያለነፍስ ነው የተፈጠረችው» ይል

ነበር:: ምንም እንኳን በዚህ ሃሳቡ ለረዥም ጊዜ ሽንጡን ገትሮ ይከራከር እንጂ የቤቱ አገልጋይ በነበረች ፍቅር ተሸንፎ ሲሰቃይ ፊትዋን ስላዞረችበት ራሱን እስከማጥፋት ደርሷል::

እግዚአብሔር ወንድ ስለሆነ ወንድን ሲፈጥር አድሎ የፈፀመ መስሎ የሚሰማቸው ብዙዎች ቢኖሩም «ወንድንም በድሎታል» በማለት የሚከራከሩም አልጠፉም:: የ18ኛው ክፍለ ዘመን ድንቅ ፈላስፋ ሞሪስን እዚህ ላይ በመጥቀስ ልሰናበት:- «እግዚአብሔርም አዳምን ጠራው:: አዳም ሆይ! መልካምና ክፉ ዜና አምጥቼልሀለሁ:: በመጀመሪያ የቱን ልትሰማ ትወዳለህ?» በማለት ጠየቀው::

አዳምም መለሰ:- «መልካሙን ዜና ጌታ ሆይ!»

እግዚአብሔርም:- «መልካሙ ዜና የምታመነዝርበትም ሆነ የምታስብበት ሰርቼልሀለሁ» አለው::

አዳምም:- «ታዲያ ክፉው ዜና ምንድነው?» በማለት ጠየቀ::

እግዚአብሔርም:- «ክፉው ዜናማ ሁለቱንም በአንድ ጊዜ መጠቀም አለመቻልህ ነው! አንዱን ስትጠቀም ሌላውን ጥለህ ነው» አለው::

ሞሪስም «ከዚህ በላይ በደል ሊኖር አይችልም» በማለት ለወንድ ሃዘኑን ይገልፃል::

# ፈርቼ የደበቅሁትን እውነት የማይፈራ አውጥቶ ይፃፈው

«ጥንት የተወለድሁት ከአክሱም ካህናት ነው:: እኔ በአክሱም አውራጃ ከልደተ ክርስቶስ በኋላ በ1592 ዓ.ም ነሐሴ 25 ቀን በሦስተኛው ዓመተ መንግሥቱ ለአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከአንድ ገበሬ ተወለድሁ:: በክርስትና ጥምቀት ዘርዓ ያዕቆብ ተሰየምሁ፣ ሰዎች ግን ወርቄ ይሉኛል...

«በልጅነቴ ስጫወት እግዚአብሔር ከሞት አወጣኝ፤ ከጓደኞቼ ጋር ስጫወት ወደ ገደል ወደቅሁ፤ እግዚአብሔር በተዓምራቱ እንዳዳነኝ እንጂ በምን እንደዳንሁ አላወቅሁም:: ከዳንሁም በኋላ ገደሉን በረዥሮም ገመድ ሰፈርሁት፤ 25 ክንድ ተስንዝርም ሁኖ ተገኘ:: እኔም ተነስቼ ድኜ የአዳነኝ እግዚአብሔርን እያመሰገንሁ ወደ መምሬ ቤት ሄድሁ::»

ይህ እንግዲህ ኢትዮጵያዊው ፈላስፋ ዘርዓ ያዕቆብ ነው:: ለዘርዓ ያዕቆብ እግዚአብሔርና ሃይማኖት ሁለት ነገር ናቸው:: በራሱ አንደበትም ሲናገር «...የቅዱሳት መፃህፍትን ትርጓሜ እንድማር ሄድሁ... መፃህፍትንም ፈረንጆች እንደሚተረጉሟቸው፣ እንደገናም የሃገራችን መምህራን እንደሚተረጉሟቸው ተማርሁ:: ትርጓሜአቸው ግን ብዙ ጊዜ ከልቦናዬ ጋር አልተስማማም:: ነገር ግን ሃሳቤን ሁሉ በልቤ ሸሽጌ ዝም አልሁ...»

ዘርዓ ያዕቆብ ከትውልዱ ቀድሞ የሄደ፣ ቀድሞም የነቃ ሰው



Scanned by CamScanner

እንደነበር የእሱ ታሪክ ፀሐፊዎች ይናገራሉ:: እግዚአብሔር ለመኖሩ ባይጠራጠርም ሰዎች ለእግዚአብሔር በሰጡት ፍቺ ላይ ግን አይስማማም:: አለመስማማቱን ግን ለመናገር ድፍረቱ አልነበረውም... የሶቅራጥስና የመሰሎቹን ፈላስፎች ዕጣ በሚገባ የተረዳ ይመስለኛል::

እንዲህ ብታደርግ፣ እንዲህም ባታደርግ እግዚአብሔርን ታገኘዋለህ ወይም ትቀደሳለህ አሉኝ፤ እኔ ግን አልተቀበልኩትም፣ አለመቀበሌን ደግሞ በልቤ ሸሸግሁት እያለን ነው:: ለነገሩ በልብ ከሸሸጉት እውነት በግልፅ የተቀበሉት ሐሰት ሳይበልጥ ይቀራል?

ዘርዓ ያዕቆብ «በቅዱሳት መፃህፍት የተፃፈው ሁሉ እውነት ይሆንን?» ብሎ ለመጠየቅ መድፈሩ በራሱ የነበረውን ነገሮችን በጥልቅ የመመርመርና የመረዳት ችሎታ ያሳየናል::

«ኋላም ይህ በቅዱሳት መፃሕፍት የተፃፈው ሁሉ እውነት ይሆን አልን? ብዬ አሰብኩ» ይላል:: ይህ ሃሳቡ በራሱ በዘመኑ ከፍተኛው ኃጢያት ተደርጎ ሊወሰድ ሲችል ቅጣቱም እንደዚያው የከበደ ይሆን ነበር... ዘርዓ ያዕቆብ በልቡ ሸሸገው እንጂ::

«በጣም አላወቅሁምና የተማሩና መርማሪዎች ሰዎች እውነት እንዲነግሩኝ ሒጄ ልጠይቃቸው ብዬ አሰብኩ:: እንደገናም ሰዎች በልባቸው የአለው ከአልሆነ በቀር ምን ይመልሱልኛል ብዬ አሰበኩ:: ሰው ሁሉ ሃይማኖቴ የቀናች ናት ይላል፤ በሌላ ሃይማኖት የሚያምኑም በሐሰት የሚያምኑ የእግዚአብሔር ጠላቶች ናቸው...»

ዘርዓ ያዕቆብ በዚህ ዓይነት የሚያነሳው ጥያቄ ሃይማኖትን ሳይሆን የእምነትን ጉዳይ የሚፈትን ነው:: የምታምነው ለመኖሩ ማስረጃ ማቅረብ ካልቻልክ የአንተ እምነት ሐሰት ነው እንደማለት ነው:: ዘርዓ ያዕቆብ አንድስ እንኳን ሰው እምነቱ እውነት ለመሆኑ የሚያስረዳኝ አላገኘሁም ይለናል::

«እኔም መጀመሪያ ስለ ብዙ የሃይማኖታችን ነገር አንድ የፈረንጆች መምህር ጠየቅሁ፣ እርሱ ግን ሁሉን እንደ ሃይማኖቱ አድርጎ ፈታው



Scanned by CamScanner

(ተረጉመው)። ኋላም አንድ ትልቅ የኢትዮጵያ መምህር ጠየቅሁ፤ እርሱም ሁሉን እንደ ሃይማኖቱ አድርጎ ተረጉመው፤ እስላምና አይሁድም ብንጠይቅ እንደ ይሁ እንደ እየሃይማኖታቸው ይተረጉማሉ። ታድያስ እውነት የአሚፈርድ የት አገኝ አለኑ? ሃይማኖቴ ለእኔ እውነት እንደ አሚመስለኝ እንደ ይሁ ለሌላው ሃይማኖቱ እውነት ይመስለዋል። ነገር ግን ፅድቅ አንዲት ብቻ ናት...»

ዘርዓ ያዕቆብ ፅድቅ የሚላትን ነገር በግልፅ ባያስቀምጣትም ከፍልስፍናው መረዳት እንደሚቻለው እግዚአብሔር ይመስለኛል።

«እኔ አዋቂ ብሆን ምን አውቃለሁ? ብዬ አሰብኩ። ከፍጥረት ሁሉ የሚልቅ ፈጣሪ እንዳለለ አውቃለኑ አልኑ። ከታላቅነቱ የተረፈ ታላላቅን ፈጥሮአልና፤ ሁሉንም የሚያውቅ ነው። ከአዋቂነቱ በተረፈ አዋቂዎች አድርጎ ፈጥሮናል፤ ለእርሱ ልንሰግድለት ይገባንአል። እርሱ የሁሉ ጌታና ሁሉንም የያዘ ነውና፤ ወደ እርሱ በፀለይን ጊዜም ይሰማናል» ይላል። ይኸ ዘርዓ ያዕቆብ እግዚአብሔር የሚለው አምላክ ከልጅነቱ ጀምሮ ስለእሱ (ስለ እግዚአብሔር) የሚነግረው (የሚያስተምረው) ሃይማኖት ባይኖር እንዴት ሊያውቀው ይችል እንደነበር በጊዜው ሊጠየቅ በተገባ ነበር። አለበለዚያ እግዚአብሔርን አውቃለሁ እያለ እሱን ያሳወቀውን ሃይማኖትን እንዴት ሊጠራጠር ይችላል?

ለምሳሌ ዘርዓ ያዕቆብ ስለ ፆም ሲናገር... «አንድ ቀን በልቶ አንድ ቀን መፆም ጤናን ያጠፋል» ይላል። እግዚአብሔር የፈጠረውን ነገር አልበላም ማለት በራሱ ኃጢያት ነው እንደማለት ነው... «በልተን ልናመሰግነው እንጂ በረከቱን ልናርም አይገባንም» ይላል።

ፆም ከፍትወተ ሥጋ ራስን መቆጠብ ነው የሚሉም አሉ። በዚህም ዘርዓ ያዕቆብ አይስማማም። «ሕገ ፆም የሥጋን ፍትወት ለመግደል የተሰራ ነው የሚሉኝ ቢኖሩም፣ ፍትወተ ሥጋ ወንድ ወደ ሴት ሊሳብ፣ ሴትም ወደ ወንድ ልትሳብ የፈጣሪ ጥበብ ነውና። እርሱ ፈጣሪ በሰራው በታወቀ በሥጋዊ መገናኘት ስርዓት ካልሆነ በቀር ማጥፋቱ አይገባም



Scanned by CamScanner

አልጉ:: ፈጣሪያችንም ይኸን ፍትወት በሰው ስጋና በእንስሳም ሁሉ በከንቱ አላስገባውም... ነገር ግን ለዚህ ዓለም ሕይወትና ለፍጥረት በተሰራለት መንገድ ሁሉ መሠረቱ ሁኖ እንዲቆም ይኸንን ፍትወት በሰው ሥጋ ዘንድ ተከለው» ይላል::

የዘርዓ ያዕቆብ ድንቅ ፍልስፍና እና ምርመራ በጊዜው በልቡ ሸሽጎት ባይቀር ድንቅ ነበር:: በአጭሩ የዘርዓ ያዕቆብን ፍልስፍና ጠጋ ብለን ስንፈትሽ ምግብ ሰጥቶ አትብላ፣ የፍትወት ሥጋ ሰጥቶ አታመንዝር የሚል አምላክ አይኖርም እንደማለት ነው:: እሱ ለፈጠረው ነገር ሰምቶ ሕግ አበጁለት ይለናል:: ሰዎች የሰሩት ሕግ ደግሞ ሃይማኖት ተባለ «ነገር ግን ሰዎች ያስተማሩትን ሃይማኖት በመረመርን ጊዜ በእርሱ ውስጥ ሐሰት ከዕድቅ እውነት ጋር ተጨምሮበታልና:: ስለዚህ በእነርሱ አንስማማም» ብሏል:: ጥያቄው እንግዲህ እውነትና ሐሰት ምንድነው? ይሆናል::

ለዘርዓ ያዕቆብ ሐሰት ወይም ኃጢአት ማለት ራሱ ሃይማኖት ነው... «እንደገናም የሰው ሃይማኖት ከእግዚአብሔር ብትሆን ክፉዎችን ክፉ እንዳያደርጉ እያስፈራራች መልካም እንዲያደርጉ ትፈቅድላቸው ነበር:: ደጉችንም በትዕግስታቸው ባፅናናቻቸው:: ለእኔም እንዲያ ያለችው ሃይማኖት ባሏ ሳያውቅ በምንዝርና የወለደች የወንድ ሚስት ትመስለኛ ለች:: ባሏ ግን ልጅ ስለመሰለው በህፃኑ ይደሰታል:: እናቲቱንም ይወዳታል:: በዝሙት እንደወለደች ባወቀ ጊዜ ግን ያዝናል ሚስቱን ከልጇ ጋር ያባርራታል::

«እንደዚሁ እኔም ሃይማኖቴን አመንዝራ ወይም ዋሾ መሆንዋን ካወቅሁ በኋላ ስለ እርሷና በዝሙት ስለተወለዱ ልጆቿ አዘንሁ...» ይለናል::

በዘርዓ ያዕቆብ እምነት የእግዚአብሔር ሥራ እጅግ መልካም ሃሳቡም ጥልቅና የማይደረስበት ሆኖ ሳለ ትንሽና ምስኪን የሆነው ሰው ለሌላው ሰው:- 'የእግዚአብሔርን ጥበብና እውነት እንድገልፅለት ከእግዚአብሔር

ዘንድ ተልኬ መጣሁ' በማለት ለምን ይዋሻል? በማለት ይጠይቃል፡፡ የዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና መቋጫ «እግዚአብሔር እኔን ለመምራትም ሆነ ለማስተማር ከበቂ በላይ ነው» ይሆናል፡፡

የዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍና ጥያቄ እንጂ መልስ የለውም የሚሉም አሉ፡፡ ለምሳሌ እግዚአብሔር በራሱ እኔን ለማስተማር በቂ ነው ይበል እንጂ እሱን ለማስተማር በቂ ነው የሚለውን እግዚአብሔር «አስተማሪዎቹ የእሱን መኖር አስቀድሞ ባይነግሩት ከእነመኖሩም ሳያውቀው በተቀመጠ ነበር» ይላሉ፡፡

ዘርዓ ያዕቆብ ፍልስፍናውን በልቡ ሸሽጐ በሚስጥርም ዕጮ ያስቀምጥ ነበር... «ብዙዎች ክርስቲያን እመስላቸው ነበር፤ እኔ ግን አልነበርሁም» የሚለው ዘርዓ ያዕቆብ ለዚህ ምክንያቱ ከላይ በመጠኑ እንደዳሰስነው ቢሆንም ለእሱ ግን እየሱስ የተናገረውን ተቀብዬ ነው ይላል፡- «ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው፡፡» (ሉቃ. 5:32)

ፈላስፋው በልቡ የሸሸገውን እውነት አንድ ቀን (እሱ ከሞተ በኋላ) የሚመረምረውና የሚጨምርበት ይነሳ ዘንድ ይመክራል... «ከእኔ በኋላ የሚመጡ እንዲያውቁኝ ግን እስክሞት ድረስ በእኔ ዘንድ ሸሽጌ የምይዘው ይህን መጽሐፍ ልፅፍ ወደድሁ፡፡ ከሞቴ በኋላ አዋቂና መርማሪ ሰው ቢገኝ ግን በሃሳቤ ላይ ሃሳቡን እንዲጨምርበት እለምነዋለሁ፡፡ ይኸውም እኔ ከዚህ በፊት ያልተመረመረውን መመርመር ጀመርሁ፡፡ የሃገራችን ሰዎች በእግዚአብሔር ረድኤት አዋቂዎች እንዲሆኑና እውነትንም ወደማወቅ እንዲደርሱ ሐሰትን እንዳይታመንዋትና አመፃንም ተስፋ አድርገው ዝም ብለው ከከንቱ ወደ ከንቱ እንዳይሄዱ እውነትን እንዲያውቁና ወንድሞቻቸውንም እንዲወዱ እንጂ ከእንግዲህ እስከአሁን እንደሚያደርጉት በከንቱ ሃይማኖታቸው እንዳይጣሉ እኔ የጀመርሁትን አንተ ጨርሰው...»

እዚህ ላይ የዘርዓ ያዕቆብ ንግግር በአጭሩና በግልፅ ሲቀመጥ፡-

Scanned by CamScanner

«እኔ የደረስሁበት እውነት አለ፤ እውነትን እንዳልናገር ግን ሞትን ፈራሁ፤ ስለዚህም ፈርቼ የደበቅሁትን እውነት የማይፈራ እውነ ይፃፈው፤ እሱም ቢሆን ግን እኔ ከሞትኩ በኋላ መሆን አለበት...» እን ማለት ነው። የዘርዓ ያዕቆብን ነፍስ እግዚአብሔር ይማር!

# «ሕይወቴ እንደተከፈተ መጽሐፍ ነው»

*«መንገዱን አውቀዋለሁ:: ቀጥታና ጠባብ ነው:: እንደሰይፍ ስለትም የሰላ ነው:: ነገር ግን በዚያ ላይ ስሄድ በደስታ ነው:: በመንገዱ ላይ ስወድቅ አለቅሳለሁ:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል 'የሚበረታ እስ አይጠፋም ይላል:: በዚህ ቃል ላይ የማይናወጥ እምነት አለኝ:: በድካሜ አንድ ሺህ ጊዜ በመንገዱ ላይ ብወድቅ እንኳን እምነትን አላጠፋም:: ሥጋዬ ለመከራ የተጋለጠ ቢሆንም በመከራዬ ውስጥ ግን ታላቅ ብርሃን እንደማይ ተስፋ አለኝ::»*

ከታላቁ የጋንዲ ባህር በጥቂቱ እንቀዳለን:: ጋንዲ ዓለም በታሪኳ ካየቻቸው መሪዎች፣ ፈላስፋዎች፣ ኃይማኖተኞች... ወዘተ ታላቅ ዕውቀትና ጥበብ የነበረው ብቻ ሳይሆን፤ አንድ ሰው የእውነትን መንገድ ከተረዳ በኋላ በዚያ መንገድ ለመሄድ የሚያስፈልገውን መስዋዕት፣ ለመክፈል ምን ያህል ብቃት በውስጡ እንዳለ ያሳየ ብቸኛው ሰው ነበር::

«መንፈሴ በአንድ መንገድ፤ ሥጋዬ ደግሞ በሌላ አቅጣጫ ይመሩኛል:: ከሁለቱ ኃይሎች ፍጭት ነፃነቴ እንደሚወጣ ግን ይሰማኛል:: ያ ነፃነት ግን ዘግይቶ እንደሚመጣ፣ በስቃይም እንደሚገኝ አውቃለሁ...» የሚለው ጋንዲ ነፃነቱን ለማግኘት የሄደበት ጉዳና በሰው ችሎታና



Scanned by CamScanner

ባህርይ ሊወጡት ይችላሉ ብሎ ማሰቡ እጅግ ይከብዳል:: ስለ ጋንዲ ሕይወት የማይታወቅ ነገር የለም ማለት ይቻላል:- «ሕይወቴ እንደተከፈተ መጽሐፍ ነው፤ ምስጢር የለኝም፤ ሰዎች ምስጢር እንዲኖራቸውም አላደፋፍርም...» የሚለው ሞሐንዳስ ካራማቻንድ ጋንዲ ኦክቶበር 2 ቀን 1869 ዓ.ም ካቲህዋር በምትባለው የሕንድ ግዛት ተወለደ:: ለቤተሰቡ ሦስተኛ ልጅ የነበረው ጋንዲ አባቱ በሕንድ የሚገኙ ሦስት ግዛቶችን በተለያየ ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትርነት አስተዳድሯል:: በልጅነቱ ከቤተሰቡ እየተደበቀ በሕንድ እምነት የተከለከለውን ሥጋ ይበላ የነበረው ጋንዲ በአንድ ወቅት ግን ይህንኑ ድርጊቱን አቆመ:- «ሥጋ መብላት ያቆምኩት ኃጢአት ሆኖብኝ ሳይሆን ወላጆቼን መዋሸቱ የከበደ ኃጢአት ሆኖ ስላገኘሁት ነው» የሚለው ጋንዲ በ19 ዓመቱ ወደ እንግሊዝ ሃገር ተጉዞ አትክልት ተመጋቢነቱን በዚያ ጀመረ::

በእንግሊዝ ሃገር የሕግ ትምህርቱን ተከታትሎ ሲጨርስ ወደ ቦምቤይ ተመልሶ የሕግ አርቃቂ ሆኖ ይሠራ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን:: ይህ የሕግ አርቃቂነት ሥራው አንድ የሕግ ብርሃንን በውስጡ አበራለት... ይኸውም የዘር መድልዎ በሕንድ ሥር የሰደደ መሆኑን መረዳቱና ይኸንንም ለመታገል ቆርጦ መነሳቱ ነበር:: ከሕንድ የእምነትና የፍልስፍና መፃሕፍት በተጨማሪ የመጽሐፍ ቅዱስና የቁራን ጥልቅ ዕውቀት እንደነበረው የሚነገርለት ጋንዲ ከምንም በላይ ግን ለራሺያው ደራሲ ቶልስቶይ ታላቅ ፍቅርና ክብር እንደነበረው በሕይወት ዘመኑ በተደጋጋሚ ተናግሯል:: በተለይም በቶልስቶይ "The Kingdom of God is within you" በተባለው ሥራው እጅግ ተማርኮ እንደነበር ታሪኩ ይነግረናል:: ጋንዲ ስለ ቶልስቶይ ሲናገር:- «ውስጣዊው እኔነቴ ላይ ታላቅ ተፅዕኖውን አሳርፏል» ብሏል::

የጋንዲን የሕይወት ታሪክ ተለክታ በተሰጠችኝ የጥበብ አምድ ቦታ ዘርዝሮ ለመፃፍ የማይታሰብ ስለሆነብኝ ከጋንዲ እምነትና ፍልስፍና በመጠኑ ልቆንጥር::



Scanned by CamScanner

ጋንዲ ስለ እውነት ከነበረው እምነት ብንነሳ፡- «በዚህ ምድር ስኖር ከእውነት በቀር የፈለግሁት ነገር የለም፡፡ መንገዱን አግኝቼዋለሁ ብዬ አስብሀ፡፡ እውነትን ለማግኘት የማያቋርጥ ትግልና መፍጨርጨር አደረግሁ፡፡ የተረዳሁት ግን እውነት ማግኘት ማለት ራስን ማወቅና መድረሻንም መረዳት ማለት እንደሆነ ነው፡፡ ይህም በአጭር ቃል ሲጠቃለል 'ፍፁም መሆን' ማለት ነው፡፡ ሕሊናዬ ግን ፍፁም አለመሆኔን ሲረዳ ያመዋል፡፡ ፍፁም ለመሆን ብርታትና ኃይሌን በሙሉ ተጠቀምሁ፡፡ ለመሆን ግን አልቻልኩም፡፡ እንደማንኛውም ሰው ፍፁም የማያደርግ ድክመት በውስጤ ነበር...» ብሏል፡

ጋንዲ በማከል እንዲህ ይላል፡- «...ለእኔ እግዚአብሔርን መፈለግ ማለት እውነትን መፈለግ ነው፤ እውነትን ለማግኘት ሕይወቴን መስዋዕት ማድረግ ቢያስፈልግ ለመስጠት ዝግጁ ነኝ፡፡ እውነትን የሚፈልግ ሰው ደግሞ ከትቢያ ባነሰ ራሱን ያዋረደ (ትሁት) ይሁን፡፡ ዓለም ትቢያን በእግሩ ጫማ ይረግጠዋል፤ እውነትን የሚፈልግ ሰው ግን በትቢያ የተረገጠ ሆኖ ራሱን ያዋርድ፡፡ ያን ጊዜ የእውነት ጭላንጭል ይበራለታል፡፡»

በእግዚአብሔር ስለመታመን ደግሞ እንዲህ አለ፡- «ከከበበኝ ጨለማ ይልቅ በደጅ የማያት የብርሃን ጭላንጭል ለእኔ ቅርብ ናት፡፡ ብዙ ጊዜ እሳሳታለሁ፣ አጠፋለሁም፡፡ እምነቴ ግን ሳይሳሳት በእግዚአብሔር ላይ ብቻ ተመስርቷል፡፡ እግዚአብሔርን ስለማምን ሰዎችን አምናለሁ፡፡ የማምነው እግዚአብሔር ባይኖር ኖሮ የማምነው ሰውም አይኖርም ነበር፡፡» ወዳጆቹንም መከረ፡- «እምነት ሳይኖርህ የምትሠራው ሥራ መጨረሻው በማይደረስበት ጉድጓድ እንደመውደቅ ይቆጠራል፡፡»

ጋንዲ በዘመኑ ሁሉ በሰው ልጅ ዘንድ እንደ ቅዱስ ይታይ እንጂ የራሱን ቅዱስ መሆን «ፈፅሞ አልቀበለውም... በአንፃሩ ቅዱስ ሳልሆን ምናልባት በሥርዓት የታነፅኩ ሰው እንደሆንኩ እንጂ» ይላል፡፡ «እኔን ቅዱስ ማለት ቅድስናና አለማወቅ ወይም ማርከስ ነው» የሚለው ጋንዲ

በአንድ ወቅት በዚሁ ጉዳይ ላይ ሲናገር፡- «ባለራዕይ ነኝ ብዬ አልዋሽም... ቅዱስ ነህ የሚሉኝንም አይደለሁም እላለሁ... እኔ ከምድር የወጣሁ ምድራዊ ነኝ... እንደ እናንተው ለብዙ ድክመቶችም ተጋልጫለሁ... ነገር ግን ዓለምን አይቻታለሁ:: ዓለምን በተከፈቱ ዓይኖቼ አስተውያታለሁ... በሰው መንገድ የተወረወሩ ፍላፃዎች በእኔም መንገድ ላይ በተደጋጋሚ ወድቀዋል... የዚህ ሁሉ ድምር ግን በሥርዓት አንፃኛል...» ብሏል::

«የሃገሬ የሕንድ ሰዎች! ራስን መስዋዕት ከማድረግ ወንጌል በቀር ሌላ ወንጌል አትከተሉ» በማለት ሕዝቡን ያስተማረው ጋንዲ ለእሱ ግድ አድራጊም ሆነ ግፍ የተዋለበት ልዩነት የለውም... ምነው ቢሉ፡. «ሁለቱም መስዋዕት በመሆን እሳት ውስጥ ያልፋሉና:: ነገር ግን የህሊናን ድምፅ ማንም ሊያጠፋት አይችልም... በሁለቱም አእምሮ እስከ ወዲያኛው ትጮኻለች» ብሏል::

«በውስጡ ያለው የህሊና ድምፅ ዕለት ዕለት እንዲህ በማለት ይቃትታል... በምድር ላይ ብቻህን ብትቀር እንኳን ከግፈኞች ጋር አትተባበር... ዓለም ዓይኗን ብታቀላብህ አንተ ግን ፈገግታህን ለግሳት... አትፍራ... በልብህ ያለውን የእውነት ድምፅ ብቻ ታመን፡- «ያ ድምፅ ደግሞ እንዲህ ይላል፡- ባልንጀራህ፣ ሚስትህ፣ ዘመዶችህ... ሁሉም ቢተዉህ... ለምትኖርለትና ልትሞት ለተዘጋጀህበት እውነት ብቻ መስክር... የመኖር ትርጉሙም ይኸው ነውና» በማለት ጋንዲ ስለ እውነት ሊከፈል ስለሚገባው መስዋዕትነት ተናግሯል::

ጋንዲ ስለምዕራባዊ ሥልጣኔ የነበረው ሐሣብ ሲመረመር ከጉዳት በቀር አንዳች ጥቅም እንደሌለው እምነቱ አሳይቶናል::

ከምዕራባውያን ሥልጣኔ አንዱ ተደርጐ በጊዜው ይውሰድ የነበረው የፓርላማ ሥርዓታቸው ነበር:: ነገር ግን ጋንዲ በተለይ ስለ እንግሊዝ ፓርላማ የተናገረውና ከበደ ሚካኤል «ሥልጣኔ ማለት ምንድነች?» በሚለው መጽሐፋቸው ያሰፈሩትን እንመልከት:- «በጠቅላላው በሚደረገው አስተያየት የፓርላማ አባሎች ግብዞችና የግል ጥቅማቸውን



Scanned by CamScanner

ፈላጊዎች ናቸው:: ሥራቸው በፍርሃት ላይ የተመሠረተ ነው:: ዛሬ የተወሰነው ነገ ሊፈርስ ይችላል:: በፓርላማ ተወጥኖ ፍፃሜው ምን እንደሆነ የሚታወቅ አንድ ሥራ እንኳን አይገባኝም:: በጣም ከባድ የሆኑት ጉዳዮች እንኳ በሚቀርቡበት ቀን የፓርላማ አባሎች የሆኑት ሲያንቀላፉ፣ በመቀመጫቸው ላይ ሆነው ሲንጠራሩ ለማየት ተችሏል:: አንዳንድ ጊዜም ሰሚዎችን እስቲያስቆጡ ድረስ እርስ በእርሳቸው የሚለፈልፉበት ሰዓት አለ:: ካርላይል ፓርለማን:- 'የዓለም መለፍለፊያ መደብር' ብሎ ሰይሞታል::... ለፓርላማ የሚባክነው ጊዜና ገንዘብ ሁሉ ዋጋ ላላቸው ሰዎች ተሰጥቶ ቢሆን ኖሮ የእንግሊዝ ደረጃ አሁን ካለበት የበለጠ ከፍ ብሎ በተገኘ ነበር:: ይህ አሁን እኔ የምሰጠው አስተያየት በተለይ ከእኔ ብቻ የመነጨ ሳይሆን ብልሆች የሆኑ ብዙ የእንግሊዝ ተወላጆች ተናግረውታል::...

«ፓርላማ ማለት ሕፃን ልጅ ነው:: ከተቋቋመ ሰባት መቶ ዓመታት በመሆኑ ትልቅ ባያደርገው ኖሮ መቼም ቢሆን የሚያድግ መሆኑ የሚያጠራጥር በሆነ ነበር...» ሲል ተናግሯል::

ጋንዲ ታሪክን መማር የማይጠቅም መሆኑን ይናገራል:: ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ የሚሰጠው የታሪክ ትምህርት ስለ ጦርነት ብቻ የሚናገር በመሆኑ «ይህ ታሪክ ተብሎ ሊጠራ አይገባውም» በማለት ያሳስባል::

ብዙዎች እብድ፣ ሥራ ፈት፣ በሰው ዘንድ ያልተለመደ ሃሳብ የተሸከመና አዕምሮው የተቃወሰ ሰው በማለት ይጠሩሃል ተብሎ በአንድ ወቅት የተጠየቀው ጋንዲ ሲመልስ:- «ይህ ሁሉ ስያሜ ለእኔ ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም እስከዛሬ በትምህርቴ ተስበው የተከተሉኝና ወደ መልካም ምግባርም የመጡ እነሱ ናቸውና» በማለት መልሷል::

«ብዘመኔ በተደጋጋሚ ኃጢአትን ፈፅሜአለሁ» የሚለው ጋንዲ «ለአንድም ቀን ግን ቀንበሩን ተሸክሜ አልዞርኩም» ብሏል:: ስለዚህም ሲናገር... «ጉዞዬ ወደ እግዚአብሔር እንደሆነ አውቀዋለሁ... የኃጢአትን ቀንበር ብሸከም ኖሮ ወደ እሱ አንዲትም እርምጃ ባልተራመድኩ ነበር» ብሏል::



Scanned by CamScanner

ጋንዲ በተደጋጋሚ በሃሣቡ የማይስማሙ ሰዎች ቢያጋጥሙትም «በሃሣብ አለመስማማት ማለት ጥላቻ ማለት አይደለም... ጥላቻ ቢሆን ኖሮ ከሚስቴ በላይ ጠላት ባልኖረኝ ነበር» የሚለው ጋንዲ «ቢያንስ በአንድ ሃሣብ የማይለያዩ ሁለት ሰዎች እስከዛሬ አጋጥመውኝ አያውቁም» ብሏል።

«ገነትን በምድር ላይ ማምጣት ከተፈለገ 'እኔ' የሚለውን ቃል ከፖለቲካ፣ ከኢኮኖሚ፣ ከሃይማኖት... ወዘተ ውስጥ መፋቅ ያስፈልጋል» ይላል ጋንዲ። ስለ ሰው ልጅ ደህንነት፣ ሰላም፣ ብልፅግና፣ ፍቅር... ከማንም በላይ ያስተማረና፣ የሰበከ ራሱንም አርአያ አድርጐ ያቀረበው ጋንዲ ታሪኩን የሰሙ፣ ያነበቡና የተረዱ ሰዎችም በዚህ ሐቅ ይስማማሉ።

ስለ ጋንዲ ሕይወት በሰፊው የዘገቡ የታሪክ ፀሐፍትም ቢሆኑ ለአንድም ቀን ቢሆን የገባውን ቃል አፍርሶ እንደማያውቅ መስክረውለታል።

ጋንዲ ስለ ሃገር መሪነትና በዙሪያው ስለከበቡት ጠላቶቹም የሚናገረው አለ:- «ከመሣሪያው ጋር የሚጣላ እሱ ክፉ አናጢ ነው፤ ጥፋትን በወታደሮቹ የሚያሳብብም እሱ ክፉ ጄኔራል ነው። እኔ ክፉ ጄኔራል እንዳልሆንኩ በሚገባ አውቃለሁ። እስከምን ድረስ መሄድ እንደምችል ጥበብ በሚገባ አስተምራኛለች። ከንቱ ሆኜ እንዳልቀር እግዚአብሔር ብርታትን ሰጥቶኛል። ለ50 ዓመታት ከሠራሁት ሥራ እግዚአብሔር የማይፈልገኝ ሰዓት ሲደርስ እንደሚወስደኝ አውቃለሁ... ነገር ግን የከበበኝ ጨለማ በአጭር ጊዜ በብርሃን እንዲዋጥ ፀሎቴ ፅኑ ነው.... ግፈኝነትን የሚቃወም ሕያው እምነት ያላችሁ ሁሉ በፀሎታችሁ ከእኔ ጋር ተባበሩ...» ብሏል።

ጋንዲ ጃንዋሪ 30/1948 ዓ.ም የምሽት ፀሎቱን ለማድረስ በመጓዝ ላይ ሳለ ከጠላቶቹ በተተኮሰ ጥይት ተገደለ።



Scanned by CamScanner

# «እግዚአብሔርም ሰውን ፈጠረ፤ ሰው ደግሞ ሰይጣንን ፈጠረ»

የዚህ ምዕራፍ ሃሣባችን የሚያጠነጥነው እኔንም እናንተንም ስለሚያስጨንቀን፣ ስለሚያሳስበን ብሎም ስለሚያስፈራን «የጠላታችን» ጉዳይ ይሆናል፡፡ ይህ «ጠላታችን» በላይኛው ዓለም እያለ ስሙ ባህታር ነበር፤ ወደ ታችኛው ዓለም ሲወርድ ብዔልዜቡል፣ ሳጥናኤል፣ ባልዒል፣ ዛምዔል፣ አህርማን፣ ማራ፣ አብዶን፣ ዲያብሎስ በሚሉ ስሞች ሲጠራ ቆየና በመጨረሻም በጣም በተለመደው ስሙ አሁን ድረስ እየተጠራ ይገኛል፡፡ ሰይጣን...

ታላቁ ደራሲ ገጣሚና ፈላስፋ ካህሊል ጅብራን "Satan" በሚለው መጽሐፋ ሰይጣንን እንደሚከተለው እንዲናገር አድርጎት ነበር፡፡ (ሰይጣን የሚናገረው ለቄስ ሳማን ነው)

*«ከፀሐይ በታች ባሉ ከተሞች ሁሉ ስሜ የሃይማኖት የጥበብና የፍልስፍና ምህዋር ሆኗል፡፡ እኔ ባልኖሮ ኖሮ አንድም ቤተ መቅደስ ባልተገነባ፤ አንድም ማማና ቤተመንግስትም ባልተሠራ ነበር፡፡ በሰዎች ልብ ውስጥ ውሳኔን ያመጣሁና፤ የአዲስ ሃሣብ ምንጭ የሆንኳቸው እኔ ነኝ፡፡ የሰዎችን እጅ ያንቀሳቀስኩ እጅ እኔ ነኝ፡፡ ሰዎች ራሳቸውን በሕይወት ያኖሩ ዘንድ የሚታገሉት ኃይል ቢኖር እኔ ሰይጣንን ነው፡፡ ከእኔ ጋር መታገል ቢያቆሙ ስንፍና አእምሮአቸውን፣ ልባቸውንና ነፍሳቸውን*



Scanned by CamScanner

ያመነበትን ቅጣት እየሰጠ ይገድላቸዋል።

«የወንዶችን አእምሮ የሴቶችንም ልብ በፍርሃት እያራድኩ በቁጣዬ ብርታት ወጀብ ሆኜ የምኖር እኔ ነኝ፤ ለእኔም ባላቸው ፍርሃት ወደተለያዩ የአምልኮ ቦታዎች እኔን ለማውገዝ፤ አሊያም ወደ ክፋው ማምለኪያ ለእኔ ፍላጐት ለመገዛትና እኔን ለማስደሰት ይጓዛሉ። መነኩሴው በእኩለ ሌሊት ከአልጋው ተነስቶ እኔን ለማባረር ሲፀልይ ለእኔ ግን ወደ አልጋቄ ከምትጋብዘኝ ሸርሙጣ ለይቼ አልመለከተውም። እኔ ዘላለማዊና ቋሚ የሆንኩ ሰይጣን ነኝ።

«የገዳማትና የማምለኪያ ቤቶች መሠረት የእኔ ፍርሃት ነው። በስግብግብነትና በራስ ወዳድነት መሠረት ላይ ደግሞ መጠጥ ቤቶችና የክፋት ሥራ ቦታዎችን ሁሉ እገነባለሁ፤ እኔ መኖር ባቆም ፍርሃትና ደስታ ከዓለም ላይ ይጠፋሉ፤ በእነሱም መጥፋት ፍላጐትና ተስፋ ያከትማል። ያን ጊዜ ሕይወት ክሩ እንደተበጠሰ በገና ቀዝቃዛና ባዶ ትሆናለች። እኔ ዘላለማዊው ሰይጣን ነኝ።

ሰው እንግዲህ አንድም በሚባርከውና ከፍ ከፍ በሚያደርገው በሌላ በኩል ደግሞ በሚረግመውና በሚፈራው ኃይል መካከል እንደተወጠረ ዘመናት አለፉ፤ ነገር ግን የአንዱን ይሁን የሌላውን ትርጉም አያውቀውም ነበር። ዛፍ በክረምት እንደሚያብብ በበጋ ደግሞ እንደሚረግፍ እንዲሁ ሰውም በሁለቱ መካከል ይገኛል።

የዜን ቡድሂዝም እምነትና ፍልስፍና ተማሪ ብሎም አራማጅ የሆነው አሜሪካዊው ዴቪድ ኩክ ለዛሬው ሃሣባችን ሰፊውን ቦታ እናስይዘዋለን። ኩክ በቅርቡ «አምላክ፣ ሰይጣንና ታዎ» የሚል ሰፊ የፍልስፍና ሥራውን በመጽሐፍ መልክ ከማሳተሙም በላይ በጉዳዩ ላይ የሰነዘረው ሰፊ አስተያየትም በመረጃ መረብ ተሰራጭቷል። በኩክ ፍልስፍና መከራና ስቃይ የሰው ልጅ ሊያመልጣቸው የማይቻላቸው እውነታዎች ናቸው። «ነገር ግን» ይላል ኩክ፡- «የመከራና የስቃይ ምንጭ ሰይጣን ነው ማለት የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት እንደመካድ ይቆጠራል...



Scanned by CamScanner

ምክንያቱም በእሱ የሚያምኑት ሁሉ 'እግዚአብሔር ለሰው ዘር ያለው እቅድ የሚፈፀመው እሱን በመዋጋትና በማጥፋት ላይ የተመሠረተ ነው' ይላሉና...

«ስለዚህ ይህ የመልካምና የክፉ ሁለትዮሽ አስተሳሰብ በእግዚአብሔር መኖርና አለመኖር ላይ ግጭት ፈጥሯል» የሚለን ዴቪድ ኩክ «...ይህ ግጭት ደግሞ በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ተፈጥሮአዊ ልዩነት ለማወቅ አዳጋች ከማድረጉም በላይ፣ በራሱ በእግዚአብሔር ላይ የተሳሳተ ግምት እንዲኖረን አድርጓል»::

«ነገር ግን የታኦኢስት ፍልስፍና በመልካምና በክፉ መካከል ያለውን ልዩነት በተለየ መንገድ እንድናየው ከማድረጉም ባሻገር «የሰይጣን ችግር»ን አስመልክቶ ያለውን ግራ መጋባት በተለየ መንገድ ያቀርብልናል» በማለት ዴቪድ ኩክ በታኦኢዝም ፍልስፍና የሰይጣን ምንነትና ችግርን እንዲህ ሊያሳየን ተነሳ...

«ሰይጣን በሁለት መንገድ ሊታይ ይችላል:: በሰዎች ውስጥ ያለ ሰይጣንና በተፈጥሮ ውስጥ ያለ ሰይጣን:: የሰይጣን ቀንደኛ ጠንሳሽና ፈፃሚውም የሰው ዘር ነው:: ክፋት፣ ጥላቻ፣ የዘር መድልዎ፣ ጦርነት፣ ነፍስ ግድያ፣ ስርቆት... እነዚህ ሁሉ የሰው ድርጊቶች ሲሆኑ የሰው ዘር ደግሞ እነዚህን ድርጊቶቹን ሊቆጣጠር ባለመቻሉ ለማመን በሚያዳግት ሁኔታ ዛሬ ድርጊቶቹ ተቆጣጥረውት እናያለን:: እዚህ ላይ ተፈጥሮም የራሷ ሰይጣን እንዳላት እናስተውል... ለምሳሌ ተፈጥሮአዊ አደጋዎችን ስንመለከት የሰይጣን ውጤት ነው እንላለን:: ነገር ግን ሰይጣን በተፈጥሮ ብቻ ሳይሆን በሰው አእምሮም ተዘርቶ፣ አድጐና አብቦ እናየዋለን::...

«በእግዚአብሔር የማያምኑት *የሰይጣን መኖር በራሱ የእግዚአብሔርን መኖር ጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል* ይሉናል:: ይህ አባባል ብዙ ዓይነት ቅርፅ ይዞ ሊወጣ ሊችል ነገር ግን ነጥቡ በአጭሩ ሲቀመጥ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ቻይ፣ ብቸኛ ፈጣሪ ከሆነ ለሰይጣን መኖር ብቸኛው ተጠያቂም እሱ ይሆናል፤ ወይም ደግሞ



Scanned by CamScanner

በሰይጣን መኖር የራሱን መኖር ጥያቄ ውስጥ ይከታል፤ ይኸ ካልሆነ ደግሞ ሰይጣንን ለማጥፋት ብቃቱ ወይም ፍላጐቱ የለውም...» በማለት ኩክ አስፍሯል፡፡

ዴቪድ ኩክ በዚህ አላበቃም:- «እነዚህ በእግዚአብሔር የማያምኑት ፈላስፎች እንደሚሉት 'ምድራዊ አባት ልጁን ከክፉ ለማዳንና ለመጠበቅ በሙሉ ኃይሉና ችሎታው የማያደርገው ነገር የለም... ይሁንና እውን በምድር ላይ ያለውን መከራና ስቃይ ለተመለከተ ሰው እንደ አባት እንዲያየው በአእምሮው የተሳለለት አምላክን አባትነቱ ከምን ላይ ነው? ብሎ መጠየቁ አይቀሬ ነው ይሉናል» በማለት ከመጽሐፍ ቅዱስ በዘፍጥረት መጽሐፍ በሰው ልጅ አፈጣጠር ታሪክ ላይ ራሱ ሊያሳየን የሚሞክረው ነገር አለ፡፡

*«እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ...» (ዘፍጥ.1:27)*

«እንግዲህ አዳምና ሔዋን ተፈጥረው ብዙም ሳይቆዩ ለፈጠራቸው እንታዘዝም አሉ፤ አለመታዘዝ ብቻ አይደለም ዋሹ፤ መዋሸትም ብቻ አይደለም ተካሰሱ *(አዳምም አለ:- [«ከእኔ ጋር እንድትሆን የሰጠኸኝ ሴት እርስዋ ከዛፉ ሰጠችኝና በላሁ፡፡» (ፍጥ.2:12)፤]* ልጃቸው ቃየን ደግሞ ወንድሙን አቤልን ገደለ፡፡ ሩቅ ሳንሄድ እግዚአብሔር በመልኩ በፈጠረው በመጀመሪያው ትውልድ ብቻ የተሠራው ሥራ የእሱን ሁሉን ቻይነትና ጠባቂነት ጥያቄ ውስጥ ይከተዋል፡፡ ካልሆነም እግዚአብሔር የዓለም ፈጣሪና ጠባቂ ነው የሚለው ሃሳብ የሚያነጣጥረው ለመልካምና ለክፉ አድራጐት ባለበት ኃላፊነት ላይ ይሆናል፤ በአጭሩ ለበጐውም ሆነ ለክፉው ድርጊት ኃላፊው ራሱ ነው» በማለት ዴቪድ ኩክ የሰይጣንን ነገር ሊያሳየን ይሞክራል፡፡

የእግዚአብሔርን ፈጣሪነትና ጠባቂነት «በፍፁም አልቀበልም» የሚለን ክላረንስ ዳሮው ደግሞ ለሰው ዘር መከራን ያተረፈችለት ምድር በሰው በራሱ እንኳን ለጥፋቱ ከሰራው መሣሪያ በኋላ ታላቅ ጥፋት ስለመጣችለት «ተፈጥሮ በራሷ የእግዚአብሔርን መኖር ጥርጣሬ ውስጥ



Scanned by CamScanner

ትከተዋለች» ይላል:: ዳሮው በመቀጠል:- «በእዚህ እምነት ገፍተን እግዚአብሔር የለም ካልን ደግሞ የምናየው ሕይወት ሁሉ የድንገተኛ ክስተት ውጤት ሊሆን ነው:: ስለዚህም ሰይጣንን የፈጠረው የራሳችን ምርጫ ይሆናል» በማለት ይናገራል::

እግዚአብሔር አለ በእርሱም እናምናለን የሚሉት ደግሞ ይህን የሰይጣን ሃሣብ ሲያጣጥሉት:- «ሰይጣንን በምርጫህ የምትከተለው ከሆነ ይህን በነፃ የመምረጥ መብት የሰጠህ እግዚአብሔር እንደሆነ ልታውቅ ይገባል:: እግዚአብሔርን እናውቀው ዘንድ በክፉና በበጎ መካከል በነፃነት ለቆናል:: እንግዲህ የሰይጣንን አሠራር የማያውቀው ሰው ሰይጣን የለም ይላል» በማለት ይከራከራሉ::

ሪክ ሮድስ ደግሞ "How Can a Good God Allow Evil" በሚለው መጣጥፉ ይህንኑ ሃሣብ ሲያጠናክር እንዲህ ይላል:- «ስለ ሰይጣን እንዲህ ዓይነቱን የፍልስፍና ትንታኔ የምንሰማው አሁን ስለ እግዚአብሔር ካለን እውቀት እናሳነት የመነጨ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ከችሎታችን በላይ ስለሆነብን ነው... ህፃን ልጅ አባቱ ይህን አድርግ ያንን ደግሞ አታድርግ የሚልበትን ምክንያት ህፃኑ ሁልጊዜ አይረዳውምና» በማለት አስፍሯል::

በሚያምኑትና በማያምኑት መካከል ክርክሩ በሰፋ ቁጥር የክፉና የበጉ ምንነት እየጠፋ መጥቷል:: ስለዚህም እያንዳንዱ ገጠመኛችን አንድም በረከት ይሆናል አሊያም እርግማን ነው፤ አንድም የእግዚአብሔር ሥራ ካልሆነም የሰይጣን ነው... እግዚአብሔር ኖረም አልኖረም በክፉና በበጉ ኃይላት ምህረት ሥር የምንገኝ ነን:: አላን ዋትስ የተባለው ፈላስፋ:- «ይህ ዓይነቱ ክርክር በፅኑ የተስፋ መቁረጥ ስሜት የተሞላ ግጭት ነው፤ ምክንያቱም ክፉ ከሌለ በጉ አይኖርም፤ በጎም ከሌለ ክፉ አይኖርም:: ሽለቆውን አስወግደን ተራራውን ለማስቀረት እየሞከርን ይመስለኛል...» ብሏል::

ዋትስ ይኸንኑ ሃሣብ በምሳሌ አስቀምጦታል:- «ክፉና በጉ ሁለት



Scanned by CamScanner

ተቃራኒ ጫፎች ነገር ግን የአንድ ነገር ውጤቶች ናቸው:: የሁለቱ ልዩነት የጐላ ነው:: የአንድ ልምጭ ሁለት ጫፍን ልብ ይሏል:: የሁለቱ ልዩነት ሰፊ ነው:: የሚገኙት ግን በአንድ ነገር ላይ ነው::... በልዩነታቸው ውስጥ አንድነት አለ... በአንድነታቸው ደግሞ ልዩነት» ይላል::

የ18ኛው ክ.ዘ. ታሪክ ፈላስፋ ሞሪስ ለመሞት ሰዓታት በቀሩትና በአልጋው ላይ ሆኖ በሚያጣጥርበት ወቅት በእግዚአብሔር አማኝ የነበረው ጓደኛው ከመሞቱ በፊት ሰይጣንን በአንደበቱ እንዲክድ መከረው:: ሞሪስም:- «አሁን ክጀው ከሞትኩ በኋላ ገሃነም ብሄድ ለሰይጣን ምን እመልሳለሁ? ወዳጄ ሆይ! ለጊዜው የት እንደምሄድ ስለማላውቅ በአንደበቴ ማንንም አልክድም» በማለት መልሶለታል::

ከ1632-77 የኖረው ታላቁ የደች ፈላስፋ ቤንዲክት ስፒኖዛ ስለ ክፉና በጐ ሲናገር:- «ሰው የሚፈልገው ነገር ሲኖር መልካም፤ የማይፈልገው ሲሆን ደግሞ ክፉ ይለዋል:: እግዚአብሔር ፍፁምና አንዳች ፍላጐት የሌለው አምላክ እንደሆነ ደግሞ እናውቃለን [God is perfect and has no needs] ...

«እንግዲህ እግዚአብሔር ፍፁም ከሆነ ፍላጐትም ከሌለው በእሱ ዘንድ ክፉና በጐ የሚባል ነገር የለም ማለት ነው:: በአጭሩ እግዚአብሔር ዘንድ የሌለው ነገር በሰው ዘንድ ከተገኘ የተፈጠረው በሰው ነው ማለት ነው:: ስለዚህም የሰው ፈጣሪ እግዚአብሔር፤ የሰይጣን ፈጣሪ ደግሞ ሰው መሆኑ ነው...» ብሏል::



Scanned by CamScanner

# «የማልጠራጠረው 'መጠራጠር መቻሌን' ብቻ ነው»

አንድ ወዳጄ ይኸን ጠየቀኝ... «ከብዙ ዓመታት በፊት የነበረው ቁመናህ፣ ንግግርህ፣ መልክህ፣ እውቀትህ፣ ፀባይህ... በሙሉ ዛሬ የለም:: ከትናንቱ ማንነትህ ዛሬ የቀረው ስምህ ጲላጦስ ብቻ ነው:: ታዲያ ትናንት የነበረው ጲላጦስ ዛሬ ከሌለ፤ የዛሬው ጲላጦስ ትናንት አልነበረም ማለት ነው?»

«መቼም ማንኛውም ፍጡር በለውጥ ውስጥ ያልፍ ዘንድ የግድ ነው:: የትናንቱ ጲላጦስም አደገ፣ ተማረ፣ ተለወጠ፣ ገዘፈ....» በማለት መለስኩለት::

«አየህ! የትናንቱ ጲላጦስ ዛሬ ከተለወጠ የትናንቱ ዛሬ የለም ማለት ነው:: ዛሬ የምናየው አዲስ ጲላጦስ ነው... የትናንቱ ጲላጦስ መኖር እውነት ቢሆን ኖሮ ዛሬ አይለወጥም ነበር» አለኝ::

ወዳጄን ጠየቅኩት:- «ታዲያ እውነተኛው ጲላጦስ የትናንቱ ነው ወይስ የዛሬው?»

«ስለሁለቱም እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም:: ምክንያቱም የዛሬው ጲላጦስ ደግሞ ነገ አይኖርምና...» በማለት መለሰለኝ::

* * *

ከፍልስፍና አባቶች አንዱ የሆነውን ፕሌቶን በቅድሚያ እንመልከት...



Scanned by CamScanner

«ከጓደኛህ ጋር በመንገድ ስትሄድ ዝናብ መዝነብ ይጀምራል:: በዚህ ጊዜ አንተ መሮጥ ትጀምራለህ፤ ነገር ግን ጓደኛህ እንዳልተከተለህ ተረድተህ ፊትህን ስታዞር እሱ ከእርምጃው ትንሽ ፍጥነት እንኳን ሳይጨምር በመጓዝ ላይ ነው:: በሁኔታው ብትገረምም ዝናብ እየመታው የማይሮጥበትን ምክንያት ቆም ብለህ መጠየቅህ አይቀርም:: ታዲያ ጓደኛህ... «የትኛው ዝናብ?» በማለት ቢጠይቅህ ጓደኛዬ አብዷል ብለህ ልትደነግጥ ትችላለህ::

«'በአይንህ የምታየው፣ በላይህ ላይ ሲወርድ የሚሰማህ ዝናብ...' በማለት ልታብራራለት ስትሞክር... 'ዝናብ ለመዝነቡ እርግጠኛ የሆንከው በስሜትህ ስለታመንክ ብቻ ነው:: ስሜት ደግሞ የእውነት መሠረት አይደለም' ይልሀል:: ይኸን ጊዜ ወዳጅህን ወደ አእምሮ ሐኪም የመውሰጃው ጊዜ እንደተቃረበ ታስባለህ::»

የፐሌቶ ነጥብ እንግዲህ እዚህ ጋ ሲያጠነጥን «የምናውቀውን ያወቅነው፣ ያወቅነውንም እውነት ነው በማለት የምናምነው በስሜት ሕዋሳችን ምክንያት ነው:: ይኸም 'ማየት ማመን ነው' እንደማለት ይሆናል::» የምታየውን ለማመን ግን መረዳት (Perception) ያስፈልጋል::

በዚህ እሳቤ ላይ ስንመሰረት ጥንታዊው የግሪክ ፍልስፍና... «እግዚአብሔር ከሌለ ሰው ለራሱ እግዚአብሔር ይሆናል፤ እውነት ከሌለ ደግሞ ሰው የራሱን እውነት ይፈጥራል» ይለናል:: እንግዲህ እውነት ለእያንዳንዱ ሰው አንፃራዊ (relative) ልትሆን ነው::

ከ1592-1650 የኖረውን ታላቁን የፈረንሣይ ፈላስፋና የሒሣብ ሊቅ ሬኔ ዴካርትን ለዛሬ በስፋት እንመልከት:: ይኸ ሰው የብዙ እውቀት ባለቤት ከመሆኑም በላይ የዘመናዊ ፍልስፍና አባት በመባል ይታወቃል:: ዴካርት ነገሮች መኖራቸውን ለማወቅና ለመረዳት ብሎም ለማመን መጀመሪያ «እንጠራጠር» ዘንድ የግድ ነው ይለናል:: «ለምሳሌ የሒሣብ ስሌት ስትሰራ አይንህን፣ አፍንጫህን ወይም ሌላው የስሜት ሕዋስህን ሳይሆን የምትጠቀመው 'ማሰብ' ብቻ ነው... ስለዚህ ለማንኛውም ነገር



Scanned by CamScanner

የእውነትነት መሠረቱ 'ማሰብ' (Reason) ነው» ይለናል።

ከዚህ በመነሳት አእምሮውን 'እስከዛሬ' የሞላውን ነገር ጠራርጎ ሊያስወጣና ከባዶ አእምሮ ሊነሳ ወሰነ። መነሻውንም ሁሉን ነገር መጠራጠር አደረገ። ይኸንንም የመጠራጠር ሂደት 'Systematic Doubt' በማለት ጠራው። በአጭሩ «ልትጠራጠር የምትችለውን ነገር ሁሉ መጠራጠር» እንደማለት ሲሆን ይኸም በሌላ አገላለፅ «በምድር ላይ የምታምነው ነገር ስለሌለ ሁሉንም መጠርጠር» እንደማለት ነው።

አንድ ብርዳማ የክረምት ቀን ዴካርት በስቶቭ የሞቀ ክፍሉ ውስጥ ገብቶ ለአንድ ሙሉ ቀን የማይታሰበውን ሲያስብ፣ የማይጠረጠረውንም ሲጠረጥር ዋለ። በዚያ ቀን እጅግ አድርጐ ካሰበበት ነገር ውስጥ 'ሰው የሚባል ነገር አለ?'... 'ይኸስ የምናየው ዓለም እውነት ነው?' የሚሉት ይገኙበታል። ራሱን እየጠየቀም ለራሱ መልስ ሰጠ።

ለነገሩ ጥያቄውን ሲሰሙት የማይረባ ሊመስል ይችላል። ሁላችንም እንዳለን (እንደምንኖር) እናውቃለን። «እናውቃለን» ስንል ለማወቃችን ምን እርግጠኛ አደረገን የሚለው ጥያቄ መነሳቱ ግን አይቀሬ ይሆናል። ኖረናል የምንለውስ በምን መንገድ ነው? ተፈጥሮአችንስ ምንድነው? ተፈጥሮስ አለን? አሁን አንተ (የእኔ አንባቢ) መኖርህን በማስረጃ ልታረጋግጥልኝ ትችላለህ? ቀላል አይመስለኝም!

ብዙዎች ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ተምረው፣ ዩኒቨርስቲውንም ጨርሰው፣ የምሁር ካባቸውንም ለብሰው... ነገር ግን መኖራቸሁን በማስረጃ አረጋግጡ ሲባሉ የሚናገሩት ይጠፋቸዋል። አንዳንዶቹም ማስረጃቸው የስሜት ሕዋሳቸው ይሆንና፦ «ራሴን በአይኔ ከአየሁት አለሁ ማለት ነው» የሚል መልስ ይሰጣሉ። እንግዲህ ዴካርት እነዚህንና መሰል ሁኔታዎችን አሰበና ይህችን ተመልከቱ አለን፦

- «በእርግጥ ራስህን በአይንህ ማየት ትችላለህ። አንድ ዱላ ውሃ ውስጥ ሲሰምጥ አይተህ ታውቃለህ?» በማለት ጠየቀ።

- «አዎን አይቻለሁ...»

- «ዱላው ውሃ ውስጥ ሲገባ ምን መስሎ ይታይሃል?»

- «ከወገቡ የታጠፈ ይመስላል...»

- «ዱላው በእርግጥ ከወገቡ ታጥፏል?»

- «አልታጠፈም፤ ቀጥ ያለ ነው::»

- «ታዲያ ልክ እንደዱላው አንተም ራስህን ስታይ የምታየው ነገር ሐሰት ሊሆን አይችልም?»

- «ሊሆን አይችልም!»

- «ዱላው ከወገቡ የታጠፈ ሲመስል አይተሃል፤ ነገር ግን ያየኸው ሐሰት ነው?»

- «ዶ/ካርት የምትለኝ ነገር በጣም የተለየ ነው፤ ምክንያቱም ዱላውን ከውሃው አውጥቼ በእጄ ስይዘው ቀጥ ያለ መሆኑን አውቃለሁና...»

- «ይኸ ማለት ደግሞ በዓይንህ ከምታየው ይልቅ በእጅህ የምትነካውን የበለጠ ታምናለህ ማለት ነው?»

- «ይህን የሚያስረዳማ የፊዚክስ ሕግ አለ!»

- «በሌላ አባባል በአይንህ የምታያቸው ነገሮች ሐሰት እንደሆኑ የሚያስረዳ ሕግ አለ ማለት ነው:: ስለዚህ 'አለሁ ብለህ አንተ ስለራስህ የምታምነውን ነገር' ይህ ሕግ ጥርጣሬ ውስጥ ይከተዋል ማለት ነው?»

- «ምናልባት::»

- «እንግዲህ ለመኖርህ እርግጠኛ አይደለህም፤ እርግጠኛ ከሆንክ ደግሞ አንተ ምንድነህ?»

- «እኔኮ እንደአንድ ዱላ አይደለሁም:: እንደዚያ ከሆንኩ የማየውና የሚሰማኝ እርስ በእርሱ ይጋጫል:: ነገር ግን እኔ እኔነቴን ማየት ብቻ አይደለም፤ የማየውም እኔነቴ ይሰማኛል...»

- «እኔነቴን እኔነቴ ይሰማዋል?»

- «በትክክል!»

- «'እኔነቴ ይሰማኛል' ማለት ምን ማለት ነው?»

- «አልገባኝም...»

- «እንግዲህ የሚሰማህ እጅህ፣ እግርህ ወይም ፊትህ ይሆናል፤ ያ አንድ ነገር ነው:: እኔነት ግን ምንድነው? እኔነት አንድ እጅ ወይም አንድ እግር ነው? እንደዚያም ከሆነ እሱም ሳይኖርህ እንዳለህ ሆኖ ሊሰማህ እንደሚችል አታውቅም? ለምሳሌ በጦርነት ወቅት እግሩን ቆስሎ የተቆረጠ ወታደር የእግሩ መቆረጥ ሳይነገረው በፊት እግሬን አመመኝ በማለት ይጮኻል:: ነገር ግን እግሩ የለም:: ስለዚህ ወታደሩ ይጮኽ የነበረው በሌለው ነገር ነው::»

- «ሊሆን ይችላል፤ እኔ ግን ራሴን እንደማየው፣ ያየሁት እኔነቴም እንደሚሰማኝ አውቃለሁ...»

- «ሕልም አልመህ ታውቃለህ?»

- «ብዙ ጊዜ::»

- «በሕልም ሰዓት አንድ ነገር ታያለህ፤ ይሰማሃልም?»

- «ትክክል::»

- «እንግዲህ በሕልም ያየኸው፣ የተሰማኸም ነገር ከእንቅልፍህ ስትነቃ ግን ውሸት ነው፤ ወይም የለም!»

- «በእርግጥ የለም::»

- «ስለዚህ በሕልምህ ለማየት ከቻልክና፣ ስሜትህም ሊሰማው ከቻለ አሁንስ እያለምክ አለመሆኑን ምን እርግጠኛ አደረገኸ? አሁን እኔን የምታየኝና ስናገር የምትሰማኝስ በሕልምህ ሊሆን አይችልም...?»

- «አሁን መጠራጠር ጀመርኩ::»

- «አንድ መጠራጠር የማትችለው ነገር መኖሩን ግን አትዘንጋ:: እሱም መጠራጠር መቻልህን ነው:: በመጠራጠራችን እየተጠራጠርን እንገፋለን፤ ከመጠራጠር የሚያወጣን ምንም ነገር የለምና::»

- «እሱማ ምን ጥርጥር አለው!»

- «መጠራጠር ደግሞ ማሰብ ነው:: መጠራጠርንም ሆነ ማሰብን ማስወገድ አይቻልም፤ ስለዚህ 'ስለማስብ አለሁ' [I think, therefore I am]፤ ማሰብ ይቀጥላል፤ ማሰብ ደግሞ የሚኖረው የሚያስብ ሲኖር



Scanned by CamScanner

ነው፤ ስለራሴ ምንም ነገር እርግጠኛ መሆን ባልችል እንኳን መጠራጠር (ማሰብ) የምችል ነገር እንደሆንኩ እርግጠኛ ሆኛለሁ:: ያንን መጠራጠር ካልቻልኩ ደግሞ በእርግጠኝነት መኖሬን አውቄዋለሁ ማለት ነው:: ስለዚህ ሌላውን ነገር ለማወቅ ጉዞ የምጀምረው ከዚህ በመነሳት ይሆናል::»

- «በእርግጥ ዴካርት ድንቅ ነገር አሁን አገኘሽ!»

ዴካርት ራሱን እየጠየቀና ለራሱም እየመለሰ ሁሉን ነገር ሲጠርጠር ቆይቶ አንድ ነገር መካድ ያልቻለው መጠራጠር መቻሉን ነበር:: ስለዚህም «መጠራጠር ከቻልኩ ማሰብ የምችል ፍጡር ነኝ» አለ:: ዴካርት ብዙ ጊዜ ሲናገር:- «አንዴ ወደ ዓለም መጥተናል ብለን የመጣንበት ዓለም ላይ ለመኖራችን እርግጠኛ ሳንሆን መቀመጥ የለብንም» ይላል:: «የሰው ተፈጥሮ ማሰብ ነው፤ ስለዚህም ሰው የሚያስብ ነገር ነው... ይኸ ማሰብ ደግሞ የሚገኘው በስሜት ሳይሆን ውስጥን በማየትና በመመርመር ነው...» የሚለው ዴካርት የመጨረሻ ሐሣቡ በዚህ ዙሪያ ሲያጠነጥን:- «የእኔ መኖር ከማሰብ ጋር ብቻ የተገናኘ ነው...:: 'እግዚአብሔር አለ፣ ይኸ ዓለም አለ፣ ሰው አለ... ወዘተ' የሚለውን ማሰብ የምጀምረው ግን ከዚህ በኋላ ነው» በማለት ተናገረ::

በዚህ የዴካርት ፍልስፍናና ትምህርት ተስበው ከነበሩት ውስጥ የስዊድኗ ንግሥት ክሪስቲና ይገኙበታል:: «ብዙ ነገር እየተጠራጠርኩ ነውና መጥተህ አስተምረኝ» በማለት ንግሥቷ ደጋግመው ለዴካርት መልዕክት ቢልኩለትም እስከ 1649 ዓ.ም. ድረስ ፍቃደኛ ሳይሆን ተቀመጠ:: በመጨረሻ ግን በዚያው ዓመት ሐሣቡን ለምን እንደለወጠ በውል በማይታወቅ ሁኔታ ወደ ስዊድን በመሄድ ንግስቷን ማስተማር ጀምሮ እንደነበር ከታሪኩ እንረዳለን:: በጠዋት ከእንቅልፍ የመነሳቱ ነገር ሞቱ የነበረው ዴካርት ንግስቷን ለማስተማር በገባው ግዴታ መሠረት በማለዳ ወደ ቤተ መንግሥት መሄድ ይገባው ነበር:: በዚህም ግዴታው ጠዋት ጠዋት እየተነሣ ወደ ንግስቲቱ ዘንድ በሚያደርገው የእግር ጉዞ በቅዝቃዜ ምክንያት በሚመጣ የPneumonia በሽታ በ53



Scanned by CamScanner

ዓመቱ በ1649 ዓ.ም. ሞተ:: ዕድሜውን በሙሉ የራሱን መኖር ሲጠራጠር ለኖረው ዴካርት ሞት ብዙም ለውጥ የሚያመጣበት አይመስለኝም::



Scanned by CamScanner

# የጥበብ መጀመሪያ አስማት መሥራት ነው

ጥንታዊው ሰው ዓለምን ሞልተዋታል በሚባሉት መናፍስት ዘንድ ሞገስ ያገኝና እርዳታቸውም ይቸረው ዘንድ የማያደርገው ነገር እንዳልነበር ታሪክ ይነግረናል:: ሬናክ የተባለ ፈላስፋ "A History of Religion" በሚለው መጽሐፉ አስማትን :- «በመንፈስ የሚኖረው የልዕለ ኃያል አምላክ (Animism) ስትራቴጂ ነው» ይለናል:: አስማተኛ ወይም መተተኛ ምንድነው? ቢያንስ ለቃሉ እንግዳ አይደለንምና በአስማት ታሪክ ዙሪያ ትንሽ ልወርውር::

በጥንት ዘመን ዝናብ ይዘንብ ዘንድ ዋናው አስማተኛ በሌሊት ዛፍ ላይ ይወጣና ውሃ ወደ ምድር ያፈስ ነበር ይባላል:: ታዲያ በማግስቱ የሃገሬው ሕዝብ ውሃው በፈሰሰበት ዙሪያ ቆሞ ከሰማይ ዝናብ ይጠብቅ ነበር:: እስከዛሬ ድረስ ባባልካን አካባቢዎችና እንዲሁም በጀርመን የገጠር ሥፍራዎች ዝናብ መዝነብ ካለበት ጊዜ ከዘገየ አንዲት ወጣት ሴት ልብሷ ከገላዋ ላይ ተገፎ ራቁቷን በአደባባይ ትቆምና በላይዋ ላይ አስማተኞች ውሃ እንደሚያፈሱ ሬናክ ከላይ በጠቀስነው መጽሐፉ አስፍሮት እናገኛለን::

በአንዳንድ የአፍሪካ ሃገሮች ደግሞ የድርቅ አደጋ ሲያንዣብብ ሚሲዮናዊ ይፈለግና ጥላውን ዘርግቶ በሜዳ ላይ እንዲመላለስ ያደርጉ



Scanned by CamScanner

ነበር ይባላል:: በሱማትራ አንዲት ሴት ልጅ መውለድ ሲያቅታት ወይም መኻን ከሆነች ከእንጨት ተቀርፆ የተሠራ የሕፃን ልጅ ምስል በጭኖቿ መሀል ለቀናት ይዛ እንድትቀመጥ ትደረግ ነበር:: በዚህም መኻንነቷ ይፈወሳል፤ ትፀንሳለችም የሚል እምነት ስለነበራቸው ነው::

በባባር ደሴቶች ደግሞ መኻን ሴት ትፀንስ ዘንድ ከቀይ ሐር አሻንጉሊት ትሠራና ጡቷ ላይ እንደምታጠባ አድርጋ በመያዝ አስማተኛው የሚነግራትን ቃል እየደገመች ለሙሉ ቀን ስትለፈልፍ ትውል ነበር:: በነጋታውም የመንደሯ ሰዎች እንኳን ደስ አለሽ ለማለት ተሰብስበው ይመጡ ነበር:: በዚያም መኻንነቷ ያበቃል ይላሉ:: በቦርኔኦ ደሴት ነዋሪዎች ዘንድ ደግሞ አስማተኛ በጥብቅ የሚፈለግበት ሰዓት ቢኖር ሴት ልጅ በምጥ ላይ ስትሆን ነው:: በምጥ ሰዓት የሚጠራው አስማተኛ ዋና ተግባሩ ልጁ ቶሎ የሚወጣበትንና የሴቷም ሕመም የሚታገስበትን «ተዐምር» መሥራት እንደነበር ሲታወቅ ይኸንንም የሚያከናውነው ሴቷ በምጥ ወደምትጨነቅበት ክፍል በመግባት «በራሱ ቋንቋ» እየተንጐራደደ ሲፀልይ ቆይቶ ከብብቱ አንዲት ጠጠር አውጥቶ በመጣል ነው:: ከዚያ በኋላ የሴቷ የምጥ ጭንቀት እንደሚቃለል ልጁንም በደህና እንደምትገላገል ሁሉም ያምናል::

ከታሪክ እንደምንረዳው በጥንት ዘመን አብዛኛዎቹ የበሽታ ፈውሶችም ሆኑ የችግር መፍትሔዎች የሚፈለጉት ከአስማተኛ ነበር:: ሰውነቱን በእከክ የተወረሰ ሰው ተወርዋሪ ኮከብ እየተመለከተ ፊቱን ቢታጠብ እከኩ ከሰውነቱ ላይ ይረግፋል ተብሎ ይታመናል:: እከኩ ካልጠፋ ሰውየው ተወርዋሪ ኮከቡን ለመመልከት አልፈጠነም ማለት ነው:: በመካከለኛው ዘመን የነበሩ ሰዎች ጠላታቸውን ለመግደል ሲፈልጉ ምስሉን ከንብ ሰም ይሠሩና በጦር ይወጉት ነበር ይባላል:: ጠላታቸውም በዚያ ቅፅበት ባለበት ቦታ ይሞታል ብለው ያምናሉ:: (በእኛ ሃገር ጥላ ወጊ ከሚባለው ጋር በመጠኑ ይመሳሰላል::) ዛሬ ድረስ ታዲያ በአንዳንድ የዓለም ክፍሎች የሚጠሉትን ሰው ምስል ከሰም ሰርቶ ማቃጠል



Scanned by CamScanner

ሰውዬውን ይገድለዋል ተብሎ ይታመንበታል:: ፔሩዎች ይህን ድርጊት ሲፈፅሙ «ነፍስን ማቃጠል» (burning the soul) በማለት እንደሚጠሩት ሬናክ በመጽሐፉ አስፍሮታል::

ብዙዎች አስማትን የሳይንስ አባት ነው ይላሉ:: አስማተኛው አስማቱን በሚያደርግበት ወቅት ካልተሳካለት መከራው በእሱ ላይ ዞሮ መምጣቱ አይቀሬ ነው፤ ይሁንና ከአብዛኛው የአስማት ሥራ በአጋጣሚ የሚሳካው አንዱ ብቻ ሲሆን ይኸም እጅግ ከበዛው አለመሳካት ይልቅ ጉልቶ የመሰማት ዕድል እንደሚያገኝ በጉዳዩ ዙሪያ የረዥም ዓመታት ጥናት ያደረጉት ምሁራን ይናገራሉ:: እንደምሁራኑ አስተያየት አብዛኞቹ አስማተኞች የአንድን ነገር ምክንያትና ውጤት ለመረዳት ከዚያም አልፎ የሚፈለገውን ውጤት ለማግኘት የሚሞክሩት ተፈጥሮአዊ ዘዴ በአስማታዊ ድርጊታቸው ውስጥ ጥበብን የማግኛ መንገዳቸው ይሆን ነበር:: በዚህም ጥበባቸው የአማልክትን ሥራ በምድር ላይ እንደሚቆጣጠሩ ተደርገው ይወሰዱ እንደነበር ከታሪክ ስንረዳ ከብዙዎቹ አስማተኞች ውስጥም አንዳንዶቹ ተዐምር አድራጊዎች፣ የሃይማኖት መሪዎች፣ የሕክምና ባለሞያዎች ሌሎቹ ደግሞ የከዋክብትና የጠፈር ሳይንቲስቶች ለመሆን በቅተዋል:: ዊል ዱራንት "The Pleasure of Philosophy" በሚለው መጽሐፉ ይኸንኑ ሲገልፅ:- «የዛሬዎቹ የዓለማችን ሳይንቲስቶች የምርምር ውጤት በትናንቱ አስማተኞች ግኝት ላይ የተመሠረተ ነው... ስለዚህም ሃይማኖትና ሳይንስ የፈለቁት ከአስማት ምድር ነው» ይለናል:: በዱራንት አባባል መሠረት የጥበብ መጀመሪያ አስማት መሥራት ሊሆን ነው::

ስለፀሐይና ጨረቃ፣ ስለምድርና በላይዋ ላይ ስለሰፈረው ፍጡር... በማሰብ ነገሮችን ሁሉ ከሰው ልጅ ሕይወት ጋር ለማቆራኘት የጥረቱ ጀማሪዎችና መሠረት ጣዮች አስማተኞች ነበሩ::

ከዚህ በመነሳት በአንዳንድ ሃገሮች የሚገኙ አስማተኞች ጥበባቸውና ችሎታቸው እጅግ ገኖ የወጣ ከመሆኑ የተነሣ አምላካቸውን ለማሸነፍ



Scanned by CamScanner

ሙከራ አድርገው ባይሳካላቸው እንኳን ከእነሱ ደካማነት ሳይሆን ከአምላካቸው ግትርነት ተደርጐ ይወሰድላቸው እንደነበር ጥንታዊ ታሪክ ይነግረናል:: በአውሬ አደን ላይ የተሰማሩ ግሪካውያን ወጣቶች አደናቸው አልሰምር ሲል ወደአስማተኛ በመሄድ ለአምላካቸው ምስል አድርገው የሠሩትን ቅርፅ እንዲገርፍላቸው ያደርጉ ነበር ይባላል:: በዚህም አምላካቸው ገርፊያው ተሰምቶት የአደን አውሬ እንደሚጠራላቸው የምታ ነበር:: የጣሊያን አሣ አጥማጆች ደግሞ ወጥመዳቸው ባሕሩ ወስጥ ተልኮ ባዶውን ከተመለሰ በአካባቢው እንዲት ድንግል ሴት ይፈልጉና ቅርጿን ከጭቃ በመሥራት ወደ ባህሩ ይጥሉ እንደነበር ሆበስ የተባለው ፈላስፋ "Morals in Evolution" በተባለው መጽሐፉ አስፍሮት እናገኛለን::

ጥንታዊ ቻይናውያን ደግሞ ከድንጋይ ሰርተው የሚሰግዱለት አምላካቸው (orisons) ፀሎታቸውን አልሰማ ሲል አውራ ጐዳና ላይ እየጐተቱ ያወጡትና:- «አንተ የውሻ መንፈስ... የሚያምር ቤተመቅደስ ሰርተን አስቀመጥንህ፣ ጣፋጭ ምግቦችን ሰርተን አመጣንልህ፣ መስዋዕትህን ዕለት ዕለት አቀረብን... አንተ ግን ምስጋና ቢስ ነህ» በማለት ሲሰድቡት፣ ሲያንቋሽሹትና በድንጋይም ሲወግሩት ይውላሉ::

እንግዲህ የጥንቱ ሰው በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ማለፍ የግድ እየሆነበት ሲመጣ ነገሮችን ሁሉ በአጋጣሚ ወይም በዕድል መተርጐም ጀመረ:: ይኸንንም ግሪኮ *Moira* ይለዋል:: ይኸ ሁኔታ በግሪክ ሃይማኖት የልዩነት ድንበር መሠረተና አማልክትና ሰው ለሁለት ተከፈሉ:: በዚህም አንዱ ወገን ወደአምላኩ ጉዞውን ሲጀምር የቀረው ደግሞ ጉዞውን ወደሳይንስ አቀና::

እንግዲህ በዚህ አካሄድ ስንመዝነው አስማት (Magic) ለሳይንስና ድራማ ብቻ ሳይሆን ለሃይማኖታዊ አምልኮ፣ ለመስዋዕትና ለፀሎትም በሩን የከፈተና እንዲያውም እነዚህ ድርጊቶች የተወሰዱት ከአስማተኝነት ልምምዶች ለመሆናቸው ማረጋገጫ ይሆነናል:: ለምሳሌ አሁን በየትኛ



Scanned by CamScanner

ውም ሃይማኖት ሲከናወኑ የምናያቸው የዐሉት ልምምዶች የተወሰዱት የጥንት ሰው አስማትን ለማከናወን ከሚያደርገው እንቅስቃሴና ንግግር ጋር በእጅጉ የተመሳሰለ ሆኖ እናገኘዋለን። ዊል ዱራንት ይህንኑ አስመልክቶ እንዳሰፈረው፡- «መልካም የሆነና ወደእኔ ይመጣል ብለህ የምታስበው ማንኛውም ዕቃ ወይም ጣዖት (Talismans)፣ በአፍህ የምታደርገው ቡራኬ (Benediction)፣ እንዲሁም እርግማን (Malediction)... ወዘተ በሙሉ የጥንቱ አስማት ውጤቶች ናቸው» ብሏል።

እያንዳንዱ ትውልድ በእያንዳንዱ ዓመት የሚያስጨንቀው ነገር ቢኖር የተሻለ የእህል ምርትን መሰብሰብ ነው። የጥንቱም ሰው ይኸው ሐሣብ ሲያስጨንቀው እርሻውን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን ዕውቀቱም አጋጣሚውም ስላልነበረው ዓመታትን ያስቆጠረው በአስማት መሬትን በማባበል ነበር። በዚህም ዘር የሚዘራበትን ወቅት ጠብቆ «የወንድ ብልት የማምለኪያ ፌስቲቫል» (Phallic Festival) ያደርግ ነበር። ይህን ፌስቲቫል የሚያደርግበት ዋነኛ ምክንያት የወንዱ ብልት ዋነኛ የመራቢያ መሣሪያ ሆኖ ስለሚታመን መሬትም እንዲሁ ዘሯን ትሰጠናለች በሚል እምነት ላይ ተመስርቶ ነው።

የሰው ልጅ የሕይወቱ መሠረት ለሆነችው መሬት ያደርግ የነበረው አስማታዊ አምልኮ ከጥንታዊ የሃይማኖት አምልኮዎች ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነበር። በዚህም ጥንታዊ አምልኮ መሬት የሕፃን ወይም የወጣት ደም መስዋዕት ይቀርብላት ነበር፤ በመቀጠል ደግሞ የሽማግሌ ደም ሲፈስላት ዓመታት ተቆጠሩ፤ ይኸም ደግሞ ሲቀር የእንስሳት ደም ማፍሰስ ተጀመረ። ይኸ ሁሉ ድርጊት እንግዲህ «ለመሬት መንፈስ» መሆኑ ነው። በዚህም ተደስታ መሬት ታበቅላለች ማለት ነው።

ለምሳሌ በኢክዋዶር የሚገኙ ሕንዶች እህል የሚዘሩበት ወቅት ሲደርስ በመካከላቸው ዕጣ ይጥሉና ዕጣው የወጣበትን ሰው በማረድ ደሙንና ልቡን ለምድር መንፈስ ያቀርቡ እንደነበር የተለያዩ የታሪክ መፃሕፍት ዘግበዋል። የቤንጋል ሕንዶች ደግሞ ለምድር መስዋዕት



Scanned by CamScanner

በማድረግ ያቀርቡ የነበረው የወንጀለኛን ሰው ደም ነበር:: የጥንት አቴናውያን በመካከላቸው ወረርሽኝ በሽታ ሲገባ አሊያም ድርቅ ሲከሰት ሁለት ወንጀለኞችን በማረድ ወንዱን የነገዱ ወንዶች፤ ሴቷን ደግሞ የነገዱ ሴቶች ወኪል በማድረግ መስዋዕት ያቀርቡ እንደነበር ሲታወቅ ይኸም የአንዱን ኃጢአት የማስተሰርይ (vicarious attonement) ሐሣብ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እንደመጣ እንረዳለን::

ለምሳሌ ኃጢአትን የማስተሰረይ አምልኮ በጥንታዊቷ የአቴና ታርጂኒያውያን ዘንድ የሚከናወነው ሁለት ፍየሎችን ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ በማቆም ኃጢአት የሰራ ሰው በድንጋይ እንዲወግራቸው በማድረግ ሲሆን ፍየሎቹ ሲሞቱም የሰዎቹ ኃጢአት አብሮ እንደሞተ ያምኑ ነበር:: ዊል ዱራንት ከላይ በጠቀስኩት መጽሐፉ «በአንዳንድ የዓለማችን ክፍሎች ከጥንት ጀምሮ የሰው ሥጋን መብላትና ደሙንም መጠጣት ኃጢአትን ያስተሰርያል በሚል እምነት ይከናወን እንደነበር ሲታወቅ በተለይ በጥንታዊ የሜክሲኮ ዘሮች ይህ ለዓመታት ሲከናወን ቆይቶ ከጊዜ በኋላ ግን ድርጊቱን ለማስቆም ከስንዴ ሊጥ የተሰራ አምላክ አቁመው አስማተኛው ለእሱ ከደገመለት በኋላ ይበሉት ነበር...» በማለት አስፍሯል::

ዱራንት በሰነዘረው ሐሣብ የአስማትን ጉዳይ ላብቃ:- «የሰው ልጅ አስፈሪው ኋላቀርነቱ አልፎ ከሰው መስዋዕት ወደ እንስሳ መስዋዕት ሲሸጋገር ለማየታችን መልካም ምሳሌ የሚሆነን አብርሃም ይስሐቅን ለመስዋዕት ካዘጋጀ በኋላ በበግ መተካቱ ነበር» ብሏል::

# የነፍስ ሙዚቃ የሥጋ ልምምድ ውጤት ነው

ከሞት በኋላ የሚኖረን «ሕይወት» የሚያሳስበን ስንቶቻችን እንሆን ቢያንስ ከሞት በኋላ የሥጋ ጉዳይ እንደሚያከትምለት የጋራ ግንዛ ይኖረናል ብዬ አምናለሁና የሚያነጋግረን ቀሪ ጉዳይ ነፍስ ትሆናለች። በዚህ ምዕራፍ ደግሞ በፈላስፎቹ ዓይን ነፍስን እንመልከታት። ነፍ (Soul) አንዳንድ ጊዜ መንፈስ (spirit) በሚል መጠሪያም ትታወቃለች መገኛዋም ሕይወት ባለው ነገር ውስጥ ብቻ ነው ይላሉ። በዚህ አካሄ ሥጋ አለ፤ ሥጋው ሕይወት አለው፤ ሕይወት ደግሞ በውስጡ ነፍ ይዟል። የሰውን አፈጣጠር ከመጀመሪያው እንመርምር:-

*«እግዚአብሔርም አለ:- ሰውን በመልካችን እንደምሳሌአች እንፍጠር»* (ዘፍጥ. 1:26)

በዚህ አካሄድ እግዚአብሔር መልክ ነበረው፤ የእግዚአብሔር መል ደግሞ መንፈስ ነው። ስለዚህም ሰው መንፈስ ነበር። እግዚአብሔር ግ የፈጠረውን መንፈስ በዚያው በቃህ አላለውም። ከአፈር አቡክቶ አሁን የሰጠውን ቅርፅ ሰራና በዚያ ውስጥ አኖረው።

*«እግዚአብሔርም አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው...»* (ዘፍጥ. 2:7

ነገር ግን ሰው አሁንም ለእግዚአብሔር ተሰርቶ ያላለቀ ዕቃ ሆነበት። ምክንያቱም ሰው ሕይወት አልነበረውምና።

ሰው እንደዚህ በብዙ ድካም ተሰርቶ ካለቀ በኋላ ትሞታለህ ተባለ:: ሲፈጠር ጀምሮ ዘላለማዊነትን በልቡ ያኖረው ሰው «በአንተ መልክ ተፈጥሬ ከሞትኩማ የአንተን ዘላለማዊነት ጥርጣሬ ውስጥ ትከተዋለህ...» አለ::

እግዚአብሔርም እኔን የሚመስለው ነገርህ ብቻ አይሞትም አለ:: ስለዚህም ይኸች የማትሞተው ነገር አነጋጋሪ ሆነችና ዛሬ ወደ እሷ አቀናን::

አንድ ሕይወት ያለው ነገር በሕይወቱ ማብቂያ ሰዓትና ከሞተ በኋላ በሥጋው ላይ «ምንም» ለውጥ አያመጣም:: ነገሩን ግልፅ አድርጎ ለማስቀመጥ «አንድ ሰው በጠዋት ቢሞት ከሰዓት በኋላ (ነፍሱም ብትወጣ) ቅፅበታዊ ለውጥ አይመጣም::» ምክንያቱም ነፍሱ ሌላ ቦታ ብትሄድም፣ ሥጋው ግን አልሄደምና:: «ስለዚህ» ይላል ፕሌቶ «ነፍስ ለእኛ እምብዛም አስፈላጊ ያልሆነች (immaterial) ነገር ነች» ካለ በኋላ ይኼንኑ ሲያብራራ «የነፍስ አላስፈላጊነት ዋነኛ ምክንያት የምትሞት ነገር አለመሆኗ ነው» ይለናል:: የእሱ ደቀመዝሙር አሪስቶትል ደግሞ «ነፍስ ከሥጋ ተለይታ ወደ ሌላ ዓለም ተሸጋግራ መኖሯን መቀበል አስቸጋሪ ነገር ነው» ብሏል::

ከ85e-86D ከኖረው ሲሚያስ ፍልስፍና በመነሳት የነፍስ ጉዞ እንጀምር:-

ሲሚያስ:- «ሶቅራጥስ ሆይ:- አንድን የሙዚቃ መሣሪያ ክሮች ብትመታቸው (ብትጫወታቸው) የምትሰማው የተዋበ (መለኮታዊ) ድምፅ ነው:: ይኸ ድምፅ አይታይም፣ ነገር ግን ከሚታይ፣ ከሚነካ፣ ከሚጠፋ ምድራዊ ነገር ወጥቶ መጣ:: (በሥጋ /አፈር/ ውስጥ ያለ ነፍስ እንደማለት ነው::) ነፍስም እንዲሁ ነች::»

ሶቅራጥስ:- «አሁን የሙዚቃ መሣሪያው ተሰበረ፣ ወይም ክሮቹ ተበጠሱ እንበል:: በአንተ መላምት መሠረት 'መሣሪያው ቢጠፋም ድምፁ



Scanned by CamScanner

አይጠፋም' እያልከን ነው? ነገር ግን የሙዚቃ መሣሪያው ሲሰበር ወይም ክሮቹ ሲበጠሱ ያ ድምፅ አብሮ ጠፋ:: ድምፁ ዘላለማዊ ቢሆን ኖሮ ጠፊ (ሟች) ከነበረው የሙዚቃ መሣሪያ ባህርይ ባልተጋራ ነበር:: ምክንያቱም ድምፁ የኖረው መሣሪያው እስከኖረ ድረስ ብቻ ነው...»

ሲሚያስ:- «እዚህ ላይ እኛ የፓይታጐረስ ተማሪዎች የሆንነው (ፓይታጐረስ ከሶቅራጥስ ዘመን በፊት 570?- 495? BC የኖረ ታላቅ ፈላስፋ ነበር) አንድ የምናምነው ነገር እንዳለ ደግሞ አትዘንጋ:: እንደምታውቀው ሥጋችን በሙቀትና ቅዝቃዜ፣ በእርጥበትና ድርቀት... ወዘተ ጫፎች መካከል ተወጥሮ የተያዘ ነገር ነው:: ነፍሳችን ደግሞ የሁለቱ ጫፎች ማዕከል ሆና የምታያይዝ (adjustment) ነች:: እንግዲህ ሥጋችን የተወጠረበትን ሁለት ጫፍ የምታያይዝ ነፍስ ስትሆን ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ከሙቀቱ ቅዝቃዜው አይሎ ሥጋችን ደንዝዞ ይቆይና ወደ ነበረበት ሲመለስ ነፍሳችን ግን አለች::»

ሶቅራጥስ:- የሙዚቃ ድምፅ የምትሰማው የሙዚቃ መሣሪያ ሲኖር ነው::

ሲሚያስ:- ትክክል::

ሶቅራጥስ:- በነገሮች መካከል መስማማት ይኖር ዘንድ ደግሞ በመጀመሪያ የሚስማማው ነገር መኖር የግድ ነው::

ሲሚያስ:- አዎን፤ እስማማለሁ::

ሶቅራጥስ:- ስለዚህ ነገሩ (ሥጋና ነፍስ) መስማማትን ይቀድማሉ እንጂ አይከተሉትም?

ሲሚያስ:- ልክ ብለሃል::

ሶቅራጥስ:- የአንዱ ነፍስ ከሌላው ነፍስ ይበልጣል ብለህ ታምናለህ?

ሲሚያስ:- አላምንም::

ሶቅራጥስ:- ነገር ግን የአንዱ ነፍስ ደግነትና እውቀት የሌላው ደግሞ



Scanned by CamScanner

ለንፍናና ክፋት ሞልቶበታል?

ሲሚያስ:- እውነት ነው::

ሶቅራጥስ:- ነፍስ በሥጋ ውስጥ የሚገኝና ከሥጋ ጋርም ተስማምቶ (Harmony) የሚኖር ነገር ከሆነ በውስጡ ክፋት ወይም ደግነት እንዴት ይገኙበታል?

ሲሚያስ:- አልገባኝም::

ሶቅራጥስ:- በዚህ መንገድ ተመልከተው:: የሙዚቃው መሣሪያ ላይ ያሉት ክሮች በሚገባ ተደርድረው ሲመቱ ጥሩ ሙዚቃ ይወጣል:: እንደማይገባ ሲመቱ ደግሞ ሙዚቃው (ድምፁ) የተበላሸ ይሆናል:: ቅንነት የሞላበት ነፍስ ውስጥ የምንሰማው ድምፅ ያማረ ሲሆን፣ ክፋት የሞላበት ነፍስ ደግሞ እንደተበላሸ ሙዚቃ ክፋትን እንሰማበታለን::

ሲሚያስ:- ትክክል

ሶቅራጥስ:- ነገር ግን የአንዱ ነፍስ ከሌላው ነፍስ እንደማይበልጥ ተስማምተን ነበር እኮ?

ሲሚያስ:- በእርግጥ አይበላለጥም::

ሶቅራጥስ:- ስለዚህ በጥሩም ይሁን በመጥፎ የተቃኘ ሙዚቃ አንዱ ከሌላው ልዩነት የለውም ማለት ነው?

ሲሚያስ:- እውነት ነው::

ሶቅራጥስ:- እንግዲህ በዚህ ሁኔታ መጥፎም ሆነ ጥሩ የምንለው ሙዚቃ የለም ማለት ይሆናል?

ሲሚያስ:- ይመስለኛል::

ሶቅራጥስ:- ታዲያ በዚህ ከተስማማን መጥፎ ሙዚቃ የክፋት፤ ጥሩ ሙዚቃ ደግሞ የደግነት አድርገን በነፍስ ውስጥ እንመልከተውና ጥያቄ እናንሳ:: እንዴት አንዲት ነፍስ ከሌላው ነፍስ የበለጠ ክፋት ወይም ደግነት ልትይዝ ትችላለች?

ሲሚያስ:- የሚቻል አይመስልም::



Scanned by CamScanner

ሶቅራጥስ:- አንተ የምትለው ግን በተቃራኒው ነበር:: 'የትኛውም ነፍስ ደግነት ካለበት ክፋት ሊኖርበት አይችልም፤ ምክንያቱም ነፍስ ዜማን ስንሰማው ጥዑም የሚያደርገው በውስጡ የተበላሸ ነገር ስለሌለ ነው' የሚል ነበር::

ሲሚያስ:- ልክ ብለሃል::

ሶቅራጥስ:- እንግዲህ ነፍስም «ነፍስ» ከሆነች ክፋት በውስጧ ሊገኝ አይችልም ማለት ነው?

ሲሚያስ:- በተነጋገርነው መሠረት ከሆነ ትክክል ነህ::

ሶቅራጥስ:- በነፍስ ተፈጥሮ ውስጥ ሁሉም ነፍስ እኩል ከሆነ የሰው ሁሉ ነፍስ በእኩል ደረጃ ጥሩ ነው ማለት ይሆናል::

ሲሚያስ:- ይመስለኛል::

ሶቅራጥስ:- ግን ይኸ አመለካከት ትክክል ይመስልሃል? ነፍስ እንደ ጥዑም ዜማ ወይም እንደተበላሸ ድምፅ ነች ከሚለው መላምት ባንነሳ ኖሮ እኮ እዚህ መደምደሚያ ላይ አንደርስም ነበር::

ሲሚያስ:- አሁንም ትክክል ነህ::

ሶቅራጥስ:- ነገር ግን ከነፍሱ ውጭ በሌላ ነገር የሚመራ ሰው አይተህ ታውቃለህ?

ሲሚያስ:- በፍፁም አላውቅም!

ሶቅራጥስ:- እንግዲህ ነፍስ የሥጋን ስሜት ትታዘዛለች ወይስ ትቃረናለች? ለምሳሌ አንድ ሰው ለመጠጣት ተጠምቶ ነፍሱ ግን እንዳይጠጣ ትገፋዋለች፤ ተርቦም እንዳይበላ ታደርገዋለች (በዘመናችን እንደፆም መሆኑ ይሆን?)፤ ስለዚህ ነፍስ የሥጋን ፍላጐት ስትቃወም ታያለህ? ነገር ግን የሙዚቃውን መሣሪያ ስትመታው የተመታውን ነገር ድምፅ እንጂ እሱን ተቃርኖ ሌላ ድምፅ አያወጣም:: ድምፁ ክሩን አያዝዘውም፤ ነገር ግን ድምፁ የክሩ ውጤት ይሆናል::

ሲያሚስ:- አሁን እየገባኝ ነው::

ሶቅራጥስ:- ነገር ግን ነፍስ በተቃራኒው ደግሞ ስትሰራ እናያታለን::



Scanned by CamScanner

የተቃኘችበትን መሣሪያ ትመራዋለች፤ መምራት ብቻም አይደለም ታገዘዋለች፤ በሕይወት አቅጣጫ ሁሉ ትቃወመዋለች፤ አንዳንድ ጊዜም ክፉ ትሆንበታለች። ስለዚህም ነፍስን እንደተቃኘ ሙዚቃ የክሩ ውጤት አድርገህ አትመልከታት... ብዙ ጊዜ ሥጋም በነፍስ ይቃኛልና...

* * *

የሶቅራጥስ ደቀመዝሙር የነበረው ፕሌቶ መልካም ነፍስ ከክፉ ነፍስ ይልቅ እንደተቃኘች ሙዚቃ ናት ይላል። ምክንያቱም የነፍስ ቃኝት ራስን ከመግዛት ይጀምራልና፡- «የሰው ነፍስ በብቃት ደረጃ እኩል ነው፤ ነገር ግን አንዱ ነፍሱን ለክፉ ሲያስለምዳት ሌላው ደግሞ ለበጎ ያስለምዳታል። ስለዚህም የነፍስ ሙዚቃ የሥጋ ልምምድ ውጤት ነው» ይለናል።

ጥንታውያን የግሪክ ፈላስፎች የሰው ልጅ ዕጣ በአማልክት እጅ ውስጥ ነው በሚለው ሐሣብ እስከተወሰነ ደረጃ ይስማሙበት ነበር። ይኸውም አማልክት (በጊዜው ብዙ አማልክት ነበሩ) በሰው ነፍስ የሚያገባቸው ሰውዬው እስከ ሞተ ድረስ ብቻ ነበር። ለዚህም ይመስላል «የሰው ልጅ ዕጣ በአማልክት እጅ መሆኗን የሚያሳዩን አማልክቱ ሞትን ለማስቆም ፍቃደኛ ባለመሆን ነው» የሚሉን።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ750 ይኖሩ የነበሩ ግሪካውያን ሙታኖቻቸውን የሚቀብሩበት ወግና ባህል ነበራቸው። ይኸውም አንድ ሰው ከመካከላቸው ሲሞት ጠለቅ ያለ ጉድጓድ ቆፍረው በመቅበር ከላዩ አፈር በደንብ ያለብሱት ነበር ይባላል። የኦሊምፐስ አማልክት ሙታንን በቅርብ ካዩ ይቆጣሉ፤ በምድርም ላይ መዓት ያመጣሉ የሚለው የመጀመሪያው ጠንካራ እምነታቸው ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሰው ነፍስ ወደታችኛው የሙታን ዓለም እንዲወርድ ከተፈለገ ጠለቅ ብሎ ሊቀበር ይገባል የሚለው ሌላው የጊዜው እምነት ነበር።

የአቴናውያኑ የሌላ ወገን እምነት ደግሞ ለሙታን የነበራቸው



Scanned by CamScanner

ክብር ከፍ ማለቱ ላይ ሲሆን በዚህም ነፍስ ከሥጋ ብትለይም ማልቀስ ተገቢ አይደለም፤ ምክንያቱም ነፍስ የለቅሶ ድምፅ ከሰማች ተመልሳ ሥጋ ውስጥ ትገባለች በማለት ያምኑ ስለነበረ ነው፡፡ ነገር ግን ሬሳው ይታጠብና ያጌጠም ልብስ ያለብሱትና ወስደው ይቀብሩታል፤ በመቃብሩ ዙሪያም ጥሩ ጥሩ ምግብና መጠጥ ያስቀምጡለታል፡፡ ነፍስ በመቃብሩ ዙሪያ ለጥቂት ቀናት ስታንዣብብ ቆይታ ስለምትሄድ (ምናልባት እስከሳልስት ይሆናል) መሰናበቻዋን ተደስታ ትሸኝ በማለት ነበር፡፡ ነገር ግን እስከዛሬ አብዛኛዎቹ ፈላስፎች በነፍስ ዙሪያ የሚያነሱት ጥያቄ የምትሄድበትን በማወቅ ላይ ያተኮረ ሳይሆን የምትገኝበትን ማወቅ እንደሆነ ቀርቷል፡፡ የነፍስን አድራሻ በሌሎች ምዕራፎች እንመረምራለን፡፡



Scanned by CamScanner

# ቁጣ እብደት ብቻ ሣይሆን ውበትም ነው

የፕሌቶ ደቀመዝሙር የነበረው አሪስቶትል ቁጣን ሲገልፀው፡- «ማንም ሰው መቆጣት ይችላል፤ መቆጣት ቀላል ነውና:: ነገር ግን ተገቢውን ሰው፣ በተገቢው ደረጃ፣ በትክክለኛው ሰዓት፣ ለትክክለኛው ዓላማ፣ በትክክለኛው መንገድ መቆጣት ግን በማንም ሰው ውስጥ የሌለ ችሎታ ብቻ ሳይሆን የማይቻልም ነው» ብሎታል::

ታላቋ አሜሪካ እንኳን በራሷ ቀርቶ እሷን በተወዳጁትም ይደርሳል ብላ የማትጠብቀው በትር ሴፕቴምበር 11/2001 ባረፈባት ማግሥት አንድ አሜሪካዊ ወጣት፡- «አንድ ወይም ሁለት ሃገር ድምጥማጡን ልናጠፋ ይገባል» በማለት በንዴት የተንገበገበ አስተያየት በቴሌቪዥን ሲሰጥ ተደመጠ:: ነገር ግን ወጣቱ ድምጥማጥ የሚጠፉትን ሃገሮች ስም አልጠቀሰም:: የሮማው ጳጳስ ደግሞ «ፍርድ እንጂ በቀል አያስፈልግም» በማለት የአሜሪካን ቁጣ ለማብረድ ሞከሩ:: ጳጳሱ ይህን ቢሉም በፍርድና በበቀል መካከል ያለውን ልዩነት እንዲያብራሩ የጠየቃቸው ሰው አልነበረም፤ እሳቸውም ሊያብራሩ አልሞከሩም::

በዘመናችን የቁጣና የእብደት ልዩነት ብዙም የሚጋነን አይደለም የሚሉ የሳይኮሎጂ ምሁራን በብዛት እየወጡ ነው:: ይሁንና ለዛሬ ቁጣን ለይተን እንዴ በተገጠመልን የጥበብ መነፅር እንድናየው እወዳለሁ::



Scanned by CamScanner

መነሻችን አሜሪካዊው የሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ምሁር ዊሊያም ሀሪስ በቅርቡ፡- "Restraining Rage: The Ideology of Anger Control in Classical Antiquity" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሐፍ ዙሪያ የሚያጠነጥን ሲሆን ይኸ ምሁር «ቁጣ እብደት ብቻ ሳይሆን ውበትም ነው» ይለናል:: «ለነገሩ የቁጣ ምንጭ ሰይጣን ወይም እግዚአብሔር አይደሉም:: ለምን ቢሉ ሁለቱም ይቆጣሉና:: ስለዚህም የእኔ መቆጣት ሰይጣንንም ሆነ እግዚአብሔርን አይወክልም» ይላል ሀሪስ::

ሀሪስ በመጽሐፉ ስለቁጣ የመጀመሪያ ምሳሌው አድርጐ ያስቀመጠው ሴኔካን ነው:: ሮማዊው የስቶይሲዝም ፍልስፍና አራማጅና የንጉሡ የኔሮ መምህር የነበረው ሴኔካ ቁጣን ሲገልፅ፡- «አንድን ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አድርጐ የሚያስነሳ ነገር ቢኖር ቁጣ ብቻ ነው» ይላል:: «ቁጣ በአንድ ሕዝብ ላይ መከራን ያመጣ ጠላት ለመበቀል የሚያነሳሳ ኃይል ነው... በአንዲት ሴት ፍቅር ተይዞ የተሰቃየ ሕዝብ የለም... ተስፋውን በገንዘብና በሀብት ላይ በአንድ ልብ የመሠረተ ሣገርም አይገኝም፤ ምክንያቱም የሀብት ምኞትም ይሁን የሴት ፍቅር ግላዊ ነውና:: ነገር ግን ቁጣ የሕዝብ የጋራ ሀብቱ ነው:: ስለዚህም የሕዝብ ቁጣ አንድና በአንድ ላይ የሚገለፅ ነው» ብሏል::

ሀሪስ በመግቢያው ይህን ካሳየን በኋላ የቁጣን ውስጣዊ ምንነት ሊያሳየን የሚነሳው በምዕራባውያን የሥነ ጽሑፍ ታሪክ ላይ ተመስርቶ ነው:: «የምዕራባውያንን የሥነ-ጽሑፍ ታሪክ ስንመረምር» ይላል ሀሪስ «ቁጣ በድርሰታቸው ቅድሚያውን ቦታ የሚሰጠው ሆኖ እናገኘዋለን:: ሆሜር በኢሊያድ ድርሰቱ የፀሎቱ መጀመሪያ ያደረገው «የአኪለስ ቁጣ፤ ዘምሪ፣ አምልኪ» በማለት ነበር ይለናል:: ስለዚህም የሥልጣኔአችን የመጀመሪያ ድርሰት የመጀመሪያው ቃል ቁጣ ሆኗል» ብሏል:: በዚህ ቁጣ ላይ የተመሰረተው የሆሜር ድርሰትም የተዋጣ ሆነ::

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ900. ዓ.ዓ. አቅራቢያ እንደተወለደ የሚገመተው አይነ ስውሩ የግሪክ ባለቅኔና ፈላስፋ ሆሜር በትክክለኛነቱ



Scanned by CamScanner

ዓለም የተቀበለውና ተፅፎ የሚገኝ ታሪክ የሌለው ሰው ነው። ከሄሬዶትስና ከፕሉታርክ ተፅፎ የተገኘ ነው የተባለው ባለሁለት ይዘት ያለው ታሪኩም ቢሆን በኋላ ዘመን በተደረገው ምርመራ በእነዚሁ ሰዎች እንዳልተሰራ ለማወቅ ተችሏል።

ቁጣን በድርሰቱ ለማሳየት የመጀመሪያው ሰው ነው የሚባለው ሆሜር በኢሊያድ ድርሰቱ ውስጥ በሚያሳየን የአኪለስ ቁጣ ዙሪያ ያለውን ታሪክ ሀሪስ በመጽሐፉ በሰፊው አስፍሮታል። በመጠኑ ልቀንጭብላችሁ:-

«...ትሮይ በወቅቱ ስማቸው ገናና የሆነ ታላላቅ ጀግኖች የሚገኙ ብት ብርቱ የሆነ ጦር የነበራት ከተማ ናት። የግሪክ ሰዎች ይህችን ከተማ ሊወጉ እንደመጡ በዙሪያዋ የነበሩ የእስያ ሃገራት ሲሰሙ ሊረዷት ወደ እሷ መጡ። ይህ የሆነበት ዋነኛ ምክንያት የትሮይ ንጉሥ የፕሪያም ልጅ የግሪክ ንጉሥ ሚስት የነበረችውን እሌኒ የተባለችውን ሴት ነጥቆ በመውሰዱ ምክንያት በግሪክና በትሮይ ብሎም በዙሪያዋ በነበሩ ወዳጆቿ መካከል የቆየ ቂም በመኖሩ ነበር።...

«...ጦርነቱ ተጀምሮ አንድ ጊዜ ግሪኮች እየገፉ የትሮይ ከተማ እስከምትገኝበት ግንብ ድረስ የትሮይን ጀግኖች ሲያባርሩ በሌላ ጊዜ ደግሞ ድሉ የተገላቢጦሽ ለትሮይ ሲሆን ጦርነቱ አሥር ዓመት ቆየ፣ በአሥረኛው ዓመት ግን ዩሊስ የሚባለው የግሪክ አርበኛ የትሮይን ግንብ ለመጣስ የሚያስችል መላ አመጣ። ይኸውም በእንጨት የተቀረፀ ትልቅ ፈረስ ሰርቶ ጦር ሠራዊቱን እዚያ ውስጥ መክተት ነበር...

«...በዩሊስ እቅድ መሠረትም ፈረሱ ተሠርቶ በሌሊት የግሪክ አርበኞች ወደትሮይ ግንብ ተጠግተው በሩን እየከፈቱ ከገቡ በኋላ እንቅልፍ ወስዷቸው የተኙትን የትሮይን ሕዝቦች ፈጇቸው፣ ከተማይቱንም በእሳት አቃጠሉ።»

ሆሜር በኢሊያድ ድርሰቱ የትሮይን መውደቅና መቃጠል ብቻ ሳይሆን በተለይ በጦርነቱ 10ኛ ዓመት ላይ የግሪኩን ጀግና የአኪለስን



Scanned by CamScanner

የቁጣ ታሪክ ሊያሳየን እንደሞከረው ሀሪስ ይነግረናል:: «ሆሚር በግጥሙ የአኪለስን ቁጣ ምንጭ ከግሪኩ የጦር አዛዥ ከአጋሜኖን ድርጊት ጋር የተያያዘ የቁጣ በቀል ነው ይለናል። አጋሜኖን በአኪለስ ላይ ለፈፀመው ስህተት አኪለስ የግሪክን ጦር በሜዳ በትኖት እንዲሸሽ አደረገው:: የጀግና መሪው የአኪለስ ከጦር ሜዳው መውጣት ያስደነገጠው የግሪክ ጦርም መበተን ጀመረ...

«...በሽሽቱ የገፋው የግሪክ ጦርን ለማዳን አኪለስ አልፈለገም፤ ፍፃሜውን ከሩቅ ሆኖ ግን መጠበቅ ጀመረ:: የግሪክ ጦር እየተበተነ ወደ መርከቡ ለመውጣት በሚሞክርበት ጊዜ የትሮይ ሰዎች አንዱን መርከብ አቃጠሉት:: በዚህ ጊዜ ለማምለጥ መንገዱ ሁሉ የተዘጋበት የአኪለስ የልብ ጓደኛ ፓትሮክለስም በትሮይ ልዑል ሄክቶር እጅ ተገደለ::

«...የጓደኛውን መገደል የተረዳው አኪለስ በዚህ ሰዓት በትሮይ ሰዎች ላይ ቁጣው ነደደ፤ ለበቀልም ተነሣ:: የአኪለስን ወደጦር ሜዳ መመለስ የተመለከተውና በሽሽት ላይ የነበረው የግሪክ ጦርም ተበራታ... የትሮይ ሰዎችንም ማሳደድ ጀመረ:: የአኪለስ የቁጣ በቀል በመጀመሪያ ያረፈችውም በጓደኛው በፓትሮክለስ ገዳይ በልዑል ሄክቶር ላይ ነበር:: አኪለስ የጓደኛውን ደም ልዑሉን ገድሎ በመበቀል ብቻ አላቆመም:: ነገር ግን የልዑሉን ሬሣ በጓደኛው መቃብር ላይ ሦስት ጊዜ በማዞር ጣለው::» ሀሪስ በመጽሐፉ ይህን ያቀረበበት ዋነኛ ምክንያትን ሲገልፅ አሁን እስከአለንበት ዘመን ድረስ የግሪኮች ቁጣ መሠረትና ምንጭ የአኪለስ ቁጣ ተደርጐ ስለሚታመንበት እንደሆነ ያትታል::

እንደሀሪስ:- «ግሪኮች ከጥንት ጀምሮ ለአኪለስ ቁጣ እጅግ ከፍተኛ ግምት ይሰጡታል:: በአንደኛው ክ.ዘ. በሃገራት መካከል የሚነሱ ጦርነቶችና በሰው ልጅ ላይ የሚደርሱ እልቂቶችም በአኪለስና በአጋሜኖን ቁጣ ይመሰሉ ነበር» ብሏል:: አኪለስ በቁጣው ብቻ ሳይሆን በጀግንነቱም ወደር የማይገኝለት ተምሳሌት ነበር:: አኪለስን ድል ለማድረግ ፈፅሞ የማይታሰብ በነበረበት በዚያ ዘመን ታዲያ መራር የሽንፈትን ፅዋ



Scanned by CamScanner

እንዲጋት ያደረገው ድክመቱ በጦላቶቹ ዘንድ በመታወቁ ሲሆን የአኪለስ ድክመትም የተረከዝ ሕመሙ ነበር። እነሆ እስከዛሬ ድረስ "Achilles Heel" የሚል ቃል በእንግሊዝኛው መዝገበ ቃላት ላይ ሰፍሮ ይገኛል። "Achilles Heel" አንድ ሰው በተፈጥሮው ላለበት ድክመት መገለጫ ሆኖ እስከዛሬ ድረስ እየተጠቀምንበት እንገኛለን።

ሀረስ በመጽሐፉ፡- «የግሪኮች ብቻ ሣይሆን የጣሊያን ጥንታዊ ሥነ ጽሑፎችም መነሻቸው ቁጣ ነበር» ይለናል። «ቁጣው የሰው ልጅ ሊሆን ይችላል ወይም ደግሞ የእግዚአብሔር፤ ነገር ግን መደምደሚያው በቀል ነበር» በማለት ሀሪስ በአውሮፓ ጥንታዊ ከሚባሉት የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች አንዱ በሆነው 'ዮሪፒደስ' ውስጥ ቁጣን ይገልፅልናል። «ንጉሥ ሂፖሊተስ ለሚያመልካት ለአርጤሚስ ሕይወቱን በመቀደስ ሰጥቷል፤ ከዕለታት አንድ ቀን ለአምላኪቷ ቀድሶ የሰጣትን ሕይወቱን ወሰደና አጉደፋት፤ በዚህም ሥራው የአርጤሚስ ቁጣ ወረደበትና በራሱ ፈረሶች ተረጋግጦ ሞተ። የአማልክት ቁጣ መገለጫ እንግዲህ ይህን ይመስል ነበር።» ይላል።

ከክርስቶስ ልደት በፊት በ60 ዓ.ዓ. የኖረው ጠቢቡ ሲሴሮ ስለቁጣ ሲናገር «በንግሥና ዙፋን ተቀምጦ በቁጣ ቀንበር ሥር እንደሚሰቃይ ንጉሥ የሚያሳዝን የለም» ይላል። ለዛሬ የስቶይሲዝም ፍልስፍና አራማጅ በነበረውና በመግቢያዬ ላይ በጠቀስኩት በሴኔካ የንጉሥ ፒሶ ታሪክ ልሰናበት፡-

«ግኔስ ፒሶ በጣም አድርጌ የማስታውሰውና በሐሣቤ ሲመጣም ቁጡነትንና ግትርነትን ከአስተዋይነት መለየት የተሳነው ሰው አድርጌ እቀርፀዋለሁ። አንድ ቀን አንድ ወታደር ለአሰሳ ከወጣበት ሲመለስ አብሮት የወጣውን የመቶ አለቃ ትቶት ብቻውን ይመለሳል። ይኽን የሰማው ፒሶ ወታደሩ እንዲገደል ትዕዛዝ ሰጠ። ለሞት ፍርዱም ምክንያት፡- «ወታደሩ መቶ አለቃውን ገድሎት ሊሆን ይችላል፤ ባይገድለውም ደግሞ አለቃውን ትቶ መምጣቱ በራሱ ብቻ ያስገድለዋል»



Scanned by CamScanner

የሚል ነበር፡፡ ገዳዩም ወታደሩን ለመግደል ወደ አንድ ከፍታ ቦታ ይዞት ይወጣና ሰይፉን ሲመዝ የመቶ አለቃው ድንገት ከተፍ አለ፡፡ ገዳዩ በዚህ ጊዜ ደስ ተሰኝቶ ሰይፉን ወደቦታው መልሶ ወታደሩንና የመቶ አለቃውን ይዞ ወደ ቤተ መንግሥት ይገሰግሳል፡፡ ይኸን ጊዜ በቤተ መንግሥቱ ደስታ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ፒሶ ሦስቱን ሰዎች ሲመለከት ቁጣው ነደደ፡፡ ወዲያውኑ ሦስቱም ተይዘው እንዲገደሉ አዘዘ፡፡ ፒሶ ለዚህ ምክንያቱን ደግሞ ሲናገር፡- «የመጀመሪያው እንዲሞት አስቀድሜ ስለፈረድኩበት ይሞታል፤ ሁለተኛው ወታደሩን እንዲገድል ትዕዛዝ ከሰጠሁት በኋላ ትዕዛዜን ባለመፈፀሙ ይሞታል፤ ሦስተኛው የመቶ አለቃ ደግሞ ለወታደሩ ሞት ምክንያት በመሆኑ እሱም ይሞታል...» በማለት ፈረደ፡፡ ሴኔካ የቁጣን ውበት ከገለፀባቸው የቁጣ ታሪኮች አንዷ እንግዲህ ይኸች ነበረች፡፡ «ከቁጣው» ይሰውረን፡፡



Scanned by CamScanner

# ከጠገበ አሳማ የራበው ሰው ይሻላል

«የጠገበ አሳማ ከመሆን የራበው ሰው መሆን እጅግ የተሻለ ነው... የጠገበ ሰነፍ ሰው ከመሆን ደግሞ የተራብ ሶቅራጥስ መሆን በጣም ይሻላል:: አሳማውም ሆነ ሰነፉ ሰው የሚኖራቸው የራሳቸው ሐሣብ ብቻ ነው::... በአንፃሩ ያሉት ግን በሁለቱም ወገን ያለውን ሐሣብ በሚገባ ያውቁታል...::» ጆን ስቴዋርት ሚስ ሄዶኒስት ነበር:: በሄዶኒዝም ደግሞ የሰው ልጅ ዋነኛ ግብ ደስታ መመኘት ነው:: እንደስቴዋርት እምነት ይኸ ደስታ በዓይነት (qualitatively) የሚወሰን ነው:: «ከአንዲት ሴት ጋር ተኝተህ የምታገኘው ደስታና አንድ መጽሐፍ ጽፈህ የምታገኘው ደስታ እኩል አይሆንም:: ምክንያቱም የሁለቱም ደስታ በዓይነት ስለሚወሰን ነው» ይለናል::

«ስለዚህም የጠገበ አሳማ ከሚያገኘው ደስታ ይልቅ የራበው ሰው ደስታ እጅግ ይበልጣል... ለምን ቢባል ሰው እየራበውም ቢሆን ማሰብ ይችላልና:: እንደማሰብ ደግሞ ደስታ የሚያተርፍልህ ነገር የለም» በማለት ስቴዋርት ሚል ይናገራል::

ሄዶኒዝም የሞራል የፍልስፍና ፈርጅ ሆኖ አትኩሮቱ «ደስታ» ላይ ነው:: የዚህ ፍልስፍና አራማጆች ደግሞ ሄዶኒስት ይባላሉ:: ቀጥሎ ከእነሱ ባህር ጥቂት እንጨልፋለን::

የሶቅራጥስ ተማሪ የነበረውና ከክርስቶስ ልደት በፊት በ435 በሊቢያ ተወልዶ በ366 አቴና ውስጥ የሞተው አሪስቲፐስ የሄዶኒዝም ፍልስፍና መሥራች እንደሆነ ይገመታል:: እንደ አርስቲፐስ እምነት:- «ለአንድ ሰው መልካም ሕይወት የሚባለው ለደስታ ብቻ ዋጋ ሲሰጥና መከራን ለማስወገድ ሲችል ነው» የሚል ነበር:: ይሁንና ለተማሪዎቹ አዘውትሮ የሚነግራቸውና የሚያስጠነቅቃቸው ደግሞ «በማንም ላይ መከራ እንዳያመጡና እነሱም ቢሆኑ መከራን እንዳይቀበሉ» ነበር:: አርስቲፐስ መምህሩ እንደነበረው ሶቅራጥስ የሚያስተምረውን ነገር በተግባር መፈተን ይወድ ነበር:- ምንም እንኳን ሰው የሕይወቱ ግብ ደስታን ማግኘት ሊሆን እንደሚገባ ቢያምንም ደስታው ግን በስግብግብነትና የህሊና ማመዛዘን በማጣት ሊሆን እንደማይገባ አዘውትሮ ያስተምር ነበር::

ሄዶኒስቶች ስለደስታ የተለያየ እሳቤ በመፍጠር ለማቅረብ ይሞክሩ እንጂ ዞሮ ዞሮ መግቢያ ማረፊያቸው ደስታ መሆኑ አልቀረም:: ለምሳሌ "Psychological Hedonism" የሚነግረን «ሰው በምድር ላይ የሚፈልገው አንድ ነገር ደስታ ብቻ ነው» የሚል ሲሆን በአንፃሩ በሌላ ወገን የሚገኘው "Ethical Hedonism" ደግሞ «የሰው ልጅ መሠረታዊ የሞራል ግዴታ ደስታና ፍሥሐን አጥብቆ መሻትና መከታተል ነው» የሚል ይሆናል::

በተለይም የሁለተኛው ጐራ "Ethical Hedonism" ሲነሳ ስሙ አብሮ የሚጠቀሰው የግሪኩ ፈላስፋ ኤፒኩረስ ነው:: በኤፒኩረስ ትምህርት መሠረት «የሕይወታችን ግብ ሊሆን የሚገባው ደስታን መጨመርና መከራን መቀነስ ነው:- እንዲያውም ሕይወታችን በዚህ ዓላማ ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል» በማለት የሰው ልጅ ከደስታ ጋር ያለውን ቁርኝት በአጭር አገላለፅ እንዲህ ይነግረናል:- «ደስታ ከሕይወታችን ጋር አብሮ የተፈጠረ የመጀመሪያው ነገር ነው፤ ከዚያ ደስታ በመነሳት ለሕይወታችን የምንመርጠውን ስንመርጥ የምናስወግደውን ደግሞ እናስወግዳለን፤ በመጨረሻም ወደ ደስታ እንመለሳለን (ምክንያቱም ጥንትም አብሮን የነበረ ነውና):: ስለዚህም የነገሮች መልካምነትም በ



Scanned by CamScanner

ክፉነት የሚመዘኑት በእኛ የደስታ ሚዛን ይሆናል» ይለናል:: ክፉም ነገር ቢሆን ደስታን ካተረፈልህ መልካም ነው እንደማለት ይሆናል::

ይኸንን በቀላል አገላለፅ ለማስቀመጥ:- «ለምሳሌ አንድ ሰው አንዲትን ሴት ቢያፈቅር የፍቅሩ መሠረት ወይም መነሻ የልጅቷ ውበት፣ ወይም ማንነቷ ሳይሆን በአፍቃሪው ውስጥ የሚገኘውና አብሮትም የተፈጠረው ደስታን የማግኘት ፍላጐት ነው:: ስለዚህም ወንዱ በፍቅር ወድቋል ስንል በሌላ አገላለፅ በራሱ ደስታ ሥር ወድቋል» እያልን ነው::

እንደኤፒከረስ አስተሳሰብ:- «ደስታህን ፈልገህ ማግኘት ቢያቅትህ እንኳን ስቃይህን ቀንስ» ይለናል:: ስቃይ ሲቀነስ ደስታ መጨመሩ አይቀሬ ነውና:: ይኸ አስተሳሰብ በመካከለኛው ዘመን ውስጥ በነበሩ የክርስትና እምነትና ፍልስፍና አራማጆች ዘንድ ከፍተኛ ውግዘትን ያስከተለ ነበር:: በተለይም «ኃጢአትን ማራቅ፣ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ መፈፀም፣ የክርስትናን መልካምና በጐ ነገር ማከናወን የደስታ ምንጮች ናቸው» በሚሉት ወገኖች ዙሪያ እንደእንግሊዛዊው ታላቅ ፈላስፋ ቶማስ ሙር ዓይነቶቹ ተሰልፈው ነበር:: ሙር በሄዶኒስቶች ላይ በሰነዘረው አስተያየት:- «ችግሩ ያለው የአእምሮ ደስታን ከሥጋዊ ደስታ ለይቶ ለማወቅ አለመቻላቸው ላይ ነው» ይላል:: «ሰው ሥጋዊ ደስታውን ትቶ አእምሮአዊ ደስታውን መከታተል ቢችል በምድራዊ፣ ሰው ሰራሽና ብሎም ጊዜያዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ጊዜውን አያጠፋም ነበር» በማለት ቀላል ምሳሌ ይሰነዝርልናል:-

«አንድ ሰው በማታ ሻምፓኝ ቢጠጣና ቢሰክር ደስታን ያተርፋል፣ በነጋታው ከመኝታው ሲነሳ ደግሞ በራስ ምታት ይሰቃያል:: ስለዚህም ስቃዩ የደስታው ውጤት ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም... እንዲህ ዓይነቱን ደስታ መፈለግ ደግሞ የሰው ልጅ በራሱ ያለውን ዋጋ ዝቅ የሚያደርገው ይሆናል» ብሏል::

በሥልጣኔ ዘመን የሚገኙ ፈላስፎች የጥንቱን የሄዶኒዝም ፍልስፍና «በራሱ ብዙም የተጋነነ ችግር የለውም» ይላሉ:: ምክንያቱም ሄዶኒዝም



Scanned by CamScanner

ከአርስቲፐስ ዕድሜም በላይና እንዲያውም የሰው ዘር በምድር ሲፈጠር አብሮ የተፈጠረ ነው በማለት የአዳምና ሔዋን የስህተት መሠረት ይኸው ሄዶኒዝም እንደነበር ይነግሩናል፡፡

*«ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች» (ዘፍጥ. 3:6)*

በዚህ አካሄድ ከአርስቲፐስ በፊት አዳምና ሔዋን ሄዶኒስት እንደነበሩ እንረዳለን፡፡ ስለአርስቲፐስ ፍልስፍና ብዙም እውቀቱ የሌላቸው ደግሞ በደቀመዝሙሩ በኤፒኩረስ በኩል ሄዶኒዝምን ተዋውቀውታል፡፡ በተለይም በዘመኑም ሆነ ከዚያ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስ የተማሩና የሕጉን መንገድ የተከተሉ ከኤፒኩረስ ተማሪዎች እንዲጠነቀቁ ተከታዮቻቸውን ይመክሩ ነበር፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ 17 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ በአቴና ከተማ የጣዖት አምልኮ መሙላቱን አስመልክቶ በብስጭት መንፈሱ ይታወካል፡፡ በዚህም ምክንያት በየቀኑ በገበያ ከሚያገኛ ቸው ሰዎች ጋር ይነጋገር ነበር፡፡

*«<u>ከኤፊቆሮስ</u> ወገንና ኢስጢኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር ተገናኙ...» (የሐዋ.ሥ. 17:18)*

መጽሐፍ ቅዱስ ኤፊቆሮስ የሚላቸው እንግዲህ የኤፒኩረስን ተከታዮች ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ከእነዚህ ሄዶኒስቶች ጋር ባደረገው ክርክር ሐሣቡ እምብዛም ተቀባይነትን አላገኘም ነበር፡፡ በወቅቱ የአቴና ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ከተማዋን የረገጠ እንግዳም አዲስ ነገር ከመናገርና ከመስማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውልም ነበር፡፡ ይኸ አዲስ ነገር ደግሞ በዋነኛነት የሄዶኒስቶች ፍልስፍና ነው፡፡

የሚያሳዝነው ግን በኋለኛው ዘመን የነበሩት የኤፒኩረስ ተማሪዎች ከአሪስቲፐስና ኤፒኩረስ የሰሙትን የሄዶኒዝም ፍልስፍና ወደተራ ደስታ አውርደውት በሥጋዊ ፍላጐት ላይ ብቻ የተመሠረተ ፍልስፍና አድርገውት እንደነበር እንረዳለን፡፡ ይኸም ቆይቶ ለሄዶኒዝም መውደቅና በተራ ቢስ እሳቤነት እንዲታይ ከፍተኛውን ሚና መጫወቱን የዘመናችን



Scanned by CamScanner

በክርስትና እምነት አራማጆች አስተሳሰብ ቁሳዊ ፍላጎት በራሱ ኃጢአት አለመሆኑን ይስማሙና ነገር ግን ይኽ ፍላጎት ኃጢአት የሚሆነው «ብቸኛው የደስታ ምንጭ ተደርጎ ሲወሰድ ነው» ይላሉ:: የሄዶኒስቶችም ሆነ የክርስትና እምነት አራማጆች ሃሣብ የሚያጠነጥነው በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ እሱም በደስታ ላይ ሆኖ ሳለ ከዚያ የመድረሻው መንገድ ላይ ግን ልዩነት አላቸው:: በቀጣዩ ታሪክ ልሰናበት:-

አንድ ቀን አንድ ሰው ወደኢየሱስ መጣና «መምህር ሆይ የዘላለም ሕይወት እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ» አለው:: ኢየሱስም «ሕግን ታውቃለህ?» በማለት ጠየቀው:: ሰውዬው በሚገባ እንደሚያውቅ ሲመልስለት ኢየሱስ «እንግዲያውስ ሕግን ፈፅም» አለው:: «ከልጅነቴ ፈፅሜያለሁ.. የጣስኩትም ሕግ የለኝ» በማለት ሰውዬው በድጋሚ መለሰ:: «በል ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥና ተከተለኝ» አለው:: ሰውዬው እዚህ ላይ እያቅማማ «ምድራዊ ደስታዬን ከማጣት መንግሥተ ሰማያት መግባት ይቅርብኝ» አለ::

ኢየሱስም «እውነት እላችኋለሁ ሄዶኒስት መንግሥተ ሰማይ ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይሻላል» አለ:: እነሆ እስከዛሬ ድረስ የሄዶኒስቶች ፍፃሜም ገሃነም ሆኗል::

# «የሚሰማህ ለመኖሩ እርግጠኛ ሳትሆን አትፀልይ»

ሳን ፍራንሲስኮ ከተማ በሚገኝ አንድ የሕክምና ማዕከል ውስጥ ለዓመታት በአንድ ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ምርምር ያደረገ ሰው ይገኛል። ይኸ ግለሰብ ራንዶልፍ ቢርድ ይባላል። ምናልባት አሜሪካ በ20ኛው ክ.ዘ. ካፈራቻቸው ታላላቅ ሳይንቲስቶች ውስጥ አንዱ ለመሆን ያበቃውን ጥናት እንዳቀረበም ብዙዎች ይስማማሉ። የቢርድ የምርምር ጥናት በቀጥታ ከሕክምና ሳይንስ ጋር የተገናኘ አልነበረም።

በኦገስት 1982 እ.ኤ.አ. ቢርድ በእሱ ሥር ከሚታከሙና እጅግ ቁጥራቸው ከበዛ ሕሙማን ውስጥ 393 ሕሙማንን በመውሰድ አንድ የምርምር ሥራ ሊያደርግ ወሰነ። በዚህም መሠረት እነዚህን ሕሙማን በመጀመሪያ በሁለት ክፍል ለያቸው። በመጀመሪያው ክፍል 201 ሕሙማን ሲገኙ በሌላው ደግሞ 192 አደረገ።

የምርምሩ ዋነኛ ዓላማ «ፀሎት የሰውን ሕመም መፈወስ ይችላል?» በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የሚያጠነጥን ነበር። በዚህ መንገድ ለ192 ሕሙማኑ እንዲፀለይ ሲያደርግ ለቀሩት ደግሞ ፀሎት ሳይደረግላቸው ጥቂት ቀናት ተቆጠረ። «ከዚያ በኋላ በሕሙማኑ ላይ የታየው አስገራሚ ለውጥ ቢኖር» ይላል ቢርድ «የተፀለየላቸው ሕሙማን የልብ ቧንቧ በተገቢው መንገድ ሲሰራ ያልተፀለየላቸው ደግሞ የልብ ቧንቧቸው የመስፋት

ችግር ታይቶበታል:: ስለዚህም ፀሎት ሕመምን ባይፈ.ወስ እንኳን ቢ.ያንስ 
ጭንቀትን ለመቀነስ የሚያስችል መፍትሔ አለው» ወደሚል ድምዳሜ ደርሷል::

በዚህ ጉዳይ ላይ ተንተርሰው አስተያየት የሚሰጡ ምሁራን «መጀመሪያ ለማን እንደምንፀልይ እንወቅ፣ ፀሎታችንን የሚሰማና የሚመልስ «ነገር» ለመኖሩ እርግጠኞች እንሁን፣ የምንፀልይለት ሰውም ቢሆን ወደማን እንደሚፀለይለት አውቆ ማመኑን እንረዳ... ወዘተ» ይላሉ::

ታዋቂው አሜሪካዊ የአክራሪ ክርስትና እምነት ተከታይና የሥነ መለኮት ምሁር ቻርለስ ሆጅ:- «ተዓምር በእግዚአብሔር ጥበብ ከውጭው ዓለም ወደዚህ ምድር የሚላክልን ክስተት ነው፤ ይህ ክስተት ደግሞ ያለፀሎት አይመጣም» ይለናል::

«ጥያቄው ግን» ይላሉ በተለይ ወደ ፍልስፍናው ዓለም ያዘነበሉት ምሁራን ደግሞ «ተዓምር በራሱ ምን ዓይነት ሳይንሳዊ ማረጋገጫ ሊቀርብለት ይችላል? ተዓምር የምንለውስ ነገር እግዚአብሔር ለፀሎት የሚመልሰው መልስ ነው ካልን የክርስትያኑ፣ የእስላሙ፣ የአይሁዱ፣ የቡድሃው... ወይስ የማን እግዚአብሔር ነው መልስ የሰጠው?» የሚል ጥያቄ ያነሳሉ::

በአሜሪካ ሀርቫርድ ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ምሁር ሄክቶር ሃቫሎስ ፀሎትን አስመልክቶ በቅርቡ ባወጣው የምርምር ሥራ ላይ የሚነግረን አለ:-

«ለምሳሌ የክርስትያኑን እግዚአብሔር ብንመለከት በሁሉም ቦታና በአንድ ጊዜ የሚገኝ (Omnipresence) ነው ይባላል:: ከዚያም አልፎ ዘላለማዊ፣ ሁሉን ቻይና ሁሉን አዋቂ (eternal, all-powerful, all-knowing) ነው:: የሰው ልጅ ደግሞ በጊዜና በቦታ ውስጉ ነው:: ታዲያ የእሱን በሁሉም ቦታና በአንድ ጊዜ መገኘት እኛ በሁሉም ቦታና በአንድ ጊዜ መገኘት የማንችለው የሰው ልጆች እንዴት አወቅን? የእሱን ዘላለማዊነትስ እኛ ዘላለማዊ ሳንሆን እንዴት ማወቅ እንችላለን?» በማለት ጠይቋል::



Scanned by CamScanner

የነበረ

«ሰዎችን በዚህ ዓለም ላይ የሚያሠቃያቸው ክስተት (ተግዳሮት) በእንድ ላይ የሁሉም ኃያል እየተናገረ ነው ብለን ለማመን በመጀመሪያ ያ ኃያል መኖሩን ማረጋገጥ አለብን። አለበለዚያ ከስሜቱ ምላሽ አግኝተናል፤ ምላሽ የሰጠንን ነገር (አምላክ) ለመኖሩ ግን እርግጠኛ አይደለሁም ማለት ማስከበ የስሜቶቻችንን እንደ መግለጥ ይሆናል» ብሏል።

እንደሂዩኖር ከሆነ- «ሁሉን አዋቂ፣ መልካም፣ ሁሉን ቻይ አምላክ ካለ ፀሎት በራሱ አላስፈላጊ ነው» ይላል። ለምሳሌ «በቤትህ ተቀምጠህ ወግ የደባትህሁት ጓደኛህ በዓለም ዙሪያ ከታወቁት ድንቅ ሐኪሞች አንዱ ነው እንበል። ይኸ ሐኪም ደግሞ ሲይዙ የደረሰባቸውን በሽታዎች ሁሉ የማዳንም ግነቡ አለው። በዚያን ወቅት ታዲያ የስድስት ወር ልጅህ በቤትህ ትጫወታለች ብለን እንገምት።

«ታዲያ በድንገት በዚያ ታላቅ ሐኪም ፊት ልጅህ ትታመምና ትወድቃለች። ለምሳሌ ልጅህ ጉሮሮዋን ምራቅ አንቋት ታፍና ብታጣጥር የሕፃኗን ችግር ይፈታልኛል ብለህ መጀመሪያ የምትመለከተው ወደማን ነው? ቢያንስ ሐኪሙ ጓደኛህ የእሱን ፍቃደኝነት ማግኘት ሳያስፈልግህ እንኳን ከመቀመጫው ተነስቶ የልጅህን ሕይወት ለማዳን እንደሚጥር ይገባሃል። በእሱ ላይ ያለህን እምነት እንድታሳየው እሱም አይጠብቅም። ልጅህ በምታጣጥርበት ወቅት ከዚያ ታዋቂና ወዳጅህ ከሆነ ዶክተር የምትጠብቀው ተነስቶ ልጅህን ማዳን ብቻ ነው።

«እንበል ይኸው ሐኪም ሕፃናትን ከሞት የሚታደግና የካንሰር በሽታን የሚፈውስ መድሃኒት አለው በማለት እንገምት። እንግዲህ ይኸ ሐኪም መድሃኒቱ አለው ብለን ካመንን ደግሞ እንደሚጠቀምበት ጥርጥር አይኖረንም። እሱ «መልካም» ሐኪም ነው ብለን እናምናለንና፡- ስለዚህም ይኸ ሐኪም የዓለም ሕፃናት ሲሰቃዩ እየተመለከተ ካልተጠየትሁ አልሰጥም ብሎ መድሃኒቱን አይነፍግም። ምክንያቱም «መልካም» ሐኪም ነውና።

«በተመሳሳዩ መልካም አምላክ ማንም ሰው ሲሰቃይ እየተመለከተ



Scanned by CamScanner

ዝም አይልም፤ ሁሉን የሚያውቅ አምላክም ማን ሊሰቃይ እንደሚችል ቀድሞ የማወቅ ብቃት አለው፤ ሁሉን ቻይ አምላክ ደግሞ መከራን ማስወገድ ይችላል። ስለዚህም...» ይላል ሄክቶር «ሁሉን ቻይና፣ ሁሉን አዋቂ እንዲሁም መልካም አምላክ ቢኖር ኖሮ አስቀድሞም ለእሱ መፀለይ አስፈላጊ አይሆንም ነበር» ብሏል።

እንደሄክቶር ገለፃ ለምሳሌ አንድ ሰው ለክርስትያን አምላኩ ተፀልዮለት ተፈወሰ ሲባል የክርስትያኑ እግዚአብሔር እንደፈወሰው ይታመናል። ነገር ግን ሁሉም ሃይማኖቶች ደግሞ የራሳቸው እግዚአብሔር ፀሎታቸውን እንደሚመልስላቸው ያምናሉ። ለምሳሌ በሂንዱዝም የቅድስና መጽሐፍ በሆነው በሕጋቫድ - ጊታ መሠረት ማንኛውም ሰው የትኛ ውንም አምላክ ቢያመልክ ፀሎትን የሚመልሰው ግን ክሪሽና ብቻ ነው ይላል። ስለዚህም «ፀሎት የቱንም ያህል ምላሽ ይገኝበታል ተብሎ ቢታመን እንኳን የየትኛው ሃይማኖት አምላክ እንደሚመልስ ስለማይታወቅ አለመፀለይ ይሻላል» በማለት ሄክቶር ሐሣቡን ይሰነዝራል።

«እንደቢርድና ደሲ ዓይነቶቹ ሳይንቲስቶች በፀሎት የሚገኝ ፈውስ ለመኖሩ መምከራቸው በራሱ የሚያሳየው ቢያንስ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፎ የምናገኘውንና እግዚአብሔር ለፀሎት ምላሽ ለመስጠት ቅድመ ሁኔታን እንዳስቀመጠ የአለማወቃቸው ውጤት ነው» የሚሉ የፍልስፍናው ጉራ ምሁራን አሉ። (በነገራችን ላይ ላሪ ደሲ እንደ "Prayer is Good Medicine" እንዲሁም "Healing words..." ዓይነቶቹን የፀሎትን የመፈወስ ኃይል ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ለማሳየት የተፃፉ መጻሕፍት ደራሲ ነው።)

እንደፍልስፍናው ጉራ ምሁራን አስተያየት «እግዚአብሔር ራሱ የተናገረውን ማሳየቱ ደግሞ ፀሎት በራሱ ፋይዳ እንደሌለው በቀላሉ እንድንረዳ ያደርገናል» ይላሉ:-

*«እጃችሁን ወደእኔ ብትዘረጉ ዓይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ፤ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም፤...» (ኢሳ. 1:15)*



Scanned by CamScanner

እንዲያውም የአይሁድ እግዚአብሔር አንዳንዶቹን ነቢያት ለሕዝባቸው እንኳን እንዳይፀልዩ ሲመክራቸው ይስተዋላል፡-

*«አንተም ስለዚህ ሕዝብ አትፀልይ፤ ከመከራቸው የተነሣ ወደእኔ በጮኹ ጊዜ አልሰማቸውምና፤ ስለእነርሱም ጩኸትና ልመና አታድርግ::» (ኤር. 11:14)*

ወደ ሄክቶር የጥናት ጽሑፍ ተመልሰን ስንመለከት ብዙዎች ከተፀለየላቸው በኋላ «አልተፈወስንም» አይሉም:: ለዚህም ዋነኛው ምክንያት «አልተፈወስንም» ማለት «የተፀለየለትን አምላክ እንደ መሳደብ ስለሚቆጠር ነው» ይላል:: አንዳንዶች በድፍረት አልተፈወስንም ቢሉ እንኳን ችግሩ ከአምላካቸው ሳይሆን ከእምነታቸው ማነስ ተደርጐ ይወሰድባቸዋል::

ስለፀሎት ሲነሳ አንድ የምንጠቅሰው ጉዳይ ቢኖር ፀሎት እንዲደረግላቸው የሚፈልጉ ሰዎች በአብዛኛው ከተፀለየላቸው በኋላ መፍትሔ የሚፈልጉት ግን ከሰው የመሆኑ ጉዳይ ነው:: ይኸ ደግሞ አስቀድሞም ለተፀለየላቸው አምላክ ጥርጣሬ እንደ ነበራቸው የሚያሳይ ነው:: ለዚህ ነው ሕሙማን ከተፀለየላቸው በኋላም እንኳን ወደ ሆስፒታል ከመሄድ የማያቋርጡት:: «ይኸ ደግሞ ችግርን መፀለዩ ብቻ ሳይሆን የተፀለየውን ችግር በራሱ «የሚሰማ» ለመኖሩ ጥርጣሬ ውስጥ የሚጥል ነው» ይላሉ ፈላስፎቹ::

ሄክቶር በጥናቱ እንደሚናገረው «ፀሎትህን የሚሰማ ለመኖሩ እርግጠኛ እስክትሆን ድረስ ባትፀልይ ይሻላል» ይላል:: እኔ ደግሞ እንደዳዊት «ፀሎቱ የተሰማለት ሰው እሱ ምስጉን ነው» እላለሁ:: የሁለቱ ልዩነት ግን እምብዛም አይታየኝ::



Scanned by CamScanner

# «ታላቅ የሚባል መንገድ የለም፤ ነገር ግን ሰው መንገዱን ታላቅ ያደርጋል»

ለዛሬ ወደጥንታዊቷ ቻይና ዘልቀን የፍልስፍናው ፈጣሪና አባት ተደርጐ የሚታመንለትን ኮንፊሺየስን እንመለከታለን፡፡ ይኸ ሰው ኢየሱስ ወደምድር ከመጣ በኋላ ለተናገራቸው ወርቃማ መመሪያዎች ወይም ድንቅ አባባሎች መሠረትን የጣለ ነው የሚሉ የፍልስፍናው ዓለም ሰዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ኮንፊሺየስ:- «ሌሎች በአንተ ላይ ሲያደርጉ የማትወደውን አንተ ለሌላው አትመኝ» ብሏል፡፡ ኢየሱስ መጣና ኮንፊሺየስን አረመው:- «ሌሎች በአንተ ላይ ሲያደርጉ የማትወደውን አንተ በሌላው ላይ አታድርግ» አለ፡፡

የኮንፊሺየስ ፍልስፍና አቅራቦት ለሶቅራጥስ፣ ለአሪስቶትልና ለጐቴ ነው፡፡ ታላቅ ሰው ማነው? ቢሉት «ታላቅን ነገር የሚያስብ...» የሚለው ኮንፊሺየስ ከክርስቶስ ልደት በፊት በ551 ሉ በተባለች የቻይና ግዛት ውስጥ እንደተወለደ ይነገራል፡፡ እሱ በተወለደበት ወቅት ደሀ ከነበረውና ነገር ግን የነገሥታት ቤተሰብ የቅርብ ዘመድ የሆነው አባቱ ገና የ3 ዓመት ልጅ ሆኖ ነበር የሞተው፡፡ ኮንፊሺየስ ደሀ ሆኖ ቢወለድም በድህነት አልሞተም፡፡ ከታናሽ ሥራ ጀምሮ ሚኒስትር ለመሆን እንደበቃ



Scanned by CamScanner

በታሪኩ ሰፍሮ እናገኛለን። ነገር ግን ሥራው ከዕውቀቱ ጋር «ባለመመጣጠኑ» ለሌሎች ዕውቀቱን ማካፈል ሥራ ላይ ተጠመደ። ለእሱ በሥልጣኑ ቦታ ከሚያበረክተው ይልቅ አስተማሪ ቢሆን ትውልዱን ይበልጥ እንደሚጠቅም እምነቱ ሆነ። ሦስት ሺ ተማሪዎችን አስከትሎም ወደፍልስፍናው ጐራ ተጓዘ። በሥልጣን ዘመኑ በዙሪያው የነበሩ ጠላቶቹም እረፍት አገኘን በማለት ተነፈሱ።

ለዛሬ ኮንፊሺየስ ከተማሪዎች ጋር ያሳለፈውን የዕውቀት ገበታ በመጠኑ እንመለከታለን።

አንድ ወቅት ተማሪው ይኸን ጠየቀው፦ «ደሀ ሆኖ ስለማይሰርቅ ሀብታም ሆኖ ደግሞ ስለማይሰራ ሰው ምን ታስባለህ?»

ኮንፊሺየስ እንዲህ አለ፦ «ሁለቱም መልካም ናቸው። ነገር ግን ከሁለቱም ደግሞ ደሀ ሆኖ ደስተኛ ይበልጣል።»

ኮንፊሺየስ ተማሪዎቹን ሲመክር «ለማንም ቢሆን መታዘዝን እወቁ» አላቸው። አንድ ተማሪ ምክሩ አልገባውም። «ምን ማለትህ ነው?» በማለት ጠየቀ። ኮንፊሺየስም፦ «አባትህ በሕይወት ሳለ ታዘዘው፤ ሲሞትም ታዘዘው፤ ከዚያም በኋላ በየዓመቱ መታሰቢያውን አድርግ» አለው። «ለአባቴና ለእናቴ የማደርገውን ለሚያገለግሉኝ ለፈረሴና ለውሻዬ ካላደረግኩ ያስተማርከኝ ርኅሩኅነት የተሟላ አያደርገውም» አለው። «አዲሱን ዕውቀት ታገኝ ዘንድ የድሮውን መርምር» አለው። ከዚያን ቀን ጀምሮ ያ ተማሪ ከኮንፊሺየስ ተለየ።

ኮንፊሺየስም፦ «በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ሰብዓዊነትን ፈፅሞ የወደደ፤ ኢ ሰብዓዊነትንም የጠላ አንድም ሰው አላየሁም። ሰብዓዊነትን የወደደ ሰው ቢኖር ከዚያ በላይ ለሕይወቱ ዋጋ የሚሰጠው ነገር አይኖርም ነበር። ኢ ሰብዓዊነትንም የጠላ ቢኖር ክፋት አጠገቡ ሲደርስ ባልታገሰ ነበር። ቢያንስ ለአንድ ቀን ራሱን ለዚህ አሳልፎ የሰጠ ሰው ይገኝ ይሆን?» በማለት ጠይቋል።

«ሰው የሚሰራው ለራሱ ጥቅምና ትርፍ ብቻ ከሆነ ያ ሰው ብዙ



Scanned by CamScanner

ጠላቶች ያተርፋል» በማለት ኮንፊሺየስ ለተማሪዎቹ ተናገረና ይኸን ጥያቄ ሰነዘረላቸው:- «ከእናንተ በሕይወቱ ታላቅ ምኞት ያለው ዛሬ ምኞቱን ይንገረኝ::»

የመጀመሪያው ተማሪ:- «እኔ ፈረስና ሰረገላ እንዲሁም ባለሐር ከፖርት እመኛለሁ...» አለ:: ሌላው ተማሪው ደግሞ ቀጠለ:- «ለተቸገረ ሰው መርዳትና ስለዚያም ድርጊቴ ፈፅሞ አለማውራት ምኞቴ ነው» አለ:: ሦስተኛው ተማሪ ተነሳ:- «መምህር ሆይ የእኔ ታላቅ ምኞት የአንተን ምኞት ማወቅ ነው» አለው:: ኮንፊሺየስም አለ:- «የጥንቱን የሚቀበል ሰው አዲሱን በሚገባ ያውቃል:: የእኔን ምኞት ስማ:: ያረጁትን መደገፍ፣ ለጓደኛ ታማኝ መሆን እንዲሁም ወጣቶችን ማድነቅና መውደድ ነው» አለ:: ይኸን ጊዜ አንዱ ተማሪው ተነሣና «እኔ ግን ጓደኛዬን አሳዝኛለሁ» አለው:: ኮንፊሺየስ በተማሪው አስተያየት ተደነቀና እንዲህ አለ:- «ሰው ሲወለድ ከጽድቅ ጋር ነው:: ይኸን ጽድቅ ጥሎ ግን በሕይወት መኖር የቻለ እሱ ዕድለኛ ነው::»

ተማሪው መልሶ ጠየቀው:- «የምትነግረኝ ጥበብ ነውን?» ኮንፊሺየስም:- «ስለጥበብ ማወቅ ትወዳለህ? ለሰው የሚጠቅም ተግባር ላይ ራስህን አበርታ፤ እንዲሁም መንፈሳዊ ሥልጣናትን አክብር፤ ነገር ግን በሩቁ ያዛቸው:: ያን ጊዜ ጠቢብ ትባላለህ» አለ::

ኮንፊሺየስ አንድ ቀን ያልተማሩና አረመኔዎች ወደሚባሉት ከምሥራቁ ክፍል ከሚገኙ ዘጠኝ ጉሣዎች ጋር ሄዶ ለመኖር መወሰኑን ለተማሪዎቹ ነገራቸው:: በዚህ ጊዜ አንዱ ተማሪ:- «እንደአንተ ዓይነት ታላቅ ሰው እንዴት አረመኔ መካከል ይኖራል?» በማለት ጠየቀው:: ኮንፊሺየስም:- «በአረመኔ መካከል ታላቅ ሰው መኖር ከቻለ እነሱስ እንዴት አረመኔ ይባላሉ?» በማለት መለሰለት::

ሌላው ተማሪ ደግሞ ስለመንፈሣዊ አገልግሎት ጠየቀው:: ኮንፊሺየስም:- «የሰውን ልጅ ማገልገል ስትችል እንዴት መንፈሣዊውን ዓለም ማገልገል ትችላለህ? አሁን ስላለህ ሕይወት ጠንቅቀህ ሳታውቅ



Scanned by CamScanner

ግዛዊ

ስለሞት ለማወቅ አትቸኩል» አለው።

አንድ ቀን ታላቅ ስለመሆን ለተማሪዎች ምክር በመስጠት ላይ ሳለ አንዱ ተማሪ አቋረጠውና፡- «ታላቅ ለመሆን እፈልጋለሁና መንገዱን አሳየኝ» አለው። ኮንፊሺየስ ሲመልስ፡- «ታላቅ የሚባል መንገድ የለም ነገር ግን ሰው መንገዱን ታላቅ ያደርጋል» አለ።

እንዲሁ በሌላ ቀን ተማሪው፡- «ሰይጣን በጣም እየፈተነኝ ነው» አለው። ኮንፊሺየስም፡- «ሰይጣን አንተን ከሚፈትነው በላይ ግን አንተ ሰይጣንን ስትፈትነው ይታየኛል...» አለው። «እንደሚገባኝ ሰይጣን ከእኔ በጣም የራቀ ነው... ምክንያቱም ስለእሱ የማስብበት ጊዜ የለኝም። አንተ ደግሞ ጊዜህን ስለእሱ በማሰብ ታሳልፋለህ... ስለዚህም ሰይጣን ባይኖር እንኳን ሃሣብህ ሰይጣን ሆኖ ይፈትንሃል» አለው። ለተማሪዎቹም እንዲህ አለ፡- «መልካሙን መንገድ ማወቅ አንድ ነገር ነው፤ በዚያ ላይ ደግሞ ለመሄድ መቻል ሌላ ነው።»

ሌላው ተማሪው ተነሣና ስለሰብዓዊነት ንገረኝ አለው። «ሰውን ማፍቀር ነው» ሲል መለሰለት። «ስለዕውቀት ደግሞ ንገረኝ» አለው። «ዕውቀት ማለት ሰውን ማወቅ ነው» አለው።

ኮንፊሺየስ ለተማሪዎቹ ስለሃገር ገገርዎች በነገራቸው ውስጥ እንዲህ የሚል አገኝሁበት፡- «የሃገር ገገር ራሱን ማነፃ ካልቻለ ቢናገርም አይሰማም፤ ነገር ግን ራሱን ማነፅ የቻለ ገገር ሳይናገር ይሰማል። የአንድ መንግሥት መልካምነቱ የሚታወቀው አጠገቡ የሚገኘው ሕዝቡ ሲወደውና፤ በሩቅ ሃገር ያሉት ደግሞ ወደሃገራቸው ለመምጣት ሲናፍቁ ነው።»

ኮንፊሺየስ ታሞ አልጋው ላይ በተኛበት አንድ ቀን ሁለት ተማሪዎቹ መጥተው ሊፀልዩለት እንደተዘጋጁ ነገሩት። ኮንፊሺየስም «ፀሎት ምንድነው?» በማለት ጠየቃቸው። «ከመንፈሣዊ ኃይላት ጋር በፀሎታችን እናገናኝህና ትፈወሣለህ» አሉት። እሱም በመገረም እየተመለከተ፡- «እኔስ እስከዛሬ ያስተማርኳችሁ ከዚህ በምን ይለያል?» በማለት መለሰላቸው።

ኮንፊሺየስ በ73 ዓመቱ በዚያው አልጋ ላይ ሞተ።



Scanned by CamScanner

# «የትምህርት መጨረሻው የጠፋብህን አእምሮ ማስመለስ ነው»

ዛሬም ከቻይና ምድር ሳንወጣ ከኮንፊሺየስ ቀጥሎ ቻይና የምትኮራበትን ታላቁን ፈላስፋዋን ሜንሲየስን እንመልከት:: ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ371-289 የኖረው ሜንሲየስ ሻንቱንግ በምትባለውና በስፋቷ በምትታወቀው የቻይና ግዛት ተወለደ:: ኮንፊሺየስም በዚህችው ግዛት ነበር የተወለደው:: የኮንፊሺየስ የልጅ ልጅ በነበረው ዙ-ሱ አስተማሪነት ያደገው ሜንሲየስ የፖለቲካ ቅራኔ፣ የሞራል ውድቀትና ምሁራዊ ግጭት በሰፈነባት ምድር ውስጥ በማደጉ ከልጅነቱ በበጎና ክፉ ዕውቀት መካከል ያለውን ልዩነት በሚገባ ለማወቅ አልተቸገረም:: በተለይም በዕውቀት ግስጋሴው ወቅት በእጅጉ የእሱን አካሄድና እምነት ይቃወሙት ከነበሩት እንደ ሞ.ዙ እና ያንግ ቹ ዓይነቶች የቻይና ታላላቅ ፈላስፎች ጋር ሙግት ገጥሞ የሚውልባቸው ቀናት ብዙ ነበሩ::

ሜንሲየስ እንደኮንፊሺየስ ሁሉ የማደጉ ልጅ ሆኖ ነው ያደገው:: እንደኮንፊሺየስ ለደሀ እናቱ ሞት ሦስት ዓመት ሐዘን ተቀምጧል፤ እንደኮንፊሺየስ በመጨረሻም ሥራውን በመተው በቤቱ እስከመቀመጥ ደርሶ ነበር:: ሜንሲየስ በእነ ፕሌቶ ዘመን ይኖር የነበረ ፈላስፋ ነው በማለት የሚናገሩ ምሁራንም አሉ:: ይሁንና ስለእሱም ሆነ ስለቤተሰቡ እምብዛም የሚታወቅ ነገር ባለመኖሩ ታሪኩ ከስሙና ፍልስፍናው ጋር



Scanned by CamScanner

ግዛዘ

«አዎ» አለ ካዎ ዘ::

«እንግዲያውስ የወፍ ላባ ንጣትና የበረዶ ንጣት ወይም [illegible] የበረዶ ንጣትና የነጭ ፈረስ ንጣት ይመሳሰላል?» በማለት ጠየቀው::

«አዎን ይመሳሰላል» አለ ካዎ ዘ::

«የወፍ ተፈጥሮና የበረዶ ተፈጥሮስ ወይም የበረዶ ተፈጥሮና የፈረስ ተፈጥሮስ?» በማለት ዳግመኛ ጥያቄውን ሰነዘረ::

ካዎ ዘ፡ም፡- «በተፈጥሮአችን ምግብና ፍትወተ ሥጋ ያስፈልገናል:: ሰብዓዊነት ውስጣዊ እንጂ ውጫዊ አይደለም፤ መልካምነትና ጽድቅ ግን በተቃራኒው ውጫዊ እንጂ ውስጣዊ አይደሉም::» በማለት ተከራከረ::

«አንድ ነጭ ነገር ተመልክቼ ነጭ ነው እንደምለው ሁሉ አንድ ሽማግሌ ሰውም አይቼ ባከብረው ያ ሽምግልና በእኔ ውስጥ የለም ማለት እንዳልሆነ ልትረዳ ይገባል:: ምክንያቱም ሽማግሌው ሰውዬ እንደእኔው ወጣት ነበርና:: ነገር ግን ያንን ውጫዊና የማየውን ነገር ተመልክቼ ሽማግሌውን እንዳከበርኩት ሁሉ መልካምነትም ሆነ ጽድቅ በዚህ መልኩ ውጫዊ ነው እላለሁ» ሜናሲየስ ይህን ተናግሮ ጥያቄ ወረወረ:-

«ነጭ ፈረስ ተመልክተህም ሆነ ነጭ ሰው ተመልክተህ ሁለቱንም ነጭ ትላለህ:: ነገር ግን ለሽማግሌ (ነጭ) ፈረስና ለሽማግሌ (ነጭ) ሰው የምትሰጠው አክብሮት ተመሳሳይ ነው? ጽድቅ (መልካምነት) የምንለውስ የሚገለጠው ለሽማግሌው ሰውዬ ወይስ ለሽምግልና ዕድሜው ነው?»

ካዎ ዘ ለሜናሲየስ የዘወትር ፈተና ነበር:: ዛሬም በቀላሉ ሊለቀው አልፈለገምና ተናገረ:- «ታናሽ ወንድሜን በጣም እወደዋለሁ:: ነገር ግን የማላውቀውንም ሆነ የማውቀውን ሰው ታናሽ ወንድም እንደዚያ አልወድም:: ምክንያቱም በውስጤ ያለውን የደስታ ስሜት የማዝዝበት እኔ ብቻ ነኝና:: ስለዚህም ሰብዓዊነት ከውስጥ የሚመነጭ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለኝም:: በሌላ በኩል የሃገሬን ሽማግሌም ሆነ የሌላ ሃገር ሽማግሌን እኩል አከብራለሁ:: ማክበሬ ደግሞ የሚመነጨው



Scanned by CamScanner

ውጫዊ በሆነውና የሁለቱም ሃገር ሸማግሌዎች በሚጋሩት የሽምግልና ዕድሜ ምክንያት ነው፡፡ ስለዚህም ጽድቅ ወይም መልካምነት በዚህ ጊዜ ውጫዊ ይሆናል፡፡»

ሜንሲየስም አለ፡- «በሃገርህም ሆነ በሌላ ሃገር የተጠበሰ ሥጋ ሲሰጥህ ትበላለህ፡፡ ምክንያቱም ጥብስ ሥጋ ስለምትወድ ነው፡፡ እና የተጠበሰ ሥጋ መውደዳችንም ውጫዊ ባህርይ ነው ለማለት እንችላለን?»

በዚህ ክርክር ወቅት የነበሩ ሌሎች ፈላስፎች የመናገርና የመጠየቅ ተራ ወሰዱ፡፡ ሜንግ ቼ ዙ ወደ ካዎ ዙ ዞሮ ጠየቀ፡- «ጽድቅ (መልካምነት) ውስጣዊ ነው ስትል ምን ማለትህ ነው?»

ካዎ ዙም፡- «ለምሳሌ ሰዎችን ማፍቀር «እንለማመዳለን» ስለዚህም መልካምነትን ከተለማመድከው ውስጣዊ ነው» በማለት መለሰ፡፡

ሜንግ ቼ ዙ፡- «ምናልባት አንድ የመንደርህ ጉልማሳ ከአንተ ታላቅ ወንድም በአንድ ዓመት ብቻ ይበልጣል ብለን እናስብና ወደቤትህ ሁለቱም ቢመጡ በፍቅር የምታገለግለው ማንን ይሆናል?» በማለት ጠየቀው፡፡

ካዎ ዙም፡- «ታላቅ ወንድሜን በፍቅር አገለግላለሁ» አለ፡፡

«እንግዲያውስ ፍቅርን ለአንዱ፤ ክብርን ደግሞ ለሌላው ሰጠህ ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ተግባርህን የወሰነው በውጭ ያለው እንጂ በወስጥህ ያለው አይደለም ማለት ነው» በማለት ወደ ሜንሲየስ ዞረ፡፡ ሜንሲየስ ሃሳብ እንዲሰነዝር መጠየቁ ገባውና እንዲህ አለ፡- «ካዎ ዙ ታላቅ ወንድሙን በፍቅር እንደሚያገለግል ነግሮናል፡፡ ነገር ግን እሱን ያሳደገው አጎቱ ቢሆንና ከአጎትህና ከታላቅ ወንድምህ በፍቅር ማንን ታገለግላለህ ቢሉት አጎቴን ይላል፡፡ ከመንደሩ ጉልማሳ ይልቅ በፍቅር አገለግለዋለሁ ያለው ወንድሙ እዚህ ላይ የት ሄደ? በአጭሩ የካዎ. ዙ ማፍቀር በቦታና ጊዜ ስለሚወሰን ነው፡፡ ብዙዎች በመልካም ዘመን መልካም ይሆናሉ፡፡ በክፉ ዘመን ደግሞ ራሳቸውን ለክፉ ነገር አሳልፈው ያቀርባሉ፡፡ ይኸ ማለት ውስጣዊው ተፈጥሮአቸው በዚህ መልክ ስለተሰራ



Scanned by CamScanner

ሳይሆን የራሳቸውን አእምሮ ግን ለክፉ ነገር በማቅረባቸው ብቻ ነው
«ለምሳሌ የስንዴን አበቃቀል ተመለከቱ፤ ዘሩን ትዘሩ፣ ...
ታስብሱታላችሁ:: መሬቱም ሆነ የመዝሪያ ወቅቱም አንድ ነው:: በመትከ...
ወቅት ግን እጅግ በዝቶ አዝመራው ይበቅላል:: የማጨጃ ጊዜም ...
ይታጨዳል:: ነገር ግን የአንዱ ዘር ብዙ የሌላው ትንሽ ቢሆን የ...
ለምነት፣ የዝናቡ መጠን ወይም ሌላ ምክንያት ይህን መለያየት ...
እንላለን:: የእኛም ልዩነት ከዚህ ውጭ አይደለም...» አለ ሚንሲየ...

የሚናሲየስ ፍልስፍና ከኮንፊሺየስ ቀጥሎ በምድረ ቻይና ...
ክብርና ተወዳጅነት እስከዛሬ የተቸረው ነው:: «ሰብዓዊነት የሰው አእምሮ
ሲሆን ጽድቅ ደግሞ መንገዱ ነው... ይኸን መንገድ ትቶ በራሱ አእምሮ
የሚጓዝ ካለ ይታዘንለታል:: እንዲሁም ልቡ ጠፍቶበት ፈልጐ ማግኘ...
ያልቻለ አለ:: ሰው ውሻው ቢጠፋበት ሲፈልገው ይሄዳል፤ ነገሮ...
ይዞት ይመለሳል:: ልቡ የጠፋበት ሰው ግን እንደዚያ ፍለጋ አይወጣም::
ዕውቀትን ለመማር የፈለገ እሱ ልቡን ለመፈለግ የወጣ ነው:: በዚ...
መንገድ ብቻ የጠፋው ልብ ይገኛልና...» ይላል:: የዚህን ሰው ...
ፍልስፍና በሚቀጥለው ምዕራፍ እመለስበታለሁ::



Scanned by CamScanner

# «የእውነትን ትርጉም ብታውቅ አትዋሽም ነበር»

ዛሬም በጥንታዊቷ የሥልጣኔና የፍልስፍና ምድር ቻይና እንገኛለን:: ከኮንፊሺየስ በኋላ በምድሪቱ ስሙ የገነነው የሜንሲየስ ፍልስፍናን ደግመን በመቆፈር ከእውነት ውሃ ምንጭ እንቅዳ::

ለሜንሲየስ ትምህርት ማለት የጠፋብህን አእምሮ ማስመለስ ነው:: ያልተማረ ሰው በእሱ ዘንድ ያለው ጥፋት አለመማሩ ሳይሆን «አእምሮው የጠፋ ሰው» መሆኑ ነው:: ይኸንንም ሜንሲየስ ባስቀመጠልን ምሳሌ በመመልከት እንጀምር:- «ለምሳሌ ከአምስት የቀኝ እጁ ጣት ውስጥ አራተኛዋ ሸባ የሆነችና የማትታጠፍና የማትዘረጋ ጣት ያለው አንድ ሰው አለ እንበል:: የዚህ ሰው ሸባ ጣት ሕመም ባይኖራት ሥራውንም ለመሥራት ችግር ባትፈጥርበት ነገር ግን ይኸችን ጣት የመፈወስ ችሎታ ያለው ሰው በሌላ ሃገር እንደሚኖር ቢሰማ ወደዚያ ይሄድ ዘንድ ግድ ይለዋል? ይኸ ሰው እርግጠኛ ነኝ እስከዕለተ ሞቱ ሌሎች ሰዎች ባላቸው እሱ ግን በሌለው ችግር ብዙም አይጨነቅም:: ምክንያቱም አብሮት ለመኖር የለመደው በመሆኑና ሕመሙም ስለማይሰማው ነው... ይኸ እንግዲህ 'የነገሮችን ተነፃፃሪ አስፈላጊነት ያለመረዳት' (Ignorance of the relative importance of things) ይባላል» ይለናል::

«አንድ ሰው አንድ ዛፍ ቢተክል እንዴት እንደሚንከባከባትና

እንደሚጠብቃት ብሎም እንደሚያሳድጋት በሚገባ ያውቃል። ይኸ እውቀቱን ግን ሰውን ወደማሳደግና መንከባከብ ሲመጣ አይጠቀምበትም። ይኸ ማለት እንግዲህ ሰውን ከዛፉ ባነሰ ደረጃ ይወዳል ማለት ነው። የሰው አላዋቂነት ሲገለፅ እንግዲህ እስከዚህ ድረስ ነው» በማለት ሚኒሲየስ ነገሩን ይበልጥ ያብራራልናል።

«አንድ ሰው ከሰውነቱ ክፍል ውስጥ አበላልጦ የሚንከባከበው የለም። ሁሉንም በእኩል ደረጃ ይንከባከባል፤ ይወዳል፤ ይጠብቃል። ከሰውነቴ ቆዳ የማልወዳት ክፍል አለች ብሎ ቆዳውን ቅባት የማይቀባና የማያጥብ የለም። ይኸንን ቢያደርግ የማይወዳት ክፍል ችግር ለሚወደው መትረፉ አይቀርምና...

«እንዲሁ ዛፍ የሚተክል ሰው አስተውሉ። ዛፉ ያፈራውን ፍሬ ስለሚወድ ፍሬዋን ለይቶ ውሃ የሚያጠጣ የለም። ይኸን ቢያደርግ ግን የዘነጋቸው የዛፍ ግንድና ቅርንጫፎች ነገ ፍሬዋን ሲያደርቋት ይመለከታል። ከመብላትና ከመጠጣት ውጭ የማያውቅ ሰውም ከአፋና ሆዱ በቀር የሚሰፉ ነገር የለውም። ከአእምሮው በመለስ የሰውነቱ ቅርፅም ተበላሽቶ ይታያል። በመብላቱና በመጠጣቱም በራሱ ገላ ላይ ትልቁን ስህተት ይፈፅማል...» በማለት ሜንሲያስ አስተማረ።

አጠገቡ የነበረው ኩንግ ቱ ዘ ከተቀመጠበት ተነስቶ ለሜንሲየስ ጥያቄ አቀረበ:- «ሁላችንም የሰው ልጆች ነን። ታዲያ ለምንድነው አንዳንዶች ታላቅ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ ታናናሽ ሆነው የቀሩት?»

ሚንሲየስም:- «አብሮ የተፈጠረላቸውም ታላቅ ባህርይ የተከተሉት እነሱ ታላቅ ሆኑ፤ የቀሩት ደግሞ ታናሾች...» አለው።

ኩንግ-ቱ ዙ አሁንም አልተቀመጠም:- «ነገር ግን ሁላችንም የሰው ልጆች ነን። ለምን አንዳንዶቹ ታላቅ ባህርያቸውን ተከተሉ፤ ሌሎች ደግሞ ደካማ ባህርያቸውን ይዘው ታናሽ ሆኑ?»

ሜንሲየስ መለሰ:- «የማየትና የመስማት ሕዋስህ በቁሳዊ ነገር ተሸፍኖ ከማሰብ ውጭ ሲንቀሳቀስ፤ ሕዋስህ ወደቁሳዊነት ይለወጥና



Scanned by CamScanner

ብትንትንህ ይወጣል። ይኸው ነው። የአእምሮ ሥራ ማሰብ ብቻ ነው። ማሰብ ስትችል የቁሳዊ ነገር ዓላማ ይገባሃል። ካልገባህ ደግሞ አእምሮህም ቆብ ይሆናል። ነገር ግን ስትፈጠር ከሰማይ የተሰጠህ አእምሮ የተለየ ነበር። በመጀመሪያ የተፈጥሮአችንን ክቡር ነገር መገንባት ከቻልን (Build up the nobler part of our nature) ታናናሹ ነገር ሊያሸንፈን አይችልም። ሰውን ታላቅ የሚያደርገውም ይኸው ነው።»

ከ1139-1193 የኖረውና የኒኦ-ኮንፌሺያኒዝም ፍልስፍና መሥራችና መሪ የነበረው ሉ ሲያንግ ሻን የእምነትና የፍልስፍና መርኽ «የተፈጥሮአችንን ክቡር ነገር መገንባት» (Build up the nobler part of our nature) ነበር። የዚህ ታላቅ ፈላስፋ ሥራ በአብዛኛው ከሜንሲየስ እንደተወሰደም ብዙዎች ይስማሙበታል።

ወደሜንሲየስ ፍልስፍና ስንመለስ፡- «የሰማይ (ገነት) ታላቅ ነገርና የሰው ታላቅ ነገር የተለያዩ ናቸው» ይለናል። ይኸንንም በምሳሌው ሲያስረዳን፡- «የሰማይ (ገነት) ታላቅ ነገር የሚባሉት ሰብዓዊነት፣ ፅድቅ፣ አክባሪነት፣ ታማኝነት፣ እንዲሁም መልካምን ነገር ሁሉ መውደድ ሲሆን የሰው ታላቅነት ደግሞ ታላቅ፣ የተከበረና የታወቀ ባለሥልጣን (ገዢ) መሆን ነው። የጥንቱ ሰው የሰማዩን ታላቅ ነገር ሲኮተኩት የምድሩ ታላቅ ነገር በራሱ መንገድ መጣለት። የዛሬው ሰው ደግሞ የሰማዩን ታላቅ ነገር በመኮትኮት የምድሩን ታላቅነት ካገኘ በኋላ የሰማዩን ታላቅ ነገር ይጥለዋል። ለዚህ ነው ብዙ ታላቅ ሰዎችን ዛሬ በምድራችን የማናየው። የሰማዩን ታላቅ ነገር ጥሎ ከምድራዊው ታላቅ ነገር ጋር የሚቆይ እስካሁን አላየሁም...» ይላል።

«የመከበር ፍላጐት የሰው ልጅ የጋራ ሀብቱ ነው» የሚለን ሜንሲየስ፡- «ነገር ግን ሁሉም ሰው በውስጡ የሚከበር ነገር አብሮት እንደተፈጠረ የሚያውቅና የሚያስብ አይመስለኝም»...

«እዚህ ላይ በተፈጥሮህ የተሰጠህ ክብርና በሰው የተሰጠህ ክብር እጅግ የተለያየ ነው። ምክንያቱም ንጉሥ እንኳን ዛሬ ያከበረውን ነገ



Scanned by CamScanner

ሲያዋርደው ይስተዋላል:: የተፈጥሮ ክብርህን ግን ማንም አልሰጠህም፤ እንዲሁም ደግሞ ማንም ነጥቆ ሊያዋርድህ አይችልም:: የራስህ አዋራጅ ራስህ ነህ...» በማለት የተፈጥሮን የተከበረ ነገር እንዲገነዘቡ ተማሪዎቹን መከረ::

«ቀስትህን እስከመጨረሻው ካልሳብከው ዒላማው ውስጥ ሄዶ እስከመጨረሻው አይገባም፤ ዕውቀትን የሚሻም ተማሪ እስከመጨረሻው የሚተጋ ብቻ ነው...» ይላል ሜንሲየስ::

አንድ ቀን ንጉሥ ሱአን ወደ ቤተመንግሥቱ አስጠራውና ጥያቄ አቀረበለት:- «ለሕዝቤ ጠቃሚ የምሆንበትን መንገድ አስተምረኝ...» አለው::

ሜንሲየስም:- «ጠቃሚ ከመሆን በፊት ሰብዓዊነትና ፅድቅን ተማር:: ለሃገርህ የሚጠቅም ነገር ንጉሥ ሆይ እንድነግርህ የምትሻ ከሆነ ይህን ስማ... ታላላቅ ባለሥልጣኖችህ ለቤተሰቦቻቸው የሚጠቅም ነገር ከጠየቁ... ታናናሽ ባለሥልጣኖችና ሕዝብህ ደግሞ ለራሳቸው የሚጠቅም ነገር ከጠየቁ... ያን ጊዜ የሃገርህ መውደቂያዋ እንደተቃረበ ተረዳ...» አለው::

«ስለድክመቴስ ምን ትላለህ? ለንዋይ ያለኝ ፍቅር ከፍተኛ ነው...» አለ ንጉሥ ሱአን::

«አንተ ንዋይን እንደምታፈቅርና የምታፈቅረውንም እንዳገኘህ እንዲሁ ሕዝብ እንዲያገኝ አድርገው...» አለ ሜንሲየስ::

ንጉሡም «ሌላው ድክመቴ ሴት እወዳለሁ.. አመነዝራለሁ...» አለው::

ሜንሲየስም «ሕዝብህም ሴት እንዲወድ አድርገው... አንተ እንደምታመነዝር እሱም እንዲያመነዝር አግዘው...» በማለት ንግግሩን ቀጠለ...« ንጉሥ ሆይ! ሚኒስትሮችህ ስለአንድ ሰው አዋቂነት ምስክርነት ቢሰጡ በቂ አይደለምና አትስማ፤ ታላላቅ የጦር ባለሟሎችህም ስለዚያ ሰው ምስክርነት ቢሰጡ አሁንም በቂ አይደለምና አትስማ... ነገር ግን ሕዝብህ ምስክርነት ቢሰጥ ያን ጊዜ ሰውዬውን ለሥልጣን አብቃው:: እንዲሁ ደግሞ የአንድን ሰው ስንፍና አስመልክቶ ሚኒስትሮችህ



Scanned by CamScanner

ምስክርነት ቢሰጡ አትስማ፤ የጦር ባለሟሎችህም ቢመሰክሩበት በቀ አይደለምና አትስማ፤ ሕዝብ ሲመሰክርበት ከሥልጣኑ ሻረው፡፡ ሚኒስትሮችህ ተሰብስበው ወደአንተ ቢመጡና በአንድ ሰው ላይ ሞት እንድትፈርድበት ቢጠይቁህ አታድርገው፤ የጦር ባለሟሎችህም በሰውዬው ላይ ሞት ፍረድበት ቢሉህ አትግደለው፤ ሕዝብ ግን ወደአንተ መጥቶ እንድትገድለው ቢጠይቅህ ያን ጊዜ ግደል፡፡ ምክንያቱም ሕዝብ ገደለው እንጂ ንጉሡ ገደለው አይባልም፡፡ በዚያ መንገድ ብቻ አንተም ለሕዝቡ እንደአባት ትሆናለህ...» አለው፡፡

አንድ ቀን ደግሞ ተማሪው «የጥንካሬህ ምንጭ ምን እንደሆነ ንገረኝ» አለው፡፡

«የማደርገውን የማደርገው ስለማምንበት እንጂ ስለምጠቀምበት አይደለም፡፡ አእምሮህ ዓላማውንና ግቡን አይርሳ፤ ነገር ግን ወደዚያ ግብ ለመድረስ የራሱን መንገድና ጊዜ ጠብቅለት እንጂ በሱንግ ከተማ እንደነበረው ሰው የራስህን መንገድ አትከተልበት፡፡ በሱንግ ከተማ አንድ ሰው ነበር፤ ይኸ ሰው በቆሎ ይዘራና ለጥቂት ቀናት እየተንከባከበ ቢጠብቀው በቆሎው ትንሽ ከመሬት ብቅ ብሎ ቁመት አልጨምር አለ፡፡ የበቆሎውን ማደግ ለመጠባበቅ ትዕግስት ያልነበረው ይኸ ሰው ከቁመቱ ላሳድገው በማለት ብቅ ያለውን በቆሎ ወደላይ ጐተተው፡፡ የበቆሎው በራሱ ጊዜ የማደግና የማፍራት ታሪክም እዚያ ላይ አበቃ፡፡ እንዲሁ አንድ ድርጊት ስትፈፅም ድርጊቱ የራሱ ጊዜና መንገድ እንዳለው አትዘንጋ» አለው፡፡

ሜንሲየስ ንጉሡን ዳግመኛ ሊጐበኘው ወደ ቤተመንግሥቱ ሄደ፡፡ ንጉሡም በደስታ ተቀብሎት ወደማረፊያ ክፍሉ እያጣደፈ ወሰደው፡፡

«እባክህ አንድ ጥያቄ አለኝ» አለው ንጉሡ መጨነቁ በጉልህ ገፅታው ላይ እየተነበበ፡፡

ሜንሲየስም፡- «ንጉሥ ሆይ! ቀልብህን ገዝተህ ጠይቀኝ፡፡ ንጉሥ ስትሆን ከሁሉ በፊት ራስህን መግዛት እንዳለብህ ግን የምታውቅ ይመስለኛ



Scanned by CamScanner

ነበር...» አለው፡፡ ንጉሥ ሱአን በድርጊቱ ሀፍረት እየተሰማው ለሜንሲየስ ጥያቄውን ወረወረ፡- «ሕዝቡ እንደ እንስሳ እያመፀብኝና እየጠላኝ ነው... ምን ይሻለኛል?» አለው፡፡

ሜንሲየስም፡- «ንጉሥ ሆይ! በአእምሮህ ስትሰራ የሕዝብህ ገዢ ትሆናለህ፤ በጉልበትህ ስትሰራ ደግሞ ሕዝብህ ይገዛሃል... ይህ ዓለም አቀፍ ሕግ ነው...

«ሕዝብህ የሚያምፅብህ ስለሚጠላህ ሳይሆን ዕውቀት ስለሌለው ነው፤ ከእንስሳት ውስጥ አንድ አዋቂ መርጠህ ልታሳየኝ እንደማትችል አውቃለሁ፡፡ እንዲሁ ደግሞ እንደእንስሳት ከመብላትና ከመጠጣት ውጭ የተለየ እውቀት በሌለው ሕዝብህ ልትፈርድ አይገባም... የሰው እውቀትን የነፈግከው ሕዝብ፤ እሱም የሰው ፍቅር ነፈገህ...» በማለት ወደቤቱ ጥሎት ተመለሰ፡፡

ሜንሲየስ በዘመኑ ሁሉ ለተማሪዎቹ አበክሮ ካስተማራቸው ነገሮች አንዱ እውነተኛ ስለመሆን ነበር፡፡ አንድ ቀን ተማሪው እንደዋሸው የተረዳው ሜንሲየስ ለምን እንደዋሸው ተማሪውን ጠየቀው፡፡ ተማሪውም «እታውቅብኝም መስሎኝ ነው» በማለት መለሰለት... ሜንሲየስም፡- «የእውነትን ትርጉም ብታውቅ አትዋሽም ነበር» አለው፡፡



Scanned by CamScanner

# አስራ አንደኛው ሕግ!

መድረሻዋንና መሸሸጊያዋን ባታውቅም በሽሽት ትሮጣለች፤ ጉልበቷ ቢዝልም ትንፋሿ ቢቆራረጥም የነበራት ተስፋ መሮጥ ብቻ ነው... አሳዳጆቿ ደግሞ ከሽማግሌ እስከ ወጣት ናቸው... በርቀት እየተመለከቷት ቁጣቸውን በእልህና በቁጭት ተሸክመውት፤ ጉጉታቸውን ደግሞ በናፍቆት እየተመለከቱት አጠገቧ ለመድረስ፣ ደርሰውም የተሸከሙትን ድንጋይ በእሷ ላይ ለማሳረፍ ቸኩለዋል፤ ይሮጣሉ... ይሮጣሉ...

የሕዝቡ የእልህና የቁጭት ብሎም የበቀል ምክንያት ገዳዮችም ሆነ ሞት የተፈረደባት በሚገባ እንደሚያውቁት የአምላካቸው ሕግ መርከሱ ነበር:: የአምላካቸውን ሕግ ያረከሰችውን፣ ትዕዛዙንም የተላለፈችውን ሴት በሚወረውሩት ድንጋይ ከሞቷ የድርሻቸውን ለመካፈል፣ ከዚያም የአምላካቸው ሕግ ፈፃሚዎች ሆነው የገነት ዋስትና ለማግኘት ያልቸኮለ፣ ያልተጣደፈ፣ እንዲሁም ያልጓጓ አልነበረም:: በዚያ ጥድፊያቸውና ሩጫቸው እያለከለኩ ወደገላጣው ሜዳ ሲደርሱ እየቀረቧት መጡ፤ የሴቷ ጉልበት ደከመ፣ ዛለ፤ ትንፋሿ ቁርጥ... ቁርጥ... ማለት ሲጀምር ለአፍታ ከሩጫዋ ተገትታ ዞራ ተመለከተች:: ወጋሪዎቿ እንደደረሱባት ስታውቅ ደግሞ ለመጮኽ ፈለገች:: ግን ለማን? ወደአምላኳ እንዳትጮኽ «ውገሯት» ብሎ «ያዘዘ» እሱ ነው:: ወደሕዝቡ ተመልሳ ምህረት እንዳትለምን ለእሷ ምህረት ከማድረግ በላይ የሚያስፈራና የሚያስጠላ

ነገር በምድር ላይ ለማሰብ አይችሉም... የአምላክ ሕግ ትዕዛዝ ፈፃሚዎች ናቸውና...

ሙሴ አንድ ማለዳ ሕዝቡን ሰበሰበና «እንድትማሩአት፣ በማድረግም እንድትጠብቁአት ዛሬ በጆሮአችሁ የምናገራትን ሥርዓትና ፍርድ ስሙ» አለ:: ሕዝቡም በዙሪያው ከበበና ይሰማ ጀመር:: አምላክህ፡- «አታመንዝር» ብሎሃል አላቸው::

በወቅቱ የእግዚአብሔር ቃል ያህል የተፈራ የነበረውን የሙሴን ቃል ላለመቀበል ያንገራገረ አልነበረም፤ «ነገር ግን አላስችል ብሎን ብናመነዝርስ?» በማለት አንዱ የጠየቀ ይመስለኛል:: የእግዚአብሔርን ሕግ «አላስችል አለኝ» ብሎ ለማፍረስ መጠየቅ ያስፈራል... ሙሴም «በድንጋይ ውገሩት» ብሎ አዘዘ:: ሕዝቡም ተቀበለ... ወደቤቱ ሲመለስ ግን ያልገባውን ጥያቄ በመንገድ ላይ አነሣ... «ማመንዘር ምንድነው?»:: ጥያቄውን የተረዳ አብራራ፡- «ማመንዘር ከአንዲት ሴት በላይ «መገናኘት»... ወይም ከሚስቱ ውጭ የሌላዋን ሴት ብብት ማቀፍ...» ነው አለ:: አሁንም ሕዝቡ ተቀበለ:: በዓመቱ ሙሴ ሄደና «ግብፃዊት» አገባ:: ግብፃዊ የእስራኤል ጠላት፤ በዚያም ላይ አሕዛብ ነው... «በድንጋይ እንውገረው» ያለ ግን አልነበረም:: ማን ባወጣው ሕግ ማን ይወገራል፤ ነገሩ ያልተዋጠላቸው በሙሴ ድርጊት አንጐራጐሩ፤ መሬት ተከፍታ ዋጠቻቸው... ግማሹም ለምፅ ያዘው:: የተረፈውና ሳያንገራግር ሕጉን የተቀበለው ደግሞ አመንዝራን በድንጋይ እየወገረ መግደሉን ቀጠለ::

ዛሬ የነዚያ የልጅ ልጆች ከሴቷ አሳዳጆች ውስጥ ይገኙበታል:: ወደሴቷ መቅረባቸውን፣ የአምላካቸውን ጠላት የሙሴንም ሕግ ያፈረሰች ሴት ለመግደል እየቀረቡ በመጡ ሰዓት ጉልበታቸው ተበራታ:: ሴቷ ተስፋ ቆርጣለች፣ ለመኖርም የቀራት በጣም ጥቂት ጊዜ እንደሆነ አውቃለች:: የመንፈስና የሥጋ ጣር በያዛትና ከሞት ለማምለጥ የመጨረሻውን መፍጨርጨር በምታደርግበት በዚያ አውላላ ሜዳ ላይ አንድ ሰው ተቀምጦ አገኘች... ከዚያ በኋላ መሮጥ አልቻለችም:: ወደዚያ



Scanned by CamScanner

ሰው የጣር ያህል እግሮቿን እየጐተተች ተጉዛ ደረሰች:: ከዚያ ሰው አጠገብ ስትደርስ አሳዳጆቿ ከኋላዋ ነበሩ:: «ጌታ ሆይ አድነኝ» በማለት ጮኻ ከፊቱ ተንበረከከች::

በቅፅበት ሕዝቡ በቦታው ደርሰው የተሸከሙትን ድንጋይ ለመዘርገፍ ባሰፈሰፉበት በዚያ ሰዓት የሚጥሉት ድንጋይ ለሰውዬውም እንደሚተርፍ አውቀዋል፤ አንዳንዶቹ የሰውዬውን ማንነት አስቀድመው የሚያውቁ:- «እሱንም እዚሁ ፊትነን አብረው እንውገራቸው» ተባባሉ... በዚህም ተስማሙና ከሕዝቡ መካከል አንዱ ወደሰውዬው ተጠጋ... «ይኽች ሴት ስታመነዝር አግኝተናታል... ሙሴ ደግሞ በሕጉ በድንጋይ ተወግራ ትሙት ብሏል:: አንተስ ምን ትላለህ?» አለው:: ሰውዬው ከተቀመጠበት አልተነሳም፣ አንገቱንም ከደፋበት አላቀናም:: አቀርቅሮ የተቀመጠበት ምድር ላይ በጣቱ መፃፍ ጀመረ... ሕዝቡ ለአፍታ ጠበቀው፤ በጉጉትና በተስፋ የተወጠረ ሕዝብ ትዕግስት አስጨናቂ ነበር... ሕዝቡ ማንጐራጐርና መጮኽ ጀመረ... «አብረው ይወገሩ...!!» ሰውዬው አልተረበሸም፤ አንገቱን ከደፋበት ቀና ሳያደርግ ቆይቶ የሕዝቡ ማንጐራጐር ማየል በጀመረበት ሰዓት ከአፉ ቃል ወጣ... «ከእናንተ ያላመነዘረ የመጀመሪያውን ድንጋይ ይወርውርባት...!» ሕዝቡ እርስ በእርሱ ተያየ:: ድንጋዩን ለመወርወር የደፈረ ግን አልነበረም:: ምክንያቱም «አታመንዝር» ያለው ሕግ «አትዋሽ» ደግሞ ብሏልና:: «አታመንዝር» ብሎ ሕግ የዚያን ቀን ተፈተነ:: አለማመንዝር ቢቻል የሴቷ ፍፃሜ የዚያን ቀን በሆነ ነበር::...

ሰውዬው ካቀረቀረበት ራሱን አቀና... ከሴቷ በቀር ማንም አልነበረም:: «ከሳሾችሽ የት ሄዱ?» አላት:: በድንጋይ ሊወግሯት ካሳደዷት ከብዙዎቹ ጋር ያመነዘረችው ሴትም ወዴት እንደሄዱ ነገረችው...

የሮማው ቄሳር የገነነበትና የነገሰበት የአይሁድ ዘርም በባርነት የሚማቅቅበት ዘመን ነበር:: በዚያ የመከራ፣ የስቃይ፣ የሰቆቃና የበደል ዘመን የአይሁዶች ተስፋ አምላካቸው ብቻ ሆኖ ቀርቶ ነበር... አምላካቸው መሲህ እንዲልክላቸው መጥቶም ከመከራቸው እንዲያድናቸው አይሁዶች



Scanned by CamScanner

ይጠብቃሉ:: «እነሆ በቤተልሔም ተወለደ...» ሲባሉ ግን አልተዋጠላቸውም:: በበግ ጉረኖ ውስጥ የሚወለድ መሲህ የለንም አሉ:: የእኛ መሲህ ቢመጣም የሚመጣው ለእኛ እንጂ ለዓለም አይደለም አሉ:: የገዟቸው፣ ያንገላቷቸው፣ የጨቆኗቸው ሮማውያንም አብረው «ነፃ» ሲወጡ ማየትና መቀበል የሚችሉት አልሆነላቸውም:: ከእሱ ይልቅ ንጉሱ ሄሮድስ ሺ ዓመት ይግዛን አሉ... ከቄሳር በቀር ንጉስ አናውቅም አሉ:: በራሱ በቄሳርም ፈተኑት...

«ለቄሳር ግብር እንድንከፍል ተፈቅዶአል?» በማለት ጠየቁት:: «አንድ ዲናር አሳዩኝ» አላቸው:: ከአጠገቡ አንዱ አወጣ:: «በዲናሩ ላይ ያለው መልክና ጽሕፈት የማን ነው?» ሁሉም በአንድ ድምፅ «የቄሳር» አሉ... «እንግዲያውስ ለእሱ ይገባል፤ በራሱ ምስል ሰርቶታልና «የቄሳርን ለቄሳር» ስጡ» አላቸው:: አንዱ ጠየቀ:- «ለእግዚአብሔር ታዲያ ምን እንስጠው?» «እሱን አስመስሎ የሰራውን ደግሞ ለእሱ ስጡ» አለ:: ሕዝቡ አልገባውም... ለቄሳር ሊገብር ሄደ::

በ1830 ኬንተኪ በተባለችው የአሜሪካ ግዛት የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ የሚል አንድ ሰው መጥቶ ነበር፤ የራሱን ወንጌል ጽፎ መስበክ ጀመረ፤ የተከታዮቹ ቁጥርም በሺዎች ደረሰ፤ አንድ ቀን ወደአንዲት ትንሽ መንደር ወንጌሉን ሊሰብክ አቀና፣ በዚያ መንደር ግን ነዋሪው በሙሉ የጀርመን ዜጋና ከጀርመን ቋንቋ በቀርም የማይሰማ ሆነበት:: በዚህ መሀል አንድ ሰው ጠየቀው:- «እንግሊዝኛ ቋንቋ ስለማንሰማ በጀርመንኛ ስበከን...::» ሰውዬው ጥቂት አንገራገረና የጀርመን ቋንቋ እንደማይችል ነገራቸው:: ሕዝቡ ተደነቀ፤ ሰውዬውም አለ:- «የእግዚአብሔር ልጅ ሆነህ እንዴት ጀርመንኛ አትችልም?» የዚያ ሰው መጨረሻም ሆነ:: «በስሜ ይመጣሉ፤ ብዙዎችንም ያስታሉ» በማለት አስቀድሞ ለሕዝቡ የነገራቸው ይኼን ነበር::

አንድ ቀን በኢየሩሳሌም መቅደስ ካህናት አገኙት... «በእርግጥ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ?» አሉት:: «እናንተ አላችሁ» አለ:: በቃላቸው



Scanned by CamScanner

አጠመዳቸው:: «በማን ሥልጣን ይህን ታደርጋለህ?» አሉት:: «የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበር ወይስ ከምድር?» አላቸው:: ከሰማይ እንዳይሉ አላመኑበትም፤ ከምድር እንዳይሉ እንደዚያች ሴት በድንጋይ ሊወገሩ ነው:: «አናውቅም» አሉ:: «እኔም አልነግራችሁም» አላቸው:: እስከዛሬም ሳያውቁ እየኖሩ ነው::

አንድ ቀን በመንገድ ሲሄድ ሀብታም ጐልማሳ መጥቶ በፊቱ ተንበረከከ:: «የዘላለም ሕይወት እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ?» አለው:: «ሕግን ጠብቅ» አለው:: «ሕግን በሙሉ ጠብቄአለሁ» አለ ጐልማሳው:: «እንግዲያውስ አንድ ነገር ቀረህ... ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥና ተከተለኝ...» አለው:: «ይኼስ ይቅርብኝ፤ ከድህነት ገሃነም ይሻላል» በማለት ወደቤቱ ተመለሰ:: ዛሬ ያ ጐልማሳ ገሃነም ይገኛል፤ ሕግን ቢፈፅምም በመርፌ ቀዳዳ ግን መሹለክ አልቻለም::

እነሆ ባሳለፍነው ሣምንት የኢየሱስ ክርስቶስን ልደት አከበርን:: በልደቱ ማግስት የምናስበው «ሀብታም መንግሥተ ሰማያት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢሾልክ ይቀላል» የሚለውን ይሆናል:: ሀብታም በሰማይ ደህም በምድር ላይ ተስፋ የሚቆርጥበት ንግግር ነው:: አሥራ አንደኛው ሕግ ይሆን?



Scanned by CamScanner

# «እግዚአብሔር ሞቶዋል...» ኒች «ኒች ሞቶዋል...» እግዚአብሔር

ፈላስፎች በጥንት ጊዜ ጉባዔ የማድረግ ልምድ በእጅጉ ተጠናውቶዋቸው ነበር። በአንዱ ጉባዔያቸው የተነሣው የመነጋገሪያ ሃሣብም «ሰው መጠራጠር ስለሚደክመው በማመን ይኖራል» የሚል ነበር። ታዲያ አንዱ ፈላስፋ በዚያ ጉባዔ ይኸን ብሏል።

«በተራሮች በተከበበች አንዲት ትንሽ ከተማ የሚኖር የ90 ዓመት ሽማግሌ አጐት አለኝ፤ ይህ አጐቴ እጅና እግሩ ዝሎ ለመንቀሳቀስ እስኪያቅተው ድረስ እርሻውን የሚያርስ ገበሬ ሆኖ ይኖር ነበር። አሁን ደክሞና ዝሎ አብዛኛውን ጊዜውን በአልጋው ላይ በሚያሳልፍበት ወቅትም አሮጊት ሚስቱ አጠገቡ ስትቀመጥ በደስታና በመፅናናት የሚያወራት አንድ ነገር በዕድሜ ዘመኑ ሁለት ጊዜ ብቻ ኃጢአት እንደሠራና ሲሞትም ይኸንኑ ኃጢአቱን ለእግዚአብሔር ተናዞ ይቅር እንደተባለለት ብሎም የገነት ደጃፎች ተከፍተው እንደሚጠብቁት ነበር። እሷም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የክርስቶስን ቃልና ልዩ ልዩ የእግዚአብሔርን የተስፋ ቃሎች እያነበበችለት በቃላት በማይነገር ደስታና ተስፋ ስትሞላው ትውላለች። እግሩን ለማፍታታት ከቤት ወጥቶ የሚዝናናው እንኳን ሙታን ባረፉበት መካነ መቃብር አካባቢ ስለሆነ በሐውልታቸው ላይ ያሉትን ክንፍ

ያላቸው መላዕክት እየተመለከተ ለእሱም «ነገ» አንድ ጠባቂ መላዕክት እንደሚመደብለት ተስፋ ያደርጋል። ታዲያ እኔ በድንገት ወደዚህ አጉቴ ቤት ሄጀ እስከዛሬ ተስፋ ያደረገው ሁሉ ከንቱና የማይረባ ነገር መሆኑን ባስተምረውና ባስረዳው የቱንም ያህል እውነት ነው በማለት ቢቀበለኝ እንኳን በምድር ላይ ያለውን ቀሪውን ሀብቱን «ተስፋን» ያጠፋሁበት ሰው በመሆኔ ብቻ ይቅር የማይለኝ ጠላቱ እንደምሆን ጥርጥር የለኝም» በማለት ተናገረ።

በጉባዔው የነበሩ ፈላስፎች የበኩላቸውን አስተያየት ሲሰጡ አንዱ ፈላስፋ «የተነገረው ታሪክ ቁንፅል እንጂ የተሟላ ነገር የሚያሳይ አይደለም» በማለት ተነሣ። «የትኛውም የሃይማኖት ስብከት የሰው ልጅ ተስፋና ደስታን በገነት እንዲጠብቅና በዚያም እንዲፅናና ከማድረግ ይልቅ የሚጠብቀውን የገሃነም እሳት በማስተማር ሰው እርስ በእርሱ እንዲጨካከንና እንዲፈራራ ብሎም ስለአምላኩ ሲያስብ በእሣት የማይራራለት ከሆነ የራሱ ጭካኔ ኢምንት ሆኖ እንዲታየው ማድረጉ እየታየ ያለ ሐቅ ነው» አለ።

በዚህ ጉባዔ የተነሣው ጉዳይ ለዘመናት የብዙ ፈላስፎች የመነጋገሪያ አጀንዳ የነበረና አሁንም የሆነ ጉዳይ ነው። «አንድ አምላክ ነበር እሱም ሞቶዋል» የሚለው ኒች የእሱ ደጋፊዎችም ቢሆኑ «ብዙዎች በሕይወታቸው የነበረው መልካም ነገር ሁሉ ወደ መጥፎ ሲገለበጥ በእግዚአብሔር ማመን ይጀምራሉ» ይሉናል። «ስለዚህም እግዚአብሔር ህያው ያደረገው በሰዎቹ ሕይወት የተፈጠረው አጋጣሚ እንጂ በራሱ ህያው ሆኖ አይደለም» በማለት የእምነትን ነገር ያጣጥሉታል።

እምነትን መጠራጠር ማለት ዘለዓለማዊነትን (eternity) ወይም ከሕይወት በኋላ የሚኖረውን ሕይወት መጠራጠር ነው። ታዲያ ይህ አባባል የሰለቻቸው ፈላስፎች «ነፍስ ያለሥጋ ብቻውን እንዴት ሕያው ሊሆን እንደሚችል ማሰቡ ግራ የሚያጋባ ነገር ቢሆንም፤ ሐሣቡ የበለጠ የሚከብደው ደግሞ ከሥጋ የተለየ ነፍስ ምን ዓይነት ደስታ ሊያገኝ

ይችላል የሚለው ላይ ነው» ይላሉ:: እንዲያውም የማይመች ሐሣብ (uncomfortable thought) ነው» ይሉታል::

እንደኤፒኩረስ የመሳሰሉ ፈላስፎች ደግሞ ሰው አምላኩ አድርጎ (ለእኛ አሁን እግዚአብሔር እንደምንለው ማለት ነው) የሚያመልካቸው እጅግ የበዙ እግዚአብሔሮች እንደነበሩት ይነግሩንና «ጥንት የነበሩ ሰዎች አሁን ከሞት ተነስተው በጊዜያቸው የሰገዱላቸው አማልክት አሁን ከአንትሮፖሎጂስቶች በቀር ማንም እንደማያውቃቸው ቢመለከቱ ከሐዘናቸው ይልቅ ለአምልኮ ባባከኑት ጊዜ እንደሚፀፀቱ ጥርጥር የለንም» ይላሉ::

«የአሁኑ እግዚአብሔር ከጥንቱ የሚለየው አለመሞቱ ነው» የሚሉን የዘመኑ ፈላስፎች እግረመንገዳቸውን የኒችንም ሐሣብ እያጣጣሉ ነው:: የጥንት ሰዎች የሚያመልኩባቸውን አማልክት «ወይ ይሞታሉ አሊያም ገና ይፈጠራሉ» ብለው ይጠብቁዋቸው ነበር:: ከጥንታውያን ፈላስፎች ታላቅ ክብር የሚሰጠው ዜኖፋነስ ከክርስቶስ ልደት 600 ዓመት በፊት አስቀድሞ እንደተናገረው «ሰዎች አምላካቸው ይወለዳል ብለው ይጠብቁታል፤ የሚጠብቁትም እንደነሱ እጅ እግር ያለው፣ እነሱን የሚመስልና የሚንቀሳቀስ ወዘተ... ይሆናል ብለው ነው:: ለምሳሌ ኢትዮጵያውያኖች ቀጭንና እና አፍንጫ ደፍጣጣ ይሆናል ሲሉ፣ ቱርሺያንስ ደግሞ ፀጉረ ዞማና ሰማያዊ ዓይን ያለው ይሆናል ይላሉ:: እንደ ሆሜር ዓይነቱ ፈላስፋ ደግሞ የአማልክት ልዩ መለያው «ዝሙት፣ ስርቆት፣ ማታለልና ሌሎች ሕገወጥ ነገሮች ናቸው በማለት አስፍሯል» ይሉናል::

ዜኖፋነስ አንድ ያስቀመጠውን ሐሣብ እዚህ ላይ ማየቱ በእርግጥ ማን ማንን ፈጠረ የሚያስብል ነው:- «ግሪኮች በጥንት ጊዜ አምላካቸው አድርገው ያመልኩበት የነበረው አምላክ በግድያ፣ ሴት አስገድዶ በመድፈርና በስርቆት የታወቀ ነበር:: ምክንያቱም በጊዜው ያንን አምላክ የፈጠሩት ይኸን ድርጊት ፈፃሚዎችና በድርጊቱ ተገቢነት የሚያምኑ



Scanned by CamScanner

ነበሩ፡፡ ታዲያ በዘመኑ ሰርቀህ ብታገኝ አምላክ የሚወደውን ፊሀምክ እንደማለት ነው» ብሎናል፡፡

ወደዘመናችን እግዚአብሔር ተመልሰን የፈላስፎችን ሐሣብ ስንቃኝ «የአሁኑ እግዚአብሔር እንደ ጥንት አማልክት የሚሞትና ደካማ ሳይሆን ነገር ግን የሠራዊት ጌታ ነው» ይሉናል፡፡ «ስሙ የሚያስፈራ፣ አሕዛብ በፊቱ የሚንቀጠቀጡለት ብቻ ሳይሆን ሚሊዮኖችን ወደ ገሃነም የመጣል ብቃት ያለው ነው፡፡ ስለዚህም ጀግና ተዋጊ ነው» ይሉናል፡፡ ይኸው ጀግንነቱ ጭካኔም አትርፎለታል፡፡ «የአይሁድን ዘር ሃገራችሁ ላስገባችሁ ብሎ በበረሃ ፈጅቶ ሁለት ሰው ብቻ ይዞ ገባ» የሚሉት ፈላስፎች «በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ እንዲህ ዓይነቱን ጭካኔ በምድር ላይ የደገመው ሂትለር ብቻ ነው» ይሉናል፡፡

«እሱ ባለበት መድረስ አልፈልግም» የሚለን ጆን ስቴዋርት ሚል «እሱ የሌለበት ገሃነም ከሆነ በደስታ ወደዚያ እሄዳለሁ» በማለት የእግዚአብሔርን ጨካኝነት ሊያሳየን ይጥራል፡፡

በጽሑፌ መግቢያ ላይ ባነሳሁት የኒች ሐሣብ ላይ የሚሳለቁት ፈላስፎች «ኒች አሁን ምድር ላይ እየኖረ ቢሆን እግዚአብሔር ሞቶዋል አይልም ነበር» ይላሉ፡፡ «እንዴት» ተብለው ሲጠየቁ መልሳቸው «ዛሬ ይሄን ሁሉ ሕዝብ እየፈጀው ያለ ማን ሆነና ነው» መልሳቸው፡፡

ይህን ባዮች የኒችን ሐሣብ በሚገባ ያልተረዱ ናቸው የሚሉም አሉ፡፡ እኔም በዚህ እስማማለሁ፡፡ ኒች የተናገረውን ላስቀምጥና ላብቃ፡፡

ኒች እንዲህ አለ፡- «እግዚአብሔር ሞቶዋል፤ የገደለውም ክርስቶስ ነው» የእግዚአብሔርን ታሪክ በሚገባ ያወቁት በኒች ሐሣብ ተስማሙ፤ የበለጠ ደግሞ የተስማሙት ክርስቶስን የሚያውቁት ናቸው፡፡



Scanned by CamScanner

# «ዕውቀት ስትበልጥ ሕይወት አስቀየመች»

ባለፈው ምዕራፍ ከፍልስፍናው በመጠኑ ቀንጭቤ ያቀረብኩላችሁን ኒች አሁን ደግሞ ማንነቱንና እምነቱን በመጠኑ ላጋራችሁ:: ፍልስፍና ስለእግዚአብሔር መኖር ብዙ ጥያቄዎችን በምታነሳበት ዘመን ኒች «መልስ አለኝ» በማለት ብቅ ያለ ፈላስፋ ነበር:: "Joyful Wisdom" በተሰኘው ሥራውም የእግዚአብሔርን ሞት አረዳን:: እግዚአብሔር ደግሞ በተራው የኒችን ሞት አረዳንና «ማንኛችን ነን ትክክል?» አለን:: የእኛ መልስ «ኒችን ጠይቀው» ቢሆንስ?

ፍሬዴሪክ ዊህልም ኒች ኦክቶበር 15/1844 በዚያን ወቅት ፕራሽያ ተብላ በምትታወቀው ጀርመን ሳክሰኒ ግዛት ተወለደ:: አባቱ የቤተክርስትያን ሰባኪ (ፓስተር) ነበር:: ከ1854-58 የጂምናስቲክ ትምህርት ሲከታተል ቆይቶ በ1958 የዘመኑን ታላላቅ ሰዎች ወደአፈራው 'ፎርታ' የአዳሪ ትምህርት ቤት ገባ:: በዚያም ትምህርት ቤት ቆይታው ለፍልስፍና ከፍተኛ ፍቅር አደረበት:: በተለይም ፕሌቶ ለእሱ ልዩና ተወዳጅ ሰው ነበር፤ የሆሜሩ አኪለስም አድናቂና ስለእሱ ሲናገር ቢውል የማይሰለቸው ሆነ:: (የሆሜሩን አኪለስ ከዚህ ቀደም በመጠኑ ለማሳየት ሞክሬአለሁ::)

በ1864 እ.ኤ.አ. ወደቦን ዩኒቨርስቲ ሲገባ ብቻውን ሳይሆን ከዓመታት በኋላ ታላላቅ የፍልስፍና ሥራዎቹን ለዓለም ካበረከተውና በዘመኑ



Scanned by CamScanner

የልብ ወዳጁ ከነበረው ፖል ዲዩሰን ጋር ነበር:: ነገር ግን ከአንድ ዓመት በኋላ ወደሊፐዚግ ተዛውሮ የታዋቂው ፈላስፋ የሪች ተማሪ ሆነ:: በተማሪነት የሁለት ዓመት ቆይታውም በርካታ የፍልስፍና ሥራዎቹን አበረከተ:: በዚያ ወቅት የባሰል ዩኒቨርስቲ የፍልስፍና ክፍል ኃላፊ የሚሆነውን ሰው በማፈላለግ ላይ ነበር:: ለዚሁ ሥፍራ ማን ይመጥናል ተብሎ ሪች ተጠየቀ:: ሪችም ተማሪውን ኒችን ጠቆመ:: በወቅቱ በዚያ ቦታ ለመቀመጥ የሚፈለገው የፐሮፌሰር ማዕረግ የነበረው ሰው ነው:: ኒች የፐሮፌሰር ማዕረግ ሳይኖረው ለቦታው የመጠነ የመጀመሪያው ሰው ሆነ::

በዚሁ ወቅትም የመጀመሪያ የፍልስፍና ሥራውን በሚወደው የሆሜር ድርሰት አሐዱ በማለት አቀረበ:: "Homer and Classical Philosophy" የተሰኘው ይኸው ሥራው ገና ከጅምሩ ታላቅ ፈላስፋነቱን ያመላከተ ሆነ:: ኒች አብዛኛውን ጊዜውን ወደታላቁ የሙዚቃ ቀማሪ ሪቻርድ ዋግነር ቤት በመሄድ ያጠፋ ነበር:: ከልጅነቱ ጀምሮ እየሰማ ያደገውን የዋግነርን ሙዚቃ ያደንቅ የነበረው ኒች በኋላ ላይ ከዚህ ታላቅ የሙዚቃ ሰው ጋር ያፈራው ወዳጅነት በሥራዎቹ ወስጥ ተፅዕኖአችው አርፎበት ተስተውሏል:: ከላይ ባነሳሁት የ"Joyful Wisdom" ሥራው ምክንያት ታላቅ ነቀፋና ትችት ከወዳጆቹ ሳይቀር የተሰነዘረበት ኒች ፍልስፍናውን ከወደማክተሙ አፋፍ ላይ ለማድረስም የተቃረበበት ጊዜ ነበር::

ነገር ግን ኒች ወደኋላ ዘመን በአርስቶትል ላይ የሰነዘረውን ትችት አንስቶ የእሱን ፍልስፍና በማብራራትና የራሱንም በማከል አዲስ መንገድ ጀመረ:: «ለምሳሌ» ይለናል ኒች ስለጥሩና መጥፎ የዚህ ዓለም ነገሮች ሲገልፅልን «አንድ ነገር ለማኅበረሰቡ እስከጠቀመ ድረስ ጥሩ ይሆናል፤ ማኅበረሱን እስከጐዳ ድረስ ደግሞ መጥፎ ነው:: ይኸ ግን ከማኅበረሰቡ መለዋወጥና ከዘመን ዕድገት ጋር አብሮ የሚለዋወጥ፣ የሚጠፋም ነው:: ስለዚህ ጥሩ ነገር ጊዜያዊ እንጂ ዘላለማዊ አይደለም:: እምነትህን



Scanned by CamScanner

ገፀበ

ደግሞ መርምር:: እምነት ወይም ደግሞ ንቃተ ኅሊና የሰውነትን ውስጥ የእምነት አስተማሪን ድምፅ ለምተህ የተከተልከው እንደ የእግዚአብሔር ድምፅ ውጤት አይደለም...

«...መናገር የሚችለው ሰው የተፈጠረው በማይናገረው እግዚአብሔር ነው ብለን ብንወስድ እንኳን በማንኛውም አቅጣጫ የሚናገረን ሰው ነው እንጂ እግዚአብሔር አይደለም... ምክንያቱም እግዚአብሔር ሲናገር የሰማው የለምና... እግዚአብሔር የማይናገር ከሆነ ደግሞ ሰው ራሱ መናገርን ከየት አመጣው? ...እግዚአብሔር በሰው አፍ የሚናገር ከሆነ ምክንያቱን ማወቅ አለብን...::» ኒች በሚያስበው ነገር እርካታ አለማግኘት ብቻ ሳይሆን ጤንነቱም በዚሁ ሐሣብ ችግር ላይ ወድቆ ነበር:: ሕክምና ለማግኘት በተለያዩ ሃገሮች ቢዘዋወርም ጤንነቱ ሰውጥ አላመጣም:: ወደሃገሩ ጀርመን በ1879 ተመልሶ የሞራልና እምነት ጉዳይ ያነሳበትን የመጀመሪያውን የፍልስፍና ሥራውን "The Dawn of the Day" ፃፈ:: ከሦስት ዓመት በኋላ በ1882 ክርስትያንነት ምን ያህል የሕይወት ጠላት መሆኑን ለማሳየት የሞከረበትን "Joyful Wisdom" ለሕትመት አበቃ:: «እግዚአብሔር ሞቷል» የሚለው በሥራው ውስጥ በሰፊው የተንፀባረቀው ፍልስፍናው «ነፃ መንፈስን» በምድር ላይ የወለደበት ነው ተብሎለታል:: ከላይ የጠቀስኳቸው ሁለቱም መጻሕፍቱ ግን በጊዜው ተወዳጅነትም ሆነ ተደናቂነት አላተረፉለትም ነበር::

ኒች በዚህ ቢበሳጭም ማሰቡን ግን አላቋረጠም ነበር:: በ1881 እ.ኤ.አ. ወደአእምሮው አንድ ሐሣብ መጣ:: ይኸ ሐሣብ «ዘላለማዊ ድግግሞሽ» የሚል ነበር:: «ዘላለማዊ በሆነው «ጊዜ» ውስጥ የሚከናወነው ማንኛውም ነገር እየተደጋገመ ነው» ከሚል ሐሣብ ተነሣ:: ለማሰብ እንኳን እጅግ ጥልቅ የሆነውን ይኸን ሐሣብ ኒች ገፋበትና በዓለም ላይ እስከዛሬ ታላቅ ሰውነቱን ያረጋገጠለትን ሥራ ከወነ... ይኸ ሥራው "Thus Spake Zarathustra" ነበር:: የፔርሺያው ጠቢብ ዛራቱስትራ በኒች ተፈጥሮ እውነትና እምነት፣ ጥበብና እውቀትን እስከዛሬ ለዓለም



Scanned by CamScanner

ይናገራል::

«ከግሪኮች በላይ ስለዓለም አስቸጋሪነት፣ ምስጢራት፣ አደገኛነት... የተረዳ የለም» ይላል ኒች:: «የእነሱ ድክመት ነገሮችን ሁሉ በመልካም ጐናቸው ብቻ የመመልከታቸው ጉዳይ ነው... እነሱ ከተመለከቱት ውበትና ጥበብ በስተጀርባ የሚገኘውን መፈለግና አስቀያሚውን ጨለማ ለማየት ግን አልቻሉም... ስለዚህም አስቀያሚው ጨለማ በእነሱ የውበት መጋረጃ ተደበቀ... የእኔ ሥራ ደግሞ መጋረጃውን ገልጠ እውነትን ማሳየት ነው...» ይለናል::

ኒች "The Birth of Tragedy" ውስጥ የሚያነሳልን ጥያቄ «ከሕይወትና ከእውቀት የሚበልጠው ማን ነው?» የሚል ይሆናል:: ብዙዎች «ሕይወት» ይላሉ:: ኒች ደግሞ «በእርግጥ ሕይወት እውቀትን በልጧል! ለዚህም ነው የሰው ልጅ ክፋት የበዛው:: ግሪኮች ሕይወትን በጥበባቸው ሲያሳምሩ እውቀትን ግን መጋረጃ ጥለውባት ነበር...

«እኔ ደግሞ ግሪኮች በሕይወት ላይ የጣሉትን የጥበብ መጋረጃ ገፈፍኩት... እውቀትም በለጠች:: እውቀት ስትበልጥ ሕይወት አስቀየመች...» ብሏል::

በ"Joyful Wisdom" ውስጥ ደግሞ ኒች እንዲህ አለ:: «የቅርብ ጊዜ የዓለማችን ክስተት 'የእግዚአብሔር መሞት ነው' ...በእግዚአብሔር ማመን በራሱ የማይረባ እምነት ነው... ይኸ እምነት ደግሞ ጥላውን በሰው ልጅ ላይ አጥልቶ ነበር... ዛሬ ዛሬ ያ ጥላ እየተገፈፈ መጥቶ ሰው በሙሉ ኃይሉና እውቀቱ መሥራት ጀምሯል... ለዚህም ዋናው ምክንያት ሳያየው ከሚመኘው ዓለም ይልቅ የሚያየውና የሚኖርበትን ዓለም በመምረጡ ነው...» ይላል::

እግዚአብሔርን እንደኒች የተቃወመው ፈላስፋ በታሪክ የለም:: "The Twilight of the Idols" የኒች ሌላው የሚደነቅበት የፍልስፍና ሥራው ነው:: በዚህ ሥራውም የእግዚአብሔርን መኖር ሲኮንን:- «በዓለም ላይ ያየሁት መጥፎ ነገር መዋሸት ነው፤ የማይታይ ነገር ከማመን በላይ



Scanned by CamScanner

ደግሞ ውሸት የለም... «ማመን የድክመትና የስግብግብነት ምልክት ነው... የሰው ልጅ በሕይወት ዘመኑ እርካታን ከማጣቱ የተነሣ ዘላለማዊ ሕይወት ተመኘ... ስለዚህም እግዚአብሔርን ፈጠረ... እኔ ደግሞ ባለኝ ሕይወት በቂነት ስለማምን «የተፈጠረን ነገር አልቀበልም... የእግዚአብሔርን መኖር አለመቀበል ደግሞ ጥንካሬዬን ገለጠልኝ... በዚህም የራሴ እግዚአብሔር ሆንኩ... ዛራስቱራንም ፈጠርኩ... እነሆ ብዙዎች ዛሬ በእሱ አምነዋል» ይላል::

ዛሬ የኒች ፍልስፍና ኒሂሊዝም በሚል መጠሪያ ይታወቃል፤ እጅግ የበዙ ተከታዮችም አሉት:: ኒች በ1889 እ.ኤ.አ. በአእምሮ መታወክ ለጥቂት ጊዜ ከታመመ በኋላ ፍፁም እብድ ሆነ:: ኦገስት 25/1900 እ.ኤ.አ. ዌይማር በምትባለው የጀርመን ግዛት በእህቱ ቤት ለጥቂት ጊዜ ከተሰቃየም በኋላ ሞተ:: ኒች በወቅቱ አብዶ ስለነበር ዓለም ለሥራው የሰጠውን ክብር ለማየት (ለማወቅ) አልቻለም:: ነፍሱ በሰላም መንግሥተ ሰማያት ትግባ::

# «አፍቃሪን ስለማፍቀሩ ብትነቅፈው ማፍቀሩን ይጨምራል»

- ሱፊዝም

በሱፊዝም ዓይን ለዛሬ ፍቅርን እናያለን:: ሱፊዝም የእስልምና እምነት የወለደው መንፈሳዊ ተመስጥኦ Mystics ነው:: እያንዳንዱ ፃድቅ ሙስሊም ከሞት በኋላ እግዚአብሔርን እንደሚያይ ያምናል:: በሱፊዝም ግን እግዚአብሔርን የሚፈልጉት አሁን ነው:: ቅፅበት በቅፅበት፣ ዕለት ተዕለት... በዚህ በዛሬው ሕይወት:: ይኸም ይቻል ዘንድ የሚፈለገውን ሁሉ ለመፈፀም የተዘጋጁ ናቸው:: የሱፊዝምን መንገድ ከተከተሉት ውስጥ ታላቅ ቦታ የሚሰጠው ጃላል-አድ ዲን አል ሩሚ ነው:: እሱም ሲናገር «ምድሪቱን ለመሳም ከመቶ በላይ መንገድ አለ...» ይላል:: ለዛሬ አንዱን እናያለን::

በሱፊዝም ለማወቅ የምትሻውን ነገር መጀመሪያ ልታፈቅረው ዘንድ የግድ ነው:: በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በትምህርት... ይሳካልን ዘንድ ማፍቀር ያስፈልጋል:: ለማፍቀር ደግሞ መንገድ አለው:: መንገዱም ሱፊዝም ነው ይላሉ:: የማፍቀር ችሎታህ ባደገ መጠን እግዚአብሔርን ማፍቀርህም እንዲሁ ያድጋል::

ብዙዎቻችን የምንፈራው ነገር ቢኖር ፍቅርን ነው:: ባፈቀርነው ሰው ስንከዳ፣ ጓደኞችን ሲንሸራተትብን የምንፈራው ፍቅርን ይሆናል::



Scanned by CamScanner

የቱርኮች ተረት እዚህ ላይ ትነሣለች:- «ሾርባ ያቃጠለው በእርጐ ይናደዳል»:: «ያሳለፍነው ሕይወት የቱንም ያህል መጥፎ ይሁን ለዳግሚያ ፍቅር የተዘጋጀ ልብ ይኑረን» ይላሉ ሱፊዎች::

ፍቅርን የምንፈራው ስለሚያሸጋግረንም ነው ይሉናል:: የምንሻገረው ወደአፍቃሪነት፣ ወደተፈቃሪነትና ወደራሱ ወደፍቅር ነው:: ይኸን ጊዜ እንደራስህ ማሰብ ታቆማለህ:: አፍቃሪም ተፈቃሪም ፍቅርም አንድ ይሆናሉ::

በሼህ ኡፍታዴ እንጀምራለን:: ሱፊ ነበሩ:: ታመው ለረዥም ወራት በአልጋ ላይ ይውሉና አላህ ምህረቱን ላከላቸው:: ከአልጋ በተነሱ ሰሞን ደቀመዝሙራቸው ሁዳይ በማለዳ ይነሣና ሼሁ ለስግደት ሲዘጋጁ የሚታጠቡበት ውሃ ያሞቃል:: ሼሁም በሞቀ ውሃ ይታጠቡና ለአላህ ይሰግዳሉ:: አንድ ማለዳ ሁዳይ እንቅልፍ ይዞት ሄዷል:: ሼህ ኡፍታዴ ለፀሎት ሲዘጋጁ ይሰማና ደንግጦ ወደ ማንቆርቆሪያው ይሮጣል:: ማንቆርቆሪያውንም በልቡ ላይ አስጠግቶ ይዞ ጥቂት ይቆይና ይቀርባል:: ሼህ ኡፍታዴ እጃቸውን ዘረጉ:: ሁዳይም እንደበረዶ ቅላጭ የቀዘቀዘውን ውሃ በእጃቸው ላይ አፈሰሰ:: ሼህ አፍታዴ ጠየቁ:- «ሁዳይ፤ ይኸን ውሃ የት አሞቅኸው?» ሁዳይም መለሰ:- «በልቤ ምድጃ ላይ...» በፍቅር የሞቀ ልብ እንዲህ ነው::

ወደራቢያ እንሻገር:: ራቢያ አገልጋይዋን ጠርታ ጠየቀችው:- «ወደምናፈቅረው አምላክ ማን ይወስደናል?» አገልጋይዋም መለሰ:- «ራቢያ ሆይ! ይኸ ዓለም ነጥሎን እንጂ ውዳችንማ ከእኛ ጋር ነው::»

በሌላ ቀን ራቢያ ተጠየቀች:- «እግዚአብሔርን ትወጃለሽ?» ራቢያም አለች:- «በጣም እወዳለሁ::»

«ዲያብሎስን ትጠያለሽ?»

«አልጠላም» አለች ራቢያ::

«እንዴት ዲያብሎስን አትጠይም...» ሼሁ ይመስሉኛል የጠየቋት::

«ጊዜዬ በሙሉ እግዚአብሔርን ለማፍቀር የተሰጠ ስለሆነ ዲያብሎስን

የምጠላበት ትርፍ ጊዜ የለኝም» አለች::

አንድ ልጨምር:: ራቢያን ወዳጇ ጠየቃት:- «ነቢይ አሁን ብታ ገኚ እንዴት ነው የምታፈቅሪው?»

ራቢያም አለች:- «በጣም የምወደው ይመስለኛል:: የፈጣሪ ፍቅር ግን እሱ ከፈጠረው ፍቅር ሁሉ ፊቴን አዙሮታል» አለች::

የሱፊ ነገር ይጣፍጣልና እንቀጥል:: አንድ ሰው ከአንዲት ወጣት በፍቅር ይወድቅና ቀንና ሌሊት አእምሮው በእሷ ሃሳብ ይያዛል:: ጭንቀቱም ያይልና ዕለት ዕለት ሲከታተላት ሰንብቶ አንድ ቀን ተሳክቶለት በመንገድ ላይ ለብቻዋ ያገኛታል:: በመንገድ ላይም አስቁሞ ከምንምና ከማንም በላይ እንደሚወዳት ለእሷ ያለው ፍቅርም የማይሞትና የማይጠፋ መሆኑና መናገር ይጀምራል::

ወጣቷ የሰውዬውን የፍቅር ልመና ለጥቂት ጊዜ በትዕግስት ሰምታ አቋረጠችውና ጥያቄ ወረወረችለት:- «ቃላትህ ይጥማሉ፤ ነገር ግን እነዚህን የፍቅር ቃላት ለእህቴ ወርውርሃቸው ቢሆኑ ኖሮ እንዴት ጥሩ ነበር:: እህቴን ብታያት ከእኔ በላይ እጅግ የተዋበች ቆንጆ ናት፤ ከእኔም በላይ እንደምታፈቅራት አልጠራጠርም፤...» አለች::

አፍቃሪው ሰውዬ ይኸን ሲሰማ እህቷን ለማየት ፊቱን ወደኋላ አዞረ:: ይኸን ጊዜ ወጣቷ በእጇ ጅርባውን መታ መታ አደረገችው:- «ለእኔ ያለህ ፍቅር የማይጠፋና የማይሞት ነው ስትለኝ አልነበረምን? ነገር ግን አሁን በነገርኩህ እንኳን ፊትህን አዞርክብኝ:: የምትናገረውን ፍቅር ትርጉሙንም አታውቀውም?» ወጣቷ መንገዷን ቀጠለች:: ስለሰውዬው አላውቅም::

የባህሉልን ፍቅር ደግሞ እንመልከት:: አታር ስለባህሉል ይነግረናል:: ባህሉል በእግዚአብሔር ፍቅር ነደደ፣ ተቃጠለ:: ማፍቀር ለባህሉል ሌላውን ነገር ማሰብ አቁሞ ስለሚያፈቅሩት ነገር ብቻ ማሰብና በዚያም መኖር ነው:: ባህሉል ደግሞ እግዚአብሔርን አፍቅሯል:: ስለእሱ የነበረው ፍቅር አንድ ቀን ለየለት:: ሥራውን ለቀቀ፤ ከቤተሰቡ ተለየ፤ ለብቻው



Scanned by CamScanner

መኖር ጀመረ:: የባህሉልን ዓላማ የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ነበር:: ስለራሱ ደህንነትም መጨነቅና ማሰብ አቆመ:: ምነው ቢሉት «ስለራሴ ማሰብ ከጀመርኩ ስለእግዚአብሔር የማስብበትን ጊዜ ይሻማብኛል» አለ:: ለዚህም ነው ልብሱ ተቀዳደ፣ ገርጥቶና ከስቶ የምናየው:: «ስለእግዚአብሔር ሳላስብ ያሳለፍኩት ጊዜ ሁሉ የባከነ ጊዜ ነው» አለ:: ማፍቀር እንደባህልሉ ተባለለት::

ሼህ ሙዛፊር ስለፍቅር ሲናገሩ:- «የፍቅር ቦታው ልብ ነው፤ ልብ ደግሞ ንፁህ ወርቅ ነው:: እግዚአብሔር በመለኮታዊ ልቡ ያነጠረውና ያብረቀረቀው ወርቅ ቢኖር ልብ ነው:: የውበት የፍቅር ፀዳል የሚንፀባረቀው በልብ መስታወት ነው:: ነፀብራቁ ደግሞ በእግዚአብሔር ፍቅር ይገለፃል...::»

ፍቅር ቤቱን የሠራበት ልብ የታደለ ነው ይላሉ ሱፊዎች:: ፍቅር ከዓለም ጭንቀት ሁሉ ማረፊያው ነውና:: ፍቅር የያዘው ሰው ስለራሱም መጨነቅ ያቆማል:: የተራራ ክምር ለእሱ እንደገለባ ብናኝ ነው:: አፍቃሪን ስለ ማፍቀሩ ብትነቅፈው ማፍቀሩን ይጨምራል::

ሼህ ሙዛፊር ይኸን ነገሩን:- «የካሊፍ ሀሩን አል-ራሺድ ዕቁባት በጣም ግልፅና እውነተኛ አፍቃሪም ነበረች:: ካሊፍ ይኸን ለመፈተን ተነሣ:: ዕቁባቶቹን ሁሉ አንድ ቀን በቤቱ ሰበሰበ:: ካዝናውንም ከፈተ፤ የምትፈልጉትን መርጣችሁ ውሰዱ» አለ:: ከዚያች ዕቁባቱ በቀር ሁሉም ካዝናው ላይ ሰፈሩና የቻሉትን ወሰዱ:: ካሊፍ ፊቷን ወደእሷ አዞረ:: ከቆመችበት አልተነቃነቀችም:: «አንቺስ ለምንድነው የማትወስጂ?» አላት:: «ወደአንተ የምመጣው ስለማፈቅርህ ነው:: ዋጋዬ ደግሞ የአንተ ሀብት ሳይሆን የልብህ ፍቅር ነው:: የምፈልገውም የአንተን ልብ ብቻ ነው» አለች:: ካሊፍም ሰጣት::



Scanned by CamScanner

# በፍቅር ውስጥ የሚመር ነገር የለም

ዳግም ከሱፊዝም ጠበል እንረጫለን:: የመጀመሪያው የምድራችን ነቢይ አዳም ነው ይላሉ:: እግዚአብሔርም አዳምን ጠርቶ «ለፈጠርኳቸው እንስሳት በሙሉ ስም አውጣላቸው» አለው:: አዳምም ያለአንድ ችግር ስም አወጣ:: የምድርን እንስሳ ሁሉ ስም ያወጣው አዳም ነው:: የእግዚአብሔር የጥበብ ዘር በውስጡ ስለነበር አልተሳሳተም:: እኛም ስንፈጠር እንዲሁ ተዘርቶብናል:: «የምንፈልገውንም ሆነ የምንመኘውን በዚያ ዘር ውስጥ እናገኘዋለን» ይላሉ ሱፊዎች::

ለሱፊዎች ኢየሱስ እግዚአብሔር የላከው ታላቅ ነቢይ መሆኑን ይቀበላሉ፤ ለዚህም ነው የእግዚአብሔር መንፈስ ብሎ የሚጠራው:: ይሁንና የእግዚአብሔር መለኮታዊ መንፈስ ደግሞ በፈጠረው ሰው ሁሉ ላይ ይገኛል:: ያ መንፈስ ከአዳም ተጀምሮ እስከዛሬ ድረስ አለ:: መንፈሱ በሙላት የሚገለጠው ግን በነቢያትና መለኮታዊ ሥልጣን ባላቸው ሰዎች ውስጥ ብቻ ነው... «ይኸንንም ማወቅ ተገቢ ነው» ይላሉ ሱፊዎች::

ሱፊዎች ኢየሱስን የሚወዱትን ያህል ለሙሴም ታላቅ ፍቅርና ክብር አላቸው:: እንዲያውም ከእግዚአብሔር ጋር የተነጋገረ ታላቅ ነቢይ ነው ይሉታል:: አንድ የሱፊዎችን ጥንታዊ ታሪክ እንመልከት:-

አንድ ቀን የእስራኤል ልጆች ወደ ሙሴ ተሰብስበው መጥተው



Scanned by CamScanner

እግዚአብሔርን እራት ሊጋብዙት እንደሚፈልጉና ይኸንኑም እንዲነግርላቸው ሙሴን ጠየቁት:: በዚህ የድፍረት ጥያቄ የሙሴ ቁጣ ነደደ:: «እግዚአብሔር የሰውን ምግብ አይመገብም፤ ወደእናንተ የራት ግብዣም አይመጣም» አላቸው:: የእስራኤል ልጆችም እያዘኑ ተመለሱ:: በነጋታው ምሽት ላይ ሙማሴ እንደለመደው ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር ወደተራራ ወጣ:: በተራራው ጫፍ ላይ ሲደርስ እግዚአብሔር ቆሟል::

እግዚአብሔርም «ባሪያዎቼ የእራት ግብዣ አድርገውልኝ ለምንድነው አሳፍረህ የመለስክብኝ...» በማለት በሀዘኔታ ጠየቀው:: ሙሴም «ጌታ ሆይ! የሰው ምግብ አትበላም ብዬ ነበር:: እንዲህ ዓይነቱን የሞኝ ግብዣም አትቀበልም የሚል እምነት አድሮብኝ ነው...» አለ:: እግዚአብሔርም አዘዘው:- «ሂድና ለሕዝቤ ንገረው:: ነገ ማታ ለእራት እመጣለሁ፤ ግብዣቸውንም ተቀብያለሁ...::»

ሙሴም በሌሊት ወደሕዝቡ ተመልሶ እግዚአብሔር የእራት ግብዣቸውን እንደተቀበለ አበሰራቸው:: «ማታ እራት ከእናንተ ጋር ነኝ፤ ተዘጋጁ ብሏል» አላቸው:: ሕዝቡም ድግሱን ማዘጋጀት ጀመሩ:: በእስራኤል ምድር ታላቅ የተባለው ግብዣም ተዘጋጅቶ መሰናዶው ወደመጠናቀቁ በተቃረበበት ሰዓት አንድ በረሃብ የከሳና የጠወለገ ሽማግሌ ድንገት ወደድንኳኑ ደጃፎ ተጠግቶ «እባካችሁ ተርቤአለሁ... ከድግሱ የምበላው ትንሽ ስጡኝ...» በማለት ልመና አቀረበ:: ሕዝቡ ግን እያዳፉና እየጮኹ አስወጡት... «እኛ የደገስነው ከእግዚአብሔር ጋር ለመብላት ነው...» በማለት አባረሩት::

የዚያን ቀን ማታ እግዚአብሔር ሳይመጣ ቀረ:: ሙሴም እጅግ አፈረ፤ ብዙዎቹም ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋግሬ መጣሁ የሚለን ሐሰት ነው በማለት ጠረጠሩት:: በነጋታው ምሽት ላይ ሙሴ በሲናይ ተራራ ወጥቶ እግዚአብሔርን መጠበቅ ጀመረ:: እግዚአብሔርም በሰዓቱ መጣ:: ሙሴም በሐዘን «ጌታ ሆይ! የራት ግብዣቸውን እንደተቀበልህ ለሕዝብህ ነግሬ ነበር... አንተ ግን ቀርተህ አሳፈርኸኝ...» አለ:: እግዚአብሔርም



Scanned by CamScanner

«ሙሴ! በራት ግብዣችሁ ላይ ቀድሜ ነበር የተገኘሁት፤ ነገር ግን ገፍትራችሁ አባረራችሁኝ» አለ:: ሙሴም:- «እኛ ያባረርነው ደሃ ሽማግሌ ነው፤ ሌላ ያባረርነው ሰው የለም» አለው... እግዚአብሔርም ጠየቀው:- «ያን ደሃ ሽማግሌስ ማን ፈጠረው?» ሙሴም «አንተ ነህ ጌታ ሆይ!» በማለት መለሰ:: ይኸን ጊዜ እግዚአብሔር:- «ታዲያ በፈጠርኩት ውስጥ መኖሬን ትጠራጠራለህ?» አለው:: ሙሴ አላስተባበለም:: ከታናናሾቹ ለአንዱ የአደረጋችሁት ለእኔ እንዳደረጋችሁት እቆጥረዋለሁ እንደማለት ነው::

እንግዲህ ሱፊዎች እዚህ ላይ ይመክራሉ:- «አገልጋይህን ስትወድ የአንተ ጆሮ የእግዚአብሔር ይሆናል፤ ስለዚህም በአንተ ውስጥ እሱ መስማት ይጀምራል:: አይንህም የእግዚአብሔር ይሆናል፤ በአንተ ዓይን እሱ ማየት ይጀምራል:: አንደበትህ የእግዚአብሔር ይሆናል፤ በአንተም ምላስ እሱ ይናገራል» ይላሉ:: አንድ የተቀደሰ ሱፊ ከአንዲት ሴት ጋር በመንገድ ላይ ተገናኝና ይኸን ጠየቃት:- «የፍቅር መጨረሻው ምንድነው?» እሷም መለሰች:- «...ፍቅር መጨረሻ የለውም::» ሱፊው ዳግመኛ ጠየቃት:- «ለምን?» እሷም በመልሷ አስደነቃቸው:- «ምክንያቱም እግዚአብሔር መጨረሻ የለውምና!!»

ሱልጣን መሐመድ እጅግ አድርገው የሚወዱትን አገልጋያቸውን አያዝን አንድ ቀን ወደገበታቸው በመጥራት ከፊታቸው ከተቀመጠው ፍሬ አንዱን አንስተው ሰጡት:: አያዝም ከሚወደው ጌታው እጅ የተቀበለውን ፍሬ በልቶ እንዳጋመሰ ሱልጣኑ ሌላ ፍሬ አንስተው አንዴ ገመጡና ትንሽ አኝከው ተፉት::

በመገረምም ወደ አያዝ እየተመለከቱ:- «እንዲህ ዓይነት መራራ ፍሬ እንዴት ተበላልህ?» አሉት::

«የምወድህ ሱልጣን ሆይ» አለ አያዝ «የጣፈጠኝ ፍሬው ሳይሆን የሰጠኝ እጅህ ነው» በማለት መለሰ:: በፍቅር ውስጥ የሚመር ነገር የለም::



Scanned by CamScanner

ማንሱር አል ሀላጅ በሕዝብ ፊት እንዲገደል ሲፈረድበት የሠራውም ወንጀል በአደባባይ ተነገረ:: ይኸውም «እኔ እውነት ነኝ» በማለት ሰብኳል የሚል ነበር:: እውነት ደግሞ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ስለዚህም ራሱን ከአምላክ ጋር አወዳድሯል ተባለና ተገደለ... የተቀደሱት ጁናይድ (ሶፊ ናቸው) ይኽን ሲሰሙ አዘኑ:: «ጁናይድ ሆይ! እኔ እውነት ነኝ ብሎ ከመስበክ ውጭ ምን ኃጢአት ይኖራል?» ተብለው ተጠየቁ:: ጁናይድም መለሱ:- «ከዚያ በላይ ኃጢአትማ 'እኔ ሐሰት ነኝ' ብሎ መስበክ ነው» አሉ::

ወደሙሴ እንመለስ:: ሱፊዎች ስለሙሴ በፃፉት ሌላ ታሪክ አንድ ቀን ብቻውን በጫካ ውስጥ ሲሄድ አንድ ጎልማሳ ለእግዚአብሔር እየፀለየና እየሰገደ አገኘው:: ምን እያደረገም እንደሆነ ጠየቀው:: ጎልማሳውም:- «የእግዚአብሔርን እጅ እየሳምሁ፣ መጎናፀፊያውንም እያጠብሁና ፀጉሩን እያበጠርሁ ነው» አለው:: ሙሴም በዚያ ጎልማሳ የድፍርት ንግግር ተናዶ ከቦታው አባረረው... በምሽት ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘ ት ወደተራራው ወጣ:: እግዚአብሔርም በቁጣ ተቀበለውና «ሙሴ! በእውነት ከልቡ ያመልከኝ የነበረውን ጎልማሳ ዛሬ ከቦታው ስላበረርክብኝ ተቆጥቻለሁ... ከእነዚያ ስለእኔ ሲያወሩ ከሚውሉት ሊቃውንትና ጠበብቶች ይልቅ እሱ በጣም ለእኔ የቀረበ እንደነበር አታውቅምን?» አለው:: ሙሴ በድርጊቱ አዘነ:: በነጋታው ያንን ጎልማሳ ፍለጋ ሙሴ ወደጫካው ወጥቶ ሊያገኘው ባለመቻሉ እያዘነ ወደከተማ ተመለሰ:: ያን ጎልማሳም ከሊቃውንት ጋር በከተማ ቆሞ አገኘው::

በሱፊዎች የመጨረሻ ምክር ለዛሬ ልሰናበት:: ሱፊዎች ከማንም በላይ ኃጢአትን የፈፀመ ሰው ነው የሚሉት ጊዜውን በከንቱ የሚያባክነውን ነው:: ለዚህም ነው ሱፊዎች:- «ከሚባክን ጊዜ በቀር ለኃጢአት ሁሉ ይቅርታ አለው» የሚሉት:: የአበሻ ንስሐን ውሃ በላው::



Scanned by CamScanner

# እግዚአብሔርን ስታምን እንደእሱ ማሰብ ትጀምራለህ

ከብዙ ዓመታት በፊት የምድራችን የሥልጣን ቁንጮ የኦቶማን ኤምፓየር ነበር:: አንድ ቀን የኢምፓየሩ ሡልጣን ታላቁን የኢስታንቡል ሼህ ሊጐበኝ ይመጣል:: ሼሁ ሱፊም ለተወሰኑ ቀናት በትምህርታቸው የሡልጣኑን አንጐል መጐብኘት ይጀምራሉ:: ሡልጣኑ በሱፊዎች ዕውቀት ተማረከ:: በመሸ በጠባም መመለሻው የሼሁ ደጅ ሆነ:: ከጥቂት ወራት ያለማቋረጥ መመላለስ በኋላ ሡልጣኑ አንድ ጥያቄ አቀረበ:- «የእርስዎን ደጃፍ ከረገጥኩ በኋላ በትምህርትዎና በጥበብዎ ተማርኬ ፍቅር አድሮብኛልና በአቅሜ ለማድረግ የምችለውን ይንገሩኝና ላድርግ...» ይላል:: ሼሁም ጥቂት አሰቡና:- «ከእንግዲህ ተመልሰህ ወደዚህ አትምጣ...» አሉት::

በዚህ ያልተጠበቀ መልስ ሡልጣኑ በጣም ደነገጠና ያጠፋው ወይም ያስቀየማቸው ነገር እንዳለ ጥያቄ አቀረበ:: ሼሁም:- «በፍፁም!» አሉት:: «ታዲያ ምን አጥፍቼ ነው የሚያባርሩኝ...?» አለ ሡልጣኑ:- «ያባረርኩት አንተን ሳይሆን እዚህ የማስተምራቸው ተማሪዎቼን ከንቱ ሐሣብና ምኞት ነው:: አንተ ወደዚህ ከመጣህበት ቀን ጀምሮ መጠበቃቸውን ከእግዚአብሔር ወደ አንተ አዙረዋል:: የእግዚአብሔርን ስጦታ እስክናውቅ ድረስ የአንተ ስጦታ ይቅርብን» አሉት::

የሱፊዎች የጥበብና የእውቀት ብርታት ዛሬም በዓለም ላይ ላቅ ብሎ የሚጠቅስና የሚነገር ነው:: ከወዳጄ ስጦታ የቃረምኩትን በመጠኑ ልበትን::

የሱፊዎች መንገድ ከዓለም የመሸሽና የመራቅ አይደለም:: ይልቁንም በዓለም ውስጥ እየኖርክ በመለኮታዊው ነገር ውስጥም በርትተህ መኖርን ማሳየት እንጂ:: በዓለም ነገር ስትጠመድ ለመንፈሣዊ ዕድገትህ፣ ፍቅርን ለመለማመድ፣ ለንቃትህ፣ ለሊጋስነት... ዕድልን ይከፍትልሃል ይላሉ:: ሼህ ሙዛፊር የሱፍ መምህር ናቸው:: እንዲህ ይላሉ:- «በዓለም ውስጥ ስትኖር እጅህ ለሥራ ልብህ ደግሞ ለእግዚአብሔር ይበርታ::»

እግዚአብሔር እጅን የሠራበት ዋነኛ ምክንያት ሼህ ሙዛፊር ሲነግሩን:- «የወደቁትን ደግፎ ለማንሣትና የሚያለቅሱትን ዕንባ ከፊታቸው ላይ ለማበስ ነው» አሉ:: ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ነገርም አለ ይላሉ:- «የሚያፅናኑ ቃላት የተሞላ ምላስና በርኅራኄ ማየት የሚችል ዓይን...»

የእምነት አባት አብርሃም አንድ ቀን የጐረቤቱን አዛውንት እራት እንዲመጡ ይጋብዛቸዋል:: ይኸን ግብዣ የሰማ ሌላ ሰው አዛውንቱ በእግዚአብሔር እንደማያምኑ ለአብርሃም ይነግረዋል:: የአብርሃም ድንጋጤ አይነገርም:: ሲሮጥ ወደ አዛውንቱ ቤት ይሄዳል:: «በማዕዴ እግዚአብሔርን ከማያምን ሰው ጋር መቀመጥ ስለማይገባኝ የእራት ግብዣውን ሰርዤዋለሁ...» አላቸው:: አዛውንቱ እንደአማራቸው ቀረ:: በነጋታው እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገለጠና ጠየቀው:- «አዛውንቱን እራታቸውን አበላህልኝ?»

አብርሃም አይዋሽም:- «በአንተ የማያምኑ ስለሆኑ አላበላኋቸውም...» አለ::

እግዚአብሔርም አለ:- «እኔ ግን ላለፉት ሰባ ዓመታት ለአንድም ቀን ሳላጓድል መግቤያቸዋለሁ:: በእኔ እንዲያምኑ ግን አልጠየቅኋቸውም ነበር...»



Scanned by CamScanner

አብርሃም ደነገጠ፣ አፈረም:: ከዚያን ቀን ጀምሮም በእግዚአብሔር ማመን ማለት እንደ እግዚአብሔር ማሰብ እንደሆነ ተገለጠለት::

ሼህ ሙዛፌር ደግሞ ሌላ ታሪክ ይነግሩናል:: ሰውዬው በአብዶች ሆስፒታል ደጃፍ ሲያልፍ አንዱን እብድ መስኮት ላይ ተንጠልጥሎ ያየውና ጥያቄ ወረወረ:- «በሆስፒታሉ የምትኖሩ ዕብዶች ስንት ትሆናላችሁ?» መስኮት ላይ የተንጠለጠለው ዕብድ ግራ ተጋባና እሱም ጥያቄ ወረወረ... «ከሆስፒታሉ ውጭ ከምትገኙትስ ስንቶቻችሁ ጤነኞች ናችሁ?» የመጀመሪያው ጠያቂ ማበዱን የዚያን ቀን አወቀ::

ተማሪው ወደሱፊ መምህር መጣና የሚተኛበት እንደተቸገረ ነገራቸው:: ሱፊው በተማሪው ጥያቄ ተደነቁና ጠየቁት:- «ከምን እንደተሰራህ አስተምሬህ ነበር?» «አዎን መምህር ሆይ ከአፈር ነው» አለ:: «ታዲያ የተሰራህበትን ከለበስከው በእሱ ላይ መተኛት እንዴት ያስፈራሃል?» አሉት:: ተማሪው ሊተኛ ሲሄድ፤ ሱፊውም ወደአልጋቸው አቀኑ::

የሼህ ሙዛፌር ጣፋጩን ታሪክ ልጨምር:: ሡልጣን ሙስጠፋ ሦስተኛ የሱፊውን ቅዱስ ወደቤተመንግሥታቸው ይጠሩና ጥያቄ ይሰነዝራሉ:- «የዚህ ዓለም ደስታ ምንድነው?» የሱፊው ቅዱስም:- «መብላት፣ መጠጣትና መፍሳት» ነው ይላሉ:: በዚህ ንግግራቸው ሡልጣኑ ይናደዱና በአሽከሮቻቸው እያስገፈተሩ ያስወጧቸዋል:: ይኸን ጊዜ የሱፊው ቅዱስ በልመና አንድ ጊዜ ሡልጣኑን እንዲያናግሩ ይጠይቃሉ:: ሡልጣንም ይፈቅዱና ያቆሟቸዋል:: የሱፊው ቅዱስም «የተከበርከው ሡልጣን! የተናገርኩት እውነት መሆኑን ታውቅ ዘንድ ትበላለህ፣ ትጠጣለህ ነገር ግን አትፈሳም» በማለት ረገሟቸው:: የሱፊውም ቅዱስ እየተገፈተሩ ወጡ::

አንድ ሣምንት አለፈ:: ሡልጣኑ ይበላሉ፣ ይጠጣሉ... የሚወጣ ነገር ግን የለም:: ይልቁንም ሆዳቸው እየሰፋ፣ እያደገ... ነጋሪት አከለ:: የሡልጣኑ ስቃይ በባሰበት ወቅት የሱፊው ቅዱስ ተጠርተው መጡ::



Scanned by CamScanner

ሡልጣኑም:- «አጥፍቻለሁ፣ ይቅርታ ያድርጉልኝ» አለ:: የሱፊው ቅዱስም:- «ይቅርታ የማደርግልህ መንግሥትህን ከሰጠኸኝ ብቻ ነው» አሉ:: ሡልጣኑም ከስቃዩ ከገላገሉት መንግሥቱን እንዲወርሱ በቃሉ አረጋገጠላቸው:: የሱፊው ቅዱስ የሡልጣኑን ሆድ በእጃቸው ጠሰቁት:: ሡልጣኑ አንድ ጊዜ ፈሳና «እፎይ!» አለ:: ይኸን ጊዜ የሱፊው ቅዱስ ተናገሩ:- «አላመንከኝም እንጂ አስቀድሞም ነግሬህ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥትህን በፈስህ ለወጥህ» አሉት:: የመጀመሪያው የሱፊ ንጉሥም የዚያን ዕለት ተገኘ::

ጠቢቡ ሞኝ ባህሉል በመንገድ ላይ ከሀሩን አል-ራሺድ ጋር ይገናኝና ከየት እንደሚመጣ ይጠይቁታል:: ባህሉልም:- «ገሃነም ደርሼ እየተመለስኩ ነው» አላቸው::

በባህሉል መልስ የተገረሙት ሃሩን:- «ገሃነም የሚወስድ ምን ጉዳይ አጋጥሞህ ነው» አሉት:: ባህሉልም «እሳት አስፈልጉን ትንሽ ለመጠየቅ ብሄድ የገሃነም አለቃ እዚህ እሳት የለም በማለት መለሰኝ» አላቸው:: ሃሩንም በመገረም:- «ቦታ ተሳስተህ ካልሆነ በቀር እንዴት ገሃነም ሄደህ እሳት የለም ትባላለህ?» አሉት:: ባህሉልም:- «እርግጠኛ ነን ጌታዬ! በገሃነም እሳት የለም:: ነገር ግን ወደዚያ የሚሄድ እያንዳንዱ ሰው የራሱን እሳት እየያዘ ነው የሚገባው...» አላቸው::

ባያዚድ ቢስታሚ ከሱፊው መምህር እግር ስር ተቀምጦ ሳለ በድንገት መምህሩ:- «ባያዚድ! ሂድህ ከመስኮቱ ላይ መጽሐፌን አምጣልኝ» አሉት:: ባያዚድም ከመምህሩ ላይ አትኩሮቱን ሳይነቅል «ከየትኛው መስኮት መምህር?» በማለት ይጠይቃል:: «እዚህ ቤት ለአንድ ዓመት ያህል ስትመላለስ የቤቱን መስኮት አይተህ አታውቅም?» አሉት መምህሩ በመገረም:: «አዎን መምህር ሆይ! እዚህ ቤት ስገባ አትኩሮቴ እርስዎ ላይ እንጂ ሌላ ነገር ላይ ስላልሆነ መስኮቱን አይቼው አላውቅም...» አላቸው:: መምህሩም:- «ልትማረው የመጣኸው ሱፊዝምም ይኸው ነው... ወደምትሄድበት ብቻ መመልከት:: ከእንግዲህ ትምህርትህን



Scanned by CamScanner

ጨርሰሃል» በማለት አሰናበቱት::

በሱፊዝሞች ምርጥ አባባል ልሰናበት:- «መሪ ሳይኖረው የሚሄድ ተጓዥ የሁለት ቀኑን መንገድ በሁለት መቶ ዓመት ይጨርሰዋል...::»



Scanned by CamScanner

# «ኢየሱስ ክርስቲያን አልነበረም...»

"Jesus was not a Christian; He was a Jew"

Wellhasen

ታላላቅ ፈላስፎች በፍልስፍናቸው ውስጥ ሰፊ ቦታ ሰጥተውት የምናገኘው እምነት የክርስትና እምነት ነው:: በተለይም ደግሞ እምነቱ ከዚህ ዓለም በኋላ ስለሚጠብቀን የገሃነም እና የገነት ዘላለማዊ ሕይወት በማንሳት ይዞት የምናገኘውን የሰውን ልጅ «ሲሆን የማጓጓት ሳይሆን ደግሞ የማስፈራራትን» ተገቢነት በትልቅ የጥያቄ ምልክት አስቀምጠውታል::

በፍልስፍናው ዓለም ታላላቅ የሆኑት ፈላስፎች ክርስትና ከሁለት ነገሮች የመጣ እምነት እንደሆነ ይገልፃሉ:: የመጀመሪያው ከረዳት አልባውና ተስፋ ቢሱ ደሃው ክፍል (ወዛደሩ) እና በጊዜው በእየሩሳሌም፣ አሌክሳንደሪያ፣ አንፃኪያ፣ አቴንስና ሮም ተስፋፍቶ ከነበረው የኢንዱስትሪና የንግድ ብዝበዛ ጋር የተያያዘ ነው ሲሉ፤ ሁለተኛው ደግሞ የአይሁዱ ሞራላዊ እሴት ከግሪክ የፍልስፍናና የሥነ መለኮት ሐሣቦች ጋር የመቀላቀሉ መንስዔ ነው ይላሉ::

ዊል ዱራንት "The Pleasures of Philosophy" «የፍልስፍና ደስታ» በሚለው መጽሐፉ እንደሚያነሳው ከሰለሞን ጊዜ ጀምሮ እየሩሳሌም



Scanned by CamScanner

ከፐርሺያ፣ ከኤስያ፣ ከባቢሎን እንዲሁም ከሌሎች ሃገሮች ጋር በነበራት የንግድ ቁርኝት የሕዝቧ ኑሮ በልዩነት ደረጃ እጅግ የተራራቀ እንደነበር በተለይም በሃብታሙና በደሃው መካከል የነበረውን ልዩነት የሰማይና የምድር ያህል እንዳደረገው ይዘረዝራል::

የዘመኑ የግሪክና የሮማ ወራሪዎችም አይሁዶችን በመውረር የአይሁድን አብዛኛውን ዘር በባርነት እንደገዙት ዱራንት በመጽሐፉ ይነግረንና «በተለይም በባቢሎን ምድር በባርነት የነበሩት የአይሁድ ተገርዎች እጅግ በድህነትና በመከራ ሕይወት የተዘፈቁ» እንደነበሩ ይገልፃል::

ኢየሱስ በተወለደበት ዘመን ናዝሬት በሮማውያኖች እጅ ለባርነት ተሸጣ ነበር:: በዚህ የመከራና የድህነት ሕይወት ውስጥ የነበረው የአይሁዱ ዘር ገዥዎቹን የሚቃወምበት አዲስ እምነት ማስፋፋት ጀመረ:: ዱራንት በመጽሐፉ እንደሚገልፀው በተለይም ይህ እምነት ደሃው በዚህ ዓለም ቢሰቃይም በሌላ አዲስ ዓለም (ከሞት በኋላ) እንደሚካስ የሚያሳምን ነበር:: (የደሀው አልዓዛርን ታሪክ ልብ ይሏል)::

በድህነትና በመከራ ሕይወቱን ለሚገፋው ሕዝብ «ቅንና ትሁት ልብ ከያዛችሁ የገነትን ተስፋ ወራሾች እናንተ ናችሁ:: ዘላለማዊ ሕይወትም ይጠብቃችኋል፤ በዚያም ትካሳላችሁ» የሚለው እምነት ከምንም በላይ መጽናኛው ሆነለት::

እንግዲህ እዚህ ላይ ነው እንደ ኒች ዓይነቱ ፈላስፋ ይነሳና «የዘመናዊው ክርስትና ትልቁ የታክቲክ ችግር ይኸ ነው» ይለናል:: «ይኸውም ክርስትና ለደሃው የተሰጠና የመጣ እምነት ሆኖ እያለ እንዴት በሃብታሙ ክፍል ላይ ጥገኛ ሆኖ መኖር እንደሚችልና እንዴት መስማማት እንደሚቻልም አለማወቁ ላይ ነው:: ምክንያቱም ክርስትና ለደሃው የመጣ እንጂ የዘመኑን ሃብታም አይመለከትምና» ይላል::

እንግዲህ ከዚህ መሠረተ ሃሳብ ተነስቶ «ኮሚኒዝምና ኢየሱስን ማየት ይገባል» የሚለን ዱራንት «ለነገሩማ የኢየሱስ ኮሚኒስትነት



Scanned by CamScanner

ጥያቄም የሚገባው አይደለም» ይለናል:: ምክንያቱም በምድር ላይ የሚገኝ አስፈላጊው ነገር ሁሉ ለሰው ልጅ ይገባል፤ ሃብታሙም ለደሃው ያለውን ሁሉ ያካፍል ወዘተ. እንደሚለው ማለቱ ሲሆን ኒች ደግሞ «ኢየሱስ በዚህ ዘመን ኖሮ ቢሆንማ ሳይቤሪያ ይላክ ነበር» ይለናል::

ፈላስፎች የማይክዱት አንድ ሐቅ ማንም የኢየሱስን ታሪክ ያነበበ ሃብታም ይሁን ደሃ፤ በእሱ ታሪክ መወሰዱ የማይቀርና በተለይም በታሪክ ውስጥ እንደ ኢየሱስ ማራኪ (appealing figure) አለመኖሩን ነው:: «የሚያሳዝነው ግን» ይላሉ ፈላስፎች «ምንም እንኳን የግድ ቢሆን ይህን የመሰለ ታላቅ አስተማሪ በየዕለቱና በየጊዜው ከሚያልፈውና ከሚጠፋው እንዲሁም ከሚለዋወጠው የቤተክርስቲያንና የሥነ መለኮት እምነት ጋር መቆራኘቱ ነው» ይላሉ::

እዚህ ላይ ፈላስፎች የሚናገሩትን አንድ ታሪክ ማንሳት ተገቢ ይሆናል:: በ1830 እ.ኤ.አ በኬንተኪ (አሜሪካ) አንድ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እየተናገረ መጣ:: በብዙ ሺህ የሚቆጠሩም አመኑት፤ የራሱን ወንጌልም በሰፊው አሰራጨ፤ ብዙዎችም ተቀበሉት:: ይህንኑ ወንጌሉን ሊያሰራጭ ጀርመን በገባበት ወቅትም ስብከቱን በእንግሊዝኛ ቋንቋ ጀመረ፤ የብዙዎች ችግር ታዲያ ጀርመንኛ እንጂ እንግሊዝኛ ቋንቋ አለማወቃቸው ነበር:: ነቢዩም ጀርመንኛ ቋንቋ አለማወቁን በተናገረ ጊዜ በዙሪያው ከተሰበሰቡት አንዱ «የእግዚአብሔር ልጅ ሆነህ ጀርመንኛ ቋንቋ እንኳን አታውቅም?» በማለት ጮኸ:: የኬንታኪው ነቢይም ጉዳይ በዚያ ላይ አበቃ::

«ሃይማኖት በድሆች በኩል ተወልዶ በሃብታሞች መካከል የሚሞት ነው» የሚሉን ፈላስፎች «የቱንም ያህል ኢየሱስ የላቀ መምህር ቢሆን በሰው ልጅ አቅምና ችሎታ ሲመዘኑ ለመቀበል የሚከብዱ እምነቶችን ሰጥቶአል» ይላሉ:: «ምን እንበላለንና ምንስ እንለብሳለን ብላችሁ አትጨነቁ፤ እነሆ የሰማይ ወፎችን አትመለከቱም...» በማለት የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር የሚለብሰውንና የሚመገበውን ብሎም ሲተወው

የማይችለውን ጉዳይ «ተው» ብሎ ሲያዘው ሊተወው እንደማይችል ጠቃሚ እንዳልሆነ አይደለም ይሉናል:: «ጠላትህን ውደድ» ብሎ ትዕዛዝ መስጠቱ በጭቶት አይደለም ይሉናል:: «ጠላትህን ውደድ» ብሎ ትዕዛዝ መስጠቱ ለዘመናት የነበረውን የሰውን ጭካኔ አይቶ ካልሆነ በስተቀር እንዴትስ ይቻላል?» በማለት ይጠይቃሉ:: እንዲያውም ይህ ትዕዛዝ ያንገበገበው የሚመስለው ኮንፊሺየስ በአንድ ወቅት «ለክፋ ፍርድን ለበጐነት ደግሞ በጐነትን ካልመለስክ፤ የበጐነት ዋጋው በምን ሲመዘን ነው?» በማለት ይጠይቃል:: ክፋትም ደግነትም ዋጋቸው አንድ ከሆነ ክፋትን ለምን አላደርገውም እንደማለት ነው::

በዚህም አለ በዚያ ፈላስፎች በታላቅ ድምጽ የሚሉት አንድ ነገር «ኢየሱስ አይሁድ እንጂ ክርስቲያን አልነበረም፤ ሆኖም አያውቅም» ነው:: እሱን ስትከተል ክርስቲያን ነህ እንደማለት መሆኑም አይደል?

የኢየሱስን ታላቅ አስተማሪነት የማይቀበል አንድ ፈላስፋ በዘመናችን ማግኘቱ ከባድ ነው:: እንዲያውም ብዙዎቹ ታላቅ መምህር ብቻ ሣይሆን ታላቅ ፈላስፋም ነበር ይላሉ:: የዘመናችን ፈላስፋ ዱራንት ይኸችን ታሪክ ይነግረናል:- «ኢየሱስ ዓለምን የሚመስላት እንደአሮጌ አቆማዳ ነው...» አንድ ቀን አሮጌዋን አቆማዳ ጠየቃት:- «ስንት ባሎች አግብተሻል?» አቆማዳዋም መለሰች:- «በቁጥር አላውቃቸውም... እጅግ ብዙ ናቸው...» ኢየሱስም «ከባሎችሽ በፍቺ ወይስ በሞት ነው የተለየሽ?» አላት:: አቆማዳዋም... «ሁሉንም እያረድኩ ገድያቸው ነው!» አለችው:: ኢየሱስም ተደንቆ ይህን ተናገረ:- «የሚደንቀኝ በሌሎቹ ላይ ያደረግሽውን እየተመለከቱ... ዛሬም አንቺን የሚመኙሽ እንዲህ መብዛታቸው ነው»::

ካልተፃፈው የኢየሱስ ታሪክ አንድ ልጨምር:-

አንድ ቀን ኢየሱስ በበረሃ ሲሄድ ተከታዮቹን አገኘና አስቆመው:- «መምህር ሆይ! ሙታንን የምታስነሳበትን ቃል ከነገርከን ለእኛ በቂያችን ነውና እባክህን እሱን ብቻ ንገረን...» በማለት ጠየቁት:: ኢየሱስም:- «ቃሉን ብነግራችሁ እንደማይገባ ትጠቀሙበታላችሁና ይቅርባችሁ» አላቸው:: ተከታዮቹም አሻፈረን በማለት ይወተውቱት ጀመር:: ኢየሱስም



Scanned by CamScanner

ውትወታቸው ሲበዛበት «የምትጠይቁትን ብታውቁ ኖሮ አታስቸግሩም ነበር» በማለት ቃሉን ነገራቸው:: ተከታዮቹም በማግሥቱ ከኢየሱስ ተለይተው በበረሃ ሲሄዱ የአጥንት ክምር ተመለከቱና የተነገራቸውን ቃል የሚጠቀሙበት ሰዓት እንደደረሰ በማመን በአንድነት ቃሉን ተናገሩ::

ቃሉ ከአንደበታቸው እንደወጣ አጥንቶች ተገጣጠሙ፣ ሥጋ ለበሱና ነፍስ ዘሩ:: በቅፅበትም የበረሃ አውሬ ከፊታቸው ቆመ:: አንዳቸውም ማምለጥ ሳይችሉ አውሬው ሰባብሮ ገደላቸው:: ኢየሱስም በተከታዮቹ ላይ የደረሰውን በሰማ ጊዜ ወደቀሪዎቹ ዞረና:- «እግዚአብሔር የሚወደውን ስለሚፈትን አትረበሹ...» አላቸው::



Scanned by CamScanner

# «ገነት ለመግባትህ እርግጠኛ ብትሆን ሞትን አትፈራም ነበር»

ባንወደውም ስለኒች መስማት ያስደስተናል፡፡ አንድ ቀን የእግዚአብሔርን መሞት ሲናገር የሰማች ሴት «ገሃነም እንደምትገባ እርግጠኛ ሆንኩ» አለችው፡፡ ኒችም፡- «ገነት ብቻዬን መግባት ስለማልፈልግ ነው...» አላትና ወደወዳጆቹ ተመለከተ፡፡ «ገነት የሚፈለገው ለአየሩ ፀባይ ብቻ ነው... ከዚያ ውጭ ወዳጆቻችን ሁሉ የት እንዳሉ እናውቃለን...» በማለት ፈላስፎቹን አስደነገጣቸው፡፡ የፈላስፎቹ መደንገጥ ገሃነም ስለሚገቡ አልነበረም፡፡ በድንገት (በስህተት) ገነት የመግባት ዕድል ቢገጥማቸው በብቸኝነት የሚያሳልፉት ሕይወት ታይቷቸው እንጂ፡፡

ዛሬ የገነትና ገሃነምን እሳቤ እንመልከት፡፡ የዜን አጭር ታሪክ በሆነችው "The Gates of Paradise" ውስጥ ያነበብኳት አለች፡-

ኖቡሽጊ ወታደር ነው፡፡ አንድ ቀን ሃኪዊን ጋ መጣና ጠየቃቸው፡፡ ሃኪዊን ታላቅ የዜን እምነት መምህር የገነትና ገሃነም ሚስጥራትንም በሚገባ የተረዱ ናቸው፡፡

«ገነት ወይም ገሃነም የሚባል ነገር አለ?! የመግቢያውስ ቁልፍ ምንድነው?» በማለት ወታደር ኖቡሽጊ ጠየቀ፡፡

መምህሩም፡- «አንተ ማን ነህ!» አሉ፡፡



Scanned by CamScanner

«እኔ ሳሙራይ ነኝ!» አለ እንደወታደርነቱ ተኮስትሮ...

«አንተ ወታደር ነህ!» በማለት መምህሩ ፈገግ አሉና:- «ምን ዓይነት አለቃ ቢኖርህ ነው ታዲያ እንዲህ ለማኝ መስለህ የምትሄድ?» አሉት::

በመምህሩ የንቀትና የዘለፋ ንግግር ወታደር ኖቡሽጊ ተቆጣና ሰይፉን ከሰገባው መዘዘ::

መምህሩ ይበልጥ ፈገግ ብለው:- «እ! ሰይፍም አለህ! ቢያንስ የእኔን አንገት ለመቁረጥ ይብቃ ዘንድ እንኳን ዱልዱም ሰይፍህን ብትስለው ጥሩ ነበር...» አሉት::

ወታደር ኖቡሽጊ ትዕግስቱ አለቀ:: የሰይፉን ስለት በመምህሩ አንገት ላይ ሊሞክር እጁን ከሰይፉ ጋር ወደሰማይ አነሣ:: ይኸን ጊዜ መምህሩ:- «እነሆ! የገሃነም ደጆች ተከፈቱ!» በማለት ጮኹ:: ወታደር ኖቡሽጊ ስለገሃነም አወቀ፤ ሰይፉንም ወደሰገባው መክተት ጀመረ:: መምህሩ ሃኩዊን አሁንም ተናገሩ:- «እነሆ አሁን ደግሞ የገነት ደጆች ተከፈቱ...::»

እንደ ይስሐቅ አሲሞብ ዓይነቱ ታላቅ የምድራችን ፈላስፋ «ከገሃነም ይልቅ የምፈራው ገነትን ነው» ይላል:: ለዚህም ምክንያቱን ሲናገር:- «ገሃነም ውስጥ በእሳት እየተቃጠልክ ስለምትሰቃይ ሌላ ለውጥ ወይም ደግሞ መሰልቸት ትዝ አይልህም... ነገር ግን ገነት ከገባህ ከሳምንት በላይ አትቆይበትም... ይሰለችሃል.... ይታክትሃል:: መከራን ካላወቅህ ደስታን እንዴት ታውቀዋለህ:: ደስታን ደስታ ያደረገው የመከራ መኖር ብቻ ነው:: መከራን ስትረሳ ደስታ ትርጉሙ ይጠፋልና...» የአሲሞብ መደምደሚያ:- «ስለገነትና ገሃነም ሳስብ ወይም ስሰማ ደስታን የሚሰጠኝ የሚጠብቀኝ የገነት አሊያም የገሃነም ሕይወት ሳይሆን ነገር ግን ገነትና ገሃነም የሚባል ነገር አለመኖሩን ይበልጥ እርግጠኛ ስለሚያደርገኝ ነው» ይላል::

አንድ ጣፋጭ የድሮ ታሪክ አለች:: አንድ ጠቢብ ሽማግሌ ሰው ነበር:: ይኸ ሰው በዘመኑ የነበረውን የዕውቀት መጽሐፍ አንብቦና መርምሮ የተረዳ ነበርና በሕዝቡ ዘንድ ተወዳጅነትን ያተረፈ ከመሆኑም



Scanned by CamScanner

ጠላይ ይበልጥ ከበሬታን ያስገኘለት ደግሞ የገነትና ገሃነም ዕውቀቱ እንደነበር ይነገራል:: አንድ ቀን የሃይማኖት መሪና ሰባኪ የሆነ ሰው ከአድካሚ የእግር ጉዞ በኋላ እግር ጥሎት በጠቢቡ ሽማግሌ ሰው ቤት ይደርስና የሚበላው ካለው እንዲሰጠው ይለምነዋል:: ጠቢቡ ሽማግሌም ምግቡን ያቀርብለትና ነገር ግን ለመብላት የሚያቀርብለትን ጥያቄ ይመልስ ዘንድ የግድ እንደሆነ ይነግረዋል::

ሃይማኖተኛውም ዝግጁ እንደሆነ ነግሮት ለጥያቄ ይጋብዘዋል:: ሽማግሌውም:- «ይኸን ምግብ ስትበላ በድሮው፣ በአሁኑ ወይስ በወደፊቱ አእምሮህ ነው የምትበላው?» የሚል ጥያቄ አቀረበለት:: ሃይማኖተኛው ሰው ለጥቂት ጊዜ አሰበ:: መልሱን ለማግኘት አለመቻሉን የተረዳው ሽማግሌው ጠቢብም ምግቡን አንስቶ ወደጓዳ ጉዞ ሲጀምር ሃይማኖተኛው ሰው መልሱን ጠየቀው:: ጠቢቡ ሽማግሌም አለው:- «ሞኝ ነህ! የምትበላው በአፍህ መሆኑን እንኳን ረስተሃል:: የምትበላውን ከአእምሮህ ጋር የሚያገናኘው አንዳች ነገር የለም...» አለው:: ረሃቡ የፀናበት ሃይማኖተኛው ሰው ምንም እንኳን በስንፍናው ቢበሳጭም:- «የተራብኩትን ብትመግብ ገነት እንደምትገባ አታስተውልምን?» አለው:: ጠቢቡ ሽማግሌም «በዚህ ምድር ላይ የማደርገውን የማደርገው በሥጋዬ ብቻ ነው:: ሥጋዬ ደግሞ እዚሁ ፈርሶና በስብሶ የሚቀር ነገር ነው:: ገነት የሚገባው ነፍስ ከሆነ በሥጋ ዕዳ አይጠየቅም... ሥጋ በጥፋቱ ይሞታልና...» በማለት አሰናበተው::

ወደሌላ ታሪክ እንለፍ:: የዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ የኬሚስትሪ ዲፓርትመንት በቅርቡ ለመጨረሻ ዓመት ተማሪዎቹ ያቀረበው ጥያቄ እንዲህ የሚል ነበር:- «ገሃነም ሙቀትን የሚረጭ ነው ወይስ ሙቀትን የሚሰበስብ?»

ብዙዎቹ ተማሪዎች ለዚህ ጥያቄ መልሳቸውን ያስቀመጡት የቦይልስን ሕግ (Boyle's Law) ተመስርተው ነበር:: በቦይልስ ሕግ መሠረት:- «ጋዝ ሲበታተን ይቀዘቅዛል፤ ሲሰበሰብ ደግሞ ይሞቃል»፤



Scanned by CamScanner

አንድ ተማሪ ግን የተለየ መልስ ሰጠ:: የዚህ ተማሪ መልስ ስለገሃነም በቂ ግንዛቤ ይሰጣል፡-

«በመጀመሪያ የገሃነም አባላት በጊዜ ብዛት እንዴት እንደሚለወጡ ማወቅ ይገባናል:: ስለዚህም ወደገሃነም ነፍሳት የሚገቡበትና የሚወጡበትን ፍጥነት ማስላት ያስፈልጋል...

«በእኔ ሐሣብ መሠረት አንድ ነፍስ ገሃነም ከገባ በኋላ ከዚያ ስለማይወጣ «ይወጣል» ብሎ ለማስላት መነሳቱ ትርፉ ድካም ነውና እንተወው...

«ስንት ነፍስ ደግሞ ወደገሃነም እንደሚገባ ለማወቅ በመጀመሪያ ስንት ሃይማኖቶች ዛሬ በምድር ላይ እንዳሉ ማስላት ይገባል... ብዙዎቹ ሃይማኖቶች ደግሞ የእነሱ አባል ካልሆንክ ወደገሃነም እንደምትገባ ይነግሩሃል:: ከዚህ ተነስተን ስናስብ አንድ ሰው አባል መሆን የሚችለው ደግሞ ለአንድ ሃይማኖት ብቻ ነው... ስለዚህም የሌላው ሃይማኖት አባል ስላልሆነ ገሃነም እንዲገባ ተፈርዶበታልና ሁሉም ነፍስ ገሃነም ይገባል ማለት ነው...

«በምድር ላይ ያለውን የውልደትና የሞት ፍጥነት ተመልክተን ገሃነም የሚገባውን ነፍሳት ብዛት ደግሞ መገመት እንችላለን::

«ከዚህ በመነሣት አሁን በገሃነም ውስጥ የሚኖረውን የቅርፅ ለውጥ ፍጥነት እንመልከት፤ ምክንያቱም በቦይልስ ሕግ መሠረት በገሃነም የሙቀቱና የግፊቱ መጠን ተመሳሳይ (ቋሚ) ይሆን ዘንድ ነፍሳት ሲገቡበት እሱም በቅርፅ ይስፋ ዘንድ የግድ ነውና:: ይኸ ደግሞ ሁለት አማራጮችን ይሰጠናል፡-

«የመጀመሪያው ገሃነም ከሚቀበለው ነፍሳት ባነሰ ፍጥነት ቅርፁ እየሰፋ ከመጣ፤ በገሃነም የሚገኘው ሙቀትና የአየር ግፊት ይጨምርና ገሃነምን ሊያፈነዳው ይችላል...

«በሁለተኛ ደረጃ ገሃነም ከሚቀበለው ነፍሳት በላይ በቅርፁ እየሰፋ ከመጣ ደግሞ የገሃነም ሙቀትና የአየር ግፊት እየወረደ ይመጣና



Scanned by CamScanner

መተዛዘን ይጀምራል...

«እንግዲህ ትክክለኛው የቱ ነው? የመጀመሪያ ዓመት ተማሪ ሳለሁ ሴቷ አስተማሪዬ ማስስ ባንያን ላቀረብኩላት የአብረን እንተኛ ጥያቄ የመለሰችልኝ፦ «...ከአንተ ጋር የምተኛው ገሃነም የቀዘቀዘ ቀን ነው...» በማለት ነበር:: እስከዛሬም ከአስተማሪዬ ጋር አብሬ ለመተኛት ያልተሳካልኝ እውነት በመሆኑ በሁለተኛ ደረጃ ያቀረብኩትና «ገሃነም ሙቀትን የሚያወጣና የማይቀዘቅዝም ቦታ ነው» የሚለው ትክክለኛ ይመስለኛል...» የሚል መልስ ሰጠ::

ከዩኒቨርስቲው ተማሪዎች "A" ያገኘ ተማሪ እሱ ብቻ ነበር::

በዚህ ልሰናበት:: ብዙዎቻችን ሞትን የምንፈራው የት እንደምንሄድ ስለማናውቅ ብቻ ነው:: ገነት ለመግባታችን እርግጠኛ ብንሆን ሞትን አንፈራም ነበር:: ቢያንስ መድረሻችን አሁን ካለንበት ሕይወት የተሻለ ነውና:: ሞት ደግሞ ገነትንም ሆነ ገሃነምን እስከዛሬ ሊያረጋግጥልን አልቻለም:: ለጊዜው ሞትን የመጨረሻ አድርገን እንውሰደው::



Scanned by CamScanner

# «ጥበብ ካልገባህ እንደእርያ መሆንህ ነው»

ታላቁ ፈላስፋ ፊሮ ዕውቀቱን ያካፍላቸው ዘንድ ወደጋበዙት ሰዎች በማለዳ አመራ:: በቦታው ሲደርስ ቁጥሩ እጅግ የበዛ ሰው ተሰብስቦ ሲጠብቀው ተመለከተና ወደተዘጋጀለት የከፍታ ቦታ በዕርጋታ ወጥቶ ቆመ:: ፊሮ ትምህርቱን ከመጀመሩ በፊት ጥያቄ ወረወረ:-

«ዛሬ እዚህ የተሰበሰባችሁ ከእኔ ልትማሩ ነው?» 'ተማሪዎቹ' በአንድ ድምፅ አዎንታቸውን ገለፁ::

«እንግዲያውስ ስለምን እንደማስተምር ታውቃላችሁ ማለት ነዋ?» አለ ፊሮ

«□ረ ምንም አናውቅም» አሉ 'ተማሪዎቹ' አሁንም በአንድ ድምፅ::

«ስለምን እንደማስተምር ካላወቃችሁማ ዝም ብዬ ማውራት አልፈልግም...» አለና ከመድረኩ ወርዶ ወደቤቱ አመራ::

በነጋታው አሁንም በዚያው ቦታ ሕዝቡ ተሰብስቦ ይጠብቀው ጀመር:: ፊሮ መጣና በእርጋታ ወደ መድረኩ ወጣ::

«ዛሬስ ስለምን እንደማስተምር አውቃችኋል?» በማለት ጠየቀ::

የተሰበሰበው ሕዝብ በአንድ ቃል አዎንታቸውን ገለፁ::

ፊሮም «ካወቃችሁትማ ወደቤቴ ልሂድ...» በማለት ከከፍታው ላይ ወረደ::



Scanned by CamScanner

በነጋታው ወደቦታው ሲያመራ አሁንም ሕዝቡ ተሰብስቦ እየጠበቀው ነው:: የዚያን ቀን ሕዝቡ መልሳቸውን አዘጋጅተው ነበር የጠበቁት::

ፊሮ ወደከፍታው ከወጣ በኋላ:- «ዛሬስ ስለምን እንደማስተምር ታውቃላችሁ...?» አለ::

ሕዝቡም:- «ግማሾቻችን እናውቃለን፤ ግማሾቻችን ደግሞ አናውቅም...» አሉ::

ፊሮም:- «እንግዲያውስ ግማሾቻችሁ የምታውቁት፣ ለግማሾቹ የማያውቁት ንገሯቸው...» በማለት ወደቤቱ ሄደ:- ፈላስፋ ከጠመመ እንግዲህ እንዲህ ነው:: ይኸች ታሪክ ዛሬ ተወራርሳ ብዙዎቹ የራሳቸው አድርገው እያወሩባት ቢገኙም ወደኋላ ተመልሰን የሶቅራጥስን ዘመን ስንጉበኝ ባገኘነው ላይ እምነት ጥለን ተቀበልናት::

በጨለማው ላይ ብርሃን ስታበራበት ብርሃን ማየት የቻለ እሱ ጠቢብ ነው፤ ጨለማው ላይ እንዳፈጠጠ ለሚቀረው ለእሱ ግን ወዮለት:: ጠቢቡ ሰለሞን በመጽሐፈ ምሳሌ ላይ እንደተናገረው:- «ጥበብን የሚያገኝ ነፍሱን ይወድዳል» (ምሳ. 19:8) ይላል:: የማያገኘው እንግዲህ ነፍሱን መጥላቱም አይደል?

ሰለሞን በአባቱ በዳዊት ዙፋን ላይ በተቀመጠ ጊዜ አንድ ነገር ጠየቀ:- «አቤቱ አምላክ ሆይ ቁጥሩ እንደ ትቢያ በሆነው በብዙ ሕዝብ ላይ አንግሠኸኛልና ለአባቴ ለዳዊት የሰጠኸው ተስፋ ይጽና:: አሁንም በዚህ ሕዝብ ፊት እወጣና እገባ ዘንድ ጥበብንና እውቀትን ስጠኝ፤ ይኸን በሚያህል በዚህ ታላቅ ሕዝብህ ላይ ይፈርድ ዘንድ የሚችል የለምና...»

እግዚአብሔርም በሰለሞን ጥያቄ ተደነቀ፤ ተደሰተ:: ጥበብን፣ እውቀትን፣ ክብርን፣ ባለጠግነትን... ዘረገፈለት:: በዚህ ያለልክ በተሰጠው ጥበብ ደግሞ ስለጥበብ ተናገረ::

«የወርቅ ቀለበት በእርያ አፍንጫ እንደሆነ
ከጥበብ የተለየች ቆንጆ ሴትም እንዲሁ ናት» (ምሳ. 11:22)



Scanned by CamScanner

የሰው ልጅ ጌጡ ጥበብ ነውና ለጠቢባን እውቀትን ያበዙ ዘንድ መናገር ተገቢ ነው:: ጥበብ ካልገባህ ደግሞ እንደእርያ መሆንህ ነው::

ዛሬም በቀልድ እያዋዛን ጥበብን እናስተምራለን:: ጠቢብ እንዲህ አለ:- «በጨለማ ማየት እችላለሁ...!» የጠቢቡን አባባል ያልተረዳ ሰነፍ ደግሞ ጠየቀ:- «በጨለማ ማየት ከቻልክ ታዲያ ለምን መብራት ይዘህ ትሄዳለህ?» ጠቢቡ ከሰነፍ የሚጠብቀው ጥያቄ ነውና ሳይደነቅ መለሰለት:- «እንዳንተ ዓይነቱ በጨለማ ማየት የማይችል መጥቶ እንዳይገጨኝ ነው» አለው:: ጠቢብ መሆን ባይቻል የጠቢብን ብርሃን ማየት ይቻላል::

ለሰነፍ ጨለማ የጠቢብ ብርሃን መድኃኒቱ ነውና ትንሽ እንጨምር:-

አንድ ቀትር ረሃብ የጐዳው ጉልማሣ አንዲት ደረቅ ዳቦ በእጁ ይዞ የሚበላበትን ነገር ለመለመን በመንገድ ዳር ወደሚገኝ ምግብ ቤት ተጠግቶ ይቆማል:: ብዙም ሳይቆይ ከምግብ ቤቱ የሚወጣው የተጠበሰ ስጋ ሽታ አፉን በምራቅ ይሞላውና ዳቦውን በምግቡ ሽታ እያጣጣመ መብላት ጀመረ:: በዚህ መሃል ግን የምግብ ቤቱ ባለቤት ነገሩን ይረዳና ሲሮጥ ወጥቶ የደሀውን አንገት አንቆ ያሸተተበትን እንዲከፍል ይወዘውዘው ጀመር:: ደሀውም ምንም ገንዘብ በኪሱ እንደሌለ ይነግረውና እንዲለቀው ካልሆነም ወደዳኛ እንዲሄዱ ይጠይቀዋል:: የምግብ ቤቱ ባለቤትም ወደዳኛ ይዞት ይቀርባል:: ዳኛው ነገሩን በሚገባ ካዳመጠ በኋላ «ደሀው ያሸተተበትን ይከፍል ዘንድ ተገቢ ነው» በማለት ፍርዱን ይሰጥና የምግብ ቤቱ ባለቤት ወደእሱ እንዲጠጋ ያዘዋል:: የምግብ ቤቱ ባለቤትም እንደታዘዘው ወዳዳኛው ሲጠጋ ፈጠን ብሎ ከኪሱ ሣንቲም ያወጣና በጆሮው ላይ አቃጭሎ ድምፁን አሰምቶ ወደኪሱ ከተተው:- «እነሆ ለደሀው እኔ ከፍዬለታለሁ፤ ወደቤታችሁ ሂዱ!» አለ::

ግራ የተጋባው የምግብ ቤቱ ባለቤት:- «ዳኛ ሆይ፣ የሳንቲምህን ድምፁን አሰማኸኝ እንጂ መች ሰጠኸኝ» አለው:: ዳኛውም መልሶ «ድሀውም አሸተተ እንጂ አልበላም!» በማለት መለሰለት::

«ጥበብ ማብዛት ትርፉ ጭንቀት ነው» ይላል ጠቢቡ:: ጥበብ



Scanned by CamScanner

ስጋዝዎ የስነፋ ጨለማ ያስጨንቅሃል:: ከአንተ ብርሃን ይልቅ የራሱ ጨለማ ደምቆ ይታየዋል:: ኢየሱስ ክርስቶስን ፈሪሣውያን በሕግ ፈተኑት ተነሱ «ሕግ የሚያወራው ስለእኔ ነው» አለ በነቢያት ትንቢት መጡበት:- «እሱም ቢሆን ስለእኔ የተነገረ ነው» አላቸው:: በመጻሕፍት ተነኩበት:- «መጻሕፍት በሙሉ ስለእኔ ነው የሚያወሩት» አላቸው:: ሰቀሉት:- «ተፈፀመ» አላቸው:: የጨለማው ፍፃሜም የዚያን ቀን ሆነ:: እንግዲህ ክርስቶስን የተከተሉት ብርሃን በራላቸው:: እነሱ የበራላቸው ደግሞ ክርስቲያን ተባሉ፤ ለምን ቢሉ ክርስቶስን ይመስላሉና!

ጥበብን ለምኖ ያለልክ የተዘረገፈለት ንጉሥ ሰለሞን ፊት ሁለት ጋለሞቶች ቀረቡ:: «ንጉሥ ሆይ! ልጇን ስለተኛችበት የዚህች ሴት ልጅ በሌሊት ሞተ... እሷም በእኩለ ሌሊት ተነሥታ የእኔን ልጅ ሰረቀች... የሞተውንም ልጇን በእኔ ብብት አደረገች...::» ንጉሥ ሰለሞን ፍርድ ሰጠ:- «ብሕይወት ያለውን ልጅ በሰይፍ እኩል አካፍሏቸው...» አለ:: ልጇ የተሰረቀባት ፍርዱን ተቃወመች:- «ንጉሥ ሆይ! አይገደል ለእሷ ይሰጥ!» አለች:: ሌላዋ ደግሞ «እንካፈል» አለች... ንጉሥ ሰለሞንም:- «ልጅሽ ቢሆን እንካፈል አትይም ነበር...» በማለት ልጁን የእሱን ፍርድ ለተቃወመች ሴት እንዲሰጥ አዘዘ::

ኢየሱስ ደግሞ እንዲህ አለ:- «ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው? ስለልብስስ ስለምን ትጨነቃላችሁ? የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ ተመልከቱ፤ አይደክሙም፣ አይፈትሉም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ ሰለሞን እንኳን በክብሩ ሁሉ ከነዚህ እንደአንዱ አልለበሰም:: እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ እናንተ እምነት የጎደላችሁ እናንተማ ይልቁን እንዴት?...» ማንን ይሆን?

# «እንደሰው መኖርና እንደሰው መታወቅ የተለያዩ ናቸው»

አሜሪካውያኖች የእኛ ስርቫንቴስ፣ የእኛ ሆሜር፣ የእኛ ቶልስቶይ፣ የእኛ ሼክስፒር... ይሉታል፡፡ እንደ□ርነስት ሔምንግዌይ ዓይነቱ ታላቅ ደራሲ ደግሞ:- «ማንኛውም የአሜሪካ ዘመናዊ ድርሰት የመጣው ከማርክ ትዌይን 'Huckleberry Finn' ነው...» ብሏል፡፡

ሴንት ሉዊስ ቢሄዱ የማርክ ትዌይን ባንክ አለ፤ በኒውዮርክ ቢደርሱ የማርክ ትዌይን «ሆቴል» አለ፤ በሲአትል የማርክ ትዌይን ት/ቤት አለ፤ ማርክ ትዌይን የሌለበት አሜሪካ የለም፡፡ በሕይወት ዘመኑ ይጠጣው የነበረው «ባስአል» የስኮች ውስኪ ማስታወቂያ የእሱ ፎቶ ነው፤ በቴኒሲ የጋዝ ካምፓኒ ማስታወቂያም እሱ ነው፤ በአሜሪካ መዲና ትልቁ ሆቴል ማስታወቂያው እሱ ነው፤ በካሊፎርኒያ ደግሞ የመቃብር ሥፍራ መጠሪያ የእሱ ስም ነው፡፡ በአጭሩ አሜሪካ ከሕይወት እስከ ሞት የእሱን ስም ያላስገባችበት ነገር የለም፡፡

በአሜሪካን የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ፕሮግራሞች ስሙ ማጣቀሻ ያልሆነበት ቢኖር በጣም ጥቂት ፕሮግራም ነው፡፡ በእሱ መጽሐፍ ('Huckleberry Finn') ያልተማረ ተማሪ፣ ያልፃፈ ጋዜጠኛ፣ ያልተመራ ፖለቲከኛ፣ ያላሰበ ፈላስፋ... የለም ማለት ይቻላል፡፡

ሳሙኤል ላንግሆርን ክሊመንስ የማርክ ትዌይን እውነተኛ ስሙ



Scanned by CamScanner

ነው፡፡ በ1835 በፍሎሪዳ የተወለደው ትዌይን ሚሱሪ በምትባለው የሚሲሲፒ ግዛት ውስጥ የልጅነት ጊዜውን እንዳሳለፈ የተፃፈ ታሪኩ ይነግረናል፡፡ የጀልባ ሹፌር በመሆን ሥራውን የጀመረው ትዌይን በአሜሪካ በተነሣው የእርስ በእርስ ጦርነት ምክንያት ሥራውን አቁሞ ለጥቂት ጊዜ ከቆየ በኋላ ወደ ኔቫዳ በመሄድ በማዕድን ቁፋሮ ሥራ ለመሰማራት ያደረገው ሙከራ ሳይሳካለት በመቅረቱ ራሱን ወደመቆፈር ተዛወረ፡፡ በዚህም የተሳካለት ፀሐፊ መሆኑን ማስመስከር ጀመረ፤ የብዕር ስሙንም ማርክ ትዌይን አለ፡፡ እስከዛሬ ድረስ አሜሪካም ለዚህ ስም ትልቅ አክብሮት አላት፡፡ በራሱ ብዕር ካሰፈረው የሕይወት ታሪኩ እንቆንጥር፡-

አንድ ሞቃታማ ቀን በሳን ፍራንሲስኮ አዘውትሬ በምገባበት የሳን ፍራንሲስኮ ሆቴል ስገባ ካፒቴን አስቦርን ተቀምጧል፡፡ እንደአስቦርን ስለራሱ ታሪክና ጀግንነት ማውራት የሚወድ ሰው በሕይወቴ ባላውቅም እሱን ሲያወራ በመስማቴ ይበልጥ የሚያስደስተኝ ግን ከወሬው ይልቅ ወሬውን ሲያዳምጡለት የሚሰማውን ደስታ መመልከት ነበር፡፡ የዚያን ቀንም እንደተለመደው በባህር ላይ ጉዞው ስለአጋጠመው አስደንጋጭና አስቸጋሪ ፈተና እየነገረኝ እኔም ማዳመጥ በጀመርኩ በጥቂት ጊዜ ውስጥ አንድ ነገር ተፈጠረ፡፡ ከዚህ በፊት በዚያ ሆቴል እምብዛም አይተነው የማናውቀው ወይም ደንበኛ ያልሆነ ሰው ወደእኛ አቅጣጫ ተጉዞ የተቀመጥኩበት ጠረጴዛ ጋ ደርሶ ቆመና አስቦርን ላይ አፈጠጠ፡፡ በሁኔታው ግራ እንደተጋባን አስቦርን፡- «ይቅርታ ወንድም ታውቀኛለህ?» በማለት ጠየቀው፡፡ እንግዳውም ሰው፡- «አንተ ካፒቴን አስቦርን፤ የባሁሩ ላይ ጀግና አይደለህም እንዴ?» በማለት አፈጠጠ፡፡ ይኸን ጊዜ የአስቦርን ፊት በራ፡፡ በፈገግታም እንደተዋጠ፡- «አዎን ግን እንዴት ልታውቀኝ ቻልክ?» አለው፡፡ ከዚያም እንግዳው ሰው በባህር ላይ አጋጥሞት ስለነበረው ፈተናና እንዴትም በጀግንነት እንደተወጣው አስቦርን አስቀድሞ ለእኛ የአጫወተንን ታሪክ ቃል በቃል ደግሞ ነገረው፡፡

ይኸን ጊዜ አስቦርን ራሱን መቆጣጠር አልቻለም:: ከመቀመጫው ተነስቶ የአንገዳውን ሰው ማንነት ጠየቀው:: እሱም በርተን ሳንደርስ እንደሚባልና እሱ በነበረበት መርከብ ውስጥም ቴክኒሺያን እንደነበር ነገረው:: አስቦርን:- «አንተን በአንድ እጄ አይደለም በሁለት እጆቼ ልጨብጥህ ይገባኛል...» በማለት በሁለት እጆቹ የሳንድርስን እጆች ይዞ ወዘወዘው... አቀፈው... ሳመው:: የዚያን ቀኑ የካፒቴን አስቦርን ግብዣም ከሳንደርስ ተርፎ ለእኛም ተዳረሰ::

...ወደግብዣው ማብቂያ ላይ ሳንደርስ ያለበትን ችግር ለአስቦርን ገልጦ ነገረው:: አስቦርንም በኪሱ የነበረውን ገንዘብ በሙሉ ዘረገፈለትና ወደፊትም እንደሚረዳው ነገረው:: ከዚያም በኋላ ባሉት ሣምንታት ሳንደርስ ከፍተኛ የገንዘብ ችሮታን ከካፒቴን አስቦርን አገኘ::

...አንድ ማለዳ በካሊፎርኒያ ጐዳና እየተጓዝኩ እግሬን ሳፍታታ ሳንደርስን አገኘሁትና ወግ ጀምረን አብረን በመጓዝ ላይ ሳለን አስቦርን በመርከበኛነቱ ጊዜ የነበረውን ባህርይ ጠየቅኩት:: እሱም ያለማንገራገር «አስቦርንን ከዚያ ቀን በፊት አላውቀውም...» አለኝ:: በመደነቅ ፊቴን አዙሬ «ታዲያ ካላወቅኸው የዚያን ዕለት ስለእሱ የነገርከውን ታሪክ ከየት አመጣኸው?» አልኩት:: እሱም ፈገግ ብሎ:- «አስቦርን ታሪኩን ሲነግራችሁ ከእሱ ጀርባ ተቀምጬ ለሣምንታት እሰማው ነበር... ይኸንኑ ነው ደግሜ የነገርኩት...» አለኝ...

* * *

በሕይወት ዘመኔ ቅንነት ያረካኛል:: ቅንነት በሉት ወይም ታማኝነት የሕይወቴ መርኅ ነበር::...

ከማንም በላይ የምወደውና ለዓመታት አብረን በመኖር ብዙ የሕይወት ውጣ ውረድ በጋራ ያሳለፍነው ጓደኛዬ ክሊንተንና እኔ አንድ ቀን ከፍተኛ የገንዘብ እጥረት አጋጠመን:: የምንፈልገው የገንዘቡ መጠን ደግሞ ሦስት ዶላር ብቻ ነበር...

ለአንድ ሰዓት ያህል በመንገድ ላይ እየተዘዋወርኩ ገንዘብ የማገኝበትን



Scanned by CamScanner

ዞሬ አሰብኩ፡፡ ነገር ግን ገንዘቡን የማገኝበት ዘዴ ሊመጣልኝ አልቻለም፡፡ ሮጥም እግሮቼን ያዛቸው፤ ከመንገዱ ዳር ወደሚገኝ ወንበር በመሄድ ተቀምጬ አሁንም ማሰላሰል ጀመርኩ፡፡ በድንገት ከሐሣቤ ያባነነኝ እጅግ በጣም የሚያምር ውሻ እግሮቼ ስር መጥቶ በተኛበት ጊዜ ነበር፡፡ ውሻውን ሳየው ወደድኩት... በእጆቼም እያሻሸሁ ስደባብሰው አንድ ጀኔራል ወደእኔ አቅጣጫ መጥቶ የምሰራውን ይመለከት ነበር፡፡

«ውሻህ በጣም ያምራል... ትሸጠዋለህ?» አለኝ ጀኔራሉ...

«አዎን ይሸጣል...» አልኩት፡፡

«መቼም እንደዚህ የሚያምር ውሻ ዋጋው ቀላል አይሆንም... ይሁንና ስንት ነው የምትሸጥልኝ...» አለኝ፡፡

«ሦስት ዶላር» በማለት ዝቅ ብዬ ውሻውን ማሻሸት ጀመርኩ፡፡ ጀኔራሉ የሰማውን ማመን አልቻለም... «የዚህን ውሻ ዋጋ ባታውቀው ነው እንጂ ከሃምሳ ዶላር በታች አይደለም፡፡... እኔም ከአንተ ላይ በማታለል ገዝቼ መውሰድ አልፈልግምና እውነተኛውን ዋጋ ንገረኝ...» አለኝ፡፡

እኔም በሃሣቤ ፀናሁ፡- «የዚህ ውሻ ዋጋ ሦስት ዶላር ነው... ከፈለግከው መግዛት ትችላለህ...» አልኩት፡፡

ጀኔራሉም ሦስት ዶላር አውጥቶ ሰጥቶኝ ውሻውን ይዞ ሄደ፡፡ ነገር ግን ብዙም ሳይቆይ አንድ በሐዘን ፊቱ የገረጣ ሰው ወደእኔ አቅጣጫ ሲመጣ ተመለከትኩት፤ ሰውዬው እኔ ጋ እንደደረሰ፡- «እባክህን ወንድም በጣም የምወደው ውሻዬ ጠፍቶብኝ እየባከንኩ ነው፡፡ ኢይተኸው እንደሆን ንገረኝና ወሮታህን ልክፈል...» አለኝ፡፡

እኔም፡- «ውሻህን አይቼዋለሁ... ፈልጌ ካገኘሁልህ ሦስት ዶላር ትከፍለኛለህ...» አልኩት፡፡ ሰውዬው የማይነገር ደስታ ፊቱን ሞላው፡፡ «ሃምሳ ዶላር እከፍልሃለሁ...» አለኝ፡፡ «የለም የምትከፍለኝ ሦስት ዶላር ብቻ ነው...» አልኩትና በዚህ ተስማማንና ከፈለኝ፡፡ እኔም በወንበሬ ላይ እንዲቀመጥ ነግሬው ጀኔራሉ ወደሄደበት አቅጣጫ ተጣደፍኩ፡፡ ብዙም ሳይርቅ ጀኔራሉን ደረስኩበትና የሰጠኝንም ሦስት ዶላር ከኪሴ አውጥቼ

ዘረጋሁለት:: ጀኔራሉ ደንግጦ ተመለከተኝ:: «ሦስት ዶላርህን እንካ... ውሻዬን መልስ» አልኩት:: መጀመሪያ ለምን እንደሸጥኩለት ጠየቀኝ::

«የሸጥኩልህማ እንድሸጥልህ ስለጠየቅኸኝ ነው፤ ውሻውን ለመሸጥ አላሰብኩም ነበር... እንድሸጥልህ ስትጠይቀኝ ግን ወዳጅ እንደሚያስፈልግህ...» ጀኔራሉ በጩኸት አቋረጠኝ:: «ምን ዓይነት መንፈስ ቢኖርህ ነው እኔ ወዳጅ እንደሚያስፈልገኝ የተረዳኸው... ደግሞም የአንተ ያልሆነን ንብረት ነው የሸጥከው...» አለኝ::

እኔም ክርክሩ ዋጋ እንደሌለውና የሰው ውሻ ቢመልስ እንደሚሻለው አስረድቼው:- «እኔ የሰው የሆነን ንብረት መሸጤና አንተም የሰውን ንብረት ዋጋው ባልሆነ ርካሽ ዋጋ መግዛትህ በወንጀል ደረጃ እኩል ነው... አሁንም ውሻውን ለባለቤቱ እንድመልስለት ስጠኝ... በእኔ ቦታ ሆነህ ራስህን ተመልከት፤ የሰውን ንብረት ሸጠህ ባለቤቱ እንድትመልስለት ቢጠይቅህ ምን ታደርጋለህ...?» አልኩት::

ጀኔራሉ ውሻውን ሰጠኝ፤ እኔም ሦስት ዶላሩን መለስኩለት:: ውሻውንም ይዤ ወደባለቤቱ ሄድኩ:: አዕምሮዬን ያረካው የማጭበርበር ድርጊት አለመፈፀሜ ስለሆነ ተደሰትኩ... ሦስት ዶላር የተከፈለኝ የጠፋ ሰው ንብረት ፈልጌ በማግኘቴ ነውና...

* * *

አንድ ቀን በለንደን ኑሮዬን በመሰረትኩበት ዘመን ለአሜሪካ ጋዜጦች የእኔን መሞት የሚያረዳ ወሬ ደረሳቸው:: በእርግጥ የዚያን ቀን የሞተው የአክስቴ ልጅና የእኔ ሞክሼ የነበረው ሮስ ክሊመንስ ነበር... በለንደን የሚገኙ የአሜሪካ ጋዜጦች ተወካዮች ወደ ቤቴ መጉረፍ ጀመሩ:: ብዙዎቹም በቤቴ ተቀምጬ ሻዬን እየጠጣሁ፣ ፒፓዬን ሳጨስ በሕይወት ስላገኙኝ ተበሳጩ:: ከእነዚህ ጋዜጠኞች አንዱን ግን ምንጊዜም አልረሣውም:: በትውልዱ የአየርላንድ ዜጋ የነበረና "Evening Sun" የተባለው ጋዜጣ ሪፖርተር ነበር:: ይኸ ጋዜጠኛ የእኔን መሞት የሚያረዳ ዜና እንደደረሰውና ይኸንኑም እንዲያጣራና ዜናውን እንዲዘግብ በአለቃው



Scanned by CamScanner

እንደታዘዘ ነገረኝ::

እኔም:- «ሪፖርቱ በጣም የተጋነነ ነው የሚል መልስ ላኩ» አልኩት:: በመልሱ አልሳቀም፤ እንዲያውም በጣም አዘነ:: በእጁ የያዘውንና ከኒውዮርክ የተላከለትን መልዕክትም አሳየኝ:- «ማርክ ትዌይን እየሞተ ነው ዜናህን በአምስት መቶ ቃላት ፃፈው፤ ሞቶ ከሆነ ደግሞ አንድ ሺህ ቃላት አድርገው...» ይኸችን መልዕክት ከጋዜጠኛው ተቀብዬ አስቀመጥኳት::

ለብዙ ዓመታት ከእኔ ጋር የተቀመጠችው መልዕክት ከአንድ ወር በፊት ለጨረታ አቅርቤያት አርባ ሦስት ዶላር ተሸጠች፤ ስሞት ደግሞ ሰማንያ ስድስት ዶላር ታወጣለች...

* * *

ጄኔራል ኔልሰን ማይልስ ኒውዮርክ በሚገኘው ቤቱ ታላቅ የራት ግብዣ ያደርግና የጥሪ ካርድ ይልክልኛል:: እኔም በራት ግብዣው ላይ ተገኝቼ ከወዳጆቼ ጋር ሳወጋ ጄኔራሉ ወደእኔ መጥቶ በአክብሮት ሰላምታ ሰጠኝና አንድ ጥያቄ ወረወረ:- «ወደኒውዮርክ ከመምጣትህ በፊት ዋሽንግተን ትኖር ነበር?» አለኝ:: እኔም አለመሳሳቱን ነገርኩት:: ጄኔራሉ እየተገረመ:- «እንዴት ታዲያ ባለፉት ሰላሳ ዓመታት አላውቅህም?» አለኝ:: እኔም «ክቡር ጄኔራል:- ባለፉት ሰላሳ ዓመታት ታዋቂ ስላልነበርኩ ይሆናላ!...» አልኩት... እንደሰው መኖርና እንደሰው መታወቅ የተለያዩ ነገሮች መሆናቸው የዚያን ቀን ለራሴም ገባኝ...

# ሥጋ ነፍስን ሲያሸንፍ ኃጢአተኛ፤ ነፍስ ደግሞ ሥጋን ሲያሸንፍ ፃድቅ ትሆናለህ

ቀደም ባሉት ምዕራፎች ስለሚስቲሲዝም ፍልስፍና ያነሳነውን አሁንም አዲስ ነገር አገኘንበት:: የሚስቲሲዝም አራማጆች አንድን ነገር በጥልቅ ማሰብ፣ ማሰላሰል ከዚያም በነገሩ ውስጥ መዋሐድ ነው ይላሉ:: ጠቢቡ ሰለሞን «ሰው በልቡ እንዳሰበ እንደዚያው ነው... /As the man thinks, so is he.../» ይላል:: የምታስበውን፣ የምታሰላስለውን ትሆነዋለህ፤ ለምን ቢሉ ከማሰብ ማመን ይመጣልና፤ ባመኑት መኖር ደግሞ የሰው ባህርይ ነው::

ሚስቲሲዝም ጅማሬው ከሃይማኖት ነው:: በጥልቅ የምታሰላስለው አንድ ነገር አለ:: በዚያ ነገር ልብህን ታፀዳለህ፤ ዕውቀትን ትቀስማለህ፤ ራስህን ወደሌላ ዓለም ታሸጋግራለህ:: በዚህም ግብህ አንድ ነው:: የምታሰላስለው ነገር ላይ መድረስ:: ያ ነገርም እግዚአብሔር ነው ይላሉ:: ለምሳሌ አንተነትህ ውጤት ነው፤ የነፍስና የሥጋ ድምር ሰው ነህና:: እውነተኛው አንተነትህ ነፍስ ነበር:: ነፍስህ በሥጋ ውስጥ ሲቀመጥ እንደነፍስ ማሰቡን አቆመና በቁሳዊ ነገር ተዋጠ:: በሚስቲሲዝም ግን ወደነፍስህ እሳቤ ትመለሳለህ::



Scanned by CamScanner

በነፍስህ ሐሣብ ውስጥ ገብተህ በተመስጦ ስታሰላስል ደግሞ የተለያዩ ሬጃዎችን ታገኛለህ:: ለምሳሌ ቁጡ፣ ስግብግብ፣ ራስህን ብቻ ወዳድ ሮተኛ ከሆንክ አንተ የመጀመሪያው ደረጃ ላይ ትገኛለህ:: በዚህ ደረጃ የሚገኙ ሰዎች ሱሰኞች ናቸው:: ከሁሉም ሱስ የሚጠናባቸው የኃጢአት ሱስ ነው:: The Commanding Self ይባላል:: የነፍስህ ጌታ ሥጋህ ነው:: በዚህ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች የመለወጥ ተስፋ የላቸውም፤ ምክንያቱም አስቀድሞም የለውጥን አስፈላጊነት አይቀበሉምና::

በቀጣዩ ደረጃ ላይ የሚገኙት ደግሞ ከመጀመሪያው ደረጃ ትንሽ ላቅ ያሉ ሲሆኑ በጨለማቸው ላይም ትንሽ የእምነት ብርሃን ፈንጥቃለች:: በዚህም ደረጃ ፍላጐትና ስግብግብነት ከፍተኛውን ደረጃ ይዟል፤ ነገር ግን በያንዳንዱ ሥጋዊ ፍላጐትና ኃጢአት ንስሐ ይገባሉ፤ ይፀፀታሉ:: እነዚህን ደግሞ The Regretful Self ይሏቸዋል:: ኃጢአትን ቢያደርግም ይፀፀታል፤ ያዝናል፤ ንስሐ ይገባል:: በሥጋና በነፍስ መካከል የሚካሄደው ጦርነት አውድማውም ይኸው ደረጃ ነው:: ጦርነቱ ግን መጨረሻ የለውም:: ሥጋ ነፍስን ሲያሸንፍ ኃጢአተኛ፤ ነፍስ ደግሞ ሥጋን ሲያሸንፍ ፃድቅ ትሆናለህ:: በነፍስ ድል ውስጥ እውነትን ታቅፋለህ:: በሥጋ ደግሞ እውነትን ትክዳለህ:: የዚህ ደረጃ የኃጢአት ሱስ ከመጀመሪያው ጠንከር ስለሚል ጠንካራ መድኃኒት ያስፈልገዋልና ሦስተኛው የሚስቲሲዝም ደረጃ ይቀጥላል::

በሦስተኛው ደረጃ የሚገኙ ሰዎች ደስታቸው ፀሎት ነው:: በዚህም መንፈሣዊ ልምምዳቸውን ያዳብራሉ:: በሚስቲሲዝም ወደመጨረሻው ደረጃ የመድረሻው መንገድ እንግዲህ ፀሎት መሆኑ ነው:: በዚህ ደረጃ ውስጥ የገባ ሰው The Inspired Self ደረጃ ደርሷል ይሉታል:: የሞራል እሴቶችን፣ መንፈሣዊውን ነገርና አምላኩን በተመስጦ ለማሰብና ለማሰላሰል በቂ ጊዜ ያለው ሰው ነው:: ምንም እንኳን የሰው ልጅ ከራሱ ፍላጐት ውጭ ሙሉ በሙሉ ለመሆን ባይችልም በዚህ ሰው ውስጥ ግን «እኔነት» ያለው ቦታ ኢምንት ነው:: የዚህ ደረጃ ሰው ልዩ መለያው

ጥበብ

ደግሞ ብስለት፣ ሰው አክባሪነትና በምላሹም የተከበረ መሆኑ ነው::

ከዚህ ያለፈው ሰው የሚገኝበት አራተኛ ደረጃ The Contented Self ነው:: በዚህ ደረጃ የሚገኝ ሰው ከሁሉ በላይ ያገኘው «ሰላም» ነው:: ያለፉት ደረጃዎች ትግልህ እዚህ ላይ ያበቃና ታርፋለህ የጥንቱ ምኞትና ፍላጎት በዚህ ደረጃ ለመግባት ከቻልክ ያበቃለታል:: አስሮ የያዘህ እኒኑት አርነት ይለቅሃል:: በአርነት ተለቀህ ስትሄድ የምታገኘው ደግሞ መለኮታዊውን ኃይል ነው:: ከሥጋህ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ትላቀቃለህ:: ነፍስም ወደፈጣሪዋ በዚህ ጊዜ ታስባለች:: የሚስቲሲዝም ከፍተኛ ደረጃ መሆኑ ነው::

ቀጣዩ ደረጃ The Pleased Self ነው:: በዚህ ደረጃ የገባ ሰው ባለው ነገር በቃኝ ብሎና ተደስቶ የሚኖር ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን በችግሮቹና በፈተናዎቹም የሚደሰት ይሆናል:: ምክንያቱም የፈተናዎቹ ምንጭ እግዚአብሔር ነው በማለት ያስባልና:: በዚህ ደረጃ ስትገባ እንደሥጋዊ ሰው ደስታን የምታሳድድና ሃዘንን የምታስወግድ ሳትሆን ነገር ግን በሃዘንህም ደስ ይልሃል:: ይኸችን ተረት በምሳሌ እንያት:-

ጌታው ለሚወደው አሽከሩ ከፊቱ ከቀረበለት ፍራፍሬ አንዱን አንስቶ እንዲበላ ይሰጠዋል፤ አሽከሩም ጌታው የሰጠውን ፍሬ እያጣጣመ መብላት ይጀምራል:: ከጥቂት ጊዜ በኋላም ጌታው ሌላ ፍሬ ለራሱ ያነሳና አንድ ጊዜ ገምጦ ይተፋዋል:: ወደአሽከሩም ፊቱን አዙሮ:- «እንዲህ የሚመር ፍሬ እንዴት ተበላልህ?» ይለዋል::

አሽከሩም:- «የቱንም ያህል የሚመር ነገር ቢሆን በአንተ እጅ ከተሰጠኝ ይጣፍጠኛል...» በማለት ቀሪውን ፍሬ አሽከሩ ማጣጣም ጀመረ::

በዚህ ደረጃ ላይ የገባ ሰው እንግዲህ ፍፁም የሚባለውን የፍቅር እርከን ረግጧል ማለት ነው:: ነፍሱ የተሰራችበትን ዓላማ በፍፁም ፍቅር ይከውናል::

ከዚህ ወደላቀው ደረጃ ደግሞ ስንገባ የምናገኘው The Self Pleasing



Scanned by CamScanner

to God ነው:: የዚህ ደረጃ ሰዎች የሚያውቁት ጥበብ
ነው:: ይኸውም በሥጋቸውም ይሁን በነፍሳቸው የሚከናወነው ከትንሹ እስከ ትልቁ ያለው ድርጊታቸው ምንጩ አንድ ብቻ ነው፡- እሱም እግዚአብሔር ይላሉ:: በዚህም በራሳችን አንዳች ማድረግ አንችልም በማለት አረጋግጠው ይቀመጣሉ:: ከዚህ በኋላ ለሥጋቸው የሚፈሩትም ሆነ የሚጠይቁት ነገር አይኖርም:: በዚህ ደረጃ ሥጋና ነፍስ ይጋባሉ፤ ሁለቱም አንድ ይሆናሉ:: ሥጋና ነፍስ ለፈጣሪያቸው ይገዛሉ:: መስታወት ቢሰበር አንዱን ምስል አንድ ሺህ አድርጐ ያሳያል:: የተሰበረው መስታወት ቢጠገን ደግሞ ምስሉን ወደድሮው አንድነቱ ይመልሰዋል:: የዚህ ደረጃ የሰው መገለጫም ይኸው ነው::

ከዚህ በኋላ የምናገኘው የመጨረሻውን ደረጃ ሲሆን እሱም The Pure Self ይባላል:: በዚህ ደረጃ የሚገኝ ሰው ራሱን መውደድ፣ ከራሱም መለየት፣ ነፍሱን ማግኘት... የሚሉት አይገልፁትም:: ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ግን ራሱን ወደዘላለማዊውና የመጨረሻው እውነት ውስጥ ይከታል:: የእግዚአብሔርንም መኖር ያውቃል::

ሰዎች እንግዲህ ከላይ ከዘረዘርናቸው ደረጃዎች ውጭ ሊሆኑ አይችሉም:: በሚስቲሲዝም ውስጥ ስትገባ ፈተናው አዳጋች ነው:: ጥቂት ታሪክ ከቻይና እንመልከት፡-

አንድ የቻይና መነኩሴ ከፍተኛውን የሚስቲሲዝም ደረጃ ይገባ ዘንድ ወታዋቂው የዜን መምህር ሄደ:: በዚያም ጥሩ አቀባበል ተደርጐለት በነጋታው ወደልምምዱ ገባ:: በጥልቀትና በፅሞታ ማሰላሰልን ተነግሮትም ጀመረ:: በመጀመሪያዎቹ አሥራ ሁለት ዓመታት ከአንደበቱ የወጣ ቃል ቢኖር፡- «የምተኛበት አልጋ አልተመቸኝም...» በማለት ለመምህሩ መናገሩ ነበር:: መምህሩ አሁንም መነኩሴውን በተመስጦ ማሰላሰሉን እንዲቀጥል ነገሩትና አሥራ ሁለት ዓመት ጨመረ:: በእነዚህ ቀጣይ አሥራ ሁለት ዓመታት ደግሞ አሁንም መነኩሴው ከአንደበቱ የወጣ ቃል ቢኖር አንድ ብቻ ሲሆን ይኸውም «ምግቡ አልተስማማኝም»



Scanned by CamScanner

የሚል ነበር:: መምህሩ ሌላ አሥራ ሁለት ዓመት አዘዙለት:: በእነዚህ አሥራ ሁለት ዓመታት ደግሞ ይበልጥ ፀጥታና ማሰላሰልን ቢያጠናክርም በመጨረሻው ዓመት ግን አንዲት ቃል ወጣው:- «በቃኝ!» የሚል ነበር:: መምህሩም ይኽን ሲሰሙ:- «እውነትህን ነው:: ባለፉት ሦስት አሥራ ሁለት ዓመታት ውስጥ የኖርከው ስታጉረመርም ነበር:: በዚህም ምክንያት የመጀመሪያውን ደረጃ እንኳን ማለፍ አልቻልክምና ቢበቃህ ጥሩ ነው...» በማለት አሰናበቱት:: በዚህ እንግዲህ የራስዎን የትእግስት ደረጃ መለካት ይችላሉ::

በሌላ ጊዜ አንድ ወጣት መነኩሴ ወደ ዜኑ መምህር መጣና በተመስጦ ለማሰላሰልና የእውነትን ጫፍ ለመጨበጥ ያደረበትን ፍላጐት ነገራቸው:: ከመምህሩ ያገኘው መልስ ግን ጩኸት የተቀላቀለበት ሳቅ ነበር:: በዚህም ተደናግጦ ወደቤቱ በሐዘን አመራ:: በነጋታው ተመልሶ ወደመምህሩ በመሄድ:- «መምህር ሆይ፤ ትናንት መጥቼ ስለሚስቲሲዝም በምጠይቅዎ ሰዓት በሳቅዎ አባረሩኝ:: ጥፋቴን ሊነግሩኝ ይችላሉ?» አለ:: መምህሩም ሳቃቸውን ጀመሩ:: ቢሆንም እንደትናንቱ አልገፉበትም:: ሳቃቸውን አቋርጠው:- «አንተ ከጥጃ አትሻልም...» አሉት:: መነኩሴው ከትናንቱ ይልቅ ዛሬ ደነገጠ:: «እንዴት ከጥጃ አልሻልም...?» አላቸው:: «የእኔን ሳቅ ጥጃ ብትሰማ እየቦረቀች ትዘል ነበር፤ አብራም ትስቅ ነበር... አንተ ግን ከመደንገጥህ የማዝንህ...» አሉት:: መነኩሴው ከጥጃ የማነሱን ጉዳይ በዚሁ ማሰላሰል ጀመረ... መምህሩም አሥራ ሁለት ዓመት አዘዙለት::



Scanned by CamScanner

# ያለሥጋ ገነትም ሆነ ገሃነም ልዩነት የለውም

የፍልስፍና አበይት ርዕስ የሆነው ዘላለማዊነት (eternity) ቀጥሎ በስፋት የምናየው ይሆናል። በተለይ ሞት በበረከተበትና በረከሰበት በዚህ ዘመን ቢያንስ ለመጽናኛ የሚሆነን ሌላ ሕይወት መኖሩን ማወቁ በራሱ የሞትን ዋጋ ዝቅ የሚያደርገው ነውና በዚህ ጉዳና ላይ እንጓዛለን።

በሰው ልጅ የታሪክ ጉዞ የታየ አንድ እውነታ ቢኖር ሞትን የዘላለም ሕይወት መጀመሪያ አድርጎ ለመቀበል አለመቻል ነው። ከሞት በኋላ ከሚጠብቀን ሕይወት ይልቅ ምድራዊው ሕይወት ለብዙዎቻችን ዋጋ አለው። ለዚህም ነው ከሞት በኋላ ይኖረናል የምንለውን ሕይወት በግምት ላይ አንጠልጥለን የተውነው። ይኸን አንጠልጥለን የተውነውን ግምት (አንዳንዶች እምነት ይሉታል) ከቦታው አውርደን ስለዚሁ በተረዳንበት የመጽሐፍ ቅዱስ መነጽር ለዛሬ እንመልከተው።

ጅማሬአችንን ከሞት በኋላ በሕይወት ስለምትኖረው ነፍስ በመናገር ይሁን:- «እባብም ለሴቲቱ አላት:- ሞትን አትሞቱም» (ዘፍጥ.3:4)። እባብ ደግሞ በታሪኩ ተወዳዳሪ የሌለው ሐሰተኛ ነው። ነገር ግን በዚህ ቦታ ለሔዋን ሞትን እንደማይሞቱ ሲነግራት በማመን አድርጉ ያላትን አደረገች። እግዚአብሔር «እንዳትሞቱ ከእርሱ አትብሉ፣ አትንኩትም...» (ዘፍጥ.3:3) ያላቸውን ፍሬ በላች፣ አዳምንም ጋበዘች። እንግዲህ ሞት



Scanned by CamScanner

መጣ:: አዳም በዘጠኝ መቶ ሰላሣ ዓመቱ ሲሞት ወደ አፈር ተቀላቀለ፤ ቀድሞም አፈር ነበርና:: ነፍሱ ወደገነት ብትሄድ በዚያ የምትገለባበጥ የነበልባል ሰይፍ ማለፊያ አሳጣችው:: ገነት መግባት አለመቻሉን ሲረዳ ወደገሃነም አቀና:: በገሃነም የሞቀ አቀባበል ተደረገላት:: የመጀመሪያው ቀዳሽ እሱ ነዋ!

እዚህ ላይ ፈላስፎቹ የሚሉን ነገር አለ:: ካለሥጋ ገነትም ሆነ ገሃነም ልዩነት የለውም:: «የሰው ልጅ ዘላለማዊነትን የሚመኘው ሕይወትን ስለሚያፈቅር ሳይሆን ሞትን ስለሚፈራ ነው» ይላሉ:: እንስሳት ሞትን አይፈሩም፤ ስለሞት አያስቡም፤ ቀድሞውንም ሞትን አያውቁም:: ስለዚህም ስለገነት አያስቡም፤ ስለዘላለማዊ ሕይወት አይጨነቁም:: የሰው ልጅ ማሰብ ሲጀምር መጀመሪያ ያወቀው መሞቱን ነበር:: የሰው ደግሞ አምላኩን ፈጠረ:: በፈጠረው አምላክ የተፈጠረ ገነትና ገሃነምንም መመኘትና መፍራት ጀመረ:: አንዳንዶች ግን ከዚህ አፈነገጡ:: ለምሳሌ ፕሌቶ:: ፕሌቶ እንዲህ አለ:- "My immortality is not in Heaven, but in the grateful memory of men." እነሆ ፕሌቶን እስከዛሬ እናውቀዋለን:: ከዚህ በላይ ዘላለማዊነት ይኖር ይሆን?

ፕሌቶ ይኸን ይላል እንጂ በነፍስ ዘላለማዊነት ላይ እሱም የሚጋራው እምነት አለ:: የፕሌቶ "Republic" የሚያስነብበን አንድ ታሪክ አለ:-

«የአርሜኒየስ ልጅ ኢር... አንድ ወቅት በጦርነት ላይ እያለ ተገደለ:: ሬሣውንም አንስተው ሲያመጡት አሥር ቀን አልፎት ነበር:: በወቅቱ ሥጋው ሊበሰብስ ቢገባውም አንዳች ምልክት ግን አላየንበትም:: በአሥራ ሁለተኛው ቀን ወደቀብሩ ሥፍራ ስናመራ በድንገት ከተኛበት ተነሣ... ባለፉት ቀናት ስለተመለከተውም አስደናቂ ከተማ ነገረን:: ፃድቅ የሆኑ ዳኞች የተቀመጡባት፣ ሁለት መግቢያ በር ያላት፣ አንዱ በር በቀጥታ ወደገነት የሚወስድ ነበራት...» ታሪኩ ይቀጥላል:: ፕሌቶ ሲደመድም «እንግዲህ በዚህ ታሪክ ብናምን ከዘላለም ሞት ያድነናል» ብሏል:: የዘመኑ ፈላስፎች ይኸን ምክር አይቀበሉትም:: ፕሌቶን የምናውቀው



Scanned by CamScanner

ታቶልን በሄደው ሥራው እንዷ በነፍሱ ዘላለማዊነት አይደለም ይላሉ፡፡ «የፕሌቶ ስውዩ በእርግጥ ሞቶ ቢሆን ኖሮ አይነሳም ነበር» በማለት የሚከተለውን ምሳሌ ደግሞ ይነግሩናል፡፡ አንድ አሜሪካዊ ወስደህ ከሞት ጋር በሚወዳደር ስመመን ውስጥ እንዲገባ ብታደርገው ሲነቃ የሚነግርህ ታሪክ አዘውትሮ የሚሄድበት ቤተክርስትያን መልአከ እጁን ይዞት ወደብርሃን ሲገባ ማየቱን ነው፡፡ በተመሳሳዩ የሕንድ ተወላጅ የሆነውን ደግሞ እንዲሁ በጥልቅ ሰመመን ውስጥ ብታስገባው የሚነግርህ በላም ላይ ተቀምጦ ገነት ሲገባ ማየቱን ነው፡፡ «የዕድሜ ዘመን ምኞታቸውን በሞቱ ሊያጣጥሩ ቢያዩት የሚደንቅ ሆኖ ሌላ ስያሜ ሊሰጠው አይገባም...» ይላሉ፡፡

ሞት መልኩ አንድ ሆኖ የተለያየ እምነት በሰው ልጅ ዘንድ ያሰጠው የዘላለማዊነት እሳቤ ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ሞት ከሌላው ሞት የተለየ ነው ይለናል ኦስካር ኩልማን፡፡ የዘመናችን የፍልስፍናና የሥነ መለኮት ምሁር ኩልማን ይኸን ሊያሳየን የተነሣው የሶቅራጥስና የክርስቶስን ሞት በማመሳከር ነበር፡፡

ሶቅራጥስ የሚገደልበት ቀን ተከታዮቹን ሲያስተምር የነበረው ስለነፍስ ዘላለማዊነትና በዚያም እምነት ፀንቶ ስለመሞት ታላቅነት ነበር፡፡ ለደቀመዛሙርቱም የፍልስፍናን እውነት በመያዝ ነፍስን ከሥጋ እስር ቤት እንዴት አርነት ማውጣት እንደሚቻል አስተማራቸው፡፡ ፕሌቶ ስለዚሁ ሲነግረን «ሶቅራጥስ የነፍስ አርነት መውጫ ሞት ብቻ መሆኑን ያውቅ ነበርና ያለአንዳች ፍራቻና ሐዘን መርዙን በእርጋታ ጨልጦ ጠጣው» ይለናል፡፡ እንግዲህ ለሶቅራጥስ ነፍስ ታላቁ ጓደኛዋ ሞት ብቻ ነበር፤ ምክንያቱም ከሥጋ እስር ቤት ነፃነት ያወጣታልና፡፡

ኢየሱስ ወደሞት የነበረው አመለካከት ደግሞ ከሶቅራጥስ ፈፅሞ የተለየ ነው፡፡ በጌተሰማኒ ኢየሱስ «ሊደነግጥም ሊተክዝም ጀመረ» (ማር.14:33) ይለናል፡፡ ለደቀመዛሙርቱም «ነፍሴ እስከሞት ድረስ እጅግ አዘነች» (ማር.14:34) ብሏል፡፡ ለኢየሱስ ሞት ታላቅ ጓደኛው ብቻ



Scanned by CamScanner

ሳይሆን ዋነኛ ጠላቱም ነበር፤ ምክንያቱም ከአባቱ ይለየዋልና። ሶቅራጥስ እንደጓደኛ ሞትን እንደተጋፈጠ ኢየሱስ አልተጋፈጠውም። እንዲያውም ሞት አፍጥጦ ሲመጣ ኢየሱስ፡- «አባ! አባት ሆይ ሁሉ ይቻልሃል፤ ይኽችን ፅዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን አለ» (ማር.14:36)

ኢየሱስ መሞት ማለት ከእግዚአብሔር መለየት መሆኑን ያውቃል። ስለዚህም በእግዚአብሐርም ሆነ በደቀመዛሙርቱ መተውን አልፈለገም። «የኢየሱስና የሶቅራጥስ ስለሞት ያላቸው አሳቤ ትልቁ ልዩነት እንግዲህ እዚህ ላይ ነው» ይለናል ኩልማን። ኩልማን ሲቀጥል፡- «ወደዕብራውያን መጽሐፍ ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ሲጽፍ፡- 'እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ...' (ዕብ. 5:7)» ይላል። ስለዚህም ኢየሱስ በሞት ፊት ሙኋል፤ አልቅሷል። ሶቅራጥስ ደግሞ ስለነፍስ ዘላለማዊነት እየተናገረ ሞትን በእርጋታና ያለፍርሃት ተቀብሎታል።

እንግዲህ ሞት ከሥጋ የመለየትና ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኘት መንገድ ከሆነ ኢየሱስ በፍፁም ሊፈራ አይገባም ነበር፤ ምክንያቱም ከአባቱ ጋር ተመልሶ የመገናኘቱን ዕድል ይሰጠዋልና። ለኢየሱስ ግን ሞት ከእግዚአብሔር ጋር የመገናኛው ሳይሆን የመለያያው መንገድ ነበር። ምክንያቱም እግዚአብሔር የሕይወትም ሁሉ ፈጣሪ ነዋ!

በሶቅራጥስና በኢየሱስ ሞት መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት የሞትን ግሪካዊና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳቤ እንመልከት። በግሪክ አስተሳሰብ የሥጋ ሞት የእውነተኛው ሕይወት ሞት አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ አሳቤ ደግሞ ሞት ማለት በእግዚአብሔር የተፈጠረ ሕይወት ሁሉ ሞት ማለት ነው። «ስለዚህም በትንሳኤ ድል የሚደረገው ሥጋ ሳይሆን ራሱ ሞት ነው» ይላል ኩልማን። የኢየሱስ ትንሳኤ በክርስትና እምነት መሠረታዊ ነገር የሚያደርገውም ይኸው ነው።

መጀመሪያ ወደተነሣንበት ተመልሰን የሞትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ



Scanned by CamScanner

እሳቤ ስንመለከት ሞት ወደዚህ ምድር የመጣው «በኃጢአት ምክንያት» እንደሆነ እንረዳለን:: እግዚአብሔር አዳምን:- «...መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ! ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና» (ዘፍጥ.2:17) ብሎት ነበር:: አዳምና ሔዋን የተከለከሉትን ፍሬ ቢበሉም ዕለቱን አልሞቱም:: ምነው ቢሉ «...ሞትን ትሞታለህ ተባለ እንጂ ትሞታላችሁ አላላቸውም» ይለናል ኩልማን:: "...dying you shall die" ማለት ደግሞ ሂደት ነው:: በኃጢአት ከመውደቃቸው በፊት የሕይወት ዛፍ ቀርቦላቸው ነበር:: ሞት ሲመጣባቸው ከዛፉ ፍሬ እየበሉ ይታደሱ ነበር:: በኃጢአት ሲወድቁ ግን እግዚአብሔር የሕይወትን ዛፍ ከለከለ:: «እግዚአብሔር አምላክም አለ:- እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደአንዱ ሆነ:: አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር...» (ዘፍጥ.3:22):: አዳም የዚያን ቀን መሞት ጀመረ::

የሰው ልጅ ከእንስሳት የተመሳሰለበት የመጀመሪያው ምዕራፍ መሞት የጀመረበት ዕለት ነበር:- ጠቢቡ ሰለሞን እንደተናገረው:- «የሰው ልጆችና የእንስሳ ዕድል ፈንታ አንድ ነው፤ ድርሻቸውም ትክክል ነው፤ አንዱ እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል፤ የሁሉም እስትንፋስ አንድ ነው፤ ሁሉም ከንቱ ነውና፤ ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም...» (መክ.3:19)

የሰው ልጅ ነፍስ ከእንስሳ ነፍስ ጋር አንድ ነው፤ ልዩነቱ የሰው ልጅ ነፍስ ወደ ላይ ስትወጣ የእንስሳ ወደምድር መሆኑ ነው:: በቀጣዩ ምዕራፍም በዚሁ ጉዟችን እንቀጥላለን::



Scanned by CamScanner

# «ብሰማይ ገሃነም ካለ በምድርም ቢኖር አይደንቅም»

ካለፈው ምዕራፍ ጀምረነው የነበረውን «የሞት ጉዳይ» አሁንም እንቀጥልበት። በዕብራይስጡ ሞት "muth" ይሉታል... ይህ ቃል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከ800 ጊዜ በላይ ተገልጿል። ስለሞት የመጀመሪያ ትርጉም ተደርጎ በሚወሰደው ቃል እንጀምር። እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን አትብሉ ያላቸውን ፍሬ በልተው ካገኛቸው በኋላ የሞትን ወደእነሱ መምጣት ለመጀመሪያ ጊዜ ተናገረ።

«ወደመጣህበት መሬት እስክትመለስ ድረስ በፊትህ ወዝ እንጀራን ትበላለህ፤ አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና» (ዘፍጥ. 3፡19)

በዚህ ቦታ የሞትን ትርጉም እናውቃለን። ከአፈር የተሠራው ሥጋ ወደአፈር መመለስ ነው። የነፍስ ሞት የሚባል ነገር የለም ማለት ይሆናል። ከሚጠፋ ነገር ነፍስ አልተሰራችምና ትጠፋ ዘንድ አይቻላትም። አፈሩ ወደአፈር ነፍስም ወደፈጣሪዋ መሆን ነው።

ታዲያ እዚህ ላይም የማትሞተው ነፍስ የመጨረሻዋ መንገድ አንድ አይደለም። ዘላለማዊነት ይጠብቃታል። ዘላለማዊነት (immortality) ቃሉ የመጣው ከግሪክ "athanasia" ሲሆን ትርጉሙ ሞት አልባ (deathlessness) ማለት ነው፤ ስለዚህም የማያቋርጥ ሕይወት ይኖረናል እንደማለት ነው። ይኸ ትርጉም በመጀመሪያ ከሩት ከእግዚአብሔር

ጋር የተገናኘ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ የማይሞት እሱ ብቻ ስለሆነ ነው። ተሞት ደግሞ ለሰው ተሰጥቶ እናያለን፤ ምክንያቱም አለመሞት የሚገባቸው ሰዎች አሉና፤ የእነሱ አለመሞት ግን በዳግም ምፅአት የሚረጋገጥ ነው ይላሉ የሥነ መለኮት ሊቃውንት። በዳግም ምፅአት ደግሞ ድል የሚደረገው ራሱ ሞት እንጂ ሥጋ አይደለም። ከዚህ በኋላ ሁለቱ መንገዶች ይገለጣሉ። አንዱ ከሞት በኋላ የጽድቅና የደስታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የእርግማንና የመከራ ቦታ ነው።

ታዲያ የገነትና የገሃነም መግባታችንን እርግጠኛነት ከሚያሳጡን ነጥቦች አንዱ በገሃነም ላይ የሚነሳ ጥያቄ ይሆናል። ወደታላቁ እንግሊዛዊ ፈላስፋ በርትርናድ ራስል ጥያቄ እንሂድ። ራስል ከ1872-1970 የኖረና በፍልስፍና ሥራዎቹ ታላቅ ከበሬታን ያገኘ እንደነበር ታሪኩ ይነግረናል። ከበርትናድ ራስል ሥራዎች ዋነኛ አትኩሮት ውስጥ ደግሞ ሞት አንዱ ነው።

«ከሞት በኋላ የሚጠብቀንን የገሃነም እሳት የነገረን ክርስቶስ ነው» የሚለን ራስል «ይኸ ደግሞ ቃላት ሊገልፀው የማይችል ጭካኔ ነው» ይላል። «በክርስቶስ የሞራል ባህርይ ውስጥ አንድ ችግር አለ ብዬ አስባለሁ... ይኸውም በገሃነም የማመኑ ጉዳይ ነው። እንደእኔ አስተሳሰብ ስለሰው መልካም የሚያስብ ህሊና ያለው ሰው ስለሰው የዘላለም ቅጣት እንዴት ማሰብ እንደሚችል ይደንቀኛል... ስለዘላለማዊ እሳት ኢየሱስ ሲያስተምር ይኸ ቅጣት የእሱን ስብከት የማይሰሙትንም እንደሚጨምር ተናግሯል...።»

እንደራስል፡- «የሰውን ልጅ ገሃነም እንደሚጠብቀው የሚያስተምር ትምህርት ሁሉ የጭካኔ ትምህርት ነው። በምድራችን ላይ እንዲያውም ጭካኔና ክፋት የበዛው የሰው ልጅ ስለገሃነም ካወቀና ከተረዳ በኋላ ነው። በሰማይ ገሃነም ካለ በምድርም ቢኖር አይደንቅምና» ብሏል።

የራስል አግራሞት ከዚህም ያልፋል። «ምድራዊ አባት የቱንም ያህል ልጁ ክፉና አመፀኛ ቢሆን ጨካኝ እሳት ውስጥ አይጨምረውም።



Scanned by CamScanner

ከምድራዊ አባት በላይ ርኀሩህ አባት ነው የሚባለው «አባታችን» የምንለው እግዚአብሔር ደግሞ እኛን ለመቅጣት የዘላለም እሳት አዘጋጅቶልን ከሆነ «አባት» ብንለውም ፈርተን እንጂ ወደን አይሆንም... ይሁንና በዚህ በእኛ ዘመን በገሃነም ላይ አትኩሮትን ማድረግ እየቀረ በመምጣቱ ሰውና እግዚአብሔር በነፃነት የመቀራረብ አዝማሚያ እያሳዩ ነው...» በማለት ራስል ካስቀመጠ በኋላ «ወደንም ይሁን ፈርተን የምንከተለው እግዚአብሔር ምክንያቱ ገሃነም ከሆነ ደግሞ ገሃነምን መመርመር የግድ ይሆናል» ይለናል...

የ18ኛው ክ.ዘ. አሜሪካዊ የሥነ-መለኮት ሊቅ የነበረው ጆናታን ኤድዋርድስ ገሃነምን ሲስልልን «ሥጋና ነፍስህ ሙሉ ይሆናሉ፤ እንዲት ትርፍ ቦታም አይኖራቸውም:: የሚሞሉትም በእሳት ነው:: ቃላት ሊገልፀው በማይችል ስቃይ ውስጥ ይገባሉ፤ መከራም አይለያቸውም፤ ዕለት ዕለትም የእግዚአብሔር ቁጣ ይጐበኛቸዋል፤ ዓይናቸው፣ ምላሳቸው፣ ክንዳቸውና ፊታቸው በእግዚአብሔር እሳት ያለማቋረጥ ይለበለባል... መጽሐፍ ቅዱስ አንብቤም ይኸ መኖሩን ተረድቻለሁ...» ይላል::

ሌላው እንግሊዛዊ ሰባኪ ቻርለስ ስፐርጃንም በተመሳሳዩ:- «በምድራዊ እሳት ልምምዱ ካለህ በላይ በሰማይም እንዲሁ እንዲጠብቅህ ተረዳ... ሥጋና ነፍስህን ዲያብሎስ በእሳት ለዘላለም ያቃጥላታል...» ብሏል:: ታዲያ የብዙዎቹ ፈላስፎች ጥያቄ «አንድ ሰው ክፉ በመሥራቱ የእግዚአብሔር ወዳጅነት ቢቀርበት የዲያብሎስ ግን ወዳጅ ይሆናል:: ዲያብሎስ ደግሞ ወዳጁን ራሱ ባዘጋጀው እሳት ውስጥ አያቃጥልም:: ይልቁንም አብረው ተዋደውና ተሳስበው ይኖራሉ እንጂ:: ዲያብሎስ እንደእሱ ክፉ አድርገው ወደሰማይ ለሚሄዱት እሳት አዘጋጅቶ ከሆነ ግን ከእግዚአብሔር ጋር ተመሳሳይ ባህርይ ሊጋራ ነው እንደማለት ይሆናል» ይላሉ::

ይኸን አገላለፅ የማይቀበሉት ደግሞ አሉ:: «የገነትም ሆነ ገሃነም



Scanned by CamScanner

ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው» ይሉናል:: ሮበርት ፐተርሰን - "Hell on Trial: The Case for Eternal Punishment" በተሰኘው መጽሐፉ ሲናገር:- «ገነትም ሆነ በገሃነም አዛገፍ እግዚአብሔር ነው... በገነት የፍቅር አባት ሆኖ በገሃነም ደግሞ በመዓቱ ቁጣ ተሞልቶ ይገኛል... ገሃነም ደግሞ መጨረሻ የለውም... በዚያ መጨረሻ የሌለው ቁጣውን ያወርደዋል:: ዲያብሎስ ግን የገሃነም አባል እንጂ አዛዥ አይደለም» ይላል:: እንግዲህ እግዚአብሔር የማይታዘዙትን በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ከቀጣ «ጠላትህን ውደድ፣ የሚረግሙህን መርቅ፣ የሚያሳድዱህን ባርክ...» የሚለው ትዕዛዝ ለትዝብት ካልሆነ ራሱም አይፈፅመውም ማለት ነው::

በብሉይ ኪዳን ገሃነም በዋነኛነት የሚገኘው በሁለት ቦታዎች ሲሆን ይኸውም በኢሳይያስ 66:22-24 እና በዳንኤል 12:1-2 ላይ ነው::

«...እንዲህ ይሆናል፥ በየመባቻውና በየሰንበቱ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በፊቴ ይሰግድ ዘንድ ዘወትር ይመጣል፥ ይላል እግዚአብሔር:: ወጥተውም በእኔ ያመፁብኝን ሰዎች ሬሳቸውን ያያሉ፥ ትላቸው አይሞትምና፥ እሳታቸውም አይጠፋምና፥ ለሥጋ ለባሽም ሁሉ አስፀያፊ ነገር ይሆናሉ» (ኢሳ. 66:22-24)

በተመሳሳዩ ነቢዩ ኢሳይያስ በምዕራፍ 14 ላይ ወደ ሲዖል የምትወርድ ነፍስ «በበታቿ ትል ተነጥፎ፣ በላይዋ ደግሞ ትል መደረቢያዋ ሆኖ እንደተዘጋጀላት» ይነግረናል:: ገሃነም የገባ ሰው የሚቀጣው በእሳት ሲሆን ትልና ብል ደግሞ አብሮ ይታዘዝለታል:: ታዲያ «የገሃነምን ትሎች ከሌሎቹ የትል ዘሮች ለየት የሚያደርጋቸው እሳቱ እነሱን አለማቃጠሉ ነው» የሚል አስገራሚ አስተያየት የሚሰነዝሩም አልታጡም::

የገሃነምን ጥያቄ ገታ አድርገን የሰው ልጅ ለመሆኑ ለገሃነም የተገባ የሚሆነው መቼ ነው? የሚል ጥያቄ መሰንዘሩ በራሱ ደግሞ የሚያሳየን ነገር ይኖራል:: «ወንድሙን ደንቆሮ ብሎ የሚሳደብ የገሃነም እሳት ፍርድ ይገባዋል...» ሲል ኢየሱስ በርትራንድ ራስል ደግሞ እዚህ ቦታ



Scanned by CamScanner

ይመጣና:- «ድርጊቱና ቅጣቱ ግን ፈፅሞ አልተመጣጠነም» ይለናል:: «ከዚህ አንድ የምንረዳው ነገር ግን ገሃነም ካለ የሚያደርሰው ጥፋት የሚለካው በዘላለማዊነቱ ነው» ይላል:: ይኸንንም በምሳሌ ሲገልፅልን:- «በይሁዳ 7 ላይ «ሰዶምና ገሞራ... በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል» ማለቱ በራሱ የሚያሳየን የከተሞቹን ለዘላለም መጥፋት እንጂ ለዘላለም መቃጠል አይደለም:: ከዚህ ከተነሣን ገሃነም የምትገባ ነፍስም ለዘላለም ትጠፋለች እንጂ ለዘላለም አትቃጠልም» ይለናል::

በሌላ ቦታ ኢየሱስ የሰውን ልጅ ለገሃነም እሳት የተገባ የሚያደርገው ያለውን ተካፍሎ አለመብላቱ ነው ብሏል:: በዚህም ላይ ራስል አስተያየት ሲሰጥ «ያልሰራ አይብላ» የሚለውን የአባቱን ሕግ በመጠኑ ሳይረሳው አልቀረም ይለናል:- «በዚህ አሳቤ ከተነዳን ደግሞ ገሃነም ለመግባት አስቀድሞም የተፈጠርን ነን እንደ ማለት ነው» ካለ በኋላ «ሐዋርያው ጳውሎስ ደግሞ የገሃነም ፍርድን የሚያያይዘው ከኢየሱስ ተመልሶ መምጣት ጋር ነው:-«ክፉዎች ለዘላለም ጥፋት» እንደተጠበቁና ይኸም የሚሆነው በኢየሱስ ምፅአት ቀን እንደሆነ የሚነግረን ጳውሎስ በእሱ የፍርድ ቀን ብዙዎች ለመከራ ለቁጣው እንደታጩ አስጠንቅቆን ይሄዳል... እንግዲህ ገሃነም የምንገባው በምፅአት ቀን ወይስ የሞትን ዕለት?» በማለት ራስል ጠይቆ:- «ለእኔ ግን የገሃነም እምነቱ እንኳን ቢኖረኝ እንደአዳምና ሔዋን ከገነት መባረር ውጭ የተለየ እምነት አይኖረኝም» ይላል::

ትልቁ ጥያቄ በበርትራንድ ራስል የሚነሳው ግን ይኸ ነው:- «ገሃነም ዘላለማዊ ነው:: የዘላለማዊው ገሃነም ፈጣሪና ጌታ እግዚአብሔር ከሆነና በዚያም ለዘላለም ከተገኘ ገሃነም ደግሞ የማያቋርጥና ዘላለማዊ ነው ካልን ገነትን ታዲያ ማን ሊጠብቅለት ነው?» በማለት ይጠይቃል::



Scanned by CamScanner

# «ዓይን ማየት ያልቻለው ፈጣሪውን ብቻ ነው»

**ተዋሉ የጆን ዊዝደም** (1904-1955) የፍልስፍና ሥራን በመጠኑ እንዲቃኝ ዘንድ እወዳለሁ:: የዊዝደም ስም እጅግ ረዥም በመሆኑ እሱም ሆኑ ጓደኞቹ የሚጠቀሙበት ስያሜ ጆን ዊዝደም ሆነ እንጂ ትክክለኛ ስሙ አለመሆኑ ይታወቅልኝ:: በካምብሪጅ ዩኒቨርስቲ እጅግ ጉበዝና የተለየ አእምሮ አላቸው ከሚባሉት ተማሪዎች ዊዝደም ታላቁን ሥፍራ እስከዛሬ ይሰጠዋል:: የዚህ ሰው የመጀመሪያ ሥራ የሆነው "Philosophical Perplexity" በፍልስፍና ታሪክ ጉልህ ሥፍራ የሚሰጠው ሥራ ተደርጎም ተወስዶለት ነበር:: ገና በመጀመሪያ ሥራው እንዲህ ዓይነት መደነቅን ያገኘው ዊዝደም ከዚያ በኋላ ለኅትመት ያበቃቸው ተከታታይ የፍልስፍና ሥራዎቹ ከፍተኛ ዝናን ያተረፉለት ሲሆኑ አማልክትን አስመልክቶ "Gods" በሚል ርዕስ ያቀረበው ሥራው ግን በእርግጥም ልዩ ሰውነቱን ያረጋገጠ ሆነ:: የዊዝደምን የአምላክና አማልክት አገላለፅ በመጠኑ በራሳችን አገላለፅ እንቃኘው::

«አንድ በእግዚአብሔር መኖር የማያምን ሰው ከምንም በላይ የሚደንቀው ነገር ቢኖር የሚያምን ሰው ሲፀልይ ማየት ነው» የሚለው ዊዝደም «ለምሳሌ በድርቅ ጊዜ ለዝናብ ወደአምላኩ የሚፀልይ ሰው ብታይ ዝናብ ለዚያ ሰው እንደማገኛውም የተፈጥሮ ክስተት ሳይሆን በእሱ አምላክ ፍቃድና ቸርነት

ብቻ የሚመጣ ነገር መሆኑን ነው። ስለዚህ የሚያምን ሰው ሲፀልይ እግረ መንገዱን አምላኩንም እየፈተነ ነው ማለት ነው። ኤልያስ በቂርሜሎስ ተራራ ወደአምላኩ ሲፀልይ ሌሎች ደግሞ ወደአማልክቶቻቸው ይፀልዩ ነበር። በዚያ መንገድ ይገኝ የነበረው የፀሎት ምላሽ እምብዛም ዛሬ የሚታይ ባለመሆኑ ኤልያስ የፀለየለትን አምላክ ማግኘቱ ለእሱ ዘመን ብቻ የተገባ ይሆናል...» ይላል ዊዝደም።

«ይሁንና በሚያምንና በማያምን መካከል ያለው አንዱ ልዩነት የመጠበቅና (expectation) ያለመጠበቅ ጉዳይ ነው። የሚያምነው ለፀሎቱ ምላሽ የሚጠብቀው ነገር አለ። መጠበቅ ደግሞ በተስፋ የተሞላ ነው። ይኸ መጠበቁ ደግሞ እስከሰድሚው ፍፃሜም ድረስ ሊዘልቅ ይችላል። ተስፋው ከሞላ በኋላም በኋለኛው ዓለምም ሊመለስለት እንደሚችል ያምናልና። የማያምነው ደግሞ ከዚህ ይለያል። እሱም በመጠበቅ የተሞላ ሆኖ ነገር ግን መጠበቁ ከውስጡ ግፋ ካለም ከዚሁ ዓለም እንጂ ሌላ የሚጠብቀው ተስፋ የለውም። ለማያምን ሰው እምነቱ ዓይነቱ ብቻ ነው...»። ጆን ዊዝደም በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ያስቀመጠውን ትንታኔ በምሳሌ ሲያስደግፈው፦ «አንድ ሕፃን አባቱ አጠገብ መቀመጥ የሚፈልግበት ሁለት ምክንያቶች ይኖሩታል... በመጀመሪያ ጥፋት አጥፍቶ ከሆነ እንዳይቀጣው በመፍራትና በመስጋት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከሚያስፈራ ነገር ጥበቃ እንዲያደርግለት ነው። ሕፃኑ አባቱ ሲሞት ግን ጥበቃንም ሆነ ቅጣት አይጠብቅም። ነገር ግን አባቱ በሕይወት ባይኖርም በሌላ ዓለም እንደሚኖርና የሚያወራውን እንደሚሰማው የሚያደርገውንም እንደሚያየው በሌሎች ይነገረዋል። ሕፃኑ በሁለት ሐሣብ ተይዞ ያድጋል... በምድር ላይ የሚሰራውን እንደሚያየው ብሎም ከሞት በኋላም ቢሆን አባቱ ወደሚገኝበት ዓለም እንደሚሄድ...

«እንደዚሁ በእግዚአብሔር የሚያምንም ሰው ሲሞት እንደማያምነው ዓይነት ሞት አይቀበልም። ምክንያቱም በእግዚአብሔር ማመን ማለት በሌላ ዓለም እንደማመን ማለት ነውና። የሚያምን ሰው ሲሞት ወደሌላ



Scanned by CamScanner

ዓለም እሄዳለሁ ብሎ ያምናል... ስለዚህም ከሞት በኋላ መጠበቅ ስላለው ለሞቱ ለራሱ ዋጋ ይሰጠዋል:: የማያምን ሰው ግን እንዲህ አይደለም:: ከሞት በኋላ የሚጠብቀው ነገር የለም:: ስለዚህ ለእሱ ሞት የነገር ሁሉ ፍፃሜ ነው:: የሁለቱ ልዩነት ግን አንድ ነው:: የሚያምነውም የማያምነውም አንድን ነገር ተመለከቱና ሁለት ትርጉም ሰጡት...

«ለምሳሌ» ይለናል ዊዝደም «ሁለት ሰዎች አንድን መጽሐፍ እንብበው በውስጡ ስላለች አንዲት ገፀ ባህርይ ይወያያሉ:: ይኸች ገፀ ባህርይ ለአንዱ ክፉና ጨካኝ ሴት ስትሆን ለሌላው ደግሞ አፍቃሪና ደግ ሆና ተገኘች:: በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ሲገለፅ ታዲያ በሴቷ ውስጥ ለአንዱ የታየው ነገር ለሌላው አልታየውም ማለት ይሆናል:: የእምነትም ነገር እንዲሁ ነው:: የሚያምነው የማያምነውን 'ማየት ቢያቅትህ እግዚአብሔር የለም ትላለህ' ሲለው የማያምነው ደግሞ የሚያምነውን 'እግዚአብሔርን የማላምነው ማየት ስለሚያቅተኝ ሳይሆን ራሱ ስለማይታይ ነው...'» ይላል:: እዚህ ላይ ታዲያ ጥያቄ እናነሳለን:: «እግዚአብሔር ዓይንን ለሰው ልጅ ፈጠረ... ዓይንም ከተፈጠረበት ቀን ጀምሮ የተፈጠረበትን ዓላማ እየፈፀመ ይገኛል... ዓይን መፈፀም ያልቻለው አንድ ነገር ቢኖር የፈጠረውን ራሱን ማየት አለመቻሉ ነው:: እንዲያይበት እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ዓይንን ከፈጠረ በኋላ ራሱ እግዚአብሔርን ማየት አልቻለም:: ስለዚህም በፈጠርከልኝ ዓይን አንተን ማየት ካልቻልኩ የለህም ማለት ነው በማለት ወሰነ::

እንደዊዝደም ገለፃ እንግዲህ:- «ከዚህ በላይ ማመን ከወዴት ይገኛል?» ይላል:: «እንዲያውም በእግዚአብሔር የሚያምን ሰው ዓይን የተፈጠረበት ምክንያት አልገባውምና ራሱ እግዚአብሔርም ሊያዝንበት ይችላል...» በማለት ወደሌላ ምሳሌ ያሸጋግረናል::

ሁለት ሰዎች ለብዙ ዓመታት ትተውትና ረስተውት ወደነበረው የአትክልት ቦታቸው አንድ ማለዳ ተመልሰው መጡ:: የአትክልት ቦታው ምንም እንኳን በአረም ተወርሶ ቢያገኙትም በውስጡ ግን በሚገባ



Scanned by CamScanner

እንክብካቤ የተደረገለት አትክልት በቅሎ ማየታቸው ደግሞ አስደነቃቸው:: የመጀመሪያው ሰው:- «በዚህ ቦታ አትክልተኛ ይኸን እንደተመለከተ ማለት ነው» አለ:: ሁለተኛው ሰው ደግሞ በሌሊት እየመጣ ይሰራል «አትክልተኛ ቢመጣ ኖሮ ሰው ይሰማው ነበር፤ ከዚያም በላይ ለአትክልቱ የሚያስብና የሚሰራ ሰው ይኸን ሁሉ አረም ዝም ብሎ አይመለከተውም...» አለ:: የመጀመሪያው ሰው ግን በሐሣቡ ፀና... «አረሙን ትተህ ለምን አትክልቶቹን አትመለከትም... አትክልት ያለአትክልተኛ እንዴት እንዲህ ሊበቅል ይችላል?» አለ:: ሁለቱም ሰዎች ስላልተስማሙ የአትክልት ቦታውን እንደገና መመርመር ጀመሩ...

«ነገር ግን ሁለቱም በራሳቸው እምነት ፀኑ:: የመጀመሪያው በአትክልተኛ መኖር ሲያምን ሁለተኛው ደግሞ «አትክልቶቹ በራሳቸው የበቀሉ አንጂ ያሳደጋቸው የለም» አለ::»

ጆን ዊዝደም በዚህ ገለፃው:- «ዓለምን እንደዚህ የአትክልት ቦታ ብንወስዳት የአትክልቱ መኖር አማኞችን የአረሙ መኖር ደግሞ የማያምኑትን እንደፈጠረ እናስተውላለን:: የሁለቱም እምነት የመጣው ግን ከማየት ነው... ለማየት የምንፈልገው ደግሞ ለማየት ያበቃንን ነው:: በዚህ ሂደት ፍለጋው ቀጠለ...

«እነሆም እግዚአብሔር አለፈ÷ በእግዚአብሔር ፊት ትልቅና ብርቱ ነፋስ ተራሮቹን ሰነጠቀ፤ ዓለቶቹንም ሰባበረ÷ እግዚአብሔር ግን በነፋሱ ውስጥ አልነበረም፤ ከነፋሱም በኋላ የምድር መናወጥ ሆነ÷ እግዚአብሔር ግን በምድር መናወጥ ውስጥ አልነበረም፤ ከምድር መናወጥ በኋላ እሳት ሆነ፤ እግዚአብሔር ግን በእሳቱ ውስጥ አልነበረም:: ከእሳቱም በኋላ ትንሽ የዝምታ ድምፅ ሆነ:: ኤልያስም ያን በሰማ ጊዜ ፊቱን በማጎናፀፊያው ሸፈነ:: ወጥቶም በዋሻው ደጃፍ ቆመ...» (1ኛ. ነገሥ. 19:11-13)

ዛሬም እግዚአብሔርን ፍለጋ ቀጥሏል:: ብዙዎች በእሳት ውስጥ አንዳንዶችም በመናወጥ ውስጥ የቀሩት ደግሞ በነፋስ ውስጥ እየፈለጉት ነው:: ነገር ግን እስከዛሬ ከኤልያስ በቀር ያገኘው የለም::



Scanned by CamScanner

# «ፍቅር ከሌለው አምልኮ ፍቅር ያለበት ኃጢአት ይበልጣል»

ሐዋርያው ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲናገር፡- «በሰዎችና በመላዕክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሽዋሽዋ ጽናጽል ሆኛለሁ። ትንቢትም ቢኖረኝ፤ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትንም ሁሉ ባውቅ፣ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ...» ይላል።

ለማወቅ የምንፈልገውን ነገር ሁሉ በመጀመሪያ እናፈቅረው ዘንድ ይገባል። ለማንኛውም የሕይወት መስክ የስኬቱ ቁልፍ ደግሞ ፍቅር ነው። ዳ.ቪንቺ. ስዕልን ከምንም በላይ አፈቅራት፤ ታወቀባትም። ሞዛርት ከሙዚቃ ጋር በፍቅር ወደቀ፤ ከፍ ከፍ አደረገችው። ለሼክስፒር ሥነ-ጽሑፍ ፍቅረኛው ሆነች፤ በስሟም አነገሣችው። ሶቅራጥስ በፍልስፍና ፍቅር ተሰቃየ፤ ያለእሱም መጠራት አቆመች። እውነተኛ ታላቅነት እንግዲህ የሚመጣው ከማፍቀር ነው።

ኢየሱስም ከሕግ ሁሉ በላይ የሆነውን ሕግ ለተከታዮቹ ነገረ፡- «እግዚአብሔር አምላክህን በፍፁም ልብህ፣ በፍፁም ነፍስህና በፍፁም ኃይልህ ውደድ...» ዞሮ ዞሮ ማፍቀር ነው። ብዙ ማፍቀር ስትችል እግዚአብሔርን መምሰል ትጀምራለህ። ይኸ ደግሞ የሕግ ሁሉ የበላይና



Scanned by CamScanner

ፃነቱ
የመጀመሪያው ሆኑ። እግዚአብሔርን ባፈቀርነው መጠን ደግሞ እያወቅነው ትመጣለህ።

ማፍቀር ስትችል ያፈቀርከውን ነገር ማወቅ ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን ወዳፈቀርከው ነገርም መሸጋገር ትጀምራለህ። በዚህም አፍቃሪም፤ ተፈቃሪም፤ ፍቅርም አንድ ይሆናሉ። በፍቅር መንገድ መስዋዕት የሚሆነው እውነተኛ አፍቃሪ ብቻ ነው። በዚሁ መንገድ እየተጓዝን የፍቅርን ስረ መሠረት በመጠኑ እንመርምር።

የጥንቱ ሰው ስለፍቅር የሚያውቀው ነገር የለም። እንዲያውም ፍቅር የሚለው ቃል ራሱ የቅርብ ጊዜ የሰው ልጅ ዕድገት የፈጠረው ነገር ነው። በዚህ አካሄድ ፈላስፎቹ ይስማማሉ። እንዲያውም ወንድ ሚስት ሲያገባ ከማሳው ቀጥፎ ወደቤቱ ከሚወስደው እሸት የተለየ ስሜት አይኖረውም ነበር ይሉናል። ለግሪኮቹ ደግሞ ፍቅር ከዚህ ይለያል። ሥጋ ያለነፍስ በድን እንደሚሆነው ሁሉ ከፍቅር የተለየች ነፍስም ዕጣ በድን መሆን ነው ይላሉ። ኸር.ሙስ ስለፍቅር የተናገረውን እዚህ ላይ እናንሣ፡- «በዓለም ላይ ያሉ ወንዶች ሁሉ ውሸታሞች፣ ከሃዲዎች፣ አጭበርባሪዎች፣ ሸፍጠኞችና አስመሳዮች ሲሆኑ ሴቶቹ ደግሞ ከንቱዎች፣ አርቲፊሻሎችና ግብዞች ናቸው። እነዚህን ሁለት የማይመሳሰሉ ነገሮች ግን ፍቅር የማዋሃድና አንድ የማድረግ ኃይል አለው» ብሏል።

«እዚህ ላይ የሁለቱን መሠረታዊ ልዩነት ግን እንዘንጋ» የሚለን ደግሞ ዊሊያም ጀምስ የተሰኘው የቅርብ ዘመን የዓለማችን ፈላስፋ፡- «በማንኛውም ፍቅር ውስጥ ጦርነት አለ። ሴቷ መዋጋቱንም ሆነ ማፈግፈጉን በሚገባ ስታውቅበት ወንዱ ግን ጦርነት ውስጥ መሆኑን እንኳን ከነአካቴውም አያውቀው... ለዚህም ነው የሚጠጣ ካገኘ ባይጠማውም ይጠጣዋል... ሴት ካየም ባያፈቅርም ፍቅርን መሥራት ይችላል። ሴቷ ግን ቢጠማት እንኳን የምትጠጣውን ትመርጣለች... ከማፍቀሯም በላይ መፈቀሯን አጥብቃ ትከታተላለች» ብሏል።



Scanned by CamScanner

ይኸን ስሜቷን ደግሞ በሚገባ የተረዳላት አምላኳ ነው፡፡ እሷን የፈጠረ ቀን ቁንጅናንም አብሮ ፈጥሯልና፡፡ ለቁንጅናዋ ደግሞ የአዳምን ጉልበት የማብረክረክና የማንበርከክ ኃይልን በውስጡ አስቀመጠለት፡፡ የወንዱ ጉልበት እንግዲህ በሴት ቁንጅና ሲብረከረክ ስናይ ፍቅር እንለዋለን፡፡ ለቁንጅና የሚከፈል ዋጋ መሆኑ ነው፡፡ የመጀመሪያውን የፍቅር ምጢር የገለጠች ሔዋን ናት፡፡

እግዚአብሔር አንድ ቀን በአትክልቱ ቦታ ሲንሸራሸር አዳምን በብቸኝነት ተክዞ ያገኘዋል... የአዳም ችግር ገባው፡፡ ወዲያውኑም «ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም» አለና አዳምን በሰመመን ውስጥ ከተተው፡፡ አዳም ከሰመመኑ ሲነቃ አጠገቡ ሔዋንን የመሰለ ቆንጆ ራቁቷን ቆማለች፡፡ አዳም እንዳይደነግጥባትና እንዳይጠላት አምላክ «ከአንተ ውስጥ ነው ያወጣኋት» አለው፡፡ ከአምላኩ ጋር አልተከራከረም፡፡ የተሰጠውን ይዞ ሄደ፡፡ አፈቀራትም፡፡ ብላ ያለችውንም በላ፡፡ የእግዚአብሔር ቁጣ ይኸን ጊዜ ነደደ፡፡ «ማን ብላ አለህ?» አለው፡፡ «አንተ የሰጠኸኝ ሴት» አለ አዳም፡፡ እግዚአብሔር መልስ የሚሰጠውን አይወድም... ሞት ፈርዶበት ሄደ፡፡ ለሴቷ ደግሞ በተጨማሪ ምጥ አዘዘላት፡፡ እግዚአብሔር ለዘመናት የደበቀባቸውን የፍቅር መሣሪያ ግን በሔዋን አማካኝነት የዚያን ዕለት ተገኘ፡፡ ለዚህም ነው ፍሬውን ሲበሉ «እርቃናቸውን» የመሆናቸው ጉዳይ የተገለጠው፡፡ የፍቅር ጉዞአቸውን የዚያን ቀን ጀመሩ፡፡ ፍቅር ከሌለበት አምልኮ፤ ፍቅር ያለበት ኃጢአትም የተሻለ ነው አሉ፡፡

የእስራኤል ንጉሥ የነበረው ዳዊት አምላኩን ለመውደዱ በራሱ በእግዚአብሔር ተመስክሮለታል፡፡ «እንደልቤ...» ይለው ነበር፡፡ አንድ ቀን ዳዊት በቤተመንግሥቱ በረንዳ ላይ ቆሞ አንዲት ቆንጆ አየ፡፡ የአዳምን ጉልበት የሚያብረከርከውና የሚያንበረክከው ያ ኃይል በዳዊትም ላይ መጣ፡፡ አዳምን የአምላኩን ትዕዛዝ ያስረሳው የሔዋን ቁንጅና እንዲሁ ለዳዊትም የተመለከታት ሴት የታማኝ ጓደኛው ሚስት መሆኗን



Scanned by CamScanner

አስረሳው። ይሏት «ወደቀ»። አሁንም የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደ። የራስህ ብዙ በጎች ሞልተው ሳለ የደሀውን አንዷት በግ ነጥቀህ በልተሃልና ኃጢአተኛ ነህ አለው። ዳዊት ቢያዝንም ውሸቱን ነበር። እግዚአብሔር በሞት አልቀጣውም። መቼም መሞቱ አይቀርም በማለት በልጁ አዋረደው። ለዳዊት ከእግዚአብሔር ቁጣ ይልቅ ከሴቲቱ መለየት አስፈራውና ሚስቱ አደረጋት። የኋላ ኋላ እግዚአብሔር በዳዊት የኀላማ ዕናት የተደሰተ ይመስለኛል። ባይደሰትማ ሰሎሞን ባልተገኘ ነበር።

ፍቅር ከኃጢአት ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም የሚሉት የዘመናችን ፈላስፎች «የሰው ልጅ የፍቅር ውሃ እየጠጣ ባይለመልም ኖሮ በአዳም ዘመን ደርቆ በረገፈ ነበር» ይላሉ። ሰው ከአምላኩ ጋር ሳይቀር ተገዳድሮ ለመስዋት የቀረበለት ነገር ቢኖር ፍቅር ብቻ ነው። እንዲያውም ላፈቀራት ሴት ለመሞት ያለውን ቁርጠኝነት ለአምላኩ የለውም። ለዚህም ነው ፍቅር ቤቱን የሠራበት ልብ ዕድለኛ ነው የሚሉት። ዓረቦች ደግሞ የዓለምን ጭንቀት ከትከሻህ ላይ የሚጥልልህ ፍቅር ነው ይላሉ። ፍቅር እንደ መብረቅ ነው፣ ትግስትና ይሉኝታ በፊቱ አመድ ይሆናሉ። ፍቅር የያዘውን ሰው ብትተቸው በፍቅሩ ልክ ለአንተ ደግሞ ጥላቻን ታተርፋለህ። አንድ ከዓረቡ ዓለም ያገኘናትን ታሪክ እንመልከት።

ከሩቅ ዘመን በፊት በመካከለኛው ምሥራቅ አንድ በእግዚአብሔር ፍቅር የነደደ ሰው ነበር። የዚህን ሰው ፍቅር የተመለከተ በራሱ ፍቅርን አለማወቁን ይረዳ ነበር ይላሉ። ቀንና ሌሊት የሚያስበውም የሚያሰላስለውም ስለሚያፈቅረው አምላኩ ነው። አንድ ቀን ግን የዚህ ሰው ፍቅር ከቁጥጥሩ ውጭ ሆነና ከቤቱ፣ ከሥራው፣ ከዘመዶቹ ተለይቶ ሄደ። ሰውዬው የሚሄድበትን የሚያውቅ በፍቅሩ ያበደለት አምላኩ ብቻ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ደግሞ ራሱን መርሳት ጀመረ። አንድ ቀን ጥንት የሚያውቀው ጓደኛው በዱር ውስጥ ያገኘው ይኸ ሰው ልብሱ በላዩ ላይ አልቆና ሥጋው ከአጥንቱ ተጣብቆ ስለነበር እጅግ ደንግጦ ምን እንደነካው ቢጠይቀው፡- «ስለራሴ ማሰብ ከጀመርኩማ የማፈቅረውን አምላክ ጊዜ



Scanned by CamScanner

ሊሸማብኝ ሆነ፤ እንዲያውም ከአንተ ጋር አሁን ሳወራ አምላኬን ረሳሁ...» በማለት ጥሎት ሄደ:: የምታፈቅረውን ሳታስብ ያሳለፍከው ጊዜ ሁሉ ከሕይወትህ የባከነ ጊዜ ነው:: በነገራችን ላይ እውነተኛ አፍቃሪ ለጥላቻ ጊዜ አይኖረውም:: በሱፊዝም «ሰይጣንን የምትጠላ ከሆነ፤ እግዚአብሔርን ከምትወድበት ጊዜ ቀንሰህ መሆኑን አትጠራጠር» እንደሚሉት ነው::

በዚህ ምድር ላይ ለጆሮአችን የሚጥም ድምፅ ቢኖር የምናፈቅረው ሰው ድምፅ ብቻ ነው:: ለእግዚአብሔርም ቢሆን እንዲሁ ነው:: እግዚአብሔር የሚወደው ሰው ሲፀልይ ፀሎቱን ቶሎ አይመልስለትም ይባላል:: ይልቁንም ድምፁን በመስማት ይደሰታል:: የክፉ ሰው ፀሎት ግን ምላሹ በፍጥነት ነው:: ለእግዚአብሔር ጆሮ ድምፁ ይሻክረዋልና:: አንድ ቀን ሙሴ በመንገድ ሲሄድ ከሰይጣን ጋር ተገናኙ:: ሙሴም:- «ሰይጣን ሆይ! እግዚአብሔርን ትወደዋለህ?» አለው:: ሰይጣንም:- «እግዚአብሔር ሰውን መውደዱ በጨመረ ቁጥር የእኔም ፍቅር እንዲሁ ይጨምራል» አለ:: መሴም «እንዲህ ከሆነማ ታስታውሰዋለህ ማለት ነዋ?» በማለት ጠየቀው:: ሰይጣንም:- «የለም! እሱ ነው እኔን የሚያስታውስ:: ምክንያቱም እርግማኔ በአንተ ላይ ለዘላለም ይኖራል ብሎኛል» አለው:: ሙሴም:- «ሰባት መቶ ሺህ ዓመታት አገልግለኸው እንዴት እንዲህ ረገመህ?» አለው:: «ከዚያ ሁሉ ዓመት በኋላማ የአገልግሎቴ ዋጋ ስላላረካኝ ፍቅሬን ከእሱ ይልቅ የእሱ በሆነው ላይ አዞርኩ...» በማለት መለሰለት:: «ቢሆንም አልከሰርክም... ክፉና ደጉን የመለየት ዕውቀት አግኝተሃል...» አለው:: በእግዚአብሔር ፍቅር የክፉ ዕውቀት የለም:: ለዚህም ነው ሔዋን የሰይጣንን የብዙ ሺህ ዓመት ድካም በጥቂት ዓመታት አግኝታ ለአፍቃሪዋ ያካፈለችው:: የፍቅርን ምስጢር የገለፀችልን ሔዋን ስሟ ለዘላለም የተባረከ ይሁን::



Scanned by CamScanner

# የይሁዳው አገረ ገዥ የረሳው ነገር

የታዋቂውን ደራሲና ፈላስፋ አናቶሊ ፍራንስ ምርጥ ድርሰት የሆነውን "The Procurator of Judea" በአጭሩ ልተረጉማት ወደድሁ::

* * *

ኢሊየስ ላሚያ ወደአቴና ለፍልስፍና ትምህርቱ ሲጓዝ በሃያ አራተኛ ዓመቱ መገባደጃ ላይ ነበር:: የፍልስፍና ትምህርቱን እንደነገሩ ተምሮ ከጨረሰ በኋላ በሮም ኑሮውን ሊመሰርት አቅዶ ወደዚያው ተጓዘ:: ነገር ግን በዚያ የገጠመው ሕይወት ቀላል አልነበረም:: በወቅቱ የነበረው የወንጀለኞች ቡድን ውስጥ ሳይወድ ገባበት:: በዚህ ድርጊቱም ተይዞ ጉዳዩ ከንጉሡ ቄሳር ዘንድ ደርሶ ከተመረመረ በኋላ ከሮማ እንዲባረር ተፈረደበት:: ከዚያ በኋላ የነበሩትን አሥራ ስምንት የስደት ዓመታት አንፆኪያ፣ ቄሳርያ፣ አርመንያ፣ ሶርያ፣ ፍልስጥኤም እንዲሁም ኢየሩሳሌም በመጓዝ አገባደደውና የቄሳርን ሞት ሲሰማ በቃዩስ ዘመን ተመልሶ ወደሮማ የመግባት ፍቃድ ተሰጠው::

ወደሮማ ሲመለስ ግን ራሱን ከቀድሞ ድርጊቱ ገትቶ በብቸኝነት ለማሳለፍ ወሰነ:: ጊዜውንም ከቀደምት የፍልስፍና ሥራዎች ጋር በማቆራኘት ይተጋና መዝናናትም ሲፈልግ ከራሱ ጋር በሚያደርገው ጨዋታ ብቻ ያሳልፍ ነበር:: አንድ ቀን ላሚያ ስድሳ ሁለተኛ ዓመቱን



Scanned by CamScanner

ዝብሬ ከአንድ ወር በኋላ እንደልማዱ መንፈስን ማራኪ በሆነው የባይ ውሃ አቅራቢ በእግሩ ሲንሸራሸር ሰዎች በብዛት የተሰበሰቡበትን አንድ የከፍታ ቦታ አስተዋለ፡፡ ካለወትሮው ወደ እነዚያ ሰዎች ሄዶ የመቀላቀል ፍላጎትም አደረበት፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላም በመካከላቸው ተገኝቶ የሚሆነውን ለመከታተል በዓይኖቹ ዙሪያውን በሚያማትርበት ወቅት ከዚህ በፊት የለመደውና እንግዳ ያልሆነበትን ፊት አስተዋለ፡፡ የተመለከተውን ፊት ለማስታወስ አፍታም አልወሰደበትም፡፡ ይልቁንም የሰውዬው ማንነት ሲታወሰው ድንጋጤም ደስታም አርበተበተውና ሰውዬው ወደቆመበት አቅጣጫ ሮጠ፡፡ ሰውዬውም የላሚያን ወደእሱ መሮጥ ተመልክቶ አጠገቡ እስኪደርስ ማንነቱን ለማስታወስ ሞከረ፡፡ ነገር ግን አስታውሶ ሳይጨርስ ላሚያ አጠገቡ ደረሰና በጩኸት፡- «ጲላጦስ... ጲላጦስ...» በማለት ተጠመጠመበት፡፡ ላሚያ የጲላጦስ ግራ መጋባትን ወዲያውኑ ተረድቶ፡- «ጲላጦስ ወዳጄ! ረሳኸኝ፤ ወዳጅህ ኢሊየስ ላሚያ ነኝ እኮ! ፀጉሬ ሸብቶ፣ ጉንጮቼ ጉርጉደው ብትመለከት ልትዘነጋኝ አይገባም...» አለ፡፡

ጲላጦስ የጥንቱ ጓደኛውን ወዲያውኑ አስታውሶ በተራው ጮኸና አቅፎ ሳመው፡፡ «ከሃያ ዓመታት በኋላ እንደገና መገናኘታችን በጣም ዕድለኞች ነን፡፡ የይሁዳ ገዢና የቂሳር መልዕክተኛ ሆኜ በዚያ አስጨናቂ የኢየሩሳሌም ከተማ አይሁድ የፈጠሩብኝን መራርና አስከፊ ሕይወት በአንተ ጓደኝነት ተወጥቼዋለሁ... ነገር ግን አሁን አረጀህ፡፡ ይሁንና አሁን ያለፈውን ታሪካችንን የምናወጋበት ዘመን ላይ ደርሰናልና ልንደሰት ይገባል» አለ፡፡

ላሚያ ጲላጦስ ለእሱ የነበረውን ደግነትና ርኅሩኅነት በተለይም የገንዘብ ችሮታውን አስታውሶ ማመስገን ሲጀምር ጲላጦስ አቋርጦት፡- «ስለማንኛውም ደግነቴ አታንሳብኝ፡፡ ይልቁንም ከእኔ የገንዘብ ደግነት ይልቅ የአንተ ጓደኝነት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው...» አለው፡፡

ላሚያ ይኸን ተከትሎ፡- «የሆነስ ሆነና አማልክትህ ፍላጎትህን

ሐሣብህን አሟሉልህ? ከይሁዳስ ከተመለስክ በኋላ ኑሮህ እንዴት ነው?» አለው::

ጲላጦስም «አሁን ኑሮዬን የመሰረትኩት በሲሲሊ ግዛት ነው:: የተደራጀ ሀብትም አለኝ፤ በቅርቡ ባሏ በሞት የተለያት ሴቷ ልጄ ደግሞ እኔ ዘንድ መጥታ ሀብቴን በማስተዳደሩ ሥራ ላይ ታግዘኛለች... በስተርጅናህ ብዙ ከመሥራት ይልቅ ብዙ መዝናናት ታበዛለህና እኔም አዘውትሬ የማደርገው ይኸንኑ ነው:: አማልክት ምስጋና ይግባቸውና አእምሮዬ አሁንም እንደወጣት ነው:: በልጅነቴ ያደረግኩትን እንኳን ማስታወስ እችላለሁ...» አለው::

«በዕድሜ የአሥር ዓመት ታላቁ ብትሆንም ይልቁንም ብርታትና ወጣትነት አይብሃለሁ... የቄሳር መልዕክተኛ ሆነህ የሰራሃቸውን ድንቅ ነገሮችም አትረሳም» አለ ላሚያ:: አንዱንም እንደማይረሳ ጲላጦስ አረጋገጠለት::

ላሚያ አስከትሎ:- «ለመሆኑ እኔ ከአይሁድ ምድር ከወጣሁ በኋላ ሳምራውያን አምፀውብህ እንደነበር ሰምቻለሁና እንዴት አድርገኸ ለማሸነፍ በቃህ?» አለው::

ጲላጦስ ጭንቅላቱን በመስማማት ነቅንቆ:- «በእርግጥ ብዙ ዓመታት ቢያልፉትም አሁንም አይረሳኝም:: ስለሳምራውያን አመፅ ብዙ ልነግርህ እችላለሁና ወደዚያ ኮረብታ ወጥተን እንቀመጥ...» በማለት ይዞት ወደኮረብታው ጫፍ ላይ ወጥተው ተቀመጡ:: ጲላጦስም ታሪኩን ቀጠለ... «...በግርዚም ተራራ አንድ ሰው ብዙዎችን እየሰበሰበ ዓይናችሁን እከፍታለሁ፤ ከዚያም የጥንቱ የአባቶቻችሁን ነገር አሳያችኋለሁ:: አርነትም ትወጣላችሁ... በማለት ይሰብካቸው እንደነበር ሰማሁ:: በተለይም ከሙሴ ጀምሮ የነበረውን ታሪካቸውን እየነገረ በቄሳር ላይ ለአመፅ እንደሚያነሳሳ ብሰማም ከእሱ ይልቅ የሕዝቡ አመፅ ስላሰጋኝ ወታደሮቼን ልኬ በቀላሉ አመፁን ገታሁት... በወቅቱ ይኸን ባላደርግ አመፀኞቹ ከግርዚም ተራራ ሥር የነበረችውን ከተማ በቁጥጥራቸው



Scanned by CamScanner

ሥር ሊያደርጓት ነበር...» ጲላጦስ ለላሚያ ብዙ ታሪኮችን አወጋለት፡፡ ላሚያም በጲላጦስ የማስታወስ ችሎታ እየተደነቀ ወጉን ሲኮመኩም አመሸና በነጋታው ጲላጦስ ቤት ሊገናኙ ተቀጣጥረው ተለያዩ፡፡

በነጋታው በጲላጦስ ቤት ተገናኝተው ወጋቸውን የጀመሩት በላሚያ አስተያየት ነበር፡፡

«ጲላጦስ ሆይ! በሰማርያውያን ላይ ግን ጭካኔ አብዝተኽባቸው እንደነበር አስታውሳለሁ፡፡ እንዲያውም ለአይሁዶች እምብዛም ርኅራኄ ስታሳይ በኢየሩሳሌም ቆይታዬ አላስተዋልሁም...» አለ፡፡

ጲላጦስ ፈገግ አለና መለሰለት፡- «ወንድሜ ላሚያ! ርኅራኄ ለአይሁድ ለማሳየት ካሰብክ በእርግጥ አንተ ሞኝ ነህ፡፡ በዚያም ባህርይ ይመስለኛ ል በቄሳር ዘንድ የተወደድሁት፤ በአይሁድም ዘንድ የተከበርኩት፡፡ በመካከላቸው ለዓመታት እንደእኔ ብትኖር የሰው ዘር ጠላት ማን እንደሆነ በሚገባ ታውቅ ነበር... ዳሩ አንተ ከሃገር ሃገር ስትዞር ስለኖርክ አይገባህም፡፡ አይሁዶችን ብትወዳቸውም ብትጠላቸውም ለአንተ የተለየ አመለካከት የላቸውም፤ ለዚህም ነው በዘዴ ስገዛቸው የኖርኩት፡፡ ለምሳሌ የቄሳርን የአምላክነት ባህርይ አይቀበሉም ነበር፡፡ ነገር ግን አምላካችን የሚሉት እነሱም የማያዩትን አምላክ ነው፡፡ የሚገርምህ ደግሞ እኛ ለጁፒተር፣ ለቬነስ አማልክቶቻችን እንደምናደርገው እነሱም ወደቤተመቅደሳቸው እርግብ እየወሰዱ ደም ያፈሱለት ነበር፡፡ ነገር ግን እኛ በእነሱ አይን የረከስን ዘሮች ነን፡፡ ለዚህም ነው ለኢየሩሳሌም ከተማ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ለማስገባት ያቀድኩትን ዕቅድ የተቃወሙት፡፡ አይሁድ ከሮማ ውሃ አይጠጡም፤ ቢጠጡ ግን ይረክሳሉ ይላሉ...

«እኛን ይፈሩናል፤ ይንቁናልም፡፡ ነገር ግን ለአይሁድ ዘር መኖር ሮማ ትልቁን ቁም ነገር ሰርታለች፡፡ ቢያንስ ሰላሟንና ብልፅግናዋን ጠብቀናል፡፡ አይሁድ ከጥንቱ ልማዳቸው ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው ማንንም አያምኑም፡፡ ያለምክንያት ይጠረጥሩሃል፡፡ ታዲያ አዋቂ ከሆንክ በፍርሃታቸው ልትጫወት ትችላለህ፡፡ የሊቀ ካህናቸውን ልብስ ወታደሬን



Scanned by CamScanner

አልብሺ በከተማው አደባባይ ያዞርኩበትም ቀን ነበር፡፡... ይልቁንም የፍርሃታቸው ምንጭ የአማልክትን ባህርይ ከአለማወቅ የመነጨ ነው፡፡ ጁፒተርን ያመልካሉ... ነገር ግን ስም አይሰጡትም፡፡ ቬነስን የሚያመልኩት ሴቶቹ ናቸው... እንዲያውም በአምልኮ ቀናቸው የእርግብ ደም ያፈሱ እንደነበር ሰምቻለሁ፡፡ አንድ ቀን አንድ እብድ ሰው ቤተመቅደሳቸው ገብቶ ገለባበጠባቸው... ከዚያ በኋላ ተራብሸው ድርጊታቸውን ተውት የሚል ነገር መስማቴንም አስታውሳለሁ፡፡»

ይኸን ጊዜ ላሚያ ድምፁን ከፍ አድርጐ መሳቅ ጀመረ፡፡ ጲላጦስም በመገረም ይመለከተው ጀመር፡፡ ላሚያም፡- «የሚያስቀኝ የአይሁዶች ጁፒተር ነው፡፡ አንድ ቀን ሮማን እንዳያጥለቀልቃት እፈራለሁ፡፡ አሁን በሮማ አደባባይ የሞሉት አማልክት ከእስያና ከአፍሪካ መምጣታቸውን መቼም አትዘነጋውም...» አለው፡፡

ጲላጦስ የታሪኩን አቅጣጫ ቀየረ፡- «የአይሁድ ሌላው የማልረሳውና የሚገርመኝ ነገራቸው እርስ በርሳቸው አለመስማማታቸው ነው፡፡ በየአደባባዩ ሲነታረኩና ዊም ለዊም ተያይዘው ሲጓተቱ ነው የምታየው፡፡ እንዲያውም ሕጋቸውን የሚቃወም ሁሉ በመለኮታዊ ሕግ እንደሚፈረድበት ያምናሉ፡፡ ሕጋችንን አፈረሰ የሚሉትን ሁሉ ወደእኔ እየጐተቱ አምጥተው ሞት ይፈረድበት ዘንድ ይጠይቁኝም ነበር... አለማወቃቸውንም እያየሁ ብዙ ጊዜ እቃወማቸው ነበር፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ከሳሾች አይሁዶች ብቻ ሳይሆኑ ተከሳሾቹም እብድ መስለው ይታዩኝ ነበር፡፡ ነገር ግን ብዙውን የሞት ፍርድ የፈረድኩት በሮማ ሕግ መሠረት ሳይሆን በራሳቸው ሕግ ነው፡፡ ለነገሩ በቂሳር የተሾምኩት የአይሁዶችን ልማድም ለማስጠበቅ አይደል? ወደሃገሬ የምመለስበት ጊዜም በተቃረበ ቁጥር እንዲህ ዓይነቱን ክስ ይዘውብኝ ሲመጡ እንደሰው ማመዛዘን እንዲችሉ እመክራቸው ነበር፤ ነገር ግን ከእኔ ምክር ይልቅ አጥብቀው የሚፈልጉት የሕጋቸውን መፈፀም ነበር፡፡...

«አይሁዶች በውስጣቸው ትዕቢትና ኩራት የተሞሉ ናቸው፡፡ በእኔ



Scanned by CamScanner

ደግነትና ማመዛዘን እንጂ በሌላ ነገር እጅ ወድቀው ቢሆን ኖሮ አስከፊ ጥፋት ያጋጥማቸው ነበር። አንድ ቀን ታሪክ የእኔን መልካም ሥራ ያወጣል» አለና ጲላጦስ መተከዝ ሲጀምር ላሚያ ቀጠለ።

«ጲላጦስ ሆይ! እኔ በኢየሩሳሌም ቆይታዬ አንድ የማልረሳው ነገር የሴቶቹን ቁንጅና ነበር። አንተ የሃገሩ ገዥ ሆነህ እንዴት በአይሁድ ሴት ፍቅር እንዳልወደቅህ ይገርመኛል» አለው።

ጲላጦስም፡- «የቱንም ያህል ሥልጣን ቢኖረኝ በአይሁድ ሴት መርገዝ ሥር የምወድቅ ሰው አይደለሁም» አለ። በዚህ ጊዜ ላሚያ በትካዜ አንገቱን ደፍቶ በሐሣብ ተዋዘ። ጲላጦስም አትኩሮ ሲመለከተው ቆይቶ ለንግግር ሲሰናዳ ላሚያ በድንገት አንገቱን አቅንቶ፡- «ወዳጄ ጲላጦስ! አንድ ታሪክ ልነግርህ ወደድሁ። በኢየሩሳሌም ኑሮዬን ስመራ ከአንዲት የአይሁድ ሴት ጋር በፍቅር ወድቄ ነበር። ይኸች ሴት አመንዝራ ተብላ በአይሁዶች የተጠላችና የተዋረደች የተሰደደችም ነበረች፤ እኔ ግን በፍቅሯ ወድቄ እሷን ለማግኘት ብዙ ዓመት ተንከራትቻለሁ። በኋላ ግን በአንድ የበጋ ወር ከአንድ የጥቂት ሰዎች ስብስብ ካለበት ቡድን ጋር ተቀላቅላ የአንድ የገሊላ መምህር የሆነና ትውልዱ ከናዝሬት የሆነ ኢየሱስ የሚባል ሰው ተከታይ ሆና አገኘኋት። እንዲያውም በኋላ ይኸን ሰው አንድ በግልፅ በማላውቀው ወንጀል ጠርጥረውት እንደሰቀሉት ሰምቻለሁ። ስለዚህ ሰው የምታውቀው አለህ?» ላሚያ እግረ መንገዱን ነበር ጥያቄውን የወረወረው።

ጲላጦስ ለአፍታ አሰበና፡- «ስሙን ኢየሱስ ነው ያልከኝ? □ረ በፍፁም አላስታውሰውም...» አለ ጲላጦስ። በጲላጦስ የማስታወስ ችሎታ ተደንቆ የነበረው ላሚያም፡- «ብዙዎችን በሥልጣን ዘመንህ ስትሰቅል ኖረሃልና አንድ ብትረሳ አይፈረድብህም...» በማለት የፍቅረኛውን ታሪክ ሊነግረው ቀጠለ።

# «ሴትና ወንድ የሚያመሰስላቸው አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ሁለቱም ሴትን አያምኑም»

"On One issue at least, men and women agree; they both distrust Women."

H.L.Hencken

ጉርኪና ቼኮብ አንድ የእረፍት ቀን በክሬሚያ አውራ ጐዳና ላይ ወግ እየሰለቁ እግራቸውን ሲያፍታቱ ቶልስቶይ የተቀመጠበት ዛፍ ሥር ደረሱ:: ይኸን ጊዜ ታላቁ ደራሲ ቶልስቶይ ከራሱ ቀና ብሎ «ስለምን ታወጋላችሁ?» ቢላቸው በአንድ ድምፅ «ስለሴቶች» አሉት:: ቶልስቶይም በፈገግታ «እንግዲያስ ውሸታሞች ናችሁ ማለት ነው:: እኔ ስለሴት እውነትን የማወራው አንድ እግሬ በመቃብር አፋፍ ላይ ተንጠልጥሎ ነው:: ያን ጊዜ እውነቱን ተናግሬ ወደ መቃብሬ እዘላለሁ» አለ:: ምናልባት የቶልስቶይ ፍርሃት እውነቱን ተናግሬ በምድር ላይ ሴቶች አያስኖሩኝም ይሆን?

መቼም የፍልስፍና ተግባር ሕይወትን መዳሰስ ሲሆን የሕይወት አንዱ ክፍል ደግሞ ሴቶች ናቸውና ፍልስፍና እነሱንም በሚገባ ዳሷል:: ወንድን ጓደኛህ ልታደርገው ስትችል ከሴት ጋር ግን ከትውውቅ በላይ (Acquaintance) ልታልፍ አትችልም ያለው ማን ነበር?

አርስቶትል ስለሴት ሲናገር «ተፈጥሮ መጀመሪያ ወንድን ፈጠረች፤ ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ወንድን መሥራት ስትጀምር የሁለተኛ ሥራዋ ከሽፈባትና ሴት ተፈጠረች» አለ:: እንግዲህ ሴት የተፈጥሮ ክሽፈት ናት



Scanned by CamScanner

ማለቱ ነው፡፡ ፕሌቶ ይኸን ሐሳብ በእጅጉ ኮንኖት «እንዲያውም ወንዶች የሚከፈትላቸው ማንኛውም ዕድል ለሴት የተከፈተና አልፎም የተመቻቸ ሊሆን ይገባል» ብሏል፡፡

ፕሌቶ ይኸን ይበል እንጂ የእሱ ደቀመዛሙርት የነበሩት ደግሞ ሲናገሩ፡- «የፕሌቶ 'ፀሎት' አንዲት ብቻ ነበረች፡፡ ይኸውም 'ፈጣሪዬ ወንድ አድርገህ ስለፈጠርከኝ አመሰግንሃለሁ' ማለት ብቻ ነበር» ይሉናል፡፡

(ዊል ዱራንትም ፕሌቶ «ወንድ ስለሆንኩ 'ፈጣሪዬን' አመሰግነዋለሁ» ብሎ መፀለዩን በአንድ መጽሐፉ ላይ ጠቅሶት እናገኛለን፡፡)

አስቀድመን ባነሳነው የአርስቶትል ሃሳብ አብዛኛዎቹ ፈላስፎች ሲስማሙ «ይኸን ጉዳይ ራሱ 'እግዚአብሔርም አምኖበታል፤ አድርጉታልም'» በማለት ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ጂሆቫ (እግዚአብሔር) ለሙሴ በመጨረሻ በሰጠው ትዕዛዝ፡- «የእሥራኤል ወንድ ልጆች ሴቶችን እናቶችንና ከብቶችን እንዲሁም የቤታቸውን ንብረት ሰብስበው እንዲወጡና እሱም እንዲመራቸው» ማዘዙን ይጠቅሱና «እንግዲህ ሴት ለወንዱ እንደ አንድ የንብረቱ ክፍል አድርጉ እግዚአብሔርም ቆጥሯታል» ይሉናል፡፡

እንደ ፒሮና ኒች ዓይነቶቹም ፈላስፎች በተለያየ ጊዜ «አይሁዶች ስለሴት የነበራቸውን እምነትና ንቀት ጂሆቫም እንዲገልፀውና ሕግ ሆኖም እንዲኖር ተሳክቶላቸዋል» ይላሉ፡፡

ታሪክ እንደሚነግረን በጥንታዊ የአይሁዶች ሕግ አንድ ሰው ሴት ልጅ ከወለደ ሻማ አያበራም፤ ሴት ልጅ የወለደች እናት የመንፃት ጊዜዋ ወንድ ልጅ ስትወልድ ከሚኖርባት እጥፍ ጊዜ ነበር (እንደ ረከሰች ትቆጠራለችና)፡፡ እንዲሁም የአይሁድ ወንድ ከጂሆቫ ጋር ራሱን የተቀራረበ አድርጐ ስለሚያምን በየዕለቱ ከሚፀልያቸው ፀሎቶች አንዱና ዋነኛው «አምላኬ ሆይ፤ አሕዛብ ወይም ሴት አድርገህ ስላልፈጠርከኝ አመሰግንሃለሁ» ነበር፡፡

ይኸ የአይሁዶች እምነት በምሥራቁ ጐራ (Eastern block) አንድ ወቅት ተስፋፍቶ እንደነበር እንረዳለን፡፡ እንዲያውም በምሥራቁ ጐራ በነበሩ አንዳንድ ሃገሮች ሴት ወንድ ልጅ እስክትወልድ ድረስ የተናቀች እንደነበረች ታሪክ ዘጋቢዎች አስፍረውት እናገኛለን፡፡

በአውቀቱ ከፍተኛ ክብርና ዝና የነበረው ኦቶ ዊኒንግር «ወንድ እንጂ ሴት ነፍስ የላትም፤ ስትፈጠር ያለነፍስ ነው የተፈጠረችው» ይል ነበር፡፡ ምንም እንኳን በዚህ ሐሳቡ ለረዥም ጊዜ ሸንጡን ገትሮ ይከራከር እንጂ የቤቱ አገልጋይ በነበረች ፍቅር ተሸንፎ ሲሰቃይ ፊቷን ስላዞረችበት ራሱን እስከማጥፋት ደርሷል፡፡

ብዙዎቹ ፈላስፎች ሴትን የተፈጥሮ ስህተት አድርገው ለመሳል ቢሞክሩም ፕሌቶ ስህተቱ የተፈጥሮ ሳይሆን የወንዶቹ ፈላስፎች ሐሳብ



Scanned by CamScanner

ነው በማለት ያጣጥለዋል:: ፕሌቶ ሲናገር:- «አንድ ቀን አንዲት ቆንጆ ልጃገረድ በአቴና አደባባይ ስታልፍ ተሰብስበን ከተቀመጥነው ፈላስፎች አንተቱን ጠምዝዞ በአይኑ ያልተከተላት፣ በልቡም ያልተመኛት አንድም አልነበረም» ብሏል::

ፈላስፎቹ ደግሞ:- «ሴቷን ውብ ያደረጋት የእኛ ምኞት እንጂ የእሷ ውበት አይደለም:: ሴት ልጅ ሚኒ ቀሚስ የምትለብሰው፣ ሊፒስቲክ የምትቀባው፣ ኩሏን የምትኳለው... የወንዱና ምኞት ለመቀስቀስ እንጂ ውበትን ለመግለፅ አይደለም» በማለት በፕሌቶ ሐሳብ በድጋሚ ይሳለቃሉ::

(እንደ እኔ ዓይነቱ ገጠሬ እዚህ ላይ ምናልባት በአእምሮው የሚጫርበት ጥያቄ ቢኖር የእነ ፕሌቶን አንገት ያስጠመዘዘችው የ20 ዓመት ኮረዳ ከ20 ዓመት በኋላ በ40 ዓመቷ በዚያው አደባባይ ብታልፍ አንገት መጠምዘዙ ቀርቶ ምናልባትም ማለፏን ልብ የሚል ፈላስፋ አይኖርም:: ስለሆነም በዚህም አለ በዚያ የወንዱ ምኞት ማቀጣጠያው የሴት ውበት በመኖሩ ነው እላለሁ::)

የቅርብ ዘመናት የዓለማችን ድንቅና ብርቅ ሰዎችም እምነት ከፈላስፎቹ ብዙም ያልራቀ ሆኖ እናገኘዋለን:: ካውንት ኬንሰርሊንግ በጋብቻ ጉዳይ ላይ የእሱና የጓደኞቹን እውነተኛ ተሞክሮ በመጣጥፍ መልክ አንድ መድብል አዘጋጅቶ ለግምገማ ሴሚናር ይጠራል:: በሴሚናሩ እንዲገኙለት ከጋበዛቸው ሰዎች አንዱ በርናርድ ሾው ነበር:: ሾው የግብዣው መልዕክት ሲደርሰው የሰጠው መልስ «ሚስቱ በሕይወት እያለች ስለጋብቻ ሕይወቱ እውነት የሚናገር አንድም ወንድ ስለሌለ በውሸት መድብል ላይ ለመተቸት አልገኝም» የሚል ነበር::

ምንም እንኳን ፈላስፎቹም ሆኑ ፀሐፍት ይህን ይበሉ እንጂ የመጽሐፍ ቅዱሱ ኢዮብ «...ምነው ጠላቴ ስለ እኔ መጽሐፍ በፃፈ» በማለት የተመኘው ሁሉ የደረሰው ለሴት ሆኖ እናገኘዋለን::

አንድ አህጉር ጠቅልሎ ለመግዛት ከዳር ደርሶ የነበረው ናፖሊዮን ቦናፓርት ሚስቱን መምራት እንዳልቻለ በራሱ አንደበት የተናገረውን ምስክር ሆኖ እናገኘዋለን:: ናፖሊዮን ሲናገር:- «ኃይሌና ብርታቴ ታላቅ ክብርና ሞገስ ያስገኘልኝ ጀግና ብሆንም በሚስቴ (ጆሴፊን) ፊት ግን ደካማና ልፍስፍስ ነበርኩ:: ይኸንን እሷም በሚገባ ታውቀው ነበር» ብሏል::

ጥንታውያን ፈላስፎች በመጨረሻ ተናግረው ያለፉት:- «የሰው ዘር የመጨረሻው ጥናት ወንድ ሲሆን፣ የመጨረሻው ሳይንስ ደግሞ ሳይኮሎጂ፣ የእሱም የመጨረሻ ምዕራፍ ሴት ትሆናለች» የሚል ሆኖ እናገኘዋለን::



Scanned by CamScanner

«እውነት ምንድር ነው?»

«እነሆ! እኔ ከደሙ ንፁህ ነኝ»

(ጲላጦስ)



ዋጋ. 13 ብር

አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት ታተመ

Scanned by CamScanner